# ጫካ ነጫኝ

(ልብወለድ)

ከጌታቸው ደመቀ

ሐምሌ 1991
አዲስ አበባ

መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው::
All Rights Reserved

Copyright- Getachew Demeke - 1999
ኮፒራይት - ጌታቸው ደመቀ - 1991

የሽፋን ስዕል - በቴዎድሮስ አሰፋ

ለአባቴ ለአቶ ደመቀ ወልደሥላሴና
ለወንድሜ ለእሸቱ ደመቀ መታሰቢያ ይሁንልኝ

ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሳለሁ ወደ ሥነጽሑፍ ዓለም ለመግባት ምክንያት ለሆነኝ መምህሬ አቶ ብቃለ ስዩም ይህንና ሌሎቹን ሥራዎቼን ሳይሰለች በማንበብ ገንቢ አስተያየቱን ስለሰጠኝ በአንባቢያን ስም አመሰግነዋለሁ::

በተጨማሪም አቶ ሺበሺ ለማ፣ አቶ ተስፋዬ ብርሃኑ፣ አቶ ተሻገር ሽፈራውና አቶ መስፍን እንድርያስ ይህን ድርሰት አንብበው ገንቢ አስተያየታቸውን ስለሰጡኝ እንዲሁም ወይዘሪት ማርታ ካሣዬ ረቂቁን በኮምፒዩተር በመጻፍ ስለተባበረችኝ በአንባቢያን ስም አመሰግናቸዋለሁ::

# 1

ሲጋራ በያዘው እጃቸው አውራ ጣት አገጫቸውን ደገፍ አድርገው፣ ከፍታ ካለው የመኖሪያ ቤታቸው በረንዳ ላይ ተቀምጠዋል። ቁልቁል፣ ግቢው ውስጥ በሚገኙት አበቦች፣ ሣሮችና ጥዶች ላይ ዓይኖቻቸውን ያሳርፉ እንጂ፣ አያዩዋቸውም። ትካዜ ደቋቁሷቸዋል። ትናንትና ቀን የገጠማቸው ነገር በስሜታቸው ላይ ለውጥ አሳይቷል። ከመሸም በኋላ እንደወትሮው መኖሪያ ቤታቸው ውስጥ በሚገኘው የግል ክሊኒካቸው የሚሰጡትን ህክምናና በንባብ ክፍላቸው ያደርጉት የነበረውን ጥናትና ምርምር ሳያካሂዱ አልጋቸው ላይ ይውጡ እንጂ፣ ዕንቅልፍ የሚሉት ነገር አልዳሰሳቸውም። ሲደክማቸው የሚያዝናናቸው፣ የሚያጫውታቸውና ይህችን ዓለም ለጥቂት ሰዓታት የሚያስረሳቸው ዕንቅልፍ እንደ አድማስ ርቋቸው ነበር። ሌሊቱ ከመቼውም ጊዜ ልቆ የጨለመባቸው፣ ከወትሮው እጅግ የጠቆረ ጽልመት ተጎናጽፎ በህይወታቸው ውስጥ ትታይ የነበረውን የተስፋ ጭላንጭል አልም አድርጎ ያጠፋባቸው ያህል ተሰምቷቸው ነበር። በምድር ላይ አሉ የሚባሉት አስፈሪ ፍጥረታት ከበዋቸው መግቢያ መውጫ ያሳጧቸው ያህል ከብዷቸው ነበር።

ሽቅብ እንደያዙት የረሱት ሲጋራ የቋጠረው አመድ ጉልበታቸው ላይ ጠብ ሲል፣ ከሰጠሙበት የሀሳብ ባህር ውስጥ ብቅ አሉ። እሳቱ መጥፋት ደረጃ ላይ መድረሱን አዩ። ልምጥጥ አድርገው ከሳቡ በኋላ ፣ ጭሱን አስወጡና እንደገና በሀሳብ ሰመጡ።

ንግሥት ረጅም ነጭ የሌሊት ልብሷን እንደለበሰች ሳሎን ውስጥ ሆና ዓይኖቿን በባለመስታወቱ መስኮት ወደ ውጭ ላከች። መደባቸው ነጭ ስኒ የሚመስሉት ትላልቅ ዓይኖቿ ተወርውረው በትካዜ ቁጥጥር ሥር የወደቁ አባቷ በራ ላይ አረፉ። እዚያው አልቀሩም። ጠይም ቆዳ ያለው ፊታቸው ላይ፣ ቀጥ ብሎ ከሚወርደው አፍንጫቸው ግራና ቀኝ ከሚገኙትና ከጉርጓዶቻቸው ውስጥ የተወሸቁ ከሚመስሉት ዓይኖቻቸው ላይም ዘለሉ። ዓይኖቻቸው ንባብ ስለሚያበዙ አንድ ቀን ተግባራቸውን ያቆማሉ ብላ ትሰጋለች - ንግሥት ። ግና በሀምሳ ዕድሜያቸው እንዲህ የሆኑ፣ ጥቂት ዓመታት ሲጨምሩ እንደ ጨው ሟሙተው ያልቃሉ ብላ አሰባለች።

የዋናውን መኖሪያ ቤት በር ከፍታ ወደ በረንዳው ወጣች።

አጠገባቸው ቆመችና፣ " እንደምን አደርክ አባባ?" አለች ሙዚቃ በሚመስለው ድምጿ።

ምንም መልስ ሳይሰጡ ቀና ብለው አይዋት። በጥያቄ ዓይነት እንደ እንግዳ ሰው ትኩር ብለው ተመለከቷት። ግን በውስጣቸው ያነሱትን ጥያቄ፣ ጠይም ፊቷ አልመለሰላቸውም። ውበቷ የሆኑት ትላልቅ ዓይኖቿ የሚፈልጉትን እውነታ አልጠቆሟቸውም። ነጫጭ ትናንሽ ጥርሶቿን የሚሸፍኑትና ስልክክ ብሎ ከሚወርደው አፍንጫዋ ሥር ጎላ ብለው የሚታዩት ከንፈሮቿም ሊነግሯቸው አልቻሉም። የዛሬ ሀያ አምስት ዓመት ገደማ ከሚወዷት ባለቤታቸው የወለዷት የራሳቸው ፍሬ መስላ አልታይ አለቻቸው – ንግሥት።

ዘወትር በዕረፍት ቀናት ቤተሰቡ ተሰባስቦ ቁርስ የሚበላው በረንዳ ላይ ነው። በሥጋና በደም የተሳሰሩት የቤተሰቡ አባላት እርሷና አባቷ ዶክተር ናትናኤል ዘለቀ ብቻ ናቸው። ቀሪዎቹ ሁለቱ፣ ሸዋዬና ተገኝ፣ የቤቱ ሠራተኞች ናቸው። በግቢው ውስጥ ብዙ የቆዩ በመሆናቸው ከቤተሰቡ ተነጥለው እንደ ባዳ አይታዩም። በዶክተር ናትናኤል ቤት አሽከርና ቀጣሪ ወይም ጌታ የሚል ልዩነት አይታወቅም። በርሳቸው ቤት የሁሉም ሰው ሰብእና እኩል ነው። ልዩነት ያለው በሥራ ድርሻቸው ብቻ ነው።

ላቀረበችላቸው ሰላምታ አፀፋውን ስላልመለሱላት ዝም ብላ አየቻቸው። እንደሁልጊዜው ዛሬ፣ "እንደምን አደርሽ ፣ ንግሥቴ?" ስላላልዋት ቅሬታ ተሰምቷታል። ትናንትና ማታ ሳታገኛቸው ወደ መኝታ ቤታቸው በመግባታቸውም፣ የአባትነት ፍቅራቸውን የሚገልፁላት ከንፈሮቻቸው ግንባሯ ላይ አላረፉም። አሁን በናፍቆት ይስሙኛል ብላ ገምታ ነበር።

ዓይኖቿን ከአባቷ ፊት ላይ ሳትነቅል፣ ከጎናቸው ካለው ወንበር ላይ ተቀመጠች።

ዶክተሩ አጠገባቸው ሰው እንደሌለ ሁሉ፣ ለልጃቸው ትኩረት ሳይሰጧት፣ እዚያው ሀሳባቸው ውስጥ ቀሩ።

በዚህ ሁኔታ ጥቂት ሲኮንዶች ካለፉ በኋላ፣ በፋሻ የተጠቀለለውን የንግሥትን አውራ ጣት አዩ–ትኩር ብለው።

ንግሥትን የአባቷ ያልተለመደ ዝምታ ሳያስደንግጣት አልቀረም። ወትሮ በግል ክሊኒካቸው ውስጥ የሚያካሂዱትን የጠዋት ህክምና ከጨረሱ በኋላ ፣ ከእርሷ፣ ከሸዋዬና ከተገኝ ጋር ለቁርስ ሲቀመጡ ሞቅ ካለ ፈገግታ ጋር የሚያደርጉት ጨዋታ ጣፋጭ ነበር። ያ ዛሬ የለም። አባቷ አንድ እንግዳ የሆነ ነገር እንዳገኛቸው ጠርጥራለች 'ምን ሆኖ ይሆን?' አለች በልቧ።



ለአባቷ ከጎናቸው ያለ ዘመድ እርሷ ብቻ ናት። እናቷ ወይዘሮ ትርንጎ ፣ ንግሥት ገና ህፃን ሳለች ነው በጡት ካንሰር የሞቱት። ከእርሷ ሌላ ቀራቢ የላቸውም። ስለዚህ፣ በሥራቸው ላይና በሌላ መንገድ ችግር ወይም እንግዳ ነገር ሲገጥማቸው የሚያማክሯት እሷኑ ነው። ዛሬ ግን፣ የገጠማቸውን ችግር አምቀው የያዙ መስለዋል።

"ምን ሆነሃል አባዬ?" አለች ንግሥት፣ ለስለስ ባለ አነጋገር።

ዶክተር ናትናኤል ምንም መልስ አልሰጡም። አሁንም ሲጋራ በያዘው የግራ እጃቸው አውራ ጣት አገጫቸውን ደገፍ አድርገው ወደ ሌላ አቅጣጫ ተመለከቱ። ሩቅ የሚያዩ ይመስላሉ።

" አባዬ!"

"ምንም አልሆንኩም" ባክሽ። "አሉና በፋሻ የተጠቀለለውን ጣቷን ተመለከቱ።

እርሷም የአባቷን ዓይኖች ተከትላ ጣቷን ተመለከተች። "ደህና ነኝ። ምንም አልሆንኩም። ደህና ነኝ።"አለች፣ በደረሰባት ጉዳት የተከዙ መስሏት፣ ለማጽናናት ብላ።

አባቷ የህክምና አዋቂ ሆነውም፣ የንግሥት ራስ ምታት ያስደነግጣቸዋል። በርሷ ላይ የሚታይ ቀላል በሽታ በቀላሉ የሚድን እንደማይመስላቸው ታውቃለች። በጣም ይጨነቁላታል። ከአንድ ዓመት በፊት፣ በ1978 ዓ.ም. በጠና ታምማ ሆስፒታል የገባችበት ጊዜ ትዝ አላት። ያን ጊዜ አባትየው የምትሞት መስሏቸው የተጨነቁት ታወሳት። ደም አስፈልጎ፣ እርሳቸው የሰጡት ከእርሷ ደም ጋር ባለመመሳሰሉና የሚሆናት እስኪመጣ ድረስ በጣም ተቻኩለው እንደነበር ሰምታለች። 'ለካ ይሄ ሰው ሲታመም መደንገጥና መጨነቅ በሀኪሞችም ዘንድ አለ?' ስትል ተገርማ ነበር፣ ከዳነች በኋላ አባቷ እንዴት እንደተጨነቁላት ሰዎች ሲነግሯት።

አጠር ብላ ወፈር ያለች ቀይ ሴት ቁርስ ይዛ መጣች። በሸክላ ሳህኖች ላይ ዳቦና የእንቁላል ፍርፍር፣ በነጭ የሸክላ ጀበና ሻይ እንዲሁም ስኒዎች አቀረበች። የእጅ ውሃ ሰጠችና ተገኝን ጠርታ ተቀመጠች።

ቁርስ መብላት ተጀምሯል። ከዶክተር ናትናኤል በስተቀር የገበታው ታዳሚዎች በወጉ እየበሉ ናቸው። እርሳቸው ግን አልቻሉም። የጎረሱት እህል አፋቸው ውስጥ ኩሬ ላይ እንደተንሳፈፈ የበቆሎ ቆረቆንዳ ይንቀዋለላል።

ንግሥት ሰረቅ አድርጋ አየቻቸው። አንድ መጥፎ ነገር እንደገጠማቸው ርግጠኛ ሆነች። ሥጋት ሥጋ እንዳየ አሞራ

እንገፀበበባት። አባቷ ላይ ያደሩት ትካዜና ሀዘን በርሷም ላይ ማደር ጀመሩ። 'ምን ነክቶት ይሆን? ሲከታተል የነበረው ምርምር ውጤት መጥፎ ሆኖ ይሆን? እንዲያም ቢሆን፣ ሁልጊዜ ሙከራ ካደረገ በኋላ ውጤቱ ጥሩም ሆነ አልሆነ ይነግረኛል። የዛሬው ጉዳይ ሌላ መሆን አለበት። ግን ማን አስቀየመው?'

ከሰዎች ጋር የሚቀያየሙበት ምክንያት አልታይ አላት። ዶክተር ናትናኤል ከሰው ጋር እጅግ ተግባቢ፣ ሳቂ፣ ተጫዋች፣ ከእርሳቸው ይልቅ የሰው ችግር ቅድሚያ የሚሰማቸውና የዋህ ሰው ናቸው። ብዙ ጊዜ ከሥራዎቻቸው ጋር ተጣምደው ስለሚውሉ ከሰዎች ጋር የሚጫወቱባቸው ጊዜያት ጥቂት ናቸው። ከሥራ እንደወጡ ቤታቸው ይመጡና በግል ክሊኒካቸው ውስጥ የህክምና ሥራዎቻቸውን፣ ከዚያ በኋላ ደግሞ በጥናት ክፍላቸው ውስጥ የምርምር ተግባራቸውን ከማከናወን በስተቀር ለሌሎች ጉዳዮች ትርፍ ጊዜ የላቸውም። ቀኑን ሙሉ ራሳቸውን በሥራ ላይ ስለሚያውሉ ከሰዎች ጋር ተገናኝተው የሚቀያየሙበት መንገድ አልታያትም።

"አትበይም እንዴ?" አለች ሸዋዬ ፣ ንግሥትን አይታ።

ንግሥት ከገባችበት ሀሳብ ውስጥ ወጣች። ሳይታወቃት እሷም እንደ አባቷ መብላቷን እንደመተው ያለች መሆኑን አላጤነችውም።

"እርስዎስ ፣ አይበሉም እንዴ ምን ሆናችኋል?" አለች ሸዋዬ በድጋሚ፣ ዶክተሩን እያየች።

"በቃኝ፤ ጠገብኩ። ይልቅ፣ በልተሽ ስትጨርሺ ወፍራም ቡና አፍይልኝ። "አሉና እጆቻቸውን እርስ በርሳቸው ከጠራረጉ በኋላ ሲጋራ ለኮሱ።

ድንገት ስልክ ከሳሎን ውስጥ ሲጮህ ተሰማ።

ሸዋዬ ገብታ ስልኩን አነሳች። "ሀሎ!"

ደዋይ የሚፈልገው ቁጥር መሆኑን ለማረጋገጥ ጠየቃት።

"አዎ ነው።"

"ንግሥት አለች?"

"ማን ልበል?" አለች ሸዋዬ።

"ግርማ።"

"ቆይ እስቲ ይጠብቁ።"

የስልኩን ማናገሪያ ስልኩ ከተቀመጠበት ጠረጴዛ ላይ አስቀምጣ ወጣች። "ንግሥቴ፣ ስልክ። "አለችና ተቀመጠች።



ንግሥት ተነስታ ወደ ሳሎን ገባች።

"ማን ነው የደወለው?" ሲሉ ጠየቁ ናትናኤል።

"ግርማ ነው።"አለች ሸዋዬ።

ለዶክተር ናትናኤል ግርማ የማይታወቅ ሰው አይደለም። አሁን ያሉበትን ቤት ሠርተው ከመምጣታቸው በፊት ይኖሩበት ከነበረው ሠፈር ውስጥ የሚኖር ጎረቤታቸው ነው። ግርማ ከንግሥት ጋር ያለውን ግንኙነት በደንብ ያውቁታል። ራሱን ለማሻሻልና ለማሳደግ ምንም ጥረት የማያደርግ ደካማ አድርገው ያዩታል። በትምህርቱ ከፍተኛ ደረጃ መድረስ ያቃተው በመሆኑና በተፈጥሮው ንዝህላል መስሎ ስለሚታያቸው፣ 'እየተራመደ የሚያንቀላፋው' ይሉታል-አንዳንድ ጊዜ ከንግሥት ጋር ስለ እሱ ተነስቶ ሲጫወቱ። ራሱን ያላነቃ፣ ራሱን ለማሳደግ ጥረት የማያደርግ ሰው ሌላውን ያደድባል የሚል እምነት አላቸው። በዚህ የተነሳ የልጃቸው ፍቅረኛ እንዲሆን አይወዱም። እንደማይሆናት ብዙ ጊዜ ለልጃቸው ቢነግሯትም፣ አልሰማቻቸውም። በዚህ ምክንያት ሰልችቷቸው ትተውታል።

ንግሥት ስልኩን አነሳች። ጠይም ፊቷ ላይ የፈገግታ ብርሀን ነግሷል። "ሀሎ!"

"ንግሥት?"ሲል ጠየቀ፣ በስልኩ ማዳመጫ ውስጥ የመጣው ድምፅ።

"አዎ፣ ደህና ነህ ግርማ? "አለች በድምፁ አውቃው።

"ደህና ነኝ። አንቺስ ደህና ነሽ?"

"አዎ። ደህና ነኝ። መቼ መጣህ?"

"ትናንት ማታ።"

"አንተ፣ በጣም ብዙ ጊዜ ሆነን እኮ! ሶስት ወራት አላለፉም?" አለች ንግሥት። ድንገት ድምጿ የመደነቅ ዜማ አዝሎ።

"ሁለት ወራት ከሶስት ሳምንታት።"

"አሁን ሥራው አለቀ?"

"አዎ። ሌላ ሥራ ካልታዘዝኩ በስተቀር ከእንግዲህ ወዲያ አዲስ አበባ ውስጥ ሳልቆይ አልቀርም። "አለ የግርማ ድምፅ።

"ሥራህ ግን አስቸጋሪ ነው። መገናኘት ባለመቻላችን ምን ያህል ቅር እንዳለኝ ታውቃለህ?" አለች እንደመከፋት ብላ።

ከግርማ ጋር በፍቅር ከተፈላለጉ ወዲህ ለመስክ ሥራ ተለይቷት ከአዲስ አበባ ወጥቶ ሲመለስ ይሄ አራተኛው ነው። ሰፋ ያለ ጊዜ አግኝተው የፍቅር ጨዋታ ተለዋውጠው አያውቁም። ይህ ሁኔታ ንግሥትን እጅግ አሳዝኗታል።

"ምን ላድርግ ንግሥትዬ? የሥራ ጉዳይ፣ የእንጀራ ጉዳይ ሆኖ እኮ ነው። ለእኔም ቅር እያለኝ ነው። ሁልጊዜ እስታውስሻለሁ።"

"ለመሆኑ ስልክ የሌለበት አገር ነው ሁልጊዜ የምትሠራው ወይስ ሳልናፍቅህ ቀርቼ ነው?"

"ናፍቆትማ የት ይቀራል ንግሥቴ? ሁልጊዜ ከዓይኖ ሀሊናዬ አትጠፊም። ድምጽሽ ፣ ሳቅሽና ጨዋታሽም ከእዝኖ ልቦናዬ አይጠፉም። ግን፣ ስልክ ማግኘት ተቸግሬ ነው። "አለ ግርማ ከልቡ።

"ስላላሰብክበት እንጂ..."

"እንቺ ደግሞ አታምኝም። " ዝም አለ። "አሁን በስልክ መነጋገሩን እናቁምና፣ ዛሬ አብረን እንዋል። ፕሮግራም አለሽ እንዴ?"

"የለኝም።"

"ታዲያ የት እንገናኝ?"

"የፈለክበት ቦታ።"

"ቬሮኒካ እንገናኝ?"

"ጥሩ። በስንት ሰዓት?"

"በስምንት ሰዓት።"

"እሺ ግን እንደ..."

ንግግሯን ሳትጨርስ ከበስተኋላዋ የአባቷ ድምጽ ተሰማት።

"ስልኩን እንዳትዘጊው። ላነጋግረው እፈልጋለሁ።" አሉ ዶክተሩ።

ንግሥት ደነገጠች። አባቷ ግርማን እንደማይወዱት ታውቃለች። ከዚህ በፊት እሱን እንኳን ለማነጋገር፣ ዓይናቸውንም ለማየት ፍላጎት አልነበራቸውም። አሁን ለምን ሊያነጋግሩት እንደፈለጉ ሊገባት አልቻለም።

"ግርማ፣ አባዬ ሊያነጋግርህ ይፈልጋል። በእኔ በኩል ቻዎ!" ብላ ስልኩን ለአባቷ አቀበለች።

ዶክተር ናትናኤል የስልኩን ማዳመጫ ጆሮዋቸው ላይ ከመደቀናቸው በፊት ልጃቸውን አይዋት።

እሷም አየቻቸው።



ከሳሎኑ ውስጥ እንድትወጣላቸው ፈልገዋል። ግን "ውጪ" ብሎ መናገሩን አልወደዱትም።

እሷ አጠገባቸው እያለች መነጋገሩን እንዳልፈለጉ አውቃ ከሳሎኑ በመውጣት በረንዳው ላይ ካለው ወንበሯ ላይ ተቀመጠች።

አባቷ ለግርማ ምን ሊነግሩት እንዳቀዱና እሷ ለምን እንዳትሰማ እንደፈለጉ ሊገባት አልቻለም። ግርማ ደህና ሰው መሆኑን ለአባቷ በቀጥታ ሳይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ ነግራቸዋለች። ግርማ እርሳቸው እንዳሰቡት ሳይሆን ለእርሷ የሚሆን ሰው እንደሆነ በአንዳንድ አጋጣሚዎች ገልፃላቸዋለች። ፍጹም ጨዋ፣ አስተዋይና ለሰው የሚያስብ መሆኑን ዘርዝራ አጫውታቸዋለች።

ዶክተር ናትናኤል የስልኩን ንግግር ጨርሰው ወደ በረንዳው ተመለሱ። ፊታቸው በቁጣ የተገለባበጠ ይመስላል። ትናንሽ ዓይኖቻቸው አባብጠው የደም ኳስ መስለዋል።

ሽዋዬ ቁርስ ያቀረበችባቸውን ዕቃዎች እንዳነሳች ተገኝም ከመቀመጫው ብድግ አለ። አጭር፣ ጠይምና ወፍራም ነው።

ንግሥት የአባቷን ፊት አነበበች። ልትረዳው የምትችለው ነገር አላገኘችም። ጭንቅ አላት። ምን ብላ እንደምትናገር አላወቀችም። ብቻ ዝም ማለቱን መረጠች።

ዶክተር ናትናኤል ሌላ ሲጋራ ለኮሱ። እንደዛሬ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ በርከት ያሉ ሲጋራዎች አጭሰው አያውቁም። ይህ ሁኔታ ደግሞ፣ በንግሥት ላይ ነፍስ ዘርቶ የነበረውን ጭንቀቷን አሳደገው።

ሲጋራቸውን በረጅሙ ምገው ጭሱን ካስወጡ በኋላ፣ "ከግርማ ጋር ምን ያህል ጊዜ አብራችሁ ቆይታችኋል?" ሲሉ ንግሥትን ጠየቋት።

በዝምታ መሀል ድንገት ብቅ ያለው ጥያቄያቸው ትንሽ አስደነገጣትና፣ "ለአንድ ዓመት ተኩል ያህል ጊዜ።"አለች።

"እ? .... ይሄን ያህል ጊዜ ፍቅረኛሞች ሆናችሁ ቆይታችኋል?"

"አይ። ለአንድ ዓመት ያህል በወንድምና እህት ጓደኝነት ነው የቆየነው። ከዚያ በኋላ ነው፣ ማለት፣ ለአምስት ወይም ለአራት ወራት ያህል ሁኔታው ተለውጦ ፍቅረኛሞች የሆንነው። ለመጋባት ያቀድነው አሁን ይሁን እንጂ፣ ከዚያ በፊት እርስ በርሳችን ስንተዋወቅና ስንግባባ ቆይተናል። እና የቸኮልን አይመስለኝም።" አለች ንግሥት፣ ያልተጠየቀችውን ጨምራ።

ዶክተሩ ሲጋራቸውን በጣም ስበው ጭስ አስወጡና ትኩር ብለው አዩዋት። ለልጃቸው አንድ ጥያቄ በማንሳት በምትሰጣቸው መልስ ከትናንትና ጀምሮ ሲያስጨንቃቸው ስለነበረው ጉዳይ ትክክለኛ ገጽታ ለማወቅ ፈለጉ። ግን የሚያነሱት ጥያቄ በልጃቸው ላይ የጥርጣሬ ስጋት ይፈጥራል ብለው ተውት።

## 2

ዶክተር ናትናኤል ንግሥትን በረንዳው ላይ ትተዋት ወደ መኝታ ክፍላቸው ገቡና የሥራ ልብሳቸውን አውልቀው፣ ጠቆር ያለ የሱፍ ኮትና ሱሪ ለብሰው፣ መኪናቸውን ወደ አቆሙበት የግቢያቸው ጋራዥ አመሩ። ከጥቂት ሴኮንዶች በኋላ መኪናቸውን አስነሱና ከግቢው መውጫ በር ላይ ቆሙ–ተገኝ በሩን እስኪከፍትላቸው ድረስ።

ንግሥት ከተቀመጠችበት ሳትነሳ አየቻቸው። እንደወትሮው የሚሄዱበትን ቦታ ሳይነግሯትና ለመሰናበቻ ግንባሯን ሳይስሟት በመቅረታቸው፣ የተለመደው ጉርሻ እንደቀረበት ህፃን ተሳቀቀች። ጠይም ፊቷ ጠቆረ። ዕንባ ወጥቷት ብታለቅስ ደስታውን አትችለውም ነበር።

ቢጫዋ የዶክተሩ ቶዮታ ከግቢው ወጣች። ድል ገበያ አካባቢ ከሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው ወደ ዋናው ጎዳና የሚወስደውን አጠር ያለ አስፋልት ለበስ መንገድ ያዘች።

ዶክተር ናትናኤል ተክዘዋል። ከትናንትና ጀምሮ ፍጹም ጤነኛ አይመስሉም። ሣር ቤት አካባቢ የሚገኘውን አደባባይ አዞሩና ወደሜክሲኮ አደባባይ ያበሯት ጀመር–መኪናዋን። አልፎ አልፎ፣ ሰዓታቸውን መመልከቱን አልተውም። አሁን ከሚሄዱበት ቦታ የሚፈልጉትን ሰው ካነጋገሩ በኋላ ሥራ መግባት አለባቸው። ቀኑ እሁድ ቢሆንም፣ ስድስት ሰዓት ላይ ሆስፒታል መገኘት አለባቸው። አነዳዳቸው ፍጥነት አለው። ለሚያያቸው ሰው ግን፣ በትክክል የሚሄዱበትን ቦታ የሚያውቁ አይመስሉም። በሀሳብ ላይ ናቸው። ሊያረጋግጡ የሚፈልጉትን ነገር በምን ዘዴ ማውጣጣት እንደሚችሉ እያሰላሰሉ ነው።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ፣ ሜክሲኮ አደባባይን አልፈው ወደ መስቀል አደባባይ የሚወስደውን ጎዳና ያዙ። የደመነፍስ ጉዞአቸውን አሁንም ቀጠሉ። መስቀል አደባባይ ሲደርሱ፣ ከአንድ ህንፃ ሥር መኪናቸውን አቆሙና ሲጋራቸውን እየማጉ ወደ አብዮት ራንዴቩ



ገቡ። በመዝናኛ ቤቱ ውስጥ ያሉ ወንበሮች በሙሉ የሚፈልጉትን ሰው አልያዙም። አንድ ባዶ ጠረጴዛ አጠገብ ያለ ወንበር ሳቡና ተቀመጡ።

አንድ የቤቱ ጣሪያ የቀረበው አሳላፊ መጣና፣ "ምን ልታዘዝ?" አለ።

ዶክተሩ ሲጋራ በያዘው እጃቸው አውራ ጣት አገጫቸውን ደገፍ አደረጉና የሚጠጡትን የመጠጦች አይነት አሰቡ። "ቡና–ወፍራም።" አሉ ወዲያው።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አሳላፊው ቡናውን አቀረበላቸው።

ሲጋራ ባልያዘው እጃቸው ስኳሩን ማሟሟት ጀመሩ። በሀሳብ ከመመሰጣቸው የተነሳ የስኳሩን መሟሟት በመርሳት ማንኪያውን ማንሸከርከር አልተውም፣ ግርማ በድንገት አጠገባቸው መጥቶ እስኪቆም ድረስ። ቀና ብለው ተመለከቱት።

የዶክተሩ ትናንሽ ዓይኖች ከእግሮቹ ሥር ጀምረው፣ ጥቁር ሰማያዊ ኮትና ራንግለር ሱሪ የለበሰውን ቀጭንና ረጅም ተክለ ቁመናውን ከቃኙ በኋላ ጠይም ፊቱ ላይ እረፍት አደረጉ።

እጁን ለሰላምታ ዘረጋላቸው። " እንደምን አደሩ ዶክተር?" አለ፣ ከአንገቱ ጎንበስ እንደማለት ብሎ።

"እንደምን አደርክ?" አሉና ጨበጡት ዶክተሩ፣ ከፊታቸው ላይ ጠንከር ያለ ጥላቻ እየተነበበ።

ልጁ ተቀመጠ። ረዘም ያለ ዝምታ ሰፈነ። ለምን ጉዳይ በአስቸኳይ ሊያነጋግሩት እንደፈለጉ ግራ ገብቶታል። ባለፉት ጊዜያት ቃለ-ምልልስ ያደረጉባቸው ብዙ አጋጣሚዎች አልነበሩም። ከእንደሱ ያለ ሰው ጋር ጨዋታ መፍጠሪያ ጊዜና አጋጣሚ አጥተው አይደለም። ከዚህ በፊት አንድ ሠፈር ውስጥ አብረው በመኖራቸው ብዙ ሊቀራረቡ በቻሉ ነበር። መንገድ ላይ ሲገናኙና ሰላምታ ሲያቀርብላቸው፣ ከአንገት በላይ የሆነ አፀፋ ይመልሱለታል። እንደሚጠሉት ያውቃል። ግን ዛሬ፣ ሊያነጋግሩት ፈልገው፣ አንድ ጠረጴዛ ተጋርተው፣ ፊት ለፊት ተቀምጠዋል።

የያዙትን የሲጋራ ቁራጭ ተርኩሰው ካጠፉ በኋላ፣ ሌላ ለኮሱ። ሲጋራውን በረጅሙ ስበው፣ የክብሪቱን እሳት ለማጥፋት እያወዛወዙ ጭሱን ከአፋቸው አስወጡ።

አሳላፊው መጥቶ ግርማ የሚፈልገውን የመጠጥ ዓይነት ጠይቆ ሄደ።

ጥቂት ሴኮንዶች አለፉ፣ ሁለቱም ሳይነጋገሩ።

ድንገት፣ "ግርማ፣..." ብለው ዝም አሉ፣ አሳላፊው ሻዩን ይዞ ሲመጣ።

ግርማ እንደመደንገጥ ብሎ ጆሮዎቹን እንደሻንጥላ ዘርግቶ፣ አፉን ከፍቶ ቀጣዩን ቃላቸውን መጠበቅ ያዘ።

"እኔና አባትህ የቆየ ወዳጅነት አለን። ሜካ መንጥረን፣ ቤት ሠርተን፣ በጉርብትና አብረን ኖረናል። የእናንተ ቤት የእኛ ሆኖ፣ የእኛ ደግሞ የእናንተ ሆኖ ቆይቷል። ጎረቤት በነበርን ጊዜ፣ ደጉንም ክፉንም አብረን አይተናል። ስለዚህ ፣ እኔና አባትህ ወንድማማቾች ነን። በሥጋ መነካካቱ አይደለም ዋናው ቁም ነገር። ለችግር ጊዜ ከዘመድ ቀርቦ የሚደርስልኝ እሱ ስለሆነ፣ ወንድሜ ነው። እናትህም ብትሆን፣ ጥሩ እህቴ ናት። ባለቤቴ እኔንና ንግሥትን ጥላ ከሞተች ጀምሮ፣ ንግሥትን እንደጎረቤት ሳይሆን እንደ ልጇ፣ እንደእናንተ፣ አይታ አስፈላጊውን ረድታለች። የእናት ምትክ ሆናለች። በዚህ ውለታዋ የልጄ እናት ናት። አንተም የንግሥት ወንድም ነህ። ታዲያ ስታስበው ከአብሮ አደግህ፣ ከእህትህ ጋር ጋብቻ ለመፈጸም ማሰቡ ጥሩ መስሎ ይታይሀል? አንተ ለንግሥትዬ አንሰህ ሳይሆን፣ ነገሩን ከዚህ አኳያ አይቼው ነው ፍቅራችሁን ያልወደድኩት። ይህንኑ ጉዳይ ለአንተም ለእርሷም ብዙ ነግሬያለሁ። አባትህና እናትህም ሳይነግሩህ አልቀሩም። እናንተ ግን ነገሩን ችላ ብላችሁ፣ ንቃችሁን፣ ስራችሁን ሠራችሁ! ወራዳ የሆነ ተግባር ሠራችሁ!" ሲሉ ጮኹ፣ እንደካውያ ቀስ በቀስ በጋለ ድምጽ።

ግርማን፣ ከጅምሩ ለዘብ ብሎ እየጠነከረ የመጣው የዶክተሩ ድምጽ አስደነገጠው። ያማስልበት የነበረውን የሻይ ማንኪያ በዝግታ አስቀምጦ ዓይናቻቸውን ማየት ጀመረ።

"ልጄን ጉድ አደረካት! እኔ አባቷ ባልኖርና ባላወጣው ኖሮ፣ ይህንን ጉዳችሁን ለመሸፈን ስትል፣ ልጄን መድሀኒት አጠጥተህ ልትገላት ነበር ሀሳብህ! " አሉና ሲጋራቸውን በእጅጉ መጠጡት– የመጉረስ ያህል።

የግርማ ልብ በድንጋጤ በወንጭፍ እንደተወረወረ ድንጋይ ቱር ብላ ልትወጣ ምንም አልቀራት። በግንባሩና በጀርባው ላይ የቀዘቀዘ ላብ መነጨ።

"ዶክተር የሚናገሩት አልገባኝም።" አለ ግርማ፣ ፈራ ተባ እያለ።

"እንዴት ሊገባህ ይችላል? ጆሮዎችህ ደንቁረዋል። ዓይኖችህ ጠፍተዋል። ስለዚህ፣ ሊደርስባችሁ የሚችለውን ችግር ቀደም ብላችሁ



ባለመገንዘባችሁ ልጄን ችግር ላይ ጣልካት! አስረገዝካት! የልጄን ህይወት አበላሸሸው!"

"እንዴ! ዶክተር ተሳስተዋል። በፍጹም!" አለ ግርማ፣ የተወቀሰው ያለአግባብ መሆኑን ለመግለጽ።

"እንዴት? እውነት አይደለም?" ሲሉ ጠየቁ፣ ዶክተር ናትናኤል።

"በእርግጥ የማልዋሾት ነገር አለ። ንግሥትን እወዳታለሁ። እሷም የምትወደኝ ይመስለኛል። በልብ ትውውቅ ብዙ ጊዜ ቢኖረንም፣ ፍቅራችንን ይፋ ያደረግንበት ጊዜ ረጅም አይደለም። እና ፣ እንኳን የእርግዝና ደረጃ ቀርቶ፣ አብረን ወጥተን አናውቅም። የወሲብ ግንኙነት ፈጽመን አናውቅም። እውነቱ ይሄ ነው።" አለ ግርማ።

ምንም ሳይናገሩ ትኩር ብለው ለጥቂት ሴኮንዶች ያህል ግርማን በጥርጣሬ አዩት። "እውነቱን ነው የነገርከኝ ግርማ? ከልብህ ነው የነገርከኝ?" ሲሉ ዶክተሩ ጠየቁ።

"አዎ፣ እውነቴን ነው። ዶክተር ፍጹም አይጠራጠሩኝ።" አለ።

የግርማ ልብ በሰማው አስደንጋጭ ዜና በቅናት እንደ ድንች መላጥ ጀምሯል። ከዶክተሩ ጋር ያለውን ቅራኔ ቢያረግብም ፣ ከንግሥት ጋር ጦርነት መክፈቱ የማይቀር ነው።

"ስማ እኔን ለማታለል አትሞክር። ልጅቷ ካለአንተ ሌላ ወንድ አታውቅም። የሠራኸውን ወንጀል ለመሸፈን አትሞክር። ምንም ልታታልሉኝ አትችሉም። ያለፈው አልፏል። በጊዜ አውቄ ልጄን አድኛታለሁ። እንዲወለድልህ ፈልገህ የነበረውን ልጅህን በማጨንገፌ ከፈለክ ልትከሰኝ ትችላለህ! ከእንግዲህ ወዲያ ግን... ከልጄ ጋር እንኳን አብራችሁ ልትውሉ ቀርቶ፣ ሰላምታ ስትለዋወጡ ማየት አልፈልግም! ገባህ? ተጠንቀቅ!" ሲሉ እንደመብረቅ ጮኹበትና ሂሳባቸውን ከፍለው ከመዝናኛ ቤቱ ውልቅ አሉ።

ግርማ በተቀመጠበት ሀውልት መስሎ ቀረ።

## 3

ስምንት ሰዓት ሆኗል–ከቀኑ። በቬሮኒካ ምግብ ቤት ውስጥ ጠረጴዛዎችን አካልለው ከሚታዩት ወንበሮች አንዱን ስቦ ከተቀመጠ አምስት ደቂቃዎች ተቆጥረዋል። ዳመን ያለ ብርሃን ካለው ከዚህ ክፍል

ውስጥ የሚገኙትን ነገሮች ሁሉ በዓይናቹ እየቃኘ አሳልፏቸዋል። ግን ልቡ የተመለከታቸው አይመስልም። አዝኗል። ደምቷል። ከሶስት ሰዓታት በፊት ከዶክተር ናትናኤል ጋር ያደረጋቸው ቃለ-ምልልሶች የልብ ቃር ፈጥረውበታል። የበቀል ስሜት በልቡ ውስጥ መፀነስ ጀምሯል። የሚወዳት ፍቅረኛው ልቧን አልሰጠችውም። ከዚህ በፊት እንደምትወደው ያሳየቻችው ምልክቶች በሙሉ የይስሙላና ማንነቷን የደበቁ ጭምብሎች መሆናቸውን አመነ። ከሌላ ሰው ጋር እየወጣች ከእርሱ ጋር መምሰሏ አናደደው። ዶክተር ናትናኤል ሁኔታውን ባይነግሩት ኖሮ፣ ከአንተ ነው ያረገዝኩት ብላ የሰው ልጅ አባት ልታደርገው ነበር።

ስምንት ሰዓት ከአምስት ደቂቃ ላይ ንግሥት የመዝናኛውን ቤት በር ከፍታ ገባች። ግራ ቀኙን በመመልከት ግርማ ያለበትን ቦታ ካየች በኋላ ወደ እርሱ ተጠጋች። እንደተጨባበጡ ጉንጮቻቸውን ለሰላምታ ካላተሙ በኋላ ከጎኑ ተቀመጠች።

" እሺ? ደህና መጣህ?" አለች ፣ አካባቢውን እየቃኘች።

"አዎ።" አለ ፣ ለዘብ ባለ ድምጽ።

"ግን፣ ተስማምቶሃል። ይሄ የመስክ ሥራ ይሆንህል ማለት ነው።" አለች ፊቱን እየተመለከተች።

ዝም አለ። ጭራሽ ወደ ሌላ አካባቢ ማየት ጀመረ።

"መቼ መጣህ?" ብላ እንደጠየቀችው አሳላፊው መጣ።

"ምን ልታዘዝ?" ሲል ጠየቀ ሰውየው።

ንግሥት ግርማ የሚጠጣውን ተመለከተችና "ቢራ አምጣልኝ።" አለች ለስለስ ባለ አነጋገር። "ምን ሆነሃል?"

"ምን ያልሆንኩት አለ?" ብሎ በረጅሙ ተነፈሰ።

ከጥቁር የቆዳ ጃኬቷ በታች የለበሰችው ነጭ ሸሚዝ ብርሃን የፈነጠቀለትን ጠይም ፊቷንና ትከሻዋ ላይ እንደ መድረክ መጋረጃ ዘርፈፍ ያለው ጥቁር ፀጉሯን አየ። እንደወትሮው ፍቅር ሳይሆን ጥላቻ ጫሩበት። በሰው አምሳያ የተፈጠረች ቆንጆ ሰይጣን መስላ ታየችው።

"እንዴት?" ስትል በድንጋጤ ጠየቀችው።

ዝም አለ።

"ጠዋት ስትደውልልኝ ደህና አልነበርክም ነበር?" ስትል በድጋሚ ጠየቀችው።

"ነበርኩ።" ብሎ ዝም አለ።



አንድ የሚያቃጥለው ነገር እንዳለ ገባት። ቅድም አባትየው ሊያነጋግሩት ከፈለጉበት ጉዳይ ጋር የተያያዘ መሆኑን ጠረጠረች። "አባዬ ቅድም በስልክ ምንድን ነው ያለህ? እሱ ይሆን ያበሳጭህ?" አለች።

ትንሽ ዝምታ ሰፈነ።

"ንግሥት፣ እወድሽ ነበር። አከብርሽ ነበር። በጣም እመካብሽ ነበር። እውነተኛ ሴት መስለሽ ትታይኝ ነበር። አመልክብሽም ነበር። ሆኖም፣ አንቺ ለዚህ ሁሉ የምትበቂ ሆነሽ አልተገኘሽም። ርካሽ መሆንሽን የዛሬዋ ቀን መስክራልኛለች!"

"እንዴ ምንድነው እሱ?" አለች ንግሥት እጅግ ደንግጣ።

"ዝም በይ ደግሞ አትጮኺ፣ ጉድሽን ሰው እንዳይሰማ።"

"ምንድነው ጉዴ?" አለች፣ ትንሽ ፈርጠም ብላ።

"ያስወረድሽው ልጅ የማነው?"

ንግሥት ድንጋጤው እንደ አክርማ ልቧን ሲሰነጥቀው ተሰማት። ከግርማ አፍ ወጥተው የሰማቻቸው ቃላት ከማታውቀው ቋንቋ የተወሰደ ይመስል አልገባ አሏት። "ያስወረድሽው ልጅ፣ ነው ያልከው?" አለች፣ ንግሥት።

"አዎ፣ ንግሥት።"

"ማ? እኔ?"

"አዎ፣ አንቺ!"

"ፍጹም የሆነ ውሸት ነው። ፍጹም የሆነ ውሸት!" ስትል ጮኸች።

"ፍጹም እውነት ነው!"

"ግርምዬ ሙት! ማነው እንዲህ ሲል የነገረህ?" አለች የምታደርገው ጠፍቷት በመርበትበት።

"አባትሽ። አባትሽ፣ ዶክተር ናትናኤል።" አለ በረጅሙ ከተነፈሰ በኋላ።

"እንዴ! ኧረ ባክህ ተው! እሱ እንዲህ አይልም! ሌላ ሰው ነው ፈጥሮ የነገረህ።" አለች።

"እኔ ነኝ ጽንሱን ያወጣሁላት እያሉኝ?"

"ግርማ ቀልድ ነው የምታወራው?" አለች ቆጣ ብላ።" አባዬ እንደዚህ ዓይነት ቅሌት አያወራም።"

ጥቂት ዝም ካለ በኋላ አየር አስወጣና "አሁን ግድየለም ንግሥት። አትደብቂኝ። አባትሽን አውቃቸዋለሁ። አይዋሹም። እሳቸው እንዳውም ከእኔ የፀነሽ መስሏቸው ዱላ ቀረሽ ማስጠንቀቂያ ነው የሰጡኝ። ከአንቺ ጋር መቀጠል እንደሌለብኝ አስጠንቅቀውኛል። እሳቸው ባይሉም ከዛሬ ጀምሮ ከእኔ ጋር ያለሽ ግንኙነት ተቋርጧል። ገባሽ?" አለ።

"ግርምዬ፣ለምን እንዲህ ትሆናለህ? ከእኔ ጋር ያለህን ግንኙነት መቁረጥ ፈልገህ ከሆነ በግልጽ ንገረኝና መለያየት እንችላለን። ግን ያላደረግሁትን ነገር እያነሳህ ብትኮንነኝ አልቀበለውም። በእንደዚህ ዓይነት ወራዳ ተግባር ላይ እንደማልሰማራ ራስህ ታውቃለህ። አባዬ ደግሞ እንደዚህ ያወራል ብዬ አልገምትም። በፍጹም።" አለች፣ አንጀት በሚበላ ዜማ።

"ታዲያ እኔ ፈጥሬ አላወራሁ። አንቺ አይደለሽ በስልክ ያገናኘሽን? ዛሬ ከቀኑ አምስት ሰዓት ላይ እንዳገኛቸው ቀጥረውኝ ተገናኘን። ቀደም ሲል የነገርኩሽን ታሪክ አሰሙኝ። በርግጥ የእኔና የአንቺን ፍቅር እንዳልወደዱት ነግረውኛል።" ሲል ተናገረ ግርማ።

ከግርማ ጋር ያላትን ግንኙነት እንድታቋርጥ አባቷ መፈለጋቸውን ታውቃለች። ብዙ ጊዜ ነግረዋታል። ይሁንና ፣ እርሷንና ግርማን ለማጣላት ሲሉ የእሷን ክብር የሚነካ ምክንያት ፈጥረው እንደማያወሩ ታውቃለች።

"አባዬ የእኛን ፍቅር አይወደውም። እኔና አንተ እንድንጣላ ብሎ ይሆናል ይህን ታሪክ የነገረህ። ግን የምትወደኝና የምታምነኝ ከሆነ የሰማኸው ነገር ፍጹም ውሸት ነው። እኔ ከአንተ ጋር የፍቅር ግንኙነት ከጀመርኩ ወዲህ ፣ ከማንም ወንድ ጋር አልታየሁም። አልወጣሁም። ከቃሌ ሌላ ምስክር የለኝም። የመሰለህን ማመን ትችላለህ። ከእኔ ጋር ለመለያየት ብትፈልግ እንኳ፣ እንደዚህ ዓይነት ክብሬን የሚነካ ምክንያት እንደማትፈጥር አምናለሁ።" አለች። ወዲያው፣ እንባዋ በፊቷ ላይ እንደኳስ ይንከባለል ጀመር። እንባዋን ለመደበቅ ሞከረች። ግን፣ አልቻለችም።

የግርማ ልብ መሸርሸር ቢጀመርም፣ ዶክተሩ የነገሩትን እውነት እንዳልሆነ የሚመሰክር ማስረጃ አላገኘም። ይሁንና፣ ንግሥት እንደምትወደው አውቋል። ከርሱ መለየት አትፈልግም። አባቷ ከርሱ አባት ጋር ያላቸውን የጠበቀ ጓደኝነት እንደምክንያት እየቆጠሩ ሊያለያዩት ቢፈልጉም፣ እርሷ የምትፈልግ አልመሰለውም። 'እኛን ለማለያየት የፈጠሩት ምክንያት ሊሆን ይችላል። ግን እንዴት



ይታወቃል?' ሲል ራሱን ጠየቀ። ወዲያው ደግሞ፣ "አባትሽ እኔን አይወዱኝም።"

"እኔ እወድሀለሁ። ይሄ በቂ መስለኝ። የእርሱ ትርፍ ነው።" አለች ቀበል አድርጋ እንባዋን እየጠራረገች። " ከአንተ ጋር ያለኝን ግንኙነት እንዳቋርጥ ደጋግሞ ነግሮኛል። እሺ ባለማለቴ ይሆናል እኔና አንተን ማጣያ ብሎ ፈጥሮ የነገረህ!" አለች ንድድ ብሏት፣ በእልህ።

"በቃ ረጋ በይ፣ ንግሥትዬ። አትናደጅ። ያን ራስ ምታትሽን እንዳትቀሰቅሺ። እንዳልሽው ሌላው ትርፍ ነው። አንቺ ከእኔ መለየት የማትፈልጊ ከሆነ እኔ እወድሻለሁ። ሌላውን ርሺው።" አለና በመሀረቡ እንባዋን ጠራረገላት።

## 4

ወደ መኖሪያ ቤታቸው እየተጓዙ ነው። መግባት ስላለባቸው ገቡ እንጂ ዛሬ በሆስፒታል ውስጥ የሠሩት ምንም ነገር የለም። በትናንትናው ቀን የሰሙት ዜና እንደቋጥኝ የሚከብድ ነገር ጭንቅላታቸው ላይ አስቀምጦአል። ቀን ሙሉ ሲያስቡ፣ ሲተክዙ፣ ሲንሚነጩና ብስጭት ሲደቁሳቸው ውለው ነው የመውጫ ሰዓት ሲደርስ መኪናቸውን አስነስተው ከሆስፒታሉ ግቢ የወጡት።

ግቢያቸው በር ላይ ሲደርሱ የመኪናቸውን ጡሩንባ አሰሙ። ተገኝ ሮጦ መጥቶ ከፈተ። መኪናቸውን ጋራዥ አስገቡና ወደ እንግዳ መቀበያው ክፍል ገቡ።

ሸዋዬ ከወጥ ቤቱ ወደ ሳሎን የሚወስደውን በር ከፍታ ገባች። ዶክተር ናትናኤልን አተኩራ አየቻቸው። ፊታቸው ላይ መረበሽ ይታያል።

"የት ሄደች ንግሥት?" ሲሉ ጠየቋት።

"እኔ እንጃ፣ አልነገረችኝም።"

ዝም አሉና ሶፋው ላይ ዘጭ አሉ—ዶክተሩ።

"የሚበላ ላቅርብ?" አለች ሸዋዬ።

"ተይው። ይልቅ፣ ወፈር ያለ አንድ ስኒ ቡና ካለ አምጭልኝ።" አሉ። እህል ደመኛቸው ሆኖ ውሏል።

ሸዋዬ ወደ ወጥ ቤቱ ገባች።

ዶክተር ናትናኤል ሲጋራቸውን ለኩሱና ሶፋው ላይ ለጠጥ ብለው የሲጋራውን ጭስ ወደ ሰማይ ለቀቁት። ለጥቂት ሴኮንዶች በዚህ

ሁኔታ ከቆዩ በኋላ ፣ የእጅ ሰዓታቸውን አነበቡ። ከቀኑ አሥራ አንድ ሰዓት ሆኗል።

ልጃቸው በአሁኗ ሰዓት የት እንዳለች ሊያውቁ ባለመቻላቸው ሳይበሳጩ አልቀረም።

ሸዋዬ ትሪ ይዛ ወደ እንግዳ መቀበያው ክፍል ገባች። በሀሳብ መስጠማቸውን አየች። አጠገባቸው መቆሟን እንኳ የተረዱ አልመሰላትም። "ዶክተር ቡናው ደርሷል። " አለች፣ ከፊት ለፊታቸው ካለው የቡና ጠረጴዛ ላይ ትሪውን እያስቀመጠች።

"እ... አመጣሽ። አፈጠንሽው።" አሉ ዶክተሩ፣ ከሀሳባቸው ወጥተው።

"አዎ። በጋዝ ነው ያፈላሁት።" አለችና ወደ ወጥ ቤቷ ስታዘግም፣ የዶክተሩን ጥሪ ሰማች።

"ሸዋዬ፣ እስኪ ነይ። የማጫውትሽ ነገር አለ። " አሉ፣ ለዘብ ባለ አነጋገር።

ርምጃዋን አቁማ ናትናኤልን ከሰማቻቸው በኋላ፣ " እሺ መጣሁ።" ብላ ከሳሎኑ ወጣች።

ሀኪሙ ለሸዋዬ ሊያጫውቷት የፈለጉትን ነገር እንዴት እንደሚጀምሩት ከበዳቸው። ሁሉን ነገር ሊነግሯት አልፈለጉም። የቱን ነግረው የቱን እንደሚተው ግን ማወቅ አልቻሉም። መጨረሻ ላይ ግን፣ ምንም ነገር ሳይነግሯት ወስነው ለሚጠይቋት ጥያቄዎች የምትሰጣቸውን መልሶች ብቻ መስማት ፈለጉ።

ሸዋዬ መጣችና ከአንደኛው የሶፋ ወንበር ላይ ተቀመጠች። 'ምን ሊያጫውቱኝ ነው?' ብላ ራሷን ጠይቃለች። ሌላ ጊዜ ለእንደዚህ ዓይነት ምስጢራዊ ጨዋታ ሲጋብዟት፣ ጉዳዩ የሚመለከተው ንግሥትን መሆኑን ታውቃለች። የዛሬው ግን ሀሳቧን ወደ እዚያ አልወሰደውም። ዛሬ ጠዋት ቁርስ ላይና ከዚያ በኋላ በአባትና ልጅ ፊቶች ላይ የታየው ያልተለመደ ነገር መነሻን የሚመለከት ነው ብላ አሰበች።

"ለእንቺስ ቡና አታመጪም?" አሉ ናትናኤል።

"ከመምጣቶ በፊት ጠጥቻለሁ።" አለችና፣ የእጅ ጣቶቿን አንቋቋች።

"ሸዋዬ አንድ ነገር ልጠይቅሽ።" አሉና እርቆ እንደሚመለከት ሰው፣ ዓይኖቻቸውን ቅዝዝ አደረጉ።

"ምን?" አለችና በጉጉት አየቻቸው።



"ስለ ንግሥቴ አንድ ማወቅ የምፈልገው ነገር አለ። መቸም ፣ ለእሷ የምንቀርባት እኔና አንቺ ነን። እኔ በአባትነት፣ አንቺ ደግሞ ባትወልጃትም ከልጅነቷ ጀምሮ በሞግዚትነት አሳድገሻታልና በእናትነት። ስለዚህ ፣ ለእሷ የማይጠቅሙ አንዳንድ ነገሮች ስታደርግ እኛ ገስፀን ማስተማር አለብን። በልጅቷ ላይ አንዳንድ የማያቸው ነገሮች አሉ። እና ... " ብለው ለጥቂት ሴኮንዶች ያህል ዝም አሉ።

ሸዋዬ ሁለመናዋ ጆሮ ሆና አየቻቸው። የተሟሸ ምጣድ የሚመስሉ ከናፍራቸው ላይ አተኮረች።

"በርከት ያሉ ፍቅረኞች አሏት ይባላል።"

ሸዋዬ እንደመደንገጥ ብላ ግንባሯን እንደ ገመድ ከመቋጠር ሌላ አልተናገረችም።

" እንደዚህ ዓይነት ነገር ለሴት ልጅ እጅግ በጣም መጥፎ ነው። ብዙ ችግሮች ያስከትላል። የወደፊት ህይወቷን ያበላሸዋል።" ብለው ዝም አሉ። "ለመሆኑ ፍቅረኞቿን ታውቂያቸዋለሽ?" ሲሉ በማስከተል ጠየቁ። አጠያየቃቸን ያበላሹ መስሎ ታያቸው።

መልስ አልሰጠችም።

"ምነው ዝም አልሽ፣ ሸዋዬ?" አሉ ቡናቸውን ፉት ካሉ በኋላ ስኒውን እያስቀመጡ።

"አይ ዝም አላልኩም።" አለች። ጥያቄያቸው ትንሽ ሳይቸግራት አልቀረም።

"ነገሩን አታክብጂው። ሁላችንም በልጅነት ጊዜያችን በእንደዚህ ዓይነት ዓለም ውስጥ አልፈናል። አንድ ፍቅረኛ መያዝ ነውር አይደለም። ግን ያንንም፣ ያንንም መያዝ ጥሩ አይደለም። ንግሥቴን ከእንደዚህ ዓይነቱ ተግባር ውስጥ ላወጣት እፈልጋለሁ። ስለዚህ ፣ ፍቅረኞቿ እነማን እንደሆኑ ማወቅ እሻለሁ። ልጅ ስለሆነች ትክክለኛው መንገድ የትኛው እንደሆነ አታውቅም። እኔና አንቺ ልንመክራትና ልንመልሳት ይገባል።" አሉ ዶክተር እንደማግባባት ብለው።

ዶክተር ናትናኤል፣ 'ንግሥት ብዙ ፍቅረኞች አሏት' የሚለውን ወሬ ሰምተው ሳይሆን፣ ከሸዋዬ ማወቅ የሚፈልጉትን ነገር በቀላሉ ማግኘት እንዲችሉ፣ እርሷን ለማሳመን የፈጠሩት ዘዴ ነው።

"ብዙ ፍቅረኞች አሏት የሚባለው ውሸት ነው። ስሟን ለማጥፋት የተወራ ነው። እኔ የማውቀው ግርማን ብቻ ነው። " ብላ ዝም አለች።

ቡናቸውን ጨለጡና፣ "ከእሱ ሌላ የምታውቂው ሰው አለ?"

"ሌላ እንኳ የማውቀው ሰው የለም።"

ከመተርኮሻው ላይ ሜታ አመድ አዝሎ የነበረውን ሲጋራቸውን አነሱና እንዴ ከሳቡ በኋላ፣ "እስታውሼ፡ ዘወትር ስልክ የሚደውሉላትን ሰዎች አስታውሺ።" አሉ ዶክተሩ።

ጥቂት አሰበችና፣ "አፈወርቅ የሚባል ልጅ ሁልጊዜ ይደውልላታል። ግን፣ ያላቸውን ግንኙነት አላውቅም።"

"የአባቱን ስም ታውቂያለሽ?"

"የአባቱ ስም ከዚህ በፊት በላከላት የደስታ መግለጫ ካርድ ላይ አለ። ካርዱን ላምጣው? መኝታ ቤቷ ይገኛል። "አለች።

"እስኪ አምጪው።"

ሸዋዬ ወደ ንግሥት መኝታ ቤት ገባች። ከጥቂት ሴኮንዶች በኋላ የደስታ መግለጫ ካርዱን ይዛ ተመለሰች።" ይኸውና ። አፈወርቅ ምንዳዬ ነው የሚባለው።"

ካርዱን ተቀበሏት።

ካርዱ ላይ በልዩ ልዩ ማራኪ ቀለማት ያሸበረቀ አበባና 'ላቭ' የሚል የእንግሊዝኛ ቃል አለ። ይህ ሁኔታ አፈወርቅ የንግሥት ፍቅረኛ ነው ብለው እንዲደመድሙ ቢጋብዛቸውም፣ ከበስተጀርባው 'ለውድ እህቴ' የሚሉት ቃላት ሀሳባቸውን አስለወጧቸው። 'ለምን አይሆንም? ሰው ለፍቅረኛው እህቴ ብሎ ሊጽፍ ይችላል። ሊሆን ይችላል።' አሉ ለራሳቸው።

ሸዋዬ ዶክተሩ ከራሳቸው ጋር ሲሟገቱ ዝም ብላ አየቻቸው።

"ለመሆኑ አድራሻውን ታውቂያለሽ?" ሲሉ ጠየቋት።

"ኸረ አላውቀውም።"

"ጥሩ። ምን ታደርጊ መሰለሽ... ቀስ ብለሽ በጨዋታ አድርገሽ አድራሻውን ትጠይቂያታለሽ። እኔ ለማወቅ እንደፈለኩ እንዳትነግሪያት።" አሉ።

"እሺ።" አለች ሸዋዬ።

"ከዛሬ ጀምሮ ስልክ ሲደወልላት፣ ከየት እንደሆነ ማወቅና ለእኔ መንገር አለበሽ። ግን፣ ይህንን ንግሥቴ እንድታውቅ አይፈለግም። እሺ?"አሉ ዶክተር።

"እሺ።"አለች።

ተነሱና ወደ ጥናት ክፍላቸው አመሩ፣ ዶክተር ናትናኤል። ከዚህ በፊት የጀመሩት ምርምር አለ። ጠንካራና ጎበዝ ከሚባሉት የህክምና ሰዎች አንዱ ናቸው። በርከት ያሉ የምርምር ሥራዎች



በግልና ከሥራ ጓደኞቻቸው ጋር አበርክተዋል። በትርፍ ጊዜያቸው በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ በሚሰጡት የህክምና አገልግሎት በሚያገኙት ገቢ የምርምር ሥራቸውን ያካሂዳሉ። ከምርምር ሥራ ሌላ በህይወታቸው የሚወዱት ተግባር የለም። ሁልጊዜ፣ የሰውን ልጅ ጤና ለሚፈታተኑ በሽታዎች መፍትሄ ከመፈለግ ወደ ኋላ አይሉም። በአሁኑ ወቅት የወባ በሽታ ማጥፊያ መድሀኒት ለማግኘት ጥረት እያደረጉ ነው።

በጥናትና ምርምር ክፍላቸው ውስጥ ካለ ወንበር ላይ ተቀምጠው ሥራቸውን ለመጀመር ሞከሩ። ግን አልቻሉም። ሳይታወቃቸው ሥራው አስጠልቷቸው ተገኘ። ክፍሉ የሚባላ መሰላቸው። ንቁ አእምሮአቸው ሥራውን አቋቋአል። በረሀ ቀመስ በሆኑ የዓለም ክፍሎች ውስጥ በወባ በሽታ የሚጠቁትን ሰዎች ለመፈወስ የሚያስችል መድሀኒት ለመፈልሰፍ የገቡትን ቃል ለመሻር የተዘጋጁ መሰሉ። የጀመሩትን ትተው ለሌላ በሽታ ማጥፊያ መድሀኒት ለመፍጠር ወሰኑ። ይህ ውሳኔያቸው የመጣው በአሁኗ ደቂቃ ሳይሆን ዛሬ ቀን በሆስፒታል ውስጥ በነበሩበት ጊዜ ነው። ግን አዲሱን ምርምር ለመጀመር የሚያስፈልጉትን ቁሳቁሶችና ገንዘብ ማግኘት አለባቸው። ይህንን በግል ማግኘት ይቸግራቸዋል። እንዴት እንደሚወጡት አሰላሰሉ። ዘዴ አልተገኘም። 'ለምን መጀመሪያ አራት ዓመታት የፈጀብኝን ምርምሬን ከግብ አላደርሰውም?' ሲሉ ራሳቸው ለራሳቸው ጥያቄ አነሱ። 'የለም። እሱን ትተህ ወቅታዊ ስለሆነው ችግር አጣዳፊ መፍትሄ ብትፈልግ ይሻላል።' የሚል መልስ አገኙ። በዚህ ሀሳብ አመኑበት። በርከት ላሉ ደቂቃዎች በዝምታ ሲያስቡ ቆዩና የጠረጴዛቸውን ኪስ በመክፈት ወረቀቶች አወጡ። ማድረግ የፈለጉትን የወሰኑ መሰለዋል። አሁን ያሰቡትን በሽታ ለማጥፋት የሚያስችል መድሀኒት ለመፍጠር በሚያደርጉት ምርምርና ጥናት ላይ፣ የሚያስፈልጓቸውን ቁሳቁሶች፣ የገንዘብ መጠን፣ የሰው እርዳታ፣ እንዲሁም በውጭ አገር ከሚገኙ መሰል ጉዳይ ተመራማሪዎች ሊያገኙ የሚችሉትን የመረጃ ዓይነቶች በዝርዝር መዘገቡ።

ከጥቂት ሰዓታት በኋላ ንግሥት ወደ ዋናው ቤት ገባች። ሳሎኑ ውስጥ አባቷን ስታጣቸው ወደ ጥናት ክፍላቸው አመራች። በሩን ከፍታ ገባች። ዶክተሩ በተመስጦ ሆነው ይጽፋሉ። መግባቷን አላጤኑትም።

ዝም ብላ ቆመች። ልታነጋግራቸው ፈልጋለች። ብዙ ጊዜ በዚህ ክፍል ውስጥ ሳሉ ማንም እንዳያነጋግራቸው አጥብቀው

እንደሚናገሩ ብታውቅም፣ ዛሬ ምንም አልመሰላትም።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ቀና ሲሉ ድንገት አይዋት። ከነበሩበት ዓለም ውስጥ ወጥተው አተኩረው ተመለከቷት።

እሷም አየቻቸው። ዓይኖቿ ዕንባ አቅርረው ነበር። ቢሆንም፣ በአባቷ ላይ ሊተከሉ የተሳቡ ቀስቶች መስለዋል።

ዶክተሩ ልጃቸው እዚህ ክፍል ውስጥ የመጣችበት ምክንያት ገብቷቸዋል። ከግርማ ጋር እንደተጣሉ ጠርጥረዋል። ያቀዱት በመሳካቱ ደስ አላቸው...

## 5

ገብሩ ደምመላሽ ከተኛበት አልጋ ጎን ከሚገኝ ወንበር ላይ እግሮቹ ተንጠልጥለው ተቀምጦአል። ሲጋራውን እየሳበ የደምመላሽን የቀይ ዳማ ፊት ተመለከተ።

"እንዴት ነው እየተሻለህ ነው?" ሲል ጠየቀ ገብሩ።

"አዎ ደህና ነኝ። የእግሬ ቁስል ቢድንም የህሊናዬ እያመረቀዘ አስቸግሮኛል።" አለ ደምመላሽ የገብሩን ጠይም ፊት በዓይኖቹ እየወጋ።

ደምመላሽ የህሊና ቁስል የሚለው የአጎቱ–የገብሩ አባት– እሟሟት በዓይን ህሊናው እየመጣ ስላስቸገረው ነው። እሱና አጎቱ፣ ይልማ ለሽርሽር ወደ ሶደሬ በመጓዝ ላይ ሳሉ በደረሰባቸው የመኪና አደጋ እርሳቸው ወዲያው ሲሞቱ እርሱ ግን እግሩ ላይ የመቁሰል አደጋ ደርሶበታል። መኪናውን በከፍተኛ ፍጥነት ከማሽከርከሩ የተነሳ፣ የአጎቱ ህይወት መጥፋቱ ፀፅቶታል። አእምሮውን እየቧጠጠው አስቸግሮታል።

"ያለፈው አልፎአል። እሱ እንደሆነ አይመለስ። አሁን ስለአንተ ጤንነት ነው ማሰብ።" አለ ገብሩ፣ እንደማጽናናት ብሎ።

"እኔማ ምን እሆናለሁ። እሱ አረፈ እንጂ። እንዴም ሳይመቸው ሲንጠላጠል አረፈው። እማማ ከሞተች ጀምሮ አንድ ጊዜ እንኳ ሳይደሰት በብቸኝነትና በሀዘን ተጨብጦ አሳለፈ። ያፈራውን ሀብት እንኳ በወጉ ሳይበላ ሞተ። ገብሩ፣ የሚያሳዝነው የእሱ ሞት ነው።"

ደምመላሽ አጎቱን፣ አባዬ የአጎቱን ሚስት እማማ እያለ ነው ያደገው። ከህፃንነቱ ጀምሮ ስላሳደጉት እንደአባትና እናቱ ነው የሚያያቸው። ለወላጅ እናትና አባቱ ምንም ፍቅር የለውም። ሌላው ቀርቶ የሚጠራው በአጎቱ በአቶ ይልማ ስም ነው። አጎቱም የእሱ ነገር



አይሆንላቸውም። ቤት ውስጥ ካሉት የሥጋ ልጆቻቸው አብልጠው ይወዱታል። የልባቸውን ያጫውቱታል። ባለቤታቸው ከሞቱ በኋላ ምስጢረኛቸው ደምመላሽ ነበር። ለዚህ ተግባር እሱን የመረጡት አስተዋይ፣ ጨዋና ቁምነገረኛ በመሆኑ ነው። በሥራ በኩልም ጎበዝ ነው። የንግድ እንቅስቃሴያቸውን የሚገመግምላቸውና ሂሣብ የሚያስብላቸው እሱ ነው። በርሳቸው ዘንድ በጣም ይታመናል። ሌሎቹን የቤተሰቡን አባላት አያምኗቸውም። አለመታመኑ በገብሩ ይብሳል።

አቶ ይልማ፣ ገብሩ ተምሮ ከፍተኛ ደረጃ እንዲደርስላቸው ትልቅ ምኞት ነበራቸው። ይሁንና፣ ገብሩ ከዘጠነኛ ክፍል ጀምሮ ያሉት ደረጃዎች የማይወጡ አቀበቶች ሆነውበታል። ዘጠነኛ ክፍል ብቻ ሶስት ጊዜ ወድቋል። ከዚህ የተነሳ ጓደኞቹ 'ኤቬሬዲ' የሚል ቅጽል ስም አውጥተውለታል። እንዲህ የሚሉት፣ በኤቬሬዲ ባትሪ ድንጋይ ላይ ዘጠኝ ቁጥርን ሾልካ ማምለጥ ካቃታት ድመት ጋር በማመሳሰል ነው። የጓደኞቹ ስላቅ እስከነአካቴው ትምህርቱን ጥሎ እቤት ውስጥ እንዲቀመጥ አደረገው። አባቱ ቦዘኔ መሆኑን ጠልተው ከሚያውቁት አንድ የመንደር ሀኪም ጋር እንዲውልና ሀኪሙን ዕቃ በማቀባበል እንዲረዳው ብሎም አንዳንድ "የህክምና ትምህርት" እንዲማር አደረጉ። ጥቂት ወራት እንደሠራ ገብሩ ከመንደር ሀኪሙ ገንዘብ ሲሰርቅ በመያዙ ተባረረ። ከዚያ በኋላ እቤት ውስጥ ተቀምጦ እያምታታ ይኖራል። በዚህ ምክንያት አባትየው በልጃቸው ላይ ቅንጣት ታክል እምነት አልነበራቸውም።

"ከመሞቱ በፊት የነገረህ ነገር አለ እንዴ? " ሲል ጠየቀ ገብሩ—እንደዋዛ።

"ምንም የነገረኝ ነገር የለም። አደጋው እንደደረሰ ራሴን ስቼ ነበር። ሰዎች ደርሰው ከመኪናዋ ውስጥ ሲያወጡን ነው የነቃሁት። በዚያን ጊዜ አባዬ ምንም ትንፋሽ አልነበረውም።" አለ ደምመላሽ ፣ ከአልጋው ላይ ቀና እንደማለት ብሎ።

የአቶ ይልማ ልጆች ደምመላሽ አብሮ አደጋቸው ቢሆንም፣ እንደወንድማቸው አያዩትም። አባታቸው ከእነርሱ ይልቅ እርሱን ስለሚያቀርቡት አይወዱትም። ልክ እንደ ሥጋ ልጃቸው ስለሚያዩት በታላቅነቱ ሀብታቸውን ያወርሱታል ብለው ይሰጉ ነበር። በርሱ ሞግዚትነት መኖር አይፈልጉም። የመናዘዣ ሥርዓት መፈፀሚያ ጊዜ ቢያገኙ ኖሮ፣ ለእርሱ ይናዘዙለት ነበር። ይህንን ገብሩ ብቻ ሳይሆን መላው ቤተዘመድ ነው የሚያውቀው። እና አሁንም ገብሩ ለደምመላሽ

ጥያቄ ያነሳው አባታቸው መናዘዝ ባለመቻላቸው ያቆዩት አደራ እንዳለ ለማረጋገጥ ነበር።

የገብሩ ልብ ረጋ አለ። አባታቸው ሳይናዘዙ ድንገት ቢሞቱም፣ በቤተዘመድ ግፊት ንብረታቸውን በበላይነት እንዲያስተዳድር ደምመላሽን መምረጥ እንዳለባቸው ያምናል። ይህንን አይፈልገውም። ዘዴ መሻት እንዳለበት ተረዳ።

## 6

መኪናቸውን አቁመው ወደ ሳሎን ገቡ። ሸዋዬ በክፍሉ ውስጥ በሚገኙት ግርግዳዎች ላይ የተሰቀሉትን ፎቶግራፎችና ጌጣጌጦች እያወረደች በላያቸው ላይ የሰፈረውን አቧራ ስትወለውል አይዋት።

"እንደምን ዋልሽ ሸዋዬ?" አሉና ወደ መኝታ ክፍላቸው ገቡ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ነጠላ ጫማ አድርገው ተመለሱ። "ሸዋዬ ስልክ ነበረኝ?" ሲሉ ጠየቁ።

"አዎ፣ ዶክተር። አቶ ምስጋናው የሚባሉ ሰው ደውለው ነበር።" አለች ሸዋዬ።

"ደውለው ነበር?"

"አዎ።"

"ምን አሉ? መልዕክት አስቀምጠዋል?" ሲሉ ጠየቁ ዶክተሩ፣ ከኪሳቸው ውስጥ ሲጋራ እያወጡ።

"አዎ። 'ከእኔ ጋር መተዋወቅ መፈለግዎን አቶ እንዳልካቸው አሳውቆኛል። ባጋጣሚ እርሱ ለሥራ ወደ ክፍለ ሀገር ስለሄደ እኔ ደውዬ እንድተዋወቆት ነግሮኛል። ስልክ ቁጥሮን የሰጠኝ እሱ ነው። ከእርሶ ጋር ለመተዋወቅ ዝግጁ ነኝ። በፈለጉ ጊዜ ደውለው ያነጋግሩኝ።' ብለዋል።"ብላ በማስታወሻ ወረቀት ላይ የመዘገበችውን የስልክ ቁጥር ሰጠቻቸው።

ዶክተር ናትናኤል ማስታወሻ ወረቀቱን ተቀበሉና፣"በማንኛውም ሰዓት ይገኛሉ ማለት ነው?" ሲሉ ጠየቁ።

"በዚህን ሰዓት ይደውሉልኝ አላሉም። እንግዲህ በማንኛውም ሰዓት ቢገኙ ነዋ።" አለች ሸዋዬ።



"ጥሩ። ማታ እደውልላቸዋለሁ።" አሉና ሶፋው ላይ ተቀመጡ።

"የታወቁ የባህል ሀኪም ናቸው። በዘመናዊ ህክምና ያልዳኑ ህሙማንን አድነዋል ይባላል።" አሉ ለራሳቸው እንደመናገር ያህል።

ሸዋዬ አልሰማቻቸውም።

"ምን ይፈልጋሉ ዶክተር? ምሳ ወይ ቡና?" አለች።

"ምንም አልፈልግም።" አሉና ሲጋራቸውን መጥጠው ጭስ አስወጡ።

"ዛሬ ብዙ ታካሚዎች ተመዝግበዋል?" ሲሉ ጠየቋት፣ በግል ክሊኒካቸው ውስጥ በትርፍ ሰዓታቸው የሚያካሂዱትን የህክምና ሥራ አስታውሰው።

"ሀያ የሚሆኑ ሰዎች ተመዝግበዋል።"አለች።

"ዛሬ ባይበዙብኝ ጥሩ ነበር። በጣም ደክሞኛል።"አሉ።

"የህክምናው ሰዓት እስኪደርስ ድረስ ሶስት ሰዓታት አለዎት። ለምን ትንሽ አይተኙም?"

"ይሻላል መሰለኝ።"ብለው ዝም አሉ።"ለመሆኑ ንግሥቴ ቢሮ አልገባችም ዛሬ?" ሲሉ ጠየቁ በማስከተል።

"እኔ እንጃ፣ ጠዋት ነው የወጣችው።" አለች።

"ቢሮ ደውዬ አጣኋት። የለችም አሉኝ። ወዴት ሄደች?"

"እኔ እንጃ።"

"የሄደችበትን ቦታ እንዴት አልነገረችሽም?"

"እኔ ምን አውቄ።"

ዝምታ ሰፈነ።

"እኔ ምልሽ ሸዋዬ ፣ ያንን ያልኩሽን ጉዳይ እየተከታተልሽ ነው?"

"አዎ።"

"ምን አዲስ ነገር አገኘሽ?"

ጥቂት እንደማሰብ አለችና፣" እስካሁን የሚደውለው ግርማ ብቻ ነው።" አለች።

"አሁንም ይደውላል?" ሲሉ በመደንገጥና በመገረም ስሜት ጠየቁ።

በዶክተሩ ስሜት ግራ ተጋባችና፣ "ይደውልላታል። ትናንት ከመስከ ሥራ እንደተመለሰ ደውሎላት ነበር።"አለች።

"እውነትሽን ነው?" ሲሉ ጠየቁ ዶክተሩ፣ አሁንም ድንጋጤ በተቀላቀለበት ሁኔታ።

"አዎ።"

"ከእሱ ጋር ለመዋል ነዋ ከሥራ የቀረችው።"

"አይመስለኝም። ነገ በስምንት ሰዓት ነው ለመገናኘት የተቀጣጠሩት።" አለች ሸዋዬ።

"ታዲያ የት ሄደች?"

"እኔ እንጃ፣ እንግዲህ። "አለች።

ዝምታ ሰፈነ።

"በቀደም ዕለት ፣ አፈወርቅ የሚባለውን ልጅ ለማነጋገር እንደሚፈልጉ ገልፀውልኝ ነበር። አነጋገሩት?"

"አላነጋገርኩትም። ጊዜ አላገኘሁም ነበር።" የእጅ ሰዓታቸውን እያዩ፣ " ለምን አሁን ሄጄ አላነጋግረውም?" ሲሉ ራሳቸውንም፣ ሸዋዬንም ጠየቁ።

ሸዋዬ የአፈወርቅን አድራሻ ከንግሥት ልታገኝ የቻለችው ዶክተር ባዘዟት በሶስተኛው ሳምንት መጨረሻ ላይ ነበር።

"እኔ እኮ እስካሁን ያነጋገሩት መስሎኝ ነበር።"አለች።

"ሸዋዬ ጊዜም ቀልብም አጥቼያለሁ።"አሉና ከመቀመጫቸው ተነስተው ወደ መኝታ ክፍላቸው ገቡ። የቆዳ ጫማቸውን አድርገው ተመለሱ።

"አሁን ሊሄዱ ነው እንዴ?" አለች ሸዋዬ።

"አዎ። ምንአልባት እኔ ከመመለሴ በፊት ከመጣች ወዴት እንደሄድኩ እንዳትነግሪያት።"አሉና ከሳሎኑ ወጡ።

## 7

ሜክሲኮ አደባባይን አልፈው ልደታ ቤተክርስቲያን አጠገብ ሲደርሱ፣ ወደ ቢሪሞ ወፍጮ አካባቢ በሚወስደው መንገድ ታጠፉ። ትንሽ እንደተጓዙ መኪናቸውን ዳር አስይዘው አቆሙ። ወረዱና አካባቢውን መቃኘት ጀመሩ። የአፈወርቅ ቤት የት እንደሆነ ሸዋዬ የሰጠቻቸው አድርሻ በቀላሉ ሊነግራቸው አልቻለም። የሚፈልጉት ቀበሌ የትኛው እንደሆነ ለማወቅ ሰዎች መጠየቅ እንዳለባቸው ተገነዘቡ።

"አንተ ልጅ ና እስኪ!" ሲሉ ተጣሩ፣ አንድ ወጣት በአጠገባቸው ሲያልፍ አይተው።



"አቤት!"አለና ተጠጋቸው፣ ልጁ።

በብጫቂ ወረቀት ላይ የተጻፈውን ማስታወሻ አዩና የሚፈልጉትን ቀበሌ በመንገር እንዲያሳያቸው ጠየቁት።

"ቀበሌው እዚህ ፊት ለፊት ከምታዩዋቸው ቤቶች ጀምሮ ማዶ እስከምታዩት ድልድይ ድረስ ነው።" አለ ልጁ።

"አፈወርቅ ምንዳዬ የሚባል ሰው ታውቃለህ?" ሲሉ ጠየቁት ናትናኤል።

"እ... የአፈወርቅን ቤት ነው የሚፈልጉት?... "አለ ልጁ እንደሚያውቀው ለማስረዳት።

"አዎ፣ ታውቀዋለህ?"

"አዎ፣ በዚህ መንገድ ወደ ውስጥ ገብተው ወደ ግራ ሲታጠፉ የሚያገኙት የቆርቆሮ አጥር የእሱ መኖሪያ ቤት ነው።" አለ።

"ጥሩ። አመሰግናለሁ።" አሉ።

ግቢው ያለበት አካባቢ ባተጠጉ ቁጥር ስሜት የሚረብሽና የሚያስጨንቅ ድምጽ ይሰማቸው ጀመር። የግቢው በር በሰፊው ተከፍቷል። ትልቅ ድንኳን ተደኩኗል። ብዙ ሰዎች ተሰብስበዋል። ለቅሶው ቅልጥ ብሏል። ወንዱ ሴቱ ይጯጯሀል።

ናትናኤል ሁኔታው አስጨንቋቸው በመጡበት እግራቸው ለመመለስ ከወሰኑ በኋላ፣ ተውት። ሰዎችም ስላዩዋቸው መመለሱ አሳፈራቸው። ወደ ግቢው ውስጥ ገቡና ከአንድ አግዳሚ ወንበር ላይ ከተቀመጡት አስተዛዛኞች ጋር ተቀላቀሉ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ፣ ከጎናቸው የተቀመጠውን አንድ ሰውዬ፣ "ማን ነው የሞተው?" ሲሉ ጠየቁት።

ቀና ብሎ አያቸውና፣"አፈወርቅ።" ብሎ ጎንበስ አለ።

ዶክተር እንደበርሀ እንጨት፣ በድንጋጤ ድርቅ አሉ። ዓይኖቻቸውን በሰውየው ፊት ላይ እንዳጣበቁ ቀሩ።። መናገር ፈለጉና አቅቷቸው አቀረቀሩ። በጣም የሚቀርባቸውን ወዳጅ ሞት ቢረዱ እንኳ ይህን ያህል የሚደነግጡ አይመስልም። ዶክተሩ፣ አይተውት የማያውቁት ሰው ሞት እንዲህ ያስደነገጣቸው ለምን ይሆን?

ሰውየው የዶክተሩን መደንገጥ አይቶ፣ "አላወቁም ነበር?" ሲል ጠየቀ።

ዶክተር ጥቂት ዝም አሉና ፣"አዎ፣ አላወቅሁም ነበር።" በማለት መለሱለት።

"ለመሆኑ፣ ምን ሆና ነው የሞተው፣ታምሞ ነበር?" ሲሉ በማስከተል፣ ሰውየውን ጠየቁት።

"መታመም እንኳ አልታመመም።" አለ ሰውዬው፣ ሀዘን ውጦት።

"ታዲያ በምን ሞተ?"

"አይ... ቢያወሩት ምን ያደርጋል!" አለና ሰውዬውም ንግግሩን ገታ።

ዶክተር በቂ መልስ ባለማግኘታቸው በጥያቄ ዓይነት ሰውዬውን ተመለከቱት።

"ራሱን ሰቅሎ ነው የሞተው።" ብሎ ዝም አለ፣ ሰውዬው።

"እውነቶን ነው?"

"አዎ!"

ድንጋጤያቸውንና ጥርጣሬያቸውን አጎላው። ምንም ሳይናገሩ ከቆዩ በኋላ ፣ "ምን ሆንኩ ብሎ ነው ራሱን የሰቀለው?" ሲሉ ጠየቁ ዶክተሩ።

"አይ... የሰው ነገር ምን ይታወቃል? ብቻ ይበሳጭ ነበር አሉ። በምን እንደተበሳጨ እንኳ የታወቀ ነገር የለም።" አለ ፣ ሰውዬው።

አፈወርቅ ተሰቅሎ የሞተበት ምክንያት ለሰውዬው ግልጽ ባይሆንም፣ ለዶክተር ግን የሆነላቸው ይመስላል። እስከዛሬ ለማንም ባልነገሩትና በልባቸው ውስጥ አፍነው በያዙት ምክንያት ነው ብለው ጠርጥረዋልም፣ አምነዋልም።

በዚህ መሀል፣"አባዬ"የሚል ድምጽ ከበስተኋላቸው በመስማታቸው፣ ዶክተር ፊታቸውን አዞሩ። አዲስ ፊት አልሆነባቸውም። ፊቷ ጥቁርቁር ብሏል። ዓይናቿ ድልህ ይመስላሉ። ረጅም ፀጉሯን በሻሽ አፍና አስራዋለች። ከወትሮው ብዙ ዕድሜ የጨመረች መስላ ታየቻቸው።

"እዚህ ምን ታደርጊያለሽ?" ሲሉ ጠየቋት።

"ሟቹን አውቀዋለሁ እኮ። ጓደኛዬ ነበር።" አለች ንግሥት፣ እንባ እየተናነቃት።

ዶክተር ከወንበራቸው ተነሱና፣ "ነይ እስኪ።" በማለት ከግቢ ወጡ።

ንግሥት ተከትላቸው ወጣች። መኪናቸውን ካቆሙበት ቦታ ደረሱ። በሩን ከፍተው ገቡ።



"አፈወርቅን የት ነበር የምታውቂው?" ሲሉ ጠየቋት፣ ፊቷን ሳያዩ።

"ትምህርት ቤት። ተማሪ ሳለሁ ነው የተዋወቅነው።"

የመኪናቸውን ሞተር አስነሱ። ጉዞ ጀመሩ።

ንግሥት አባቷን ትኩር ብላ አየች።"ወዴት ነው የምንሄደው?" ስትል ጠየቀች።

"ወደቤትሽ" አሉ ፈርጠም ብለው። " ከእንግዲህ ወዲያ እዚህ ቦታ መታየት የለብሽም።" አሉ በትዕዛዝም፣ ሀሳብ በመስጠትም ዓይነት።

"እንዴ! ሳላስቀብር? አስክሬን ለምርመራ ወደ ሆስፒታል ሄዶ አልተመለሰም። እስኪመለስ ጠብቄ ማስቀበር አለብኝ።"

"በፍጹም አይቻልም!" በማለት አፈጠጡባትና ዓይናቻቸውን እንደገና ወደ መንገዱ አዞሯቸው።

"ምነው አባዬ፣ ብዙ ጊዜ አብሮኝ የቆየ ጓደኛዬ ነበር እኮ። እስክ ሠልስት እንኳ መቀመጥ ባልችል፣ ሥጋውን አፈር ማልበስ የለብኝም?" አለች፣ ዕንባዋ እየቀደማት።

"የለብሽም። ከዛሬ ጀምሮ እዚህ መድረስ የለብሽም። ይገባሻል? ከእኔ ቃል የምትወጪ ከሆነ..." ብለው ንግግራቸውን ገቱት።

የአባቷ ሁኔታ አስደነገጣት። ፈጽሞ ያልጠበቀችው ባህሪያቸው አሳሰባት። እሷ አባቷን የምታውቃቸው በርኅሩህነታቸውና ለማኅበራዊ ኑሮ ባላቸው ትልቅ ግምት ነበር። ዛሬ ግን የወትሮው አባቷ፣ ዶክተር ናትናኤል፣ ሆነው አልተገኙላትም። ዛሬ ብቻ ሳይሆን፣ ከጥቂት ቀናት ጀምሮ ጭራሽ ተለውጠዋል። አብሯት ያደገው ፍቅራቸው እንደጠወለገ አበባ እየረገፈ መምጣቱን ካወቀች ሰንበትበት ብሏል።

"አባዬ ምን አጥፍቼ ነው?... የሠራሁት ነገር ካለ ልወቀውና ይቅርታ ልጠይቅህ። ከጥቂት ቀናት ወዲህ ለእኔ ያለህ ፍቅር ተለውጦብኛል። ጠልተኸኛል። ታኮርፈኛለህ። ልጅህ ነኝ። ለምን ጥፋቴን ትደብቀኛለህ? በማላውቀው ምክንያት ከማኅበራዊ ኑሮ ለምን ታገለኛለህ?" አለች ስቅስቅ ብላ እያለቀሰች።

ሊገስጿት ፈልገው ነበር። ግን አልቻሉም። ለቅሶዋ ልባቸውን ሸረሸረው። አዘኑ። የልጃቸው መከፋት በርሳቸው ላይም ሀዘን ጫረ። ሳያውቁት፣ ሳይፈልጉት ለልጃቸው ፍቅራቸውን ነፍገው እንደነበር

ተገነዘቡ። ያለእርሳቸው ማንም ለሊላት አንድ ልጃቸው ፊት በመንሳታቸው ተፀፀቱ።

የመኪናቸውን ፍጥነት ቀነሱ። በመጨረሻም አቆሙና ንግሥትን ተመለከቷት። እጃቸውን ትከሻዋ ላይ ጣል አደረጉ። "ንግሥቴ፣ አንድ ልጄ፣ አንድ ዘመዴ፣ እስከፋሁሽ፣ ቅር አሰኘሁሽ፣ ወድጄ እኮ አይደለም። አንቺን ጠልቼ አይደለም። ማኅበራዊ ኑሮም ጠልቼ አይደለም። የሰውን ልጅ ስለወደድኩ እንጂ። አውቃለሁ፣ አንቺን በመጥላት፣ አንቺን በመበደል ለሊላው.... " አሉና እያስጨነቁቻቸው ከውስጣቸው የሚወጡትን ቃላት ገቱ። በመቀጠልም፣ "ንግሥቴ፣ ይቅርታ። ይቅርታ ልጄ።" በማለት ሀዘኔታና ፀፀት ባለው ድምፀት ጠየቋት።

የአባትየው ፀፀት ልቧ ውስጥ ገባ። ዕንባዋ እንደአባተ ገሞራ ፈንድቶ ከቀኝ ትከሻቸው ላይ ልጥፍ አለች።

ዶክተሩ በዓይናቸቸው ባያነቡም፣ በልባቸው አለቀሱ። ውስጣቸው በሀዘን ታመሰ። ለጥቂት ደቂቃዎች ያህል በዝምታ ከተዋጡ በኋላ ልጃቸውን ቀና አደረጓት። ዕንባዋን ከጠረጉላት በኋላ ግንባሯ ላይ ሳሟት።" ይቅርታ አድርጊልኝ የእኔ እመቤት። ንግሥቴ ይቅርታ።" አሉ፣ ፍጹም በሆነ ትህትናና ፀፀት ባዘለ ድምጽ።

እሷም አልጨከነችባቸውም። ጠባሳ አልባ የልጅነት ቂሟን ከልቧ ውስጥ ፋቀች። መኪናቸውን አስነስተው ወደ መኖሪያ ቤታቸው መንዝ ጀመሩ። በመንገድ ላይ ምንም ቃላት አልተለዋወጡም። ሁለቱም በልቦቻቸው የሚያወሯቸውና የሚያሟግቷቸው ጉዳዮች ነበሩ...

እቤት ገቡ።

"ሸዋዬ ... ሸዋዬ፣... "ሲሉ ተጣሩ ዶክተሩ።

ሸዋዬ ከወጥ ቤቱ ወጣች። " እቤት ዶክተር! እንደምንዋልሽ ንግሥቴ?" አለች ንግሥትን ወዲያው ስታይ።

"ደህና ዋልሽ?" አለች ንግሥት።

"እስኪ ምሣ አቅርቢላት። እህል የቀመሰችም አትመስልም፣ ዛሬ።" አሉ ዶክተር።

"እንዴ አባዬ! አስክሬኑ ሳይቀበር?"

"ተቀበረ አልተቀበረ እሱ አንዴ ሞቷል። ራስሽን አትጉጂ። ለማንኛውም እህል ቅመሺ።" አሉ ዶክተር።

"እኔ አልበላም።" አለች ንግሥት።

"ለምን?"



"ምን ማለትህ ነው አባዬ የቆየ ጓደኛዬ እኮ ነው!"

"ታዲያ አብረሽው ልትቀበሪ ነው ወይስ ምንድን ነው አሳብሽ?" አሉ፣ ሳይታወቃቸው በመቆጣት።

ደንግጣ ዝም አለች። ወዲያው ደግሞ፣ "ሳላስቀብር እህል አይዋጥልኝም።" ስትል ተናገረች።

"ከቤት መውጣት እንደሌለብሽ የነገርኩሽ መሰለኝ። ከእንግዲህ ወዲያ እዚያ ቤት መሄድ የለብሽም።" አሉ ዶክተር፣ የሰውዬው ራሱን መግደያ ምክንያት እርሷ ናት ብለው በመገመት።

"ለምን አባዬ?" አለች አሁንም፣ እንባዋ እያነቃት።

"እንዲሁ። መሄድ አትችይም። ከቃሌ መውጣት የለብሽም!" አሉና የቅድሙን ንዴታቸውን አመጡት።

ስቅስቅ ብላ አለቀሰች።

## 8

ንግሥት መኝታ ቤቷ ውስጥ ገብታ ተኝታለች። ዛሬ በአፈወርቅ ሞት ከልቧ በማዘኗና ከአባቷ ጋር በተነሳው ግጭት ምክንያት ብዙ አልቅሳለች። ለቅሶው ለከፉ ራስ ምታት ዳርጓታል። እህል ያልቀመሰው ሆዷ ለድካም አሳልፎ ሰጥቷታል። ድካም በተራው ደግሞ፣ ለዕንቅልፍ ወርውሯታል።

ሸዋዬ ስትገባ ንግሥት ሀይለኛ ዕንቅልፍ ይዟት አየች። ተጠጋቻትና ፣ "ንግሥት፣... ንግሥት፣... ንግሥት፣..."አለች።

ንግሥት ነቅታ በብዥታ ሸዋዬን አየቻትና ተመልሳ ጋደም አለች።

"ተነሽ እንጂ። ብዙ ተኛሽ እኮ። እህል ሳትቀምሽ እንቅልፍ ዋጋ የለውም እኮ።"

"ተይኝ ባክሽ ሸዋዬ።"

"ተነሺ። ቆንጆ መክሰስና ቡና አዘጋጅቼልሻለሁ። በይ ተነሺ። ጎሽ የኔ እህት።" አለች ሸዋዬ ንግሥትን እንደማባበል ብላ።

ሸዋዬ ንግሥትን እንደ ልጇ ነው የምትንከባከባት። ከአባቷ ሌላ ለንግሥት የሚያዝንላት ፣ የሚያስብላትና የሚሳሳላት ሰው ቢኖር ሸዋዬ ብቻ ናት። ንግሥትን በጣም ትወዳታለች። ንግሥትም የዚያኑ ያህል ሸዋዬን ታከብራታለች፣ ትወዳታለች። ሲከፋት፣ ሲቸግራት

የምታማክረው ሞግዚቷን ሸዋዬን ነው። በመሀከላቸው የሥጋ ዝምድና ያለ ይመስላል–ለሚያያቸው።

"ባይሆን ቡናውን ስጪኝ፣ የሚበላው ይቅርብኝ።" አለች፣ ከአልጋዋ ላይ ቀና ብላ እየተቀመጠች።

"እንዴ ምን ማለትሽ ነው? በባዶ ሆድ ቡና አይጠጣም። መጀመሪያ እህሉን መብላት አለብሽ። ከሁሉም በፊት እስኪ መታጠቢያ ቤት ሂጅና ፊትሽን ታጠቢው። ይቀልሻል። ወይስ በማስታጠቢያ ላምጣልሽ?"

"እይ። ተይው ሂጂ እታጠባለሁ። " አለችና ከአልጋው ላይ ወርዳ ነጠላ ጫማዎቿን አጠለቀች። ታጥባ መጣች።

"በይ ተቀመጭ። እኔም አልበላሁም አብረን እንብላ።" አለችና ተከድኖ የነበረውን ማዕድ ከፈተችው። የወጥ ሳህኖቹን ተራ በተራ እያነሳች ወጥ ጨለፈችና፣ " በይ ጀምሪ ንግሥትዬ።" አለች።

መብላት ጀመሩ። አልፎ አልፎ፣ ሸዋዬ "ብይ" ከማለቷ በቀር፣ ሌላ ቃላት ሳይለዋወጡ ጥቂት ደቂቃዎች አለፉ።

"ብይ እንጂ ምን ማለትሽ ነው?"

"በቃኝ ሸዋዬ። ብዙ በላሁ።"

"እንዳንጣላ እንግዲህ! እሺ አልጫውን ብቻ ብይ።" አለች ሸዋዬ፣ ፍቅርን ባዘለ ስሜት በመቆጣት።

"በቃኝ። አልበላም። ቡናውን ቅጂልኝ።"

ቡናው ተቀዳ።

ንግሥት በስኒው ውስጥ ያለውን ስኳር ለማሟሟት ማንኪያውን ማዟዟር ጀመረች። ማንኪያውን ማስቀመጫያው ላይ ካኖረች በኋላ የስኒውን ጆሮ በመያዝ ፉት አለች።

"አባዬ የት ነው ያለው?" ስትል ሸዋዬን ጠየቀቻት።

"ክሊኒክ ገብተዋል። ሥራ እየሠሩ ነው።"

"አሥር ሰዓት ሆኗል እንዴ?" አለች፣ የእጅ ሰዓቷን እያየች።

"አዎ።" አለች ሸዋዬ።

ዝምታ ነገሠ። ሸዋዬ ገበታውን አነሳችና ይዛ ሄደች። ከጥቂት ቆይታ በኋላ ስትመለስ ንግሥት አልጋዋ ላይ ጋደም ብላ መጽሔት ስታገላብጥ አየቻት። ከአልጋዋ ጫፍ ላይ ተቀመጠችና ከቡና ማቅረቢያው የሸክላ ጀበና ውስጥ ቡና ቀዳች።

"ንግሥትዬ ደገምሽ ?"



"አልደገምኩም። ካለ ቅጂልኝ።" አለች ሸዋዬን ሳታይ መጽሔቱንእያየች።

"ሽረ አለ።" አለችና ቀድታ ስኳሩን አማስላ ሰጠቻት።

ጥቂት ዝምታ ተፈጠረ።

"ንግሥትዬ ፣ ዛሬ ከዶክተር ጋር በምን ተጣላችሁ?" ስትል አለሳልሳ ጠየቀቻት።

ዝም አለች-ንግሥት።

"ምነው ዝም አልሽ? አልሰማሽኝም ወይስ ከእኔ ጋር ላለማውራት ፈልገሽ ነው?"አለች ሸዋዬ።

ንግሥት ቀና ብላ እየቻትና ፣"ምንድን ነው ያልሽኝ?" አለች፣ ሸዋዬ ያነሳችላትን ጥያቄ ያልሰማች መስላ።

"ከዶክተር ጋር ዛሬ በምን ተጣላችሁ?"

"ምን ዛሬ ብቻ፣ ከርሱ ጋር መጣላት ከጀመርን ቆይቷል። በየሄድኩበት እንደጥላዬ ይከተለኛል። የማደርገውን ሁሉ በየቀኑ ይጠይቀኛል። ምን እንዳደረኩ እግዜአብሔር ይወቀው!" አለች፣ ምሬት ባለው ድምፀት።

ቡናውን ፉት ካለች በኋላ ስኒውን አስቀመጠች።"ንግሥትዬ፣ እሳቸው እኮ ለአንቺ ብለው ነው።"

"ምኑን ነው ለእኔ ብሎ? "አለች፣ እንደመቆጣት ብላ።

"የአንቺ ሕይወት ሲያምር ይወዳሉ። ጥሩ ትዳር አግኝተሽ ፣ ጥሩ ቤተሰብ መሥርተሽ፣ ደስ የሚያሰኝ ኑሮ እንድትኖሪ ነው የሚፈልጉት። ይህ እንዲሆን ደግሞ የአባትሽ ምክር አስፈላጊ ነው።"

" በየት ወጣሽ በየት ገባሽ መባሉ ነው ምክር? ይሄ እኮ አንድ ቀናተኛ ባል በሚስቱ ላይ የሚያሳየው ድርጊት ነው።"

"መስሎሽ ነው እንጂ አይደለም። ለአንቺ ጥሩ ከማሰብ የተነሳ፣ ከእነማን ጋር እንደምትውይ ለማወቅ ነው። አየሽ፣ ሰውን የሚያለማውም የሚያበላሸውም ጓደኛ ነው። እና፣ ጥሩ ጓደኛ መምረጥ እንድትችይ መሰለኝ ዶክተር የሚከታተሉሽ።" አለች ሸዋዬ።

"እኔ ህፃን ልጅ ነኝ? ራሴን የማውቅና መቆጣጠር የምችል ሰው ነኝ እኮ!" ስትል ተቆጣች።

"ነሽ። ግን፣ በወጣትነት ዕድሜያችን የምናደርጋቸው ድርጊቶች ሁሉ ለእኛ ትክክል ቢመስሉንም፣ ዕድሜ በጠገቡ ሰዎች ዘንድ ግን ትክክል ላይሆኑ ይችላሉ። በወጣትነታችን ችኩሎች ነን። ስለዚህ እንሳሳታለን። ከመሳሳትሽ በፊት ሊያርሙሽ ስለፈለጉ ብቻ ነው

የሚከታተሉሽ።" አለች ሸዋዬ፣ ዶክተር አንድ ጊዜ ስለንግሥት ሲነሳ የነገሯትን እስታውሳ።

"እሺ አንቺ ያልሽው ከሆነ አይከፋም ነበር። ግን አይመስለኝም። ዛሬ ለቅሶ ቤት ድረስ ተከትሎኝ መጥቶ ከቤት እንዳትወጪ ብሎ በመቆጣት ይዞኝ መጣ። ከሰዎች ጋር መቀላቀል አለብኝ እኮ። በሀዘናቸውና በደስታቸው ጊዜ ተካፋያቸው ካልሆንኩ ብቻዬን እኮ ነው የምቀረው። ይህን ለምን እከለክላለሁ? ምንድን ነው ሰው አይይሽ ፣ ከቤት አትውጪ ብሎ ነገር?" አለች በመቆጣት።

ሸዋዬ ዝም አለች። "ለመሆኑ ማን ነው የሞተው?" ስትል ጠየቀች።

"አንድ ጓደኛዬ ነው። አፈወርቅ እያልኩ ብዙ ጊዜ አንስቼልሻለሁ። ታውቂዋለሽ።" አለች ንግሥት።

"ውይ! በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ! ምን ነካው?" አለች በሁለት እጆቿ ጭንቅላቷን ይዛ።" ታሞ ነበር?"

"ኧረ አልታመመም።"

"ታዲያ በምን ሞተ?"

"ራሱን ሰቅሎ።" አለች፣ እንባ እየተናነቃት።

"በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ! ምን ሆንኩ ብሎ ተሰቀለ? ምን ቸገረው?" አለች ሸዋዬ ፣ ዘግንኗት።

"አልታወቀም።"

"አይ የኛ ነገር! ትዕግስት የለን! ለሚያልፍ ነገር እንቸኩላለን። የመሥሪያ ቤት ጓደኛሽ ነበር?"

"አይደለም። ትምህርት ቤት ሳለሁ ነው የተዋወቅሁት።"አለች ንግሥት፣ እንደመተከዝ ብላ።

"ፍቅረኛሽ ነበር እንዴ?" አለች፣ በፈራ ተባ።

"አልነበረም። እንዲሁ ጓደኛሞች ነበርን። ምስጢረኛዬ ነበር። ይገርምሻል፣ በጾታችን ምክንያት በሚያጋጥሙን ችግሮች ላይ ሁሉ እንነጋገርባቸዋለን። መፍትሄ የምንለውን እንለዋወጣለን። በጣም ግልጽና የዋህ ልጅ ነበር። ትምህርት ቤት ሳለን፣ ክፍል ውስጥ አብረን እንቀመጣለን፣ አብረን እንውላለን ፣ ወደ ቤታችንም ስንሄድ አብረን ነበር። ከዚህ የተነሳ ተማሪዎች እንኳ ሮሚዮና ዡሊት እያሉ ይጠሩን ነበር–ፍቅረኛሞች መስለናቸው። ታዲያ ይህን የመሰለ ጓደኛዬ ሲሞት ማዘን የለብኝም? እስከ ሰልስት ባልቀመጥ፣ መቅበር የለብኝም? ይህን



እንዳላደርግ እኮ ነው አባዬ የተቆጣኝ። ተገቢ ነው? እንዲህ ነው ቁጥጥር?" አለች ንግሥት፣ ከልቧ አዝና።

"እንዲህ ከሆነስ አጥፍተዋል። ዶክተር ልክ አይደሉም። እሳቸውም ደህና አይመስሉኝም። መበሳጨት፣ ማዘን፣ መተከዝ ጀምረዋል። እኔ ደግሞ ይህ የሚያደርጉት ምርምር፣ ውጤት አልባ ሆኖባቸው የተበሳጩ ነበር የሚመስለኝ። ግን ሲውል ሲያድር በዚህ ሳይሆን በሌላ ምክንያት ነው መስሎ የታየኝ። ብቻ ምንም ይሁን ምን፣ አንቺ ያሉሽን መፈጸም አለብሽ። እዚያ ቦታ አትሂጂ አሉሽ ፣ በቃ አትሂጂ።

"እንዴ ምን ማለትሽ ነው ሸዋዬ? በመቃብሩ ላይ ባለመገኘቴ ተነስቶ ባያየኝም፣ ቤተሰቦቹ ይታዘቡኛል። በጣም ይቀየሙኛል።"

"ግዴየለም፣ መቅበር ባትችይም ማታ እንደምንም ተደብቀሽ ደረስ ብለሽ እንድትመጪ ሁኔታዎችን አመቻችልሻለሁ። እንዴ ደረስ ብለሽ ትመጫለሽ።" አለች ሸዋዬ በማባበል።

"ቀብር ላይ ሳልገኝ ቤት ስደርስ ሰው ምን ይለኛል?"

"ምን ይልሻል? ታመሽ እንደነበር መግለጽ ነው። አውቀሽ አይደለም የቀረሽው። ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው። ይሄ አያሳስብሽ።" አለች ሸዋዬ።" አሞሽ እንደነበር ንገሪ–ለሚጠይቅሽ ሰው።" አለች በመቀጠል።

"አሁን ስንት ሰዓት ሆኗል?"

"አሥራ አንድ ሰዓት ተኩል። አንድ ሰዓት ላይ ትሄጃለሽ፣ዶክተር ህክምና ጨርሰው ወደ ጥናት ክፍላቸው ከገቡ በኋላ። እዚያ ከገቡ ቢያንስ ሁለት ሰዓታት ስለሚቀዩ አንቺ ቶሎ ደረስ ብለሽ ትመጪያለሽ። አይሻልም?"

"ምን አልባት የት አለች ብሎ ቢጠይቅሽስ?"

"አይጠይቁም። ከጠየቁ ተኝታለች ብዬ እነግራቸዋለሁ። መቼም መኝታ ቤትሽ አይገቡም።"

"ጥሩ።"አለች ንግሥት።

"ሰዓቱ እስኪደርስ ድረስ ትንሽ ተኚ። እኔም ወደ ሥራዬ ልሂድ። መጥቼ እቀሰቅስሻለሁ።" አለችና የመኝታ ቤቱን በር ዘግታ ወጣች።

## 9

ለቅሶው ቆሟል። በድንኳኑ ውስጥ ብዙ ሰዎች ተቀምጠው በዝቅተኛ ድምጽ ያወራሉ። ንግሥት ከጓደኛዋ ፣ ከሲሳይ ጋር ሴቶቹ ካሉበት ክፍል ውስጥ ተቀምጣለች። አስከሬኑ ሳይቀበር በማደሩ ደስ ብሏታል። ሲያስጨንቃት የነበረው ራስ ምታትና ሀሳብ ጥሎአት በርሯል።

"ሲሳይ፣ መሸ። እንሂድ። ሶስት ሰዓት አለፈ።"አለች ንግሥት፣ የእጅ ሰዓቷን እያየች።

"ትንሽ እንቆይ። አርአያ መኪና ይዟል። ይሸኘናል።" አለች ሲሳይ።

"መጥቷል እንዴ?" ስትል ጠየቀች።

"አዎ። አልተገናኛችሁም እንዴ?"

"አላገኘሁትም። የት ነው ያለው?"

"ድንኳን ውስጥ ነው።"

ሻምበል አርአያ የሲሳይ ፍቅረኛ ነው። ሲሳይ የንግሥት የቅርብ ጓደኛ ብትሆንም፣ ስለ ፍቅረኛዋ ብዙ አውርታላት አታውቅም።

"ያው እንደውም መጣ።" አለች፣ እነሱ ወደ አሉበት ክፍል ሲያመራ እይታው።

ንግሥት ነጭ ጃኬትና ጥቁር ሱሪ የለበሰ የቀይ ዳማ ሰው እነርሱ ወዳሉበት ሲቀርብ አየች። ከዚህ በፊት ብታየውም ከሲሳይ ረጅም ቁመት ጋር አወዳድራው ነው መሰል ዛሬ አጠረባት። ሲሳይ አንድ ጊዜ በርሷና በርሱ መሀከል የስምንት ዓመታት ልዩነት እንዳላቸው ነግራት ነበር። ግን አርአያ ሰላሳ ሶስት ዓመት የሆነው አልመሰላትም። ቅጥነቱ ሳይሆን አይቀርም ጎረምሳ ያስመሰለው።

"ሲሳይ አትሄጂም? አልመሸም?" እያለ ንግሥትን፣ ሠረቅ አድርጎ አያት። እጁን ዘረጋና፣ "ጤና ይስጥልኝ!" አለ ለንግሥት።

"ጤና ይስጥልኝ! "አለችና ጨበጠችው።

"ደህና ነሽ ንግሥት?" አለ አርአያ።

"ደህና። አንተ ደህና ነህ?" አለች ንግሥት።

"ምነው ጠፋሽ? "አለ ሻምበሉ።

"አንተ ነህ የጠፋኸው።" አለች፣ ንግሥት ፈገግ ብላ።

"እኔ አለሁ። እንሂዳ።" አለ እጁን ወደ በሩ እየዘረጋ።



ከግቢው ውጭ ወደ ቆመችው ላንድ ሮቨር ተጠጉ። በሩን ከፍቶ ከገባ በኋላ በቀኝ በኩል ያለውን በር ከፈተላቸው።

ሁለቱም ሴቶች ከፊት ለፊት ካለ ወንበር ላይ ተቀመጡ።

አርአያ ሲጋራውን ለኮሰና የመኪናውን ሞተር አስነሳ።"ንግሥት የት ነው ቤትሽ?" ሲል ጠየቃት።

"ድል ገበያ።" አለች።

"ጥሩ።" አለና መኪናዋን አንቀሳቀሳት። ወደ ቀኝ ታጠፈና ወደ ሜክሲኮ አደባባይ የሚወስደውን ጎዳና ያዘ።

"ቀብሩ ነገ በስንት ሰዓት ነው የሚፈፀመው?" ሲል ጠየቀ አርአያ።

"በአሥር ሰዓት ነው። እንደዚያ መሰለኝ? "አለችና ንግሥትን አየቻት፣ ሲሳይ።

ንግሥት በአዎንታ ራሷን ነቀነቀችና፣ "አዎ።" አለች በመቀጠል።

ዝምታ ተፈጠረ።

"እኔን መጀመሪያ አድርሰኝ።"አለች ሲሳይ፣ ሜክሲኮ አደባባይ መድረሷን ስታይ።

"ቆይ። አንድ ቦታ ቢራ ልጋብዛችሁ።" አለና ወደ ንግድ ሥራ ትምህርት ኮሌጅ የሚወስደውን መንገድ ያዘ።

"እንዴ፣ መሽቷል እኮ!" አለች ሲሳይ።

"አዎ፣ መሽቷል። እኔ ቶሎ መግባት አለብኝ። " አለች ንግሥት፣ ጭንቅ ብሏት።

"በየቤታችሁ ነው የማደርሳችሁ። አትስጉ። ብዙ አንቆይም ደግሞ።" አለና የመኪናዋን ፍጥነት ጨመረ። ሀንኮክ ምግብ ቤት በር ፊት ለፊት መኪናውን አቆመና የመኪናውን ጥሩንባ ነፋ።

አንድ አሳላፊ እየሮጠ መጣና፣ "አቤት ምን ልታዘዝ?"አለ።

"ሶስት ሚታ ቢራ አምጣልን።" አለ አርአያ።

ቢራው መጥቶ መጠጣት ጀመሩ። ጨዋታው ሞቀ። የንግሥት ልብ ተሰቅሏል። እንዴት ሆና ከቤቷ እንደወጣች አርአያና ሲሳይ አያውቁም። እርሷም አልተናገረችም። አባቷ እንዳትወጣ እንደከለከሏት ማንም እንዲያውቅና እንዲወቀሱ አትፈልግም።

"ተጫወቺ እንጂ ንግሥት። ዝምታ አበዛሽ። ጠጪ እንጂ ደግሞ።"ብሎ ፈገግ አለ።

"እሺ። እየተጫወትኩ ነው።" አለች ፈገግ ብላ።

ንግሥት፣ አርአያ ይሆናል ብላ የገመተችው ሰው ዓይነት አልሆነም። በዚህች አጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ አውርቷል። ስለራሱ ደግነት፣ ቅንነት፣ አንባቢ ስለመሆኑ በራሱ እንደበት ሲናገር ዝቅተኛ ግምት ሰጥታዋለች። እና፣ ለዚህ ይመስላል–ማዳመጥንና መታዘብን የመረጠችው።

"ማዳመጥ ብቻ ምን ዋጋ አለው? ማውራትም ያስፈልጋል።"አለ ቢራውን ከተጎነጨ በኋላ።" ይልቅ ጠጡና ድገሙ።" አለ በመቀጠል።

"ኸረ መሽቷል። እኔን ተው ብትሸኙኝ... ቤተሰቦቼ በጣም ያስባሉ። ሳልነግራቸው ስለወጣሁ ይጨነቃሉ።" አለች ንግሥት። የጠጣችው ሶስት ጠርሙስ ቢራ በቂ ምግብ ባለመብላቷ ነው መሰል እናቷን እያንኳኳው ነው።

"አዎ ፣ መሽቷል። እንሂድ አርአያ። በቃን። ከዚህ በላይ መጠጣት ለሴት ልጅ ጥሩ አይሆንም።"አለች ሲሳይ። ቀይ ፊቷ ደም መምሰል ጀምሯል።

አርአያ ሂሣቡን ከከፈለ በኋላ የመኪናዋን ሞተር አስነሳ። ወደ ሜክሲኮ አደባባይ የሚወስደውን መንገድ ያዘ።" መጀመሪያ ሲሳይን ላድርሳት።"አለ።

"አዎ መጀመሪያ እኔን አድርሰኝ። ከዚያ በኋላ ንግሥትዬን ሰፈሯ ካደረስካት በኋላ ወደ ቤትህ ትሄዳለህ።" አለች ሲሳይ።

"ጥሩ።" አለች ንግሥት።" አንተ ግን አይመሽብህም?" ስትል ጠየቀች፣ በመቀጠል።

"አይመሽም። ደግሞ እኔ ወንድ ነኝ። ቤቴም ቅርብ ነው።" አለ አርአያ።

ሜክሲኮ አደባባይ ሲደርሱ መኪናዋን ወደ ቀኝ አዞረና አምስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ወረድ ብሎ ከሚገኘው የሲሳይ ቤት ግቢ በር ላይ አቆመ።

ሲሳይ የመኪናውን በር ከፈተችና፣" በሉ ደህና እደሩ።" እያለች ወረደች።

ከተሰናበቷት በኋላ አርአያ መኪናውን አዙሮ የመጡበትን መንገድ ያዘ። ሜክሲኮ አደባባይን ዞሮ ወደ ከርቸሌ የሚወስደውን መንገድ ጀመረ።

"እንዴ! ወዴት ነው የምትሄደው?" ስትል ጠየቀች፣ በድንጋጤ።

"ቆይ፣ እዚህ፣ አንድ ቦታ ደረስ እንበል ብዬ ነው።"አለ።



"ኸረ ባክህ መሽቷል።"አለች ተጨንቃ።

ዝም ብሎ ጉዞውን ቀጠለ። አርቢስ ጋራዥ አካባቢ ከመድረሱ በፊት ወደ ግራ ታጠፈና አንድ በር የሌለው ግቢ ውስጥ ገባ። መኪናውን አቆመና፣ " መጣሁ። አንድ ወይም ሁለት ደቂቃዎች ብቻ ነው የምቆየው።" ብሎ ፣ የአንድ ቤትን በር ከፍቶ ገባ።

ንግሥት የእጅ ሰዓቷን አየች። አራት ሰዓት አልፏል። አካባቢው ጭር ብሎ የሙታን መንደር መስሏል። የሚያፏጨው ንፋስ በአስፋልቱ ግራና ቀኝ የተተከሉትን የጥድ ዛፎች ከነሥሮቻቸው መንቅሎ ይዞ ለመሮጥ የከጀለ ይመስላል። ንግሥት በወጉ ከማታውቀው ሰው ጋር እንዲህ ባለ የሚያስፈራ ምሽት መቆየት አሳሰባት። ሥጋት እንደማስቲካ አኘካት። እንደዛሬ አምሽታ አታውቅም። አንዳንድ ጊዜ በአንዳንድ አጋጣሚ ብታመሽም እንኳ በቅድሚያ ለቤተሰቦቿ አሳውቃ ነው። 'አባዬ እኔን ከፈለገኝ ከሸዋዬ ጋር መጣላቱ አይቀርም። ምን ይሻላታል? ለእኔ ብላ መቀያየሟ የማይቀር ነው።' አለች፣ በልቧ።

ወዲያው ሻምበሉ መጣ። ንግሥት ከተቀመጠችበት ጎን ያለውን በር ከፈተና፣ " ንግሥት ትንሽ መቆየቴ የማይቀር ነው። እዝናለሁ፣ ያልጠበቅሁት ነገር ገጥሞኛል። በዚህች ደቂቃ እደውላለሁ ያለ ሰው ስላለ እስኪደውል ድረስ መጠበቅ አለብኝ።" አለ።

"ወይኔ!" በማለት ጭንቅላቷን ያዘች።"ምን ዓይነት እዳ ነው ዛሬ የገባሁት! ታዲያ አድርሰኸኝ ብትመለስስ ትደርስ የለ?"

"እንደሱማ አይሆንም። ምክንያቱም ሊያጡኝ ይችላሉ። እደውሉ ማስታወሻውን፣ 'በአራት ሰዓት ተኩል አካባቢ እንደውልልሀለን። ለአስቸኳይ ጉዳይ እንፈልግሀለን።' ይላል። አላት።

አነበበችው። ተስፋ በመቁረጥ አየችው። " ለምን አንተ ደውለህ አታነጋግራቸውም? በአሉበት ሰዓት ላይደውሉ ይችላሉ እኮ።" አለችው በመጨነቅ ስሜት።

"ቁጥሩን አላውቀውም። ችግሩ እኮ ይሄ ነው። አትስጊ፣ ቤትሽ አደርስሻለሁ።"

"አባቴ የት እንደሄድኩ አላወቀም። ቢያውቅ ኖሮ፣ ግድ የለኝ ም።" አለች፣ እንደመናደድ ብላ።

"እሺ ቤት ግቢና ደውለሽ ንገሪያቸው።" አለ አርአያ፣ ቤት እንድትገባ ፈልጎ።

ዝም አለች። አባቷ ቤት ውስጥ መሆኗን እንጂ ውጭ መሆኗን እንደማያውቁ ገምታለች። ይሁንና፣ ሸዋዬ መጨነቋ አይቀርም። የእሷን

ልብ ረጋ እንዲል ለማድረግና አባቷ ሳይሰሙ የግቢውን በር እንድትከፍትላት ለመንገር፣ መደወል አስፈላጊ መሆኑን ተገነዘበች።

"ነይና ደውይላቸው።" አለ።

ንግሥት ከመኪናው ወረደችና አርአያን ተከትላው ገባች።

የእንግዳ መቀበያዋ ጠባብ ብትሆንም፣ ንጹህ ናት። የቤት ዕቃዎች ከአቅሟ በላይ አጭቃለች። የሶፋ ወንበሮች፣ ኮንትሮ ቡፌ፣ የልብስ ቁምሳጥን፣ አነስተኛ አልጋና በርጩማዎችን ይዛለች።

"የት ነው ያለው ስልኩ?" አለች፣ በእንግዳ መቀበያ ክፍሉ ውስጥ ያሉትን ዕቃዎች በሙሉ ከቃኘች በኋላ።

"እዚያ ክፍል ውስጥ ነው።" በማለት፣ የተዘጋውን በር ከፍቶ አሳያት።

በጣም ጠባብ የሆነች ክፍል ናት። መኝታ ቤት መሆኗ ነው። አንድ ከእንጨት የተሰራ ሰፊ አልጋና ስልክ የተቀመጠበት አነስተኛ ኮመዲና ይታያሉ።

የስልክ ቁጥሮችን ማዞር ስትጀምር ወደሳሎን ተመለሰና የመውጪያውን በር ቀረቀረ። ከኮንትሮ ቡፌው ውስጥ ጠርሙስ ውስኪና ሁለት መለኪያዎች ይዞ መኝታ ቤት ገባ። የመኝታ ቤቱን በር ቀረቀረ።

"እየጠራ ነው?" ሲል ጠየቃት፣ ውስኪውን በመለኪያዎቹ እየቀዳ።

ንግሥት የስልክ ማናገሪያውን ጆሮዋ ላይ አድርጋ በድንጋጤና በጥርጣሬ ስሜት ውስጥ ሆና አየችው።" ለምን ዘጋኸው በሩን?" አለች፣ ዓይናቿን ከፊቱ ላይ ተክላ።

"ይሄ ክፍል በጣም ይበርዳል። ለዚህ ነው።" ሲል ዋሸ። የኤሌትሪኩን ምድጃ ለኮሰና አንድ ብረት ድስት ጣደ።

"ሀሎ!" አለች ንግሥት ስልኩ ሲያገናኛት።

"ሀሎ!" አለች ሸዋዬ።

"ሸዋዬ፣ ንግሥት ነኝ።"

"ምነው አንቺ? ደህናም አይደለሽ?"

"ደህና ነኝ። ሳላስበው አመሸሁኝ። አሁን እመጣለሁ።"

"እንዴ? አሁን እንዴት ብለሽ ትመጫለሽ? በዚህ ሰዓት?"

"የሚያደርሰኝ መኪና አግኝቻለሁ።"

"እኮ ቶሎ ነያ። ስትገቢ ታድያ ድምጽ እንዳታሰሚ።"

"እሺ። አባዬ ተኝቷል እንዴ?"



"አልተኙም። ጥናት ክፍላቸው ውስጥ ነው ያሉት።"

"እኔን አልጠየቁም?"

"ጠይቀው ነበር። ተኝታለች አልኳቸው። ከቤት መውጣትሽን አላወቁም። አንቺ ብቻ፣ ሳታመሺ ቶሎ ነይ።"

"መጣሁ። ቻዎ!" አለችና ስልኩን ዘጋችው።

በመሰቦወርቅ ከዳን ተሸፍና የነበረውን ትሪ አቀረበና፣ "ስለቸኮላችሁ ራት ሳልጋብዛችሁ መጠጥ ጠጣችሁ።" አለ። ሠራተኛው በጠርሙስ ሞልታ ያስቀመጠችለትን ውሃ አነሳና የእጅ ማስታጠቢያ ሳህን በመያዝ ፣" ታጠቢ። ቤት ያፈራውን እንብላ።" አለ።

እያቅማማች ታጠበች። ሰዓቷን እያየች፣ "ዛሬ መቼም ጉድ ነው? አምስት ሰዓት ሊሆን እኮ ነው! ሰዎቹ እስካሁን ለምን አልደወሉም?"

"ተይዞባቸው ይሆናል-አንቺ ስትነጋገሪ። " አለና. ወጡን ጨለፈው። "እንግዲህ የወንደላጤ ነገር፣ ምኑም አያምርም።"

"አይዞህ፣ ሲሳይ እስክትገባ ድረስ ነው። መቼ ነው የምትጋቡት?" አለች ንግሥት፣ እንጀራውን እየቆረሰች።

"አይ! ከሲሳይ ጋር ነው ጋብቻ?"

"እንዴት?"

"አሁን እህሉን እንብላ።" ብሎ እንዴ ጎረሰና የቀዳውን ውስኪ አቀበላት።

"እሺ።"አለች፣ ፈገግ ለማለት ሞከራ። ስጋት ይዟታል። አሁን የምትፈራው ስለመሸባት ብቻ አይደለም። ምንነቱን በትክክል ያላወቀችው ስሜት አድሮባታል።

ሻምበሉ ቴፕሪኮርደሩን ከፈተና፣ "ብይ እንጂ።"አለ።

ንግሥት ቢርባትም ቶሎ ማቋረጡን መረጠች፣ ከዚህ ቤት ውስጥ የምትወጣበትን ጊዜ ለማቅረብ ብላ።"በቃኝ። ጠገብኩ።" አለች።

"መቼ በላሽና? በደንብ ብይ እንጂ።"

"እውነት፣በላሁ። ከቤት ስወጣ ራቴን በልቼ ነው የመጣሁት።"

"እሺ ውስኪውን ጠጪ።" አለና ለመከላከል ጊዜ ሳይሰጣት መለኪያውን ሞላው።

"ኸረ በቃኝ! እኔ አልጠጣውም። በፊት የጠጣሁትም ጭንቅላቴ ላይ ወጥቷል።" አለች በመንገፍገፍ፣ ፊቷን መራር መድሀኒት የተጋተ ህፃን አስመስላ።

"ውስኪ እኮ ነው። ብትጠጪው ፊት ያሳምራል እንጂ አይጎዳም።"

"በልክ ሲሆን ነዋ። ይሄ ደግሞ እምቦ ውሀ ወይም በረዶ የለውም።" አለች።

"እምቦ ውሀ በአሁኑ ሰዓት አይገኝም። በረዶ ደግሞ ማቀዝቀዣ የለኝም። ባዶውን ቢሆንም፣ ውስኪ ለከፉ አይሰጥም። ይልቅ ጠጪና ድገሚ።"

"እ? ጭራሽ ድገሚ? ሆሆ!... መሽቷል እኮ! ኸረ ባክህ ቶሎ እንሂድ!"

"ቆይ ትንሽ እንጠብቅ–ሰልኩን።"

"መደወል ቢፈልጉ እስካሁን ይደውሉ ነበር። ከእንግዲህ ወዲያ አይደውሉም። አድርሰኝና ተመለስ።" አለች። ሞቅ እንደማለት ብሏታል።

"እሺ የያዝሽውን ጠጪ።"

ንግሥት ያለአግባብ የተሞላውን መለኪያ አንስታ መጨለጥ አስፈራት። ረጋ ብላ እንዳትጠጣው ሊመሽባት ሆነ። ሞቅ እንዳላት ተሰምቷታል። ጨልጦ መጠጣቱን መረጠች። ጅው አድርጋ ጠጣችና፣ "በል እንሂድ።" አለች ከተቀመጠችበት እየተነሳች።

"አንድ ድገሚ።"

"በፍጹም አልጠጣም!"

"ፕሊስ!"

"እንዴ ምን ነካህ ? መሽቷል እኮ!"

"ባክሽ አንቺ ደግሞ..." አለና እጇን ጎትቶ አልጋው ላይ አስቀመጣት።

"ምን ማለትህ ነው? አስወጣኝ፣ በእግሬ እሄዳለሁ!" አለች፣ ቆጣ ብላ።

"ከእንግዲህ ወዲያ መሽቷል። እዚሁ እደሪ።" አለ እርሱም ለስለስ ባለ ቁጣ።

"ምን አልክ?"ስትል ፣ ጮኸች።

"እዚሁ እደሪ። ካስፈለገ፣ ስልክ ደውለሽ ንገሪያቸው ለቤተሰቦችሽ።"

"ምንድን ነው የምታወራው?" አለች፣ ፍጹም በመደንገጥ።

"እማርኛ።" አለ፣ እንደማፌዝ ብሎ። ለቅሶው ቤት ከመሄዱ በፊት ጀምሮ ጠጥቶ ስለነበር እሱንም ሞቅ ብሎታል።



"ቀልድህን አቁምና በሩን ክፈትልኝ"አለች። ንዴት በውስጧ ያለውን አልኮል ሲያፍለቀልቀው ተሰማት።

"ቀልድሽን አቁሚና ስለበሩ መከፈት አታንሺ። ከእኔ ጋር ማደር ያለብሽ መሆኑን ልታምኚ ይገባል።"

"በፍጹም አላደርጋትም! ክፈትልኝ ልውጣ! መጨማለቁን ተውና ክፈትልኝ!" አለች፣ በቁጣና በመጠጡ ኃይል ምላሷ ተሳስሮ።

"በሩ ከእንግዲህ ወዲያ አይከፈትም። አዳሪ መሆንሽ ይግባሽ።"

"ኸረ! ማነው እንዲህ ያለው?"

"እኔ።" አለ፣ ሊያቅፋት እየሞከረ።

"ልቀቀኝ! አትንካኝ!"

አንቆ ያዛት።

"እጮሀለሁ! ልቀቀኝ!"

"እምቢርቂው!" አለ፣ በአንድ እጁ አንገቷን አቅፎ፣ በሌላ እጁ የቴፕሪኮርደሩን ድምጽ ከፍ እያደረገ።

አልጮኸችም። ድመት እንደያዛት አይጥ መፈራገጥ ጀመረች። ሊስማት ሲሞክር ፊቱን በጥፍሯ ቧጠጠችው።

በጥፊ አላጋት።

እሷም አላጋችው።

እጇን እንደ ጎማ አሽከርክሮ ጉንጮቿን እያፈራረቀ ሰፊድ በሚያክለው እጁ ወለወላት። ጣሪያው ወለል፣ ወለሉ ጣሪያ ሆነውባት ቤቱ እንደእንዝርት ተሽከረከረባት። ዝልፍልፍ ብላ አልጋው ላይ ወደቀች። ልብሶቹን ማወላለቅ ጀመረ። ቀጠለና የንግሥትንም ልብሶች መግፈፍ ጀመረ።

## 10

ጋቢ ለብሳ፣ በረንዳው ላይ ተቀምጣ፣ የንግሥትን መምጣት እየተጠባበቀች ነው። የምሽቱ ብርድ ቆዳ ይልጣል። ጨረቃ የለችም። ጨለማው አካባቢውን ወርሯል። ንፋሱ በግቢው ውስጥ ያሉትን ዛፎችና አትክልቶች ሲያወዛውዛቸው የሚፈጠረው ድምጽ እርስ በርሳቸው የሚንሾካሾኩ አስመስሏቸዋል። አንዳንዱ ዕፅዋት በንፋሱ ውስጥ ሲወዛወዝ እየተራመደ የሚቀርባት አስፈሪ አውሬ መስሎ ይታያታል–ለሸዋዬ። ንግሥት እስካሁን ባለመምጣቷ ጨንቋታል።

ጨለማውም አስፈርቷታል። ተገኝ በጊዜ ስለተኛ ብቻዋን ናት። መንፈቀ ሌሊት ቀርቧል።

'ምን ሆንኝ ይች ልጅ ዛሬ?' ስትል፣ ለራሷ ተናገረች

በዚህ ሀሳብና ጭንቀት ውስጥ ሳለች ዶክተር ያሉበት ክፍል በር ሲከፈት ሰማች። ድንጋጤዋ ጋመ።

ዶክተር የቤቱ መግቢያ በር በዚህ ሰዓት ክፍት ሆኖ በማየታቸው ወደ በረንዳው ወጡ። በንባብ የደከሙ ትናንሽ ዓይኖቻቸው ከሸዋዬ ጋር ተፋጠጡ። "እስከአሁን አልተኛሽም ነበር እንዴ?" አሉ።

"እዎ።" አለች።

"ምነው? ምን ትሠሪያለሽ እዚህ ?"

ዝም አለችና ተቀምጣበት የነበረውን ወንበር ይዛ፣ ወደ እንግዳ መቀበያው ክፍል ገባች።

ተከትለዋት ገቡ። "ተገኝ አልገባም እንዴ?"

"ከረ ገብቷል።"

"ታዲያ በዚህ በጨለማ ደጅ ምን ትሠሪያለሽ ? ሰዓቱም ሂዷል እኮ!"

የምትናገረው ጠፋት። "እየሩ ደስ ብሎኝ ነው።" ስትል ዋሸች።

"ታዲያ ብቻሽን ጥሩ ነው?" ሲሉ ከጠየቁ በኋላ፣ ከሸዋዬ መልስ ሲያጡ፣ "ንግሥት እንደተኛች ናት?" አሉ።

"እዎ ተኝታለች።" ስትል፣ አሁንም ዋሸች።

" ራት በላች ወይስ ቀን እንደተኛች ናት?"

"አይ፣ ተነስታ በልታ ነው እንደገና የተኛችው።"

ወደ መኝታ ክፍላቸው መራመድ ጀመሩና ቆም አሉ። ከንግሥት ጋር ዛሬ ያደረጉት ግጭት ትዝ አላቸው። ልጃቸውን ከፋኛ አሳዝነዋታል። የወትሮ የአባትነት ፍቅራቸውን ሰውረውባታል። ትክክል አለመሆናቸውን ተረድተው ይቅርታ ቢጠይቋትም፣ እንደገና አለመግባባት በመፈጠሩ አዝናባቸዋለች። ወደው አልነበረም ረግበ የነበረውን ግጭት እንደገና እንዲያንሰራራ ያደረጉት። ርምጃቸው ትክክል መሆኑን አምነውበት ነበር። ይሁንና፣ በአሁኗ ደቂቃም ፀፀት ልባቸውን እንደጋለ ብረት ላስ አደረገው። እንደገና ይቅርታ ሊጠይቋት ወሰኑ። ወደ ንግሥት መኝታ ክፍል አመሩ። ጨልሟል። መብራት አበሩና ጨለማውን አባረሩ። የልጃቸውን አልጋ አዩ። ባዶ ነው።



ሸዋዬ፣ ዶክተር ወደ ንግሥት መኝታ ቤት ሲገቡ አይታ በድንጋጤ አተር አከለች። ዓይኖቿን መሬት ላይ ተከለች። ሲሰርቅ እጅ ከፍንጅ እንደተያዘ ሰው ሸምቀቀ አለች።

ዶክተር ተመልሰው እንግዳ መቀበያው ክፍል ገቡና፣" ወዴት ሄደች ንግሥት?"ሲሉ ጠየቁ።

ሸዋዬ ደርቃ ቀረች። ስህተት መሥራቷ አሁን ነው የታወቃት። ከንግሥት ይልቅ፣ ለዶክተር ታማኝ ሆና መቅረብ እንደነበረባት አሁን ነው የተረዳችው።

ዶክተር ዝምታዋ ገባቸው። ሶፋው ላይ ቁጭ አሉ።"በረንዳ ላይ ተቀምጠሽ የነበረው እሷን ጥበቃ ነዋ? የት ሄዳ ነው?" አሉ ቆጣ ብለው። "ለምን ትዋሺያለሽ ? ወትሮ የሌለብሽ ፀባይ ከየት መጣ? ምንድን ነው ጉዳዩ? እውነቱን ንገሪኝ? የት ነው የሄደችው?" አሉ አሁንም በቁጣ። ካለ ዛሬ ተቆጥተዋት አያውቁም። ጠይም ቆዳቸው ጥቀርሻ መሰለ–በንዴት።

"ለቅሶ ቤት ነው።" አለች፣ መሬት እያየች።

"አትሂጂ አላልኳትም ነበር? የኔን ቃል አላከብር ማለቷ ነው? ጥሩ ሥራ ነው! መልካም ነው! አንቺም ተባባሪ ሆንሽ! እኔ አትሂጂ፣ ከቤት አትውጪ እያልኩ ስቆጣት እየሰማሽ ፣ ስትሄድ ዝም ማለትሽ ለምንድን ነው? ደግሞ መዋሸትሽ!" አሉና ሲጋራ ለኮሱ።

"ዶክተር፣ እሷም እኮ ትክክል ናት። የጓደኛዋ ለቅሶ ነው። ማስተዛዘን አይገባም ነው የሚሉ?" አለች፣ ለስለስ ባለ አነጋገር። "በርግጥ፣ እኔ መዋሸት አልነበረብኝም። አጥፍቻለሁ። በተረፈ እርሷ ግን ትክክል ናት። አይመስሎትም?"

ዶክተር ዓይኖቻቸውን ትዝዝ አድርገው ሩቅ የሚያዩ መሰሉና፣"ሸዋዬ፣ አንቺ የማታውቂው ነገር አለ። እሷም አንቺም ያልተረዳችሁት ነገር አለ። ልቢ ውስጥ እኔ ብቻ የማውቀው ችግር አለ። ንግሥቴ ከሰዎች ጋር መኖር አትችልም። መራቅ፣ መደበቅ ነው ያለባት። እኔም እኮ ስለእሷ ተሰቃየሁ። እረፍት አጣሁ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ስለእሷ እያሰብኩ በቁጫ አለቅሁ። ንግሥቴ ከቤት መውጣት የለባትም። ያውም እዚህ ለቅሶ ቤት የሰው መጠቋቆሚያ ለመሆን?"

ሸዋዬ ግራ ገባት።" ዶክተር የሚናገሩት ሁሉ አልገባኝም። ምንድን ነው የተፈጠረው ነገር?"

ሲጋራቸውን ሳቡናፕ"ተይው ሸዋዬ። ትርፉ መብሰል ነው፤ የእኔው ይበቃል። ብቻ ንግሥቴ ከሰዎች ጋር መግጠም እንደሌለባት ግወቁ ይበቃሻል። ይህንን ተረጂልኝ።" አሉ።

ዝምታ ነገሠ።

የዶክተሩ ንግግር አስደነገጣት። አንድ የደበቁት ምስጢር እንዳለ ከዚህ በፊት ጥርጣሬ ነበራት። ዛሬ አረጋገጡላት። ግን እርሳቸው ብቻ አፍነው የያዙት፣ ሌላ ሰው እንዳይሰማ የፈለጉት ነገር ምን እንደሆነ ሊገባት አልቻለም።

"አሁን ተኚ። እሷ ከእንግዲህ ወዲያ የምትመጣ አይመስለኝም፣ እስካሁን ካልመጣች ታድራለች ማለት ነው።"

"ትመጣለች።"

"ከአሁን ወዲያ ?"

"አዎ። ደውላ እመጣለሁ ብላኛለች።"

"በምን ልትመጣ ነው?"

"መኪና አግኝታለች መሰል።"

ለጥቂት ሴኮንዶች ያህል ከራሳቸው ጋር ሙግት ገጠሙና "ጥሩ። እስከዚያ ድረስ ሶፋው ላይ ጋደም በይ። እኔ ደክሞኛል ፣ ልተኛ።" ብለው መኝታ ቤታቸው ውስጥ ገቡ።

ሸዋዬ በሩን ዘግታ ረጅሙ ሶፋ ላይ ጋደም አለች። ግርግዳው ላይ ካለው ሰዓት ላይ ከማፍጠጥና ሥጋት ከማብዛት በቀር የዓይኖቿን በሮች የሚያስከድን ኃይል ብቅ አላለም።

## 11

ዕንቅልፍ ሊወስዳት አልቻለም። ፊቷ በዕንባ ታጥቧል። ጉንጮቿ ሰንበር አውጥተዋል። በሻምበሉ ቦክስ የተመታው ከንፈሯ ደም ቋጥሯል። ልቧ ቆስሏል። ካጠገቧ የተጋደመው እንስሳ ልቧ ያልፈቀደውን ነገር አድርጓል። ሞራሏን ነክቶታል። የሥነ ልቡና ጥቃት አድርሶባታል።

ሻምበል አርአያ አምሮቱን ለመፈፀም አልፎ አልፎ ከመንቃቱ በስተቀር እንቅልፉን ሲለጥጥ ነው ያደረው። ለእርሱ እንደዚህች ያለች ሌሊት አዲስ አይደለችም። በዚህች ጠባብ የመኝታ ክፍል ውስጥ መሰል ታሪክ ብዙ ጊዜ ፈጽሟል።

አርአያ ሲፈጥረው ለሴት ሙት ነው። ቀሚስ የለበሰች አሻንጉሊት ካየ እንኳ ልቡ ይመኛታል። ሴቶችን ማጥመጃ ዘዴ መፍጠር ለእርሱ ከባድ አይደለም። ግን፣ ከአንዲት ሴት ጋር



ከተዋወቀ በኋላ አብሯት ሊቆይ የሚችለው ቢበዛ ለአንድ ወር ያህል ጊዜ ብቻ ነው።

ከሲሳይ ጋር ብቻ ነው ረዘም ላለ ጊዜ የቆየው። ምክንያቱን በማያውቀው ሁኔታ ሲሳይን ቶሎ ሊለያት አይፈልግም። እንደምትወደው ያውቃል። ከእርሱ ጋር አብራ ለመኖር ማሰቧን አልፎ አልፎ በምታሳያቸው ምልክቶች ተገንዝቧል። ግን፣ ይህ ሊሆን እንደማይችል ያውቃል።

ንግሥት ሰዓቷን አየች። ከሌሊቱ አሥራ አንድ ሰዓት ሆኗል። እስኪነጋላትና ሲሳይን አፍንጫዋ ድረስ እስክትነግራት ቸኩላለች። አርአያ ፍቅረኛዋ መሆኑን ሲሳይ የነገረቻት፣ እውነት እንዳልሆነ አመነች። ትናንት ማታ በጊዜ ቤቷ እንዳትገባ ያስመሸቻት ለአርአያ ልታቃጥራት እንደሆነ አድርጋ ገመተች። የሰይጣን መልዕክተኛ ሆና ታይታታለች። ሲሳይን ለመበቀል ወሰነች። ብትችል ፊቷን በጥፍሮቿ ቡትርፍርፍ አድርጋ የደም ምንጭ ልታስመስላት አቅዳለች።

ከአልጋው ላይ ብድግ ስትል፣ አርአያ ነቃና እጇን ያዘው።"የት ልትሄጂ ነው በዚህ ሰዓት?"

"ልቀቀኝ! የትስ ብሄድ ምን አገባህ ?"

ጎትቶ እቅፉ ውስጥ ከተታት። ከንፈሮቿን ሊስም ሲሞክር ምራቋን ጢቅ አደረገችበት።

በጥፊ አገላብጦ መታት። በእልህ ተፈራገጠች። ግን ልታመልጥ አልቻለችም። እንደብረት በጠነከረ እጁ ጨምድዶ አግረካት። እንደፈለገው ሆነችለት..

የሚፈልገውን ካደረገ በኋላ ፣" አሁን መሄድ ትችያለሽ። የፈለግሽበት ልትበሪ ትችያለሽ፣ የእኔ እመቤት። ኮንትራትሽ አልቋል።" በማለት ካፌዘባት በኋላ ተኛ።

አፍጣ ንዴቷን ከመግለጽ በስተቀር ማድረግ የምትችለው አልነበረም። አቅሙ ቢኖራት ኖሮ አርአያን አሲድ እንደነካው ጨርቅ ብትበጣጥቀው ደስ ባላት ነበር።

ያንን ማድረግ ባለመቻሏ እልህ ተናነቃትና አለቀሰች። እንደ ሴጣን ከምታየው ሰውና እንደ መቃብር ከከበዳት ቤት ውስጥ ለመሸሽ ሮጠች።

ጭለማው ላለመሸነፍ ከንጋት ጋር ግብግብ መፍጠር ጀምሯል። ብርሃን ምድርን ጋርዶ የነበረውን ጥቁር መጋረጃ በጨረሮቹ እየበሳሳ ድል መቀዳጀት ጀምሯል።

እፎይ ብላ አድራ የነበረችው ህይወት እንደገና መንቀሳቀስ ጀምራለች። የወፎች ጫጫታ፣ ንጋት ከጨለማ ጋር የሚያደርገውን ትግል በአሸናፊነት እንዲወጣ የተደረገ ማበረታቻ ይመስላል።

ንግሥት ሽቅብ ወደ ሜክሲኮ አደባባይ የሚወስደውን መንገድ በፍጥነት ጀመረችው። ከአደባባዩ ስትደርስ መኪኖችና አልፎ አልፎ የሚታዩ ሰዎች ተመለከተች። አፍሪካ ሆቴልን አልፋ ከተጓዘች በኋላ አምስተኛ ፖሊስ ጣቢያ አጠገብ ስትደርስ ወደ ግራ ታጠፈች። ፊቷ ርብሽብሽ ብሎ፣ ፀጉሯ እንዳልሆነ ሆኖ በጥድፊያ የምታደርገው የደመ ነፍስ ጉዞ፣ ከዚህች ዓለም አምልጣ ወደ ሌላ ለመሄድ የተነሳች አስመስሏታል። በደረሰባት በደል፣ ሥጋዊ አካሏን ጠልታ፣ ሽምበል አርአያን ሲታገል የነበረው መንፈሷን ብቻ አንጠልጥላ ብትሄድ በወደደች ነበር። የሚቻላት ቢሆን።

የሲሳይ መኖሪያ ቤት በር አጠገብ ስትደርስ ማንኳኳት ጀመረች።

"ማነው?" አለ፣ አንድ ዕንቅልፍ ያሻከረው ድምጽ።

"እኔ ነኝ!" አለች ንግሥት።

"አንቺ ማን?"

"ንግሥት።"

የግቢው በር ተከፈተ። ዕንቅልፍ የደቆቆሳቸውን ዓይኖቻቸውን እፍጠው ብቅ አሉ እንድ ሴትዮ።

አተኩረው አዩዋት። ፀጉሯ ተመሰቃቅሎና እንደ ከረዩ በሬ ቀንድ ተገትሮ ታያቸው። ዓይኖቿ ደም ለብሰዋል። ፊቷ ምጥጥ ብሎ አስከሬን መስላለች። ግንባሯና የላይኛው ከንፈሯ ላይ አነስተኛ እብጠት ይታያል። ቀሚሷ ከደረቷ ላይ ተቀዷል። ጀማሪ እብድ መስላ ታየቻቸው።

ሴትየዋ ደነገጡ።" ውይ! ምን ሆንሽ?"

መልስ አልሰጠቻቸውም። ዘው ብላ ገባች። "ሲሳይ የት ነው ያለችው?" ብላ ጥያቄ ብታነሳም፣ መልስ አልጠበቀችም። የሲሳይን መኝታ ቤት ታውቀዋለች። ከዋናው ቤት በስተጀርባ ከሚገኙት ተጓዳኝ ቤቶች ውስጥ፣ አንደኛውን በር አንኳኳች።

ሲሳይ በሩን ከፍታ ብቅ አለች። አጭር ፀጉሯን በሻሽ ሸፍናዋለች። ረጅም የሌሊት ልብስ ለብሳለች። ንግሥትን በዚህ ሰዓት እንዲህ ሆና ስታያት ደነገጠች።



ንግሥት ፍየል እንዳየ ነብር ዘላ አነቀቻት። ሲሳይ ደንግጣ ወደ ኋላዋ ለመሸሽ ብትሞክርም፣ አልቻለችም። ጮኸች። በሁኔታዋ ተደናግጠው ከንግሥት ኋላ ይከተሉ የነበሩት ሴትዮ ደርሰው የንግሥትን ወገብ ጥርቅም አርገው ያዙ። መላወስ አልቻለችም። አስቀመጧት። እንደተመኘችው የሲሳይን ሥጋ ዘልዝላ ባለመበቀሏ ጨሰች። እልኳን በስድብ መወጣት አማራጭ ሆና አገኘችው።

"አንቺ አቃጣሪ! አንቺ እምነተ ቢስ! እኔን ነው ለዚህ ርኩስ የምታቃጥሪኝ! አንቺ ሴጣን! እኔን ነው የምትሸጪኝ?" አለች። አሉ በሚባሉ አፀያፊ ስድቦች ሁሉ ተጠቅማ እንደጅራፍ ብትገርፋት በወደደች። ግን፣ ይህ ከአቅሟና ከልምዷ በላይ ሆና አገኘችው። ከዚህ በላይ መናገር አልቻለችም። ስቅስቅ ብላ አለቀሰች።

በሁኔታው ግራ የተጋቡት የሲሳይ እናት ንግሥትን ለማባበል ሞከሩ። ንግሥት ግን ልትሰማቸው አልቻለችም።

በጠዋት ያልጠበቀችው ነገር ቢገጥማትም፣ ንግሥት ላይ የደረሰው ነገር ምን እንደሆነ ሲሳይ ጠርጥራለች። ማታውኑ፣ እሷኑ ሸኝተው ሲመለሱ ነው ጥርጣሬዋ ልቧ ውስጥ የተቀበረው። ትናንት ቢጤ ደቆስ አድርጓት ነበር። ከዚህ በፊት ስለንግሥት ደህንነት አርአያ አዘውትሮ የሚጠይቃትንና ስለ ውበቷ የሚሰጣቸው አንዳንድ አስተያየቶችን አትወዳቸውም ነበር።

"ንገሪኝ፣ ምንድነው?" አሉ አሮጊቷ።

– "ምንም አይደለም! እኔና እሷ እንተዋወቃለን!" አለችና ከተቀመጠችበት ተነሳች። "ይህንን ሥራሽን ግን፣ እግዜር ይክፈልሽ! እኔ ሌላ ምንም ማድረግ አልችልም። እኔ ለአንቺ ክፉ አልነበርኩም! እግዜር ይይልሽ!" ብላ ውልቅ አለች።

ሲሳይም ስቅስቅ ብላ ማልቀስ ጀመረች...

## 12

ሸዋዬ በሥጋት ስትሰቃይ ብታድርም፣ ሲነጋጋ ዶክተር ናትናኤል ከመነሳታቸው በፊት ንግሥት በመምጣቷ ደስ ብሏታል። ንግሥት ገላዋን ታጥባ እንደወጣች ሸዋዬ አተኩራ አየቻት።

"ለመሆኑ በደህናሽ ነው ንግሥትዬ?" ስትል በትህትና ላነሳችላት ጥያቄ መልስ ባለማግኘቷ፣ ንግሥትን ተከትላት ወደ መኝታ ክፍሏ ገባች።

ንግሥት ምንም ሳትናገር አልጋዋ ላይ ወጣችና ተጠቀለለች።

ሸዋዬ በንግሥት ላይ ያለተጠበቀ ሁኔታ በማየቷ ደነገጠች። ፊቷን አተኩራ አየችው–የንግሥትን። በመቁሰሏ ደነገጠች።

"ንግሥትየ አንቺ ምን ሆነሻል?"

"ምንም አልሆንኩም። ተይኝ ልተኛበት።"

"ዛሬ ሥራ አትገቢም?"

"አልገባም።"

"ምን ሆነሽ ነው ፊትሽ ያባበጠው?" አለች ሸዋዬ፣ ከልቧ አዝና።

"ተይኝ ባክሽ ሸዋዬ። ልተኛበት።"

ጥቂት ዝም አለች። ግን አላስችል አላት። 'ንግሥት አንድ ትልቅ ችግር አጋጥሟታል' ብላ አሰበች። 'ከማን ጋር ተጣልታ ነው? ዱርዬዎች መተዋት ይሆን?' ስትል ጠየቀች። ወዲያው ደግሞ፣"የት አደርሽ ማታ?" ስትል ጠየቀች።

መልስ የለም።

"ንግሥትዬ፣ አንቺ፣ ምነው ብትነግሪኝ? ለምን ታስጨንቂኛለሽ? አንቺ?"

አሁንም ዝም አለች።

ሸዋዬ ጨነቃት። የምታደርገው ጠፋት። ወጣችና ትንሽ ቆይታ ተመለሰች። አንድ እጇን ንግሥት ግንባር ላይ ለጠፈችና ሙቀቷን ለካች። ደጅ እንዳደረ ብረት ቀዝቅዟለች። ለእርሷ በሚገባት መንገድ ምንም በሽታ አላገኘችባትም። "ንግሥትዬ፣ አንቺ!.... ምን ልስራልሽ? ሻይ ላምጣልሽ?"

"ምንም አልፈልግም።"

"እሺ ምን ሆነሻል?"

"ምንም አልሆንኩም። መተኛት ስለፈለኩ ብቻ ነው።"

"ለምን ትደብቂኛለሽ? ከእኔ የሚደበቅ ነገር አለሽ?" አለች ሸዋዬ እንደመከፋት ብላ።

ምንም መልስ አልሰጠቻትም።

ሸዋዬ ትታት ወደ ሥራዋ ሄደች።



## 13

ሲሳይ፣ ንግሥት ቤቷ መጥታ ከሄደችበት ጊዜ አንስቶ ልቧ እንደጧፍ ሲነድ፣ እንጀቷ እሳት ውስጥ እንደገባ ሥጋ ሲኮማተር፣ ጭንቅላቷ በራስ ምታት እንደ እንጨት ሲፈለጥ ነው የቆየችው– በቅናትና በንዴት። እርእያን ለማግኘትና እውነቱን ለማወቅ ቸኩላለች። ቢሮ ገብታ ደውላ የምታናግርበትን ደቂቃ ናፍቃው ነበር። ከገባች በኋላ ሁለት ጊዜ ደውላ አጥታዋለች። እርእያ ቢሮው እንዳልገባ ነው የተነገራት። ቤቱ ደውላ የሚያነሳ ባለመኖሩ መውጣቱን አረጋግጣለች። ሠራተኛዋ ባለመግባቷ ወዴት እንደሄደ ማወቅ አልቻለችም። አሁን ለሶስተኛ ጊዜ ስትደውል ስልኩ ተነሳ።

"ሀሎ!" አለ ስልኩን ያነሳው ሰው ድምጽ።

የምትፈልገው ቁጥር መሆኑን ጠየቀች።

"አዎ፣ ነው።"

"ሻምበል እርእያን ፈልጌ ነበር።"

"ነኝ። ማን ልበል?"

"እንደምን አደርክ? ሲሳይ ነኝ።" አለች፣ ርጋታ ባለው ድምጽ።

"እንደምን አደርሽ? አንቺ ነበርሽ ቀደም ሲል የደወልሽው?" አለ፣ ለስለስ ባለ ስሜት።

"አዎ፣ ሁለት ጊዜ ደውዬ አጣሁህ። ይሄ ሶስተኛዬ ነው።" አለች።

"ምነው በጠዋት እንዲህ ፈለግሽኝ?"

ከምን እንደምትጀምር ግራ ገባት። "ማታ ንግሥትን ቤቷ አደረስካት?" አለች፣ ሳይታወቃት ድምጿ ከፍ ብሎ።

"ይህንኑ ለማወቅ ነው የደወልሽው?"

"አዎ!"

"ታዲያ እኔን ደውለሽ ስታጪኝ፣ ለርሷ ለምን አትደውይም ነበር?"

"ለነገሩማ ተገናኝተናል። ቤቴ መጥታ ነበር።"

"መቼ?" አለ፣ የድንጋጤ ቃና ባለው ድምጽ።

"ዛሬ ጠዋት። ከአንተ ቤት በቀጥታ ወደ እኔ ነው የመጣችው።"

"ታዲያ እሷኑ አትጠይቂያትም ነበር። እኔ ጋ ምን አስደወለሽ?" አለ ቆጣ ብሎ።

"ምን አስቆጣህ?" አለች፣ ጠንከር ባለ አነጋገር።

"መች ተቆጣሁ? እሷኑ ካገኘሻት ለምን አትጠይቂያትም ነበር ማለት ቁጣ ነው?" አለ፣ ለስለስ ብሎ።

"እሷንማ ጠይቄ ጉዷን ነግራኛለች።"

"ምን ነገረችሽ?"

"አስገድደህ በማሳደር እንደደፈርካት አልቅሳ ነገረችኝ።" አለች። ልቧ ለምን እንደሚመታ አልገባትም።

ከስልኩ የወዲያኛው ጫፍ የሚመጣው ድምጽ ሞተ።

"ምነው ዝም አልክ?"

"ታዲያ አሁን ከኔ ምንድን ነው ለማወቅ የምትፈልጊው?" አለ፣ ትዕቢት በተሞላበት ድምጽ።

"ነገሩ እውነት ነው ወይ?" ስትል በቁጣ ጠየቀች።

"አዎ፣ እውነት ነው። ሌላስ ማወቅ የምትፈልጊው ነገር አለ?" ሲል፣ በማሾፍ ጠየቃት።

"ልክስክስ!" ብላ ስልኩን ጆሮው ላይ ዘጋችበት።

## 14

ከቀኑ ስምንት ሰዓት እስኪሆን ድረስ ንግሥት ከመኝታዋ ላይ አልተነሳችም። ሸዋዬ አልፎ አልፎ ብቅ እያለች ብታያትም አልቀሰቀሰቻትም። የሚበሉና የሚጠጡ ነገሮች ባለመውሰዷ ትጎዳለች ብላ ሰግታለች ። የሲሳይ መምጣት አስደስቷታል።

"ነይ ግቢ ። ተኝታለች።" አለች ሸዋዬ ቀደም ብላ ወደ ንግሥት መኝታ ቤት ወደ ሚወስደው መተላለፊያ እየገባች።

"ምነው አመማት እንዴ?" አለች ሲሳይ ።

"አይ ደህና ናት ። ትንሽ ተጫጭኗት ነው ።"

ሲሳይና ሸዋዬ ተከታትለው ንግሥት መኝታ ቤት ውስጥ ገቡ።

"እስቲ ለአንቺ እሺ ትልሽ እንደሆን ቀስቅሻት። ከኔ ጋ እህል በአፏ አልዞረም።" አለች የሲሳይን ቀይ ፊት እያየች።



ሲሳይ ፈራ ተባ እያለች ወደ ንግሥት ተጠጋች ። ንግሥት ተከናንባ ተኝታለች።

"ንግሥት! ንግሥትዬ! አንቺ!" በማለት በአንድ እጇ ትከሻዋን ደገፍ አደረገች ።

ንግሥት ብንን እንደማለት ብላ ነቃች ። እንደ ፍሬቻ ዓይኖቿን ብልጭ ድርግም አድርጋ ሲሳይን ደጋግማ እየቃኘችና ተመልሳ ተኛች ። ጠዋት ሲሳይ ጋ ደርሳና ቤት ገብታ አልጋዋ ላይ ከወጣች በኋላ፣ ሲሳይን በአይነ ህሊናዋ እምጥታ ስትመረምራት ነው የዋለችው ። በርሷ ላይ ለደረሰው ግፍ ተጠያቂ ሆና ባታገኛትም፣ ሙሉ ለሙሉ ንፁህ ሆና አልታየቻትም ። ያን ያህል ሰዓት እንድታመሽ የገፋፋቻትና ለአርአያ እንስሳዊ ተግባር ሳታውቅም ቢሆን፣ ጥሩ አጋጣሚ የፈጠረችው ሲሳይ መሆኗን አምናለች ። ስለዚህም የጠዋቱንም ያህል ባይሆን ስትረግማት ነው የዋለችው ።

ሸዋዬ ሲሳይን እያየች በሹክሹክታ፣ "እስቲ እሺ ትልሽ እንደሁ፣ ተነሺና እህል ቅመሺ በያት ። እስከዚያው ድረስ ላቅርብ" ብላ ወጣች ።

ሲሳይ ጭብጥ ብላ አልጋው ጫፍ ላይ ተቀመጠች ። "ንግሥትዬ፣ እንዴት ባላደረኩትና ባላሰብኩት ነገር ትጠረጥሪኛለሽ? እኔ ራሴ ስትነግሪኝ በጣም ነው ያዘንኩት ። እንደዚህ ዓይነት እንስሳ መሆኑን ያወቅሁት፣ አንቺ ስትነግሪኝ ብቻ ነው። እጮኛዬ እያለ ሲያታልለኝ መኖሩን አሁን ነው ያወቅሁት ። ንግሥትዬ ሙች! እመኚኝ። "ንፁህ ጓደኛዋ መሆኗን ለማሳወቅና ንግሥትን ለማሳመን ከሚረዱ ቃላት ይልቅ፣ ዕንባዋ ቀደማት ። ይቅርታ በመጠየቅ ዓይነት ንግሥት ላይ ወደቀች ።

ንግሥት ምንም አልተናገረችም።

"ንግሥትዬ ሙች፣ ያሰብሽው ሁሉ ውሸት ነው ። አርአያ የምወደው ሰው መሆኑን ታውቂያለሽ ። ብዙ ጊዜ አውርቼልሻለሁ ። ይህንን እያወቅሽ እኔ ሁኔታውን እንዳመቻቸሁለት እንዴት ትጠረጥሪያለሽ? እባክሽ እመኚኝ ። ከአንቺ ይልቅ እኔ ነኝ ያዘንኩት። ሰው ነው ብዬ ስለቀረብኩት ነው እንደዚህ ሊያታልልሽ የቻለው ። ይህ ሁኔታ ከአንቺ ይልቅ እኔን አሳዝኖኛል። ጥራልሽንና ክብርሽን የሚነካ ግፍ በመፈፀሙ ብቻ አይደለም ያዘንኩት። እስከዛሬ በሚጣፍጡ ቃላት እያታለለ፣ ከምላጭ በሰላ ምላሱ ልቤን እየላጨ፣ የስሜቱ ማርኪያ ዕቃ አድርጎኝ በመቆየቱም ነው። ንግሥትዬ በእንዲህ

ያለ ሀዘን ውስጥ ሆኜ ባላሰብኩትና ባላደረኩት ነገር አንቺ ስትቀየሚኝ ደግሞ ምን ያህል እንደምጎዳ እወቂልኝ እንጂ::" ስትል ተማፀነች::

ንግሥት ከአልጋዋ ላይ ተነሳችና ሲሳይን ቀና አደረገቻት:: ርህራሄ ተሰማት:: ይዛባት የነበረው ቂም ውሀ ውስጥ እንደገባ ሳሙና መሟሟት ጀመረ:: ጓደኛዋ ከአርአያ ጋር ያላትን የፍቅር ግንኙነት ብትጠረጥርም እርሷን ለርሱ ለማቃጠር እንደማትደፍር ታውቃለች:: አንዳንድ ሴቶች ጓደኞቻቸውን ለወንዶች ወጥመድ እንደሚያመቻቹ ብታስታውስም፣ ሲሳይን ግን በዚህ አትገምታትም:: ሲሳይ በተፈጥሮዋ በትቧቃ ናት:: በልቧ ውስጥም ክፋት የሚባል ነገር የለም:: የዋህ ናት:: ያም ሆኖ ግን፣ ንግሥት ሲሳይን ረግማ ነበር :: አቃጣሪ ብላትም ነበር፣ ዛሬ ጠዋት::

"ንግሥትዬ፣ እመኚኝ::" አለች ሲሳይ::

አመነቻት:: "በቃ ተይው ሲሳይ:: ትቻለሁ:: ግን እሱ እንስሳ ነው! ከሴት ልጅ የተፈጠረ አይመስልም:: ምን ያደርጋል! ብቸኛ መሆኔ ነው እንጂ አስረግጠው ነበር! እግዜር የሥራውን ይስጠው! ጉልበቴን መከታ አድርጎ ደፈረኝ:: ለእርሱም ጉልበተኛ ይዘዝለት! ግን ይቅርታ አድርጊልኝና የሚሆንሽ ሰው አይደለም! የምታደርጊውን ብታደርጊ ይሻላል::" አለች ንግሥት፣ አልጋው ላይ ተቀምጣ::

ሸዋዬ፣ በአንድ እጇ እንጀራ ያለበት ትሪ፣ በሌላ እጇ የሻይ ስኒዎች የተቀመጡበት ማቅረቢያ ይዛ ገባች:: "ሻይ አፈላሁላችሁ:: ንግሥትዬ እህል ሳትቀምስ ነው የዋለችው:: ቆይ የእጅ ውሀ ላምጣላችሁ::" ብላ ያመጣቻቸውን ዕቃዎች አስቀምጣ ወጣች::

"ኧረ ቆይ! መታጠቢያ ቤት ሄደን እንታጠባለን::" አለች ሲሳይ::

ሸዋዬ የእጅ ውሀ ይዛ መጣች:: ሁለቱንም አስታጥባ ወጣች:: ሣልፋዎች የጎረሱ ሁለት ባለክዳን ሳህኖች ይዛ ገባች:: ጨለፈችላቸውና፣ "ብሉ ብሉ:: እኔ ትንሽ ሥራ አለብኝ:: በኋላ፣ ዶክተር ሲመጡ፣ ከርሳቸው ጋር እበላለሁ:: ወጡን እየጨለፋችሁ ብሉ:: ያነሰ ነገር ካለ ንገሩኝ:: ቆይ ሻዩን ይገፍላችሁ ልምጣ::" ብላ ወጣች:: ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ተመልሳ ባለኒኬል የሻይ ጀበናና ስኳር የያዘ ዕቃ አስቀምጣላቸው እንደገና ወጣች::

የቀረበላቸውን ምግብ ለጥቂት ደቂቃዎች ያህል በዝምታ መብላት ጀመሩ::

"ንግሥትዬ፣ እቤቱ እንዴት ሊያስገባሽ ቻለ?" ስትል፣ እየፈራች ጠየቀቻት::



ንግሥት ሲሳይ ላነሳችላት ጥያቄ ወዲያው መልስ አልሰጠችም:: ሻዩን ፉት አለችና አርአያ እንዴት አታልሎ እንዳስገባት ተረከችላት::

"የሚገርም ነው:: በጣም የሚያሳዝን ሰው ነው::" አለች ሲሳይ፣ እንደማዘን ብላ:: የቆሰለው ልቧ አመረቀዘ::

ስልክ ጮኸ፣ ከሳሎን::

ሸዋዬ አነሳችው:: "ሀሎ!..."

"የዶክተር ናትናኤል መኖሪያ ቤት ነው?"አለ፣ አንድ የወንድ ድምጽ::

"አዎ::" አለች ሸዋዬ::

"እባክዎ ንግሥትን ፈልጌ ነበር::"

"ቆይ እስኪ..." የስልኩን መነገሪያ አስቀመጠችና ወደ ንግሥት መኝታ ቤት አመራች – ሸዋዬ::

"ንግሥትዬ፣ ስልክ ይፈልግሻል::"

"ማነው የፈለገኝ?"

"ስሙን አልጠየቅሁም::"

"ወንድ ነው?"

"አዎ::"

ከመኝታ ክፍሏ ወደ ሳሎን ወጣች:: ስልኩን አነሳችው:: "ሀሎ!..."

"ንግሥት ነሽ?"

ድምጹን ስትሰማ፣ ወዲያው አወቀችው:: እንደሚደውል ርግጠኛ ነበረች:: "አዎ::"

"ግርማ ነኝ::"

"አውቄሃለሁ:: ደህና ነህ?"

"ደህና ነኝ:: ምነው ምን ሆንሻል?"

"ምንም አልሆንኩም::"

"ቀጠሮ አልነበረንም ዛሬ? መቼም የሚረሳ አይመስለኝም::"

"አልረሳሁትም:: ትንሽ ችግር ተፈጥሮ ነው::"

"የምን ችግር?" አለ ግርማ፣ ትንሽ ደንገጥ ብሎ::

"ራሴን አመም ስላደረገኝ ነው::"

"መቼ ጀመረሽ?"

"ዛሬ ጠዋት::"

"ሥራ አልገባሽማ?"

"አልገባሁም።"

"በጣም ነው እንዴ ያመመሽ?"

"አይ አሁን ተሽሎኛል። ደህና ነኝ።"

"አትዋሺኝ።"

"ሙት፣ ደህና ነኝ።"

"ደህና ከሆንሽ ዛሬ ማታ አብረን እናምሽ?"

"ዛሬ?"

"አዎ።"

"ዛሬ እንኳ ከቤት የምወጣ አይመስለኝም። አሞኛል ብዬ ተኝቼ ውዬ ማታ ስወጣ ሰውስ ምን ይለኛል?"

"ስለሰው ምን አስጨነቀሽ?"

"እንዴ፣ ለምን አልጨነቅም?"

ዝምታ ተፈጠረ።

መልስ ስታጣ፣ "ባይሆን ነገ ወደ ከሰዓት በኋላ አካባቢ መገናኘት እንችላለን።"

"ጥሩ። እንዳውም ቴአትር እንገባለን።"

"ደስ ይለኛል።"

ጥቂት ካወሩ በኋላ በማግስቱ የሚገናኙበትን ቦታና ጊዜ ወስነው ስልኩ ተዘጋ።

ተመልሳ መኝታ ቤቷ ገባች።

ሲሳይ መብላቱን አቁማ እየጠበቀቻት ነበር።

"አትበይም ነበር እንዴ? እኔን ምን አስጠበቀሽ?"

"እንዴ፣ ለምን?" አለችና ንግሥት አስከትቀመጥ ጠበቀቻት። "ማን ነው የደወለልሽ?"

"ግርማ ነው።" አለች። በዝምታ ትንሽ ከቆዩ በኋላ፣ "አስቀበርሽ እንዴ?" ስትል ንግሥት ጠየቀች።

"ኸረ አልሄድኩም። ጠዋት ካገኘሁሽ ጀምሮ ራሲ ብው ብሎ ነው የዋለው። ሰው ማየት ጭራሽ አስጠልቶኝ ነበር። ሥራ ገብቼ የሠራሁት ነገር የለም። ቶሎ ነው ወደ ቤት የተመለስኩት። ያንቺን ሁኔታ ልይ ብዬ ነው የመጣሁት። አንቺም ተኝተሽ እንደዋልሽ፣ ሽዋዬ ነገረችኝ።"



"አዎ፣ ከአንቺ እንደተለየሁ ቀጥታ ወደ እዚህ ነው የመጣሁት።"

"ሰዎች ምን ይሉን ይሆን?"

"የፈለጉትን ይበሉን ባክሽ።"

ዝምታ ሰፈነ።

ሲሳይ ሻይዋን ፉት ካለች በኋላ፣ "ነገ ከቻልን ሄደን ለስልስት እናድራለን።"

"ምናልባት።"

## 15

ቀኑ እሁድ ነው። ግርማና ንግሥት ምሳ ከበሉ በኋላ፣ በቀጥታ ወደ ብሔራዊ ቴአትር ነበር ያመሩት። ከአራት ሰዓታት ቆይታ በኋላ፣ የመድረኩ መጋረጃ ሲዘጋ ከአዳራሹ ወጡ።

ፀሐይ ራሷን ከጋራ ሥር መደበቅ ጀምራለች። አየሩ ደስ የሚል ስሜት ይፈጥራል። በብሔራዊ ባንክ ፊት ለፊት፣ወደ አምስተኛ ፖሊስ ጣቢያ የሚወስደውን ጎዳና ይዘው በዝግታ ርምጃ መጓዝ ጀመሩ። ትንሽ እንደተራመዱ ወደ ግራ ታጠፉና በአንድ ትልቅ ግቢ ውስጥ ከሚገኝ መዝናኛ ውስጥ ገቡ።

"ቤት ቶሎ መግባት እፈልጋለሁ ግርምሽ።" አለች ንግሥት፣ የመጣላትን ቢራ በብርጭቆ ውስጥ እየቀዳች።

"ለምን? የምትቸኩይበት ጉዳይ አለሽ እንዴ?"

"አይ፣ የለኝም።" አለችና ወዲያው አንዳች ነገር ትዝ አላት። "ወይኔ! ምን ይሻለኛል?"

"ምነው ምን አስታወስሽ?"

ጥቂት ዝም ብላ ከቆየች በኋላ፣ "ከሲሳይ ጋር ዛሬ ለቅሶ ቤት ሄደን ስልስት እናድራለን ብለን ነበር።" አለች በመቀጠል።

"ነገ ጠዋት ትደርሻለሽ ባክሽ። አሁን እርሱን እርሺውና ጠጪ።" አለ ግርማ ቢራ የሞላውን ብርጭቆ አንስቶ። ሁለቱን ከሚመለከት ነገር ውጭ ስለሌላ ጉዳይ ማውራት አልፈለገም።

በዝቅተኛ ድምጽ የተከፈተው ለስላሳ ሙዚቃ፣ ከጣሪያው ስር እንደጉንብ ቀፎ ከተሰቀለው ድምጽ አጉሊ መሣሪያ ውስጥ እየፈለቀ የምሽቱን አየር በመሰንጠቅና ጆሮን እየበረበረ በመግባት መንፈስን ያስፈነድቃል። ግርማና ንግሥት ጨዋታቸውን አሞቁት። ቢራውን ደጋገሙት። ጭለማው ምድርን ወርሮ ተቆጣጥሯታል።

"ግርማ፣ መሸ እኮ።"

"ባክሽ ገና ነው። እንዳውም ዛሬ ብናድርስ?"

"በፍጹም አይሆንም።"

"ምነው ምን ችግር አለ?"

"አባቴ አያስገባኝም። የት አደርኩ እላለሁ?"

"ለትሶ ቤት አድራለሁ አላልሽም ነበር?"

"ለሱም ቢሆን ዘዴ ፈጥራ እንጂ..." አለችና ንግግሯን ቆረጠች።

"ታዲያ ለዚያ የምትፈጥሪው ዘዴ ለዚህ አይሆንም?"

ዝም አለች።

"በይ እንጂ፣ ንግሥትዬ።"

"ምን ልበል?" አለች፣ ጠረጴዛው ላይ ዓይኖቿን ተክላ። "ለምን ሌላ ቀን አይሆንም?" አለች፣ ቀና ብላ እያየችው።

"ነገ ለመስክ ሥራ ወደ ክፍለ ሀገር እሄዳለሁ። ትንሽ ሳልቆይ አልቀርም።"

"ያንተ የመስክ ሥራ ደግሞ አያልቅም!" አለች፣ ኮስተር ብላ ተናግራ።

"የሥራዬ ፀባይ ነዋ።"

"እሺ ስትመጣ እናደርገዋለን።" አለች፣ ፈገግ ብላ።

"ከአንቺ ጋር የምሆንበትን ጊዜ ምን ያህል እንደምናፍቀው አታውቂም? መቼ ነው እኔና አንቺ አብረን አንድ ሌሊት የምናሳልፈው? ለስሙ ፍቅረኛሞች ከሆንን፣ በርከት ያሉ ቀናት አልፈዋል። ግን፣ ፍቅረኛሞች የሚያደርጉትን እስካሁን አላደረግንም።"

"እሱ እኮ የኔ ጥፋት አይደለም። የሥራህ ፀባይ ያመጣው ጉዳይ ነው።"

"አይደለም። አዲስ አበባ ባለሁባቸው ቀናትም ሁሉ እኮ አልቻልንም። አይመቸኝም። እዚህ ቦታ እሄዳለሁ፣ ስትይ መቼ እጅ ትገቢያለሽ?"

"እሺ አሁን ምንድን ነው የምትለኝ?"

"ዛሬ አብረን እንደር። ለቤት ደውለን እንነግራለን።"

"ምን ብለን?"

"ለትሶ ቤት አድራለሁ ብለሽ።"



ዝም አለች። ሳታስበው፣ ሌሊቱን ከግርማ ጋር እንድታሳልፈው መፈለጓን ልቧ ነገራት። ቢራውን እንደዋዛ ፉት አለችና አየችው ግርማን።

"ምን አሰብሽ?"

"እሺ።" አለች፣ ጎንበስ ብላ ሀፍረት በተሞላው ድምጽ።

ከዚህ በኋላ ብዙ አልተቀመጡም። ከመዝናኛ ቤቱ ወጡ። ቁልቁል ወደ ብሔራዊ ባንክ ወረዱ። ወደ ግራ ታጠፉና የቸርቸር ጎዳናን መንገድ ያዙ። ጥቂት እንደሄዱ ጎላ ሚካኤል ወደሚወስደው ጎዳና ታጠፉና አንድ ሆቴል ውስጥ ገቡ። መኝታ ቤት ተከራይቶ እስኪመጣ ድረስ፣ ንግሥት ስልክ ለሸዋዬ ደወለችላት።

"የት እናምሽ? ወደ ታች እንውረድ።" አለና ወደ መጡበት አካባቢ ተመለሱ።

ለብ ያለው የምሽቱ አየር ፊት ላይ ሲያርፍ በሀሣን እጅ የተዳበሱ ያህል ለስልሶ ይሰማል።

"ግርምሽ ፣ ለምን ለቅሶ ቤት ደረስ ብለን አንመጣም? ፊቴን አሳይቼ ብመጣ ደስ ይለኛል።"

"አሁን እሱ ምን አሳሰበሽ? ነገ ጠዋት አትደርሽም?"

"እይ አሁን ስደውል ሲሳይ ቤት መጥታ እንደነበርና ለቅሶ ቤት እንደምትጠብቀኝ መልዕክት አስቀምጣልኛለች።"

ግርማ ጥቂት አሰበ። "የት አካባቢ ነው?"

"ልደታ። አንድ አፍታ በታክሲ ደረስ ብለን እንምጣ።"

"እንቆይም ግን።"

"አሥራ አምስት ደቂቃ ብቻ።" አለች።

ታክሲ ያዙ። ልደታ ቤተክርስቲያን አካባቢ ወረዱ። ወደ ቢሪሞ ወፍጮ ገሠገሡ። ለቅሶ ቤት ሲደርሱ ሰው ግጥም ብሎ አገኙ። ድንኳኑ በሰዎች ተሞልቷል። ግርማ፣ ወንዶች ያሉበት አካባቢ ተቀመጠ። ንግሥት ሴቶች ወዳሉበት አካባቢ ሄደች። ሲሳይን አገኘቻት። ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ተቀመጠች።

"ምነው ጋቢ ሳትለብሽ መጣሽ?" አለች ሲሳይ።" ምን ለብሰሽ ልታድሪ ነው?"

"አላድርም።" አለች ንግሥት።

"ለምን?" አለች ሲሳይ፣ ድንግጥ ብላ።

"ግርማ ነገ ሊሄድ ነው። ለሥራ ክፍለ ሀገር ስለሚሄድ ዛሬ ከርሱ ጋር ለማሳለፍ ነው የፈለኩት።"

ፈገግ አለችና፣ "እውነትሽን ነው?" ስትል ጠየቀች፣ ሲሳይ።

"አዎ። ለሸዋዬ እዚህ እድራለሁ ብዬ ነው የነገርኳት።"

"ታዲያ ብቻሽን ነው የምትመለሽው?"

"ግርማ አብሮኝ መጥቷል እኮ።"

"የታለ?"

"ድንኳን ውስጥ ነው።"

"ቆይ ስትወጪ ሰላም እለዋለሁ።"

"ብዙ አንቆይም። ከአምስት ደቂቃ በኋላ እንሄዳለን።"

"ለምን? ትንሽ አትቆዩም?።"

"የለም። መሽቷል።"

"የት ነው የምታድሩት፣ ቤቱ ነው?"

"ምን ቤት አለው፣ ግርማ። ከወላጆቹ ጋር እኮ ነው የሚኖረው። ሆቴል ነው የምናድረው። መኝታ ይዘናል።"

"ሩቅ ነው ቦታው?"

"ሐረር ፔንሲዮን።"

"እ... ቅርብ ነው ታዲያ።"

"ታክሲ አይገኝም።"

ለጥቂት ደቂቃዎች ያህል ከቆዩ በኋላ፣ ግርማና ንግሥት ከለቅሶ ቤት ወጥተው ወደ ሆቴላቸው አመሩ።

## 16

ከምሽቱ ሶስት ሰዓት ሲሆን፣ ዶክተር ናትናኤል በግል ክሊኒካቸው ውስጥ የሚሰጡትን የህክምና አገልግሎት ጨርሰው ወደ እንግዳ መቀበያ ክፍላቸው ገቡ። ሸዋዬ ሶፋው ላይ ቁጭ ብላ የእጅ ሥራ ትሰራለች።

"ሸዋዬ እስኪ ቡና አፍይልኝ።" አሏት።

ደክሟቸዋል። ዛሬ ቀኑን ሙሉ ከቤት አልወጡም። አዲስ ለጀመሩት ምርምር የሚረዷቸውን መጻሕፍት፣ ሠነዶች፣ መጽሔቶችና ደብዳቤዎች ሲያገላብጡ ነው የዋሉት። ከዚህ በፊት በዚህ የበሽታ ዓይነት ላይ ምርምር ከጀመሩት የውጭ ሀገር ድርጅቶችና ግለሰቦች ጋር ሀሳብ ለመለዋወጥ የሚያስችሏቸውን ደብዳቤዎች ሲጽፉ ውለዋል። በዚህ ምርምር ላይ በገንዘብ፣ በቁሳቁስና በሀሳብ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ሊረዷቸው የሚችሉ ሰዎችን ዝርዝር እንደገና



አውጥተው ደብዳቤ አዘጋጅተውላቸዋል። ከዚያ በኋላም፣ ከቀኑ አሥራ አንድ ሰዓት ጀምሮ በግል ክሊኒካቸው ውስጥ የሚሰጠውን ዕርዳታ ለማግኘት የመጡትን ህሙማን ሲያስተናግዱ አምሽተዋል።

ዶክተር ናትናኤል የዕረፍት ጊዜ የሚባል ነገር አያውቁም። የልጃቸው እናት፣ ባለቤታቸው፣ ከአሥራ ዘጠኝ ዓመታት በፊት በሞት ከተለዩዋቸው በኋላ፣ የዕረፍት ጊዜያቸውን በንባብና በምርምር ነው የሚያሳልፉት። ከማኅበራዊ ጉዳዮች ከተገለሉ እጅግ ብዙ ዘመናት አልፈዋል። ከዘመዶቻቸው ጋር እምብዛም አይጠያየቁም። በእነዚህ ረጅም ዓመታት ለኢትዮጵያ ህክምና መሻሻልና መዳበር፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ስላሉ የባህል መድሐኒት ጠቃሚነትና ጎጂነት በሚመለከት የማስተማሪያ መጻሕፍት አዘጋጅተዋል። በማስተማር፣ በህክምናና በምርምር ሥራዎቻቸው ላይ በሚያሳዩት ትጋት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲና ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የማበረታቻና የምሥጋና ደብዳቤዎች ጎርፈውላቸዋል።

"ቡናው እስኪደርስ ድረስ ራት ላቅርብ?" አለች ሸዋዬ።

"አዎ፣ እንዳውም ርቦኛል።" አሉ ወደ መታጠቢያው ቤት እየተራመዱ። እግረ መንገዳቸውን ወደ ንግሥት መኝታ ቤት ጎራ አሉ። ጠዋት ቁርስ ላይ ከተገናኙ በኋላ አላይዋትም ነበር። የመኝታ ክፍሏን መብራት አበሩ።

ንግሥት የለችም።

ራሳቸውን እየነቀነቁ ወደ ሳሎን ሲመለሱ፣ ሸዋዬ እንጀራ የያዘ ትሪ ይዛ ከወጥ ቤት ስትወጣ አየቻቸው። ስቅቅ አለች–በድንጋጤ።

"ንግሥት ወዴት ሄደች፣ ሸዋዬ?" ሲሉ እንደዋዛ ጠየቁ።

ትሪውን የምግብ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠች ጥያቄያቸውን ያልሰማች መስላ። ይሁንና ማምለጥ እንደማትችል ከገፃቸው ተረዳች፡ "ነገ ሰልስት ስላሆነ፣ ለቅሶ ቤት አድራለሁ ብላ ነው የሄደችው።" አለች በፍርሀት።

ምንም አልተናገሩም። ወደ ማዕዱ ቀረቡ።

ሸዋዬ ወጥ ለማምጣት ወደ ወጥ ቤቱ ሄደች።

ሀሳብ ውስጥ ሰጠሙ። ለጥቂት ሴኮንዶች ርቀው ሄዱ፡ ወዲያው ደግሞ፣ ድንገት ምንጭቅ ብለው በመነሳት ወደ መኝታ ክፍላቸው ገቡና ነጩን የሥራ ገዋን አውልቀው ኮትና ካፖርት ለብሰው ወጡ።

ሸዋዬ ወጥ የያዙ ሳህናች ይዛ ብቅ አለች።

"መጣሁ።" አሉና ወደ በሩ ገሠገሡ።

ሸዋዬ በድንጋጤ እየቻቸው። "ዶክተር የት ይሄዳሉ? ራት ቀርቦ ወዴት ይሄዳሉ?"

"አልበላም።" አሉና ወጡ። መኪናቸውን አስነሱ። የግቢውን በር እንዲከፍትላቸው ለተገኝ መልዕክት ሰጡ።

ሸዋዬ በረንዳ ላይ ሆና ዶክተር መኪናቸውን እያሽከረከሩ ከግቢ ሲወጡ በዓይኖቿ ተከተለቻቸው። ሁኔታቸው ፈጽሞ ሊገባት አልቻለም። ወዴት እንደሚሄዱ አልገባሽ አላት። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የዶክተር ፀባይ እጅግ ተለውጦባታል። ከአንድ ቀን አንድ ቀን ይሻላቸዋል ብላ ብታስብም፣ እየባሰባቸው ነው የሄደው። የዶክተሩ ንጭንጭ፣ ብስጭትና ንትርክ እየከረረና እየጋመ ሄዷል። የእነዚህ ስሜቶች መነሻና መድረሻ ምን እንደሆነ ለማወቅ ጓጓች።

## 17

የዶክተር ናትናኤል መኪና ከፊት ለፊቱ የተጋረጠውን ጨለማ በመብራቶቹ እየሰነጠቀ መክነፍ ጀምሯል። የጣር ቤትን አደባባይ ዞረው፣ የአፍሪካ አንድነት ጽሕፈት ቤትን አልፈው፣ የሜክሲኮ አደባባይን ወደ ኋላ በመተው፣ ወደ ልደታ ቤተክርስቲያን የሚወስደውን መንገድ ጀምረዋል። ጥቂት እንደተጓዙ ወደ ቢሮዎ ወናፍጮ የሚወስደውን መንገድ ያዙ። መኪናቸውን አቁሙና ድንኳን ወደ ተተከለበት ግቢ ገቡ።

በእጃቸው የያዙትን ሲጋራ ሳያጠፉ፣ መላጣቸውን እያንተገተጉ፣ ጫት ቅሞ እንደተነሳ ሰው ዓይኖቻቸው ፈጠው፣ ያዩዋቸው የሀዘን ቤት ዕድምተኞች፣ በትኩረት ተመለከቷቸው። አንዱ እንዲቀመጡ ከጎኑ ያለውን ወንበር አሳያቸው።

ተቀመጡ።

በድንኳን ውስጥና በቤቱ በረንዳ ላይ ቡድን ፈጥረው የተቀመጡትን ሰዎች በሙሉ አንድ በአንድ አዩዋቸው። ምንም የሚያውቁት ሰው አላገኙም። ትንሽ ተቀመጡ። ስለንግሥት የሚጠይቁት ሰው አጡ። በድጋሚ ዓይኖቻቸውን ሲወረውሩ፣ ሲሳይ ከዋናው መኖሪያ ቤት ውስጥ ወደ በረንዳው ስትወጣ አዩዋት። እስከታያቸው ድረስ ጠበቁት። ከሴቶቹ ጋር ከተቀመጠች በኋላ፣ አየቻቸው።

ጠሯት በእጅ ምልክት።

መጣች። "እንደምን ዋሉ ዶክተር?"



የዶክተር በዚህ ሰዓት መገኘት አስደንግጧታል። የንግሥት አለመኖር ደግሞ ጭንቀቷን አንሮታል።

"እንደምን ዋልሽ?" ብለው ከመቀመጫቸው ተነሱ። ሀዘንተኛውን ሳይሰናበቱ፣ ከግቢው ይዘዋት ወጡ።

ሲሳይ በድንጋጤ ውስጥ ሆና ተከተለቻቸው። ንግሥትን ፈልገው እንደመጡ ማወቅ አልተሳናትም።

"ንግሥትን ጥሪያት እስኪ።" አሉ። "በጣም ፈልጊያት ነበር።" ሲሉ ቀጠሉ፣ ንግግራቸውን።

ሲሳይ የምትናገረው ጠፋት። ምን ብላ ትመልስላቸው? አፏ ተሳሰረ። በተፈጥሮዋ ድንጉጥ ናት።

"አሁን ወጣች።" አለች፣ ዓይኖቻቸውን ሳታይ።

"ወዴት?"

"ቡና መጠጣት ፈልጊያለሁ ብላ ወጣ አለች።"

"ብቻዋን?"

"አይ ሰው አለ።"

"ጥሩ። መኪና ውስጥ ሆኜ እጠብቃታለሁ።" አሉና የመኪናቸውን በር ከፍተው ገቡ።

ዝም አለች። ምን እንደምትላቸው ጠፋት። ተመልሳ ወደ ለቅሶ ቤቱ መግባቱን መረጠች። ግን፣ በሰላም መቀመጥ አልቻለችም። ንግሥት እንደማትመለስ ታውቃለች። ይሁንና፣ ይህንኑ ለዶክተሩ አልነገረችም። በትመለሳለች ተስፋ እየጠበቋት ነው። 'አትመለስም። አይጠብቋት።' ማለት ፈራች። 'ወዴት ሄደች?' የሚል ጥያቄ ማስከተላቸው አይቀርም። ወዴት ሄደች ትበል? ጠብቀው ሲሰለቻቸው ይሄዳሉ ብላ መቀመጡን መረጠች። ግን ደግሞ እንደማይሄዱ አወቀች። ዶክተሩ ልጃቸውን በጣም እንደሚፈልጉ ተናግረዋል። ከሁኔታቸው፣ የግድ እሷን ማግኘት እንዳለባቸው ተረድታለች። በመሰልቸት የሚመለሱ አልመሰላትም። መዋሸቷ እንዲታወቅባት አልፈለገችም።

ተነሳችና ከግቢው ወጣች። የዶክተር መኪና ወደ ቆመችበት ቀረበች። ዶክተር ናትናኤል ሀሳብ ውስጥ ሆነው ሲጋራቸውን በረጅሙ ሲስቡ አየች።

አጠገባቸው ስትቆም አይዋትና፣ "እህ... መጣች?" አሉ።

"አይ አልመጣችም። እዚህ የምትመጣ አይመስለኝም።" አለች፣ ፈራ ተባ እያለች።

"እንዴት?... ወደ ቤት ትሄዳለች?"

"ቤትም የምትሄድ አይመስለኝም።"

ሲሳይ ለጥያቄያቸው የሰጠችው መልስ፣ በንቃት እንዲመለከቷት አደረጋቸው።

"ታዲያ ወዴት ነው የሄደችው?" አሉ፣ በጥርጣሬ ስሜት።

ሲሳይ መልስ አልሰጠችም።

"ጭራሽ ወደዚህ አልመጣችም?"

"መምጣትማ ከአንድ ሰዓት በፊት መጥታ ነበር።"

"ታዲያ ወዴት ሄደች? ከማን ጋር ነው የሄደችው?"

"እኔ እንጃ።" ስትል ዋሸች፣ ሲሳይ።

ዶክተር ይበልጥ ጠረጠሩ። ከቤታቸው ሲገሰግሱ የመጡት፣ ንግሥት ውጭ ካደረች እርሳቸው የማይፈልጉትን ነገር ታደርጋለች ብለው ሠግተው ነበር። አሁን ሁኔታው፣ የጠረጠሩት ነገር እውነት መሆኑን እየነገራቸው ነው።

"አትዋሽኝ። እውነቱን ንገሪኝ። እኔ የማላውቀው ምንም ምስጢር የላትም። አሁን የፈለኳት፣ አንድ አስቸኳይ ነገር ገጥሞኝ ነው። ምንአልባት፣ ያለችበትን አሳይተሽኝ ካነጋገረችኝ በኋላ፣ ልታድር ያሰበችበት ቦታ መሄድ ትችላለች። ከማን ጋር ነው የወጣችው?"

"ከግርማ ጋር።"

የሚያውቁት ሰው ስም ሲነሳ ልባቸውን እንዳች ነገር እንደመርፌ ጠቅ አደረገው። ከግርማ ጋር ያላትን ግንኙነት ንግሥት፣ ቆርጣለች ብለው አስበው ነበር። ግን አላደረገችውም። ልባቸው ተጨነቀ። ከእንግዲህ ወዲያ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ማወቅ ተሳናቸው። ይሄን ያህል ጊዜ ግርማና ንግሥት ሳይለያዩ አብረው መቆየታቸውን ሲረዱ፣ ተስፋቸው ጨለመ።

ሲሳይ ፍዝዝ ብላ አየቻቸው።

"ወዴት እንደሄዱ የምታውቂው ነገር አለ?" ሲሉ ጠየቁ፣ ዶክተር።

ዝም አለች።

"ባክሽ ንገሪኝ። አትደብቂኝ። ተቸግሬ ነው። ንግሥትን አሁኑኑ ማግኘት አለብኝ።"

"ሐረር ፔንሲዮን ነው ለማደር ያሰቡት።"

"የት ነው ሐረር ፔንሲዮን? አሳይተሺኝ ትመለሺያለሽ? እኔ ራሴ መልሼ አመጣሻለሁ። ባክሽ አሳይኝ።" ሲሉ ተማፀኗት።

ሲሳይ ዶክተር ለአንድ ጥብቅና አስቸኳይ ጉዳይ ንግሥትን ለማግኘት እንደፈለጉ አመነች። ባይሆን ኖሮ፣ እንደዚህ ያለ ቦታ ተገኝ



ተው ልጃቸውን ለማሳቀቅ አይደፍሩም ነበር። ይሁንና፣ ከርሳቸው ጋር ሄዳ በንግሥት ላይ የሚታየውን የድንጋጤ ስሜት ማየት አልፈለገችም። ስለዚህ፣ ሆቴሉ የሚገኝበትን ቦታ በምልክት ነግራቸው መቅረት ፈለገች።

"እያሳስትም እኮ። አሁን የነገርኮትን አቅጣጫ ይዘው ከሄዱ የሆቴሉ ስም በትልቁ ስለተጻፈ በቀላሉ ያገኙታል።" አለች።

"ምልክቱን እንደገና ንገሪኝ እስኪ።"

"ነገረቻቸው።"

መኪናቸውን አስነስተው በረሩ።

## 18

በሆቴሉ ውስጥ የተከራዩትን ክፍል ከፍተው ከገቡ ቆይተዋል። ራት አስመጥተው በልተዋል። አሁን ቢራ በመጠጣት እያወሩ ነው። ትንሽ ለብ ያላቸው ይመስላሉ። የቢራው ሀይል ነፃ ሆነው እንዲጫወቱ አድርጓቸዋል። ዓለም የያዘችው እነሱን በማስተናገድ ላይ ያለችውን ክፍል ብቻ ሆኖ ተሰምቷቸዋል።

ግርማ ጫማዎቹንና የእግር ሹራቦቹን አወላለቀና አንዱን ትራስ በግርጌ በኩል አድርጎ በመደገፍ ጋደም አለ። ንግሥትም ጫማዎቿን በእጇ ሳይሆን፣ በእግሮቿ አወላለቀችና ሌላኛውን ትራስ ተደግፋ በራስጌ በኩል ጋደም አለች።

ለጥቂት ሴኮንዶች ያህል ሳይነጋገሩ ቆዩ። ሁለቱም የልቦቻቸውን ምቶች የሚያዳምጡ ይመስላሉ።

ንግሥት የግርማን የውስጥ እግር በጥፍሮቿ ቧጠጥ አደረገችው።

ከስጠማበት ሀሳብ ውስጥ ፍንጥር ብሎ ወጣ። "ተይ እንጂ! አልወድም። ባክሽ ተይ!" እያለ እግሮቹን ሊሰበስብ ቢሞክርም፣ አልቻለም።

ንግሥት እየሳቀች፣ እግሮቹን እያፈራረቀች ስትቧጥጥ፣ እጇን ያዘው። እንደመጠምዘዝ ሲያደርገው ጮኸች። አልጨከነባትም። መጠምዘዙን ትቶ እጇን እንደዋዛ ያዘው። ተያዩ። ዓይኖቻቸው በራሳቸው ቋንቋ ተነጋገሩ። የፍቅር መልዕክት ተለዋወጡ። አገጯን ቀና አደረገው። ከንፈሮቻቸው ተቀባለሉ። የዚህችን ምድር ነገረ ዓለም ረስተው ራሳቸው በፈጠሩት ብሩህና ጣፋጭ ድባብ ውስጥ ሆነው አልጋው ላይ ወደቁ።

ከጥቂት ሴኮንዶች በኋላ፣ በሰላም፣ በፍቅርና በደስታ የተሞላውን መኝታ ቤት ድንገተኛ የሆነ ድምጽ ረበሸው። የክፍሏ በር ኳኳታ ሁለቱን ጉብሎች መጥቀው ከነበሩበት ዓለም ውስጥ እንደ ዓሣ መንጥቆ አወጣቸው። ሁለቱም ከአልጋቸው ላይ ቀና አሉና ባሩድ እንደሸተታት ሚዳቋ ጆሮዎቻቸውን አቅንተው በሩን ተመለከቱና ርስ በርሳቸው ተያዩ።

"ማነው?" አለ ግርማ፣ የንዴት ቃና ባለው ድምጽ።

"እኔ ነኝ። አንድ ጊዜ ይከፈቱ እስኪ።" አለ፣ የሆቴሉ አሳላፊ።

ግርማ ከአልጋው ላይ ወረደና ጫማዎቹን ያለካልሲ በማድረግ በሩን ከፈተው።

"ምንድን ነው?" ሲል ጠየቀ።

"አንድ ጊዜ አንድ ሰው ሊያነጋግሮት ይፈልጋል።" አለ አሳላፊው።

"እኔን?"

"ግርማ ባዩ፣ እርስዎ አይደሉም?"

"ነኝ።"

ግርማ ክፉኛ ደነገጠ። በዚህ ሰዓት፣ በዚህ ደቂቃ፣ እርሱ እዚህ ክፍል ውስጥ መሆኑን አውቆ ሊፈልገው የመጣ ሰው ምንና ለምን እንደሚሆን ሊገባው አልቻለም።

"በጣም አስቸኳይ ለሆነ ጉዳይ ነው የምፈልጋቸው ብለዋል።" አለ አሳላፊው።

"የት ነው ያለው ሰውዬው?"

"ቡና ቤት ውስጥ ነው።"

"መጣሁ።" አለና ተመልሶ ወደ ክፍሉ ገባ።

"ምንድን ነው?" ስትል ጠየቀች፣ ንግሥት።

"አይ ምንም።" አለ።

የእግር ሹራቡንና ጃኬቱን ለባብሶ ሲዘጋጅ አየችው።

"የት ልትሄድ ነው?"

"መጣሁ። የመኝታ ቤት ፎርም ሞልቼ መጣሁ።" ሲል ዋሸትና ወጣ።

አሳላፊውና ግርማ ያደረጓቸውን ቃለ ምልልሶች ባለመስማቷ አልተጠራጠረችም።

ግርማ ከክፍሏ ወጥቶ ወደ ቡና ቤቱ ሲገባ፣ አሳላፊውን አገኘው። ፈላጊውን ሰው አሳየው።



ሰውዬውን ሲመለከት ዓይኖቹን ማመን አቃተው። ልቡ በድንጋጤ ትርትር አለ። መላ አካሉ ሙሽሽ አለ።

ሲጋራቸውን እያጨሱ ቡና ይዘው ቁጭ ብለዋል።

ለግማሽ ደቂቃ ያህል ቆሞ ተመለከታቸውና ፈራ ተባ እያለ ተጠጋቸው።

"እንደምን አመሹ፣ ዶክተር?" ሲል ለስለስ ባለና ፍርሀት ባዘለ አነጋገር ሰላምታ አቀረበ።

ዶክተሩ ምንም ቃል ሳይተነፍሱ ጨበጡት። ብርጭቆው ውስጥ የቀረችውን ቡና ጨለጡና ሂሣቡን ጠረጴዛው ላይ አስቀምጠው ተነሱ። "እንውጣ። ለጥብቅ ጉዳይ እፈልግሀለሁ።" ብለው እጁን ይዘው ወጡ።

ሁኔታቸው አስፈራው። የዶክተሩ ገጽታ የተለመደ ሆኖ አልታየውም። ግንባራቸውና መሀል አናታቸው ላይ ላብ ኩሬ ሰርቷል። ዓይኖቻቸው ከጉርጓዶቻቸው ቱር–ብለው ለመውጣት የተዘጋጁ ይመስል ተጎልጉለዋል። አለባበሳቸውም አላማረውም። ነገር ዓለሙን ንቆ የተገኘ እብድ አስመስሏቸዋል።

መኪናዋ ውስጥ ገቡና ተቀመጡ።

ዶክተሩ ሊናገሩ የፈለጉትን ነገር ከምን እንደሚጀምሩ የከበዳቸው ይመስላል። በሀሳብ ሰጥመው፣ ሲጋራቸውን መሳብ ብቻ ሆነ።

ግርማ ከቅድሙ ይልቅ አሁን በጣም ደንግጦአል። ከዚህ በፊት ከንግሥት ጋር ያለውን ግንኙነት እንዲቆርጥ አበክረው አስጠንቅቀውት ነበር። ይሁንና፣ እሱም ሆነ ንግሥት የሰውዬውን ቃል አክብረው አልተገኙም። በድብቅ እንቀጥለዋለን ያሉት ነገር አሁን ያለበት ደረጃ አድርሷቸዋል። በዚህ ሁኔታ ዶክተሩ መናደዳቸው ግልጽ ነው። ለዚህ ጥፋት ርምጃ ለመውሰድ እንደመጡ ገብቶታል። ግን ምን ዓይነት እንደሆነ ለመገመት አልቻለም።

ዶክተሩ ግርማን በእነዚያ ተዋጊ በሚመስሉ ዓይኖቻቸው ተመለከቱት። ለመናገር ከንፈሮቻቸውን አላወሱ...

## 19

በክፍሏ ውስጥ ተፈጥረው የነበሩት ሰላም፣ ደስታና ፍቅር በበሩ ኳኳታ ቢደናቀፉም፣ በንግሥት ስሜት ላይ እንዳሉ ናቸው። በጀርባዋ ጋለል ብላ ከሴኮንዶች በፊት ተፈጥሮ የነበረውን የደስታ

ጊዜና ከሁለት ቀናት በፊት ከአርአያ ጋር ያሳለፈችውን የተረገመ ሌሊት አወዳደረች። ሴት ልጅ ከወንድ ጋር የሚኖራት ግንኙነት በዚያን ቀን ማታ ባየችው እንስሳዊ ተግባር የሚገለጽ ከሆነ ፍቅር፣ ሰላምና ደስታ የሚባሉ ነገሮች የሉም። እነርሱ ከሌሉ ደግሞ ሕይወት አትጥምም።

'ያለ የጋራ ፍላጎት የሚሆን ነገር ሁሉ ፍሬ አልባ ነው። አንዱ ሲደሰት አንዱ የሚያዝን ከሆነ፣ የተሟላ ደስታ አይኖርም። በአንዱ ቁስል ሌላው የሚረካ ከሆነ፣ ሕይወት አስቀያሚ ትሆናለች። የሚጣፍጥ ነገር ታጣለች። የሚደረገው ነገር ሁሉ ዋጋ የለውም። ወሲባዊ ግንኙነት በሁለት ተቃራኒ ጾታዎች እኩል ፍላጎት ካልተካሄደ፣ የአንዱን ልብ አቁስሎ የሌላውን የሚያሽር ከሆነ፣ እርባና ቢስ ነው የሚሆነው። ይህ ግንኙነት የፍቅር ቁንጮ በመሆኑ በፍላጎት ከተደረገ የማይደርቅ ደስታና ሰላም ይገኛል ።' አለች ለራሷ። ወዲያው እንዲህ ያለ ትንተና ውስጥ ለምን እንደገባች ራሷን ጠየቀች። ትንሽ የተፈላሰፈች መሰላት። እንዲህ ሊያሳስባት የቻለው ምን እንደሆነ ሊረዳት አልቻለም። በአርአያ ላይ ያለው ጥላቻ መሆኑ ግን ቀስ ብሎ ገባት። ሁኔታውን ለመርሳት ዓይኖቿን ከደነች። ረሳችው። ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ከግርማ ጋር ያደረጓቸው የፍቅር ጨዋታዎች ድቅን አሉባት። ' በጣም የሚጣፍጡና የሚያስደስቱ።' አለች በልቧ። ከግርማ ጋር ረጅም ሰዓታት ሲያሳልፉ የዛሬው የመጀመሪያ ነው። የተመቻቸ አጋጣሚ አግኝተው አያውቁም ነበር። ባለበት የሥራ ፀባይ ብዙ ጊዜ አዲስ አበባ ውስጥ አይገኝም። በሚገኝባቸው ቀናት ደግሞ፣ ብዙ ጊዜ እርሷ አይመቻትም ነበር። ሁለቱም እንደዚህች ያለችውን ቀን ናፍቀው ነበር።

የእጅ ሰዓቷን አየች። " እንዴ ! ወዴት ሄደ?" ስትል ለራሷ ተናገረች። ከወጣ አሥራ አምስት ደቂቃዎች ተቆጥረዋል። ትንሽ እንደመጨነቅ ብላለች። ቸኩላለች። ደቂቃዎች በዘለሉ ቁጥር ደግሞ፣ ጭንቀቷ እየናረ ሄደ። ከአልጋው ላይ ቀና አለች። አነስተኛ ጠረጴዛ ላይ የተቀመጠውን ጠርሙስ አየች። ጠርሙሱ ውስጥ የቀረውን ቢራ ጨለጠችና ጋደም አለች።

ግርማ ከክፍሏ ከወጣ ከሀያ ደቂቃዎች በኋላ ተመለሰ።

የንግሥት ልብ በደስታ መምታት ጀመረ። ፊቷን እንዳያይባት ብላ የአልጋ ልብሱን ተከናንባ ተኛች።

እንደገባ በሩን ዘጋና አልጋው ላይ ተቀመጠ። ፊቱ በሀዘን ተጥለቅልቋል። ጫማዎቹንና ካልሲዎቹን አወላለቀና አልጋው ላይ ወጣ።



ልብሶቹን ሳያወልቅ ጋደም አለ። መላ አካሉ እንደተቀቀለ ጎመን ሙሽሽ ብሏል።

የንግሥት ስሜት ተቅበጥብጧል። የግርማ አጠገቧ መገኘት የልብ ትርታዋን ጨምሮታል። እንደተከናነበች ድምጿን አጥፍታ የግርማን ርምጃ በናፍቆት ጠበቀች። ሆኖም፣ ከግርማ ምንም መልስ የለም። የአልጋ ልብሱን ገልጣ ቀና ብላ አየችውና ከንፈሮቹ ላይ ሳመችው። ዓይኖቹ ፈዘው ሩቅ የሚያዩ መስለዋል። ፊቱ ምጥጥ ብሎ አስከሬን መስሏል። ይህ ሁኔታ የንግሥትን ልብ ቆንጠጥ አደረገው።

" ምን ሆነሀል ?" ስትል ጠየቀችው ከፉኛ ደንግጣ።

ዝም አለ።

" ግርማ፣ የት ነበር የቆየኸው?"

" ተይኝ ባክሽ። ልተኛበት።"

ይበልጥ ቀና ብላ በትኩረት አየችው። " ምን ሆንክ?"

" ምንም አልሆንኩም።"

" ማን ነበር የጠራህ ?"

" አሳላፊው።"

" ከሰው ጋር ተጣላህ እንዴ ?"

" ባክሽ ተይኝ፣ ንግሥት። ልተኛበት። አንቺም ተኚ። ነገ የሥራ ቀን ነው።"

ደነገጠች። ግርማ አንድ የተከፋበት ነገር እንዳለ ገባት። ንዴቱን ለማስረሳት ብላ በአንድ እጇ አንገቱን እቅፍ አድርጋ በሌላ እጇ ጣቶች ደግሞ አንዴ ፀጉሩን ሌላ ጊዜ ደግሞ ደረቱን እየደባበሰች ብትሞክርም፣ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት በክፍሏ ውስጥ ሰፍኖ የነበረውን የፍቅር ድባብ መልሳ ማምጣት አልቻለችም። ሁኔታው ሳይሳካላት ሲቀር ጊዜ፣ የጠየቀውን እንደከለከሉት ህፃን ተሳቀቀች። የግርማ መንቻካነት አናደዳት። ብሽቅ እንዳለች ነጋላት...

## 20

መጠጥ ቤቱ ውስጥ ያለው ትርኢት ምሽቱን ወደ ሰዓት አላፊ ድንበር የሚያቀርቡት ደቂቃዎች በተጨመሩ ቁጥር እየደመቀ፣ ይበልጥ እየሳበ አትውጡ የሚያሰኝ ሆኖ አገኘው። የሙዚቃ መራጩ የጠጪዎችን ስሜት የሚመስጡ ዜማዎች ተራ በተራ ያስደምጣል። በምሽቱ መጀመሪያና መገባደጃ ላይ የሚሰሙ ሙዚቃዎች የራሳቸው

የሆን ተልዕኮ አላቸው:: ምሽቱ እያረጀ በሄደ ቁጥር ወደ ሞቅታው ዓለም ዘው የሚሉትን የቡና ቤቱን ታዳሚዎች ከመቀመጫቸው ተነስተው እንዲደንሱ ፈንቅሎ ያስነሳቸዋል::

የቡና ቤቱ አስተናጋጆችም ጠጪዎችን ከማስተናገድ ሌላ፣ በምሽቱ ልዩ ልዩ ሰዓታት የሚያሳይዋቸውን ድርጊቶች ይለያሉ:: ከሴት ጋር ለማደር ፈልጎ የሚመጣን ወንድ በቡና ቤት ውስጥ ባሳለፉት የሥራ ቆይታ ያውቁታል:: በሚያዘው የመጠጥ ዓይነት፣ በሚወስደው የመጠጥ ብዛትና በዓይኖቹ እንቅስቃሴ ያውቁታል:: ሊያድር ከጅሏል ብለው ያሰቡት ወንድ ጎን ጠጋ ጠጋ በማለት ሲያልፉ ሲያገድሙ መቀመጫቸውን በማውረግረግ ወይም የሚያልፉ መስለው አካልን በማነካካት ፍላጎቱን ለማሳደግ ይሞክራሉ::

ተሰማ፣ እስከዛሬዋ ምሽት ድረስ በአዲስ አበባ ውስጥ አሉ የሚባሉትን ቆነጃጅት ሴተኛ አዳሪዎች በብዙ ቡና ቤቶች ውስጥ ጎብኝ ቷል:: በፒያሳ፣ በካዛንቺስ፣ በመርካቶ፣ በተክለሀይማኖት፣በ 'ካንቦዲያ' ፣በሳሪስ፣ በአራት ኪሎና በሰንጋተራ የሚገኙ ስም ያላቸው ቡና ቤቶች ውስጥ ከሚገኙ ቆንጆ ከሚላቸው ሴተኛ አዳሪዎች ጋር አድሯል:: ግን፣ እዚህ ቡና ቤት ውስጥ እሱ ከተቀመጠበት አካባቢ ያሉትን ደንበኞች ከምታስተናግደው ልጅ እግር ሴት የበለጠ ማራኪ አይቶ አያውቅም::

ልጅቷ ስታልፍ - ስታገድም፣ ያም ያም ጎሸም ስለሚያደርጋት ነው መሰል ለእሷ ያለው ፍላጎት እጅግ ከፍ አለ:: ጠቀሳት:: አጠገቡ መጣች::

"ቁጭ በይ:: "አላት:: ከጎኑ ያለውን ባዶ ወንበር እያሳያት::

ተቀመጠች - ለወጉ እንደመሸኮርመም ብላ::

"እኔን ምሰያ:: " አለ፣ የሚጠጣውን ውስኪ እያሳያት::

ፍንጭት ጥርሶቿን በቀይ ዳማ ፊቷ ላይ ብልጭ አደረገቻቸውና መጠጥ ይዛ ለመምጣት ተነስታ ወደ ባንኮኒው ሄደች::

በቤቱ ውስጥ ያሉ አብዛኞቹ ወንዶች ቀጠን ብሎ የሚወርደውን ወገቧንና ዳሌዋን በዓይኖቻቸው ተከተሉ::

ይህ ሁኔታ ተሰማን አስደሰተው:: የብዙ ሰዎችን ትኩረት ከያዘች ሴት ጋር ማደር 'እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል ' አላማውን በቀላሉ እንደሚያሳካለት ያምናል::

ተሰማ የኤድስ ህዋስ በደሙ ውስጥ እንዳለ ለአባቱ ቅርብ በሆነ አንድ የህክምና አዋቂ ከተነገረው ጊዜ ጀምሮ በህይወት ላይ



ያለው ተስፋ በንኗል:: ደስተኛ አይደለም:: ይበሳጫል:: ከሰዎች ጋር ይጣላል:: ከቤተሰቡ ጋር ይጨቃጨቃል:: ከአንድ ራሱ ጋር ይጋጫል::

ይህ ሁኔታ ራሱን እንዲደብቅ ይገፋፋዋል:: 'ጥፋ-ጥፋ፣ ሽሽ-ሽሽ!' ይለዋል:: ከሚያውቁት ሰዎች ቢደበቅም፣ ቀን- ቀን ከተወለደበት፣ የልጅነት ጨዋታውን ከተጫወተበትና ከአደገበት አካባቢ ቢርቅም፣ ከአንድ ራሱ ሊደበቅ አልቻለም:: ይህ ሁኔታ ለመጠጥ ተገዢ አድርጎታል:: መጠጥ ሲጠጣ ራሱን መጥላትና መሸሽ ይተውና ሰዎችን ይጠላል:: ያሳድዳቸዋል:: የምቀኝነትና የሰይጣናዊ ስሜት ያድርበትና እርሱ ከእግር እስከራሱ የተዘፈቀበት የዘመኑ ስቃይ ውስጥ ሌሎች ሰዎችን ለመክተት ይዘጋጃል::

የዚህ ዓለማው ማሳኪያ ዘዴ ብሎ የያዘው በየቡና ቤቶች ውስጥ ያሉ ሴተኛ አዳሪዎችን የበሽታው አከፋፋይ አድርጎ መውሰድ ነው:: ለዚህ ተግባር ማሳኪያ ባለፉት ዘመናት ያፈራቸውን መኖሪያ ቤትና ዘመናዊ የቤት ዕቃዎች ሸጧል :: አባቱ በርሱ ስም የገዙትን የጭነት መኪና፣ እሳቸው ሳይሰሙ፣ ለመሸጥ በመስማማት ቀብድ በልቷል:: ከመሥሪያ ቤቱ የቁጠባና የብድር ማኀበር የተፈቀደለትን ገንዘብ ወስዷል:: በተጨማሪ፣ ባንክ የፈቀደለትን ብድር በእጁ አግብቷል::

በዚህ ሁሉ ብር፣ በሽታው እስካቆየው ድረስ፣ እየተዝናና ብዙ ተከታዮችን የማፍራቱን ተግባር ሥራዬ ብሎ ተያይዞታል::

ልጅቷ በመለኪያ የተቀዳውን ውስኪ ይዛ መጣችና ተቀመጠች::

"ኖር!" አለ፣ ከመቀመጫው ሳይነሳ::

"በእግዜር!" አለች፣ ልጅቷ:: እንደሌሎቹ ሴተኛ አዳሪዎች በአንገቷ ላይና በግንባሯ ላይ ንቅሳት የለም::

"ሙዚቃ አመራረጣችሁ በጣም ጥሩ ነው::" አለ፣ ንግግር ለመጀመር ብሎ::

"አዎ ጥሩ ነው:: ብዙ ሰዎች ይወዱታል::" አለች::

"እኔ ያለዛሬ ይሄን ቤት አይቼው አላውቅም:: ከሩቅ አካባቢ ነው ዝናውን ሰምቼ የመጣሁት::" አለ መንደሪን የመሰሉ ጉንጮቹን አፈራርቆ እየተመለከተ:: ነካ ቢያረጋቸው የሚፈርጡ ይመስላሉ::

"ብዙ ናቸው፣ ከሩቅ አካባቢ የሚመጡት::" አለች::

"በዚህ ጠባብ ቤት ይሄ ሁሉ ሴት ተቀጥሮ ነው?" አለ፣ በቡና ቤቷ ውስጥ የሚዋከቡትን ሴቶች አይቶ::

"ጥቂት ነን እዚህ ተቀጥረን የምንሠራው። ሌላው የ'ኮቴ' ክፍሎ የሚሄድ ሴት ነው።" አለችና ውስኪውን ተጎነጨች።

"ኮቴ ደግሞ ምን ማለት ነው ?"አለ መኮላተፍ እየቃጣው።

ፈገግ አለችና፣ "እነዚህ ሁሉ ሴቶች ለገበያቸው ብለው ነው እዚህ የመጡት። እዚህ ቤት ውስጥ ወንድ አግኝተው ካደሩ ሶስት ብር ለቡና ቤቱ ባለቤት ይከፍላሉ። ይሄ ነው የኮቴ ክፍያ የሚባለው።" አለች።

"እሀ!..." አለና ሴቶቹን በመገረም ያያቸው ጀመር። ከዚያም ዓይኖቹን መለሰና ያፈጠጡ ጡቶቿን በሹራቧ ውስጥ ዘልቆ አየ። ውበቷ ሁሉ ያለው እዚህ ላይ መሰለው። የወሲብ ፍላጎቱ ተቀሰቀሰበት።

"ተጫወት !"አለች፣ ልጅቷ።

"እሺ።" ብሎ ትንሽ ቆየት ካለ በኋላ ፣ "ሰው አለሽ እንዴ ዛሬ?" ሲል ጠየቃት።

"አዎ!" አለች፣ መለኪያውን ጠረጴዛው ላይ እያንሸራሸረች።

ተሰማ እንደመናደድ ብሎ ዝም አለ። ይሁንና፣ ከልጅቷ ጋር የማደር ፍላጎቱ ናረ። "ምን ያህል ሊከፍልሽ ነው የተስማማው?"

"ሠላሳ ብር። " ስትል፣ ዋሸች።

"ፈንግይው። እኔ አርባ እሰጥሻለሁ።" አለ፣ ተሰማ በሞቅታ።

"አይከብድም?"

"ምን ይከብዳል? መፈንጋገል ያለ ነው!"

"ጥሩ። የት ነው አልጋ የያዝከው?"

"ከዚህ ቤት ቀጥሎ ያለው ሆቴል ውስጥ።"

"ጥሩ።"

"ውስኪ ድገሚና እንሂድ።"

"ገና እኮ ነው ሰዓቱ። አሁን አራት ሰዓት ነው። በአምስት ሰዓት ነው ሥራ የምናቆመው።"

"እዚህ ያለው ቢቆምም፣ እዚያ እንቀጥለዋለን።" አለ ፈገግ ብሎ።

እሷም ፈገግ ብላ፣ "አይሆንም። በጊዜ የምወጣ ከሆነ የመውጫ የሚባል ነገር አለ። ባለቡና ቤቱ አሥር ብር ያስከፍሉኛል።" አለች።

"ምንድን ነው ደግሞ እሱ?"



"ከሰዓቱ በፊት ከወንድ ጋር የምወጣ ከሆነ ለባለቡና ቤቱ የሚከፈል ነው።"

"ይኼም አለ?"

"አዎ!"

"እሺ ድገሚና እንሂድ። እከፍላለሁ። "አለ ተሰማ።

"ከከፈልክ ጥሩ ነው።" አለችና የእሱንም፣ የእሷንም መለኪያዎች ልታስቀዳ ይዛ ሄደች።

ተሰማ ሲጋራ ለኮሰና ከበስተኋላ በዓይኖቹ ተከተላት።

ሙዚቃው ልዩ ቃና አለው። ልብን ሰርስሮ የመግባት፣ አእምሮን የማዝናናት ሀይል አለው። ደብዘዝ ያለው ብርሀን የደስታ ድባብ በቡና ቤቱ ውስጥ አንግሷል።ግርግሩ እንደቀጠለ ነው።

ልጅቷ መለኪያዎቹን ይዛ መጣች።

አሁንም፣ "ኖር!" አለ።

"በግዜር!"

የሲጋራውን ፖኮ ወደ እሷ አስጠጋና፣ "ሲጋራ ተጋበዢያ።" አለ።

"አሁን አላጨስም። በኋላ አጨሳለሁ።" አለች።

"አሁንም በኋላም ይቻላል። "አለ፣ መኮላተፍ እየቃጣው።

"እኔ ሲጋራ ማጨስ የምወደው ከእንትን... በኋላ ነው። ያው ይገባሀል።" አለች በፊቷም፣ በጥርሶቿም፣ በዓይኖቿም እየሳቀች።

"እሀ!... ጥሩ።" አለና መለኪያውን አነሳ።

"አንድ ነገር ሳልነግርህ... " አለችና ንግግሯን ቆረጠችው።

"ምን?" አለ ተሰማ። ቀይ ፊቱ በርበሬ መምሰል ጀምሯል።

"ከእኔ ጋር የሚያድሩ ወንዶች አንዳንድ በሽታዎች ከእኔም እንዳይወስዱ ከእነሱም እንዳልወስድ ኮንዶም ገዝተው እንዲመጡ እጠይቃለሁ።" አለች።

ተሰማ ድንገጥ ብሎ በእጁ የያዘውን መለኪያ ጠረጴዛው ላይ አስቀምጦ አያት። ፊቱ ይበልጥ ቀላና የበሰለ ቲማቲም መሰለ። ስለ እሱ የሰማችው ነገር ያለ መሰለው። በጥርጣሬ አያት። 'የትኛዋ የቡና ቤት ሴት ናት ስለ ራሷም ሆነ ስለሌላው ጤንነት የምታስብ? አንድ የሰማችው ነገር አለ። 'አለ በልቡ። በቡና ቤቱ ውስጥ ያሉትን ሰዎች በሙሉ ቃኘ። የሚያውቀው አንዳችም ሰው የለም።

ስለርሱ በሽታ የሚያውቁ ሰዎች፣ የመረመሩት ሀኪም፣ አባትና እናቱና ያሳደጉት ልጅ፣ አፈወርቅ ምንዳዬ፣ ብቻ ናቸው። ሀኪሙ ለማንም እንዳይናገሩ የተሰማ አባት በገንዘብ ደልለዋቸዋል። የቤተሰቡ አባላት ደግሞ የልጃቸውን ጉድ ለሰሚ አያደርሱም። ከቤተሰቡ ተጣልቶ የነበረውን፣ አፈወርቅ ምንዳዬን፣ የልጃቸውን የተሰማን ምስጢር በበቀል እንዳያወጣ፣ አባቱ በመርዝ አስገድለው ራሱን እንደሰቀለ ካስመሰሉ በኋላ፣ ከመሬት ውስጥ መግባቱን አረጋግጧል። ይሁንና ይህቺ ሴት ጠርጥራዋለች። ወይም አውቃለች።

በሀሳብ መዋጡን አየችና፣" ምነው ዝም አልክ ?ይህንን ያልኩት እኔ በሽታ አለብኝ ብዬ አይደለም። እኔ ሙሉ ጤነኛ ነኝ። ግን እኔም አንተም ከሀሳብ ነፃ እንድንሆን በኮንዶም እንጠቀም ብዬ ነው።" አለች በማባበል።

"ጥሩ። ደስ ይለኛል። በይ ጠጪና ተነሽ። ገዝቼ መጣሁ።"አለና ወጣ።

ከትንሽ ደቂቃዎች በኋላ ወደ ቡና ቤቱ ተመለሰና ልጅቷን ይዞ ወደ ክፍሉ አመራ። እንደገቡ በሩን ቆለፈና ልጅቷን አንቆ አልጋው ላይ ሊወረውራት ሲሞክር አፈትልካ ወጣች።

"መጀመሪያ ሂሳብ ስጠኝ። "አለች።

ከኪሱ ውስጥ ቦርሳ አወጣና ከብዙ የብር ኖቶች መሀል ሀምሣ ብር መዝዞ ሰጣት።

ብሩን ከተቀበለች በኋላ፣ "ኮንዶሙንስ ገዛህ ?" ስትል ጠየቀችው።

"በዚህ በጨለማ ከየት ይገኛል ብለሽ ነው?"

የተቀበለችውን ብር ወርውራለት ልትወጣ ስትል እጇን ይዞ አስቀራት።

"በእኔ በኩል አትጠራጠሪ ጤነኛ ነኝ።" አለ፣ በመቀጠል።

"አልፈልግም! አልችልም! " ብላ መንጭታ ልትወጣ ስትል፣

"ቆይ!" አለ። ቦርሳውን እንደገና ከኪሱ አውጥቶ፣" ፍጹም ጤነኛ ነኝ። በኮንዶም ሴክስ ማድረግ ስለማያረካኝ ነው። ከፍላጎትሽ ውጭ ከእኔ ጋር በማደርሽ ሌላ ተጨማሪ ሀምሳ ብር ልስጥሽ። "አለ። የሀምሣ ብር ኖት እንደገና መዝዞ ሰጣት።

በእጁ የያዘውን ብርና ፊቱን እያፈራረቀች ተመለከተች። ብሩ አጓጓት። በአንድ ሌሊት አዳር ይሄን ያህል ገንዘብ የሚከፍል ወንድ አጋጥሟት አያውቅም። እንደገና ፊቱን ተመለከተችው። ጤነኛ



ነው ብሎ የመሰከረላት ይመስል ተጽናናች። ከፊቷ የቀረበውን የማታ ሲሳይ ማለፍ አልፈለገችም።

'አዎ! ሁኔታው ጤነኛ ይመስላል። ከእንደዚህ ዓይነት ሰው የኤድስ በሽታ ሊገኝ አይችልም።' ስትል ራሷን አበረታችና ብሩን ተቀበለች።

ምሽቱ ከሕይወት ወደ ሞት የቀረበችበት ጊዜ ሆነ.....

## 21

ዛሬ ያለወትሮዋ ሁለት ሰዓት ሳይሞላ ነው ቢሮዋ የገባችው። የቢሮዋን መስኮቶች ከፋፍታ ወንበሯ ላይ አረፍ እንዳለች፣ አንድ ሰው ገባ።

"እንደምን አደርሽ ንግሥት?" አለና እጁን ለመጨበጥ ዘረጋላት።

ግራ በተጋባስሜት አተኩራ ተመለከተችው -ከቀይ ዳማ ፊት ጋር ተፋጠጠች። 'የት ነው የማውቀው?' በሚል ሁኔታ መላ አካሉን በዓይኖቿ ቃኘችው።

መካከለኛ ቁመት አለው። ዕድሜው ሠላሳ አምስት ቢሆን ነው። ፀጉሩ አጠር ባለ ሁኔታ ተከርክሟል። ዓይኖቹ ጎላ ጎላ ያሉ ናቸው። አወራረዱ ካማረ አፍንጫው ሥር ያለው ሪዙ ጥቅጥቅ ያለ ነው። ደልደል ያለ ሰውነት አለው። ቡላማ ሙሉ ሱፍ ለብሷል። ጠቆር ባለ ሸሚዙ ላይ፣ በግራጫ መደቡ ላይ ፈዘዝ ያለ ውሀ ሰማያዊ ሸንተረር ያለው ክራቫት አስሯል።

"ደህና እግዚአብሔር ይመስገን!" አለችና ከመቀመጫዋ ተነስታ ጨበጠችው።

"ዘነጋሽኝ መሰለኝ?"

በመዘንጋቷ አፈር ብላ፣ "አዎ! የት ነበር የምንተዋወቀው?" አለች።

"እዚሁ ነው። የመሥሪያ ቤታችሁ ባለጉዳይ ነኝ። ከአንድ ከሁለት ወራት በፊት ነው ለመጨረሻ ጊዜ የተያየነው። ሥራ አስኪያጁ የሚፈርሙበትን ለእኔ የሚሰጥ አስቸኳይ የሥራ ደብዳቤ የሚጽፍልኝ ታይፒስት ባለመኖሩ የምሣ ሰዓትሽን ሰውተሽ አዘጋጅተሽልኝ ነበር። በዚህ ውለታሽ አልረሳሁሽም።" አለ በፈገግታ።

ንግሥት አሁን ትዝ አላት። "እ!... አስታወስኩ! ደህና ነህ"

"ደህና። ደህና ነሽ አንቺ?"

"ደህና ነኝ። ይቅርታ በመዘንጋቴ። እዚህ ብዙ ባለጉዳዮች ስለሚመጡ ሰዎችን ለይቶ ማስታወሱ አስቸጋሪ ነው።"

"አዎ፣ ያስቸግራል።"

"ተቀመጥ። ሻይ ቡና ይምጣልህ።"

"አይ፣ አልጠጣም። አመሰግናለሁ።" አለና ተቀመጠ። "ባለፈው ጊዜ ያደረግሽልኝ ውለታ በእውነት በጣም አስደስቶኛል። በማግስቱ ወደ ውጭ ሀገር በረራ ነበረብኝ። ያን ደብዳቤ በወቅቱ ባላገኘው ኖሮ ከጉዞዬ እስናከል ነበር። ብዙ ነገርም አጣ ነበር። በእውነት፣ እንዲህ ነው ብዬ ላጣ የምችለውን መናገሩ አስፈላጊ ባይሆንም፣ በደፈናው ለእኔ ትልቅ የምለውን አድርገሽልኛል። የምሳ ጊዜሽን ሰውተሽ ደብዳቤውን ስለፃፍሽልኝ ቶሎ ደረሰለኝ። በጣም ነው የማመሰግንሽ።" አለ በእጁ የያዘውን የተጠቀለለ ነገር እያሳያት፣ "ይህችን ትንሽ ስጦታ አምጥቼልሻለሁ።" አለ።

ንግሥት ፈገግ ብላ ተቀበለችው። "ምንም እኮ አልነበረም። አያስፈልግም ነበር። በጣም አመሰግናለሁ። "አለች።

"አይ፣ በጣም ቀላል ነገር እኮ ነው። እንደ አንቺ ያሉ ቅን ሰዎችን ጓደኛ ማድረግ በጣም ደስ ይለኛል። ዳንኤል ፈጠነ እባላለሁ።"

"ንግሥት ናትናኤል እባላለሁ።" አለች።

"ፈቃድሽ ከሆነ ዛሬ ምሳ ብጋብዝሽስ ?"

ጥቂት አሰበችና "በሌላ ቀን ቢሆንስ?" አለች።

"ደስ ይለኛል። በፈለግሽው ቀን ታዛዥ ነኝ።" አለ ከመቀመጫው በመነሳት።" ነገስ? ቅዳሜ ነው። ከሰዓት በኋላ ሥራ የለሽም። ብዙ መጫወትም እንችላለን።" አለ በድጋሚ።

ዝም አለች።

"ምነው ፣ አይመችሽም?"

" አላወቅሁትም።"

" ጥሩ። የምትችይ ከሆነ በዚህ ስልክ ቁጥር ደውይልኝ። " አለና አድራሻውን የያዘ ካርድ ሰጣት።

" እሺ።" ብላ ተቀበለች።

" ከቻልሽ ዛሬ ማታ ብትደውይልኝ ጥሩ ነው። እጠብቃለሁ።"



" እሺ ፣ እሞክራለሁ። " አለች።

ተሰነባብተው ተለያዩ።

## 22

ስድስት ሰዓት ሆና ከመሥሪያ ቤቷ ቅጥር ግቢ ከወጣች በኋላ፣ በታክሲ ተሳፈረችና ጉዞዋን ወደ ቀጠሮው ቦታ አደረገች።

ዳንኤል ፈጠነ ትናንትና ጠዋት ቢሮዋ መጥቶ የፓሪስ ሽቶ ሰጥቷት ከሄደ በኋላ፣ ስለ እርሱ ማሰብ አላቋረጠችም። ያደረገችለት ውለታ ምን እንዳስገኘለት ባታውቅም፣ ዋጋው ውድ የሆነ ስጦታ ስላደረገላት ብዙ አሳስቧት ነበር። የታቀደላትን የምሳ ግብዣ በፈቃደኝነት መቀበል እንዳለባትና እንደሌለባት በማሰላሰል ፣ ስታወጣ ስታወርድ፣ ብዙ ሰዓታት አሳልፋ ነበር። የልጅ አዝማሚያና የምሳ ግብዣው ውጤት ምን እንደሚሆን መገመቱ ከባድ ሆኖባታል። ይሁንና፣ የሚሆነውን ለማየት ወሰነለች።

የግርማ ነገር አልቆረጠላትም። በአንድ ምሽት እንደተኮራረፉ ካደሩ በኋላ፣ ድምጹ ጠፍቶባታል። ለመስከ ሥራ እንደወጣ አድርጋ ነበር የገመተችው። ይሁንና፣ እዚህ አዲስ አበባ ውስጥ መሆኑን ከሰዎች ጠይቃ ልትረዳ ችላለች። እዚሁ ሆኖ ለምን እንዳልደወለላት ሊገባት አልቻለም። ለምን እንደሸሻትና እንደጠላት ባታውቅም፣ ከዚያች ቀን ምሽት ጀምሮ ከአእምሮዋ አውጥታው አታውቅም። ሲያብከነክናት ኖሯል። ምን እንዳየባትና ለምን እንደጠላት ሊገባት ባይችልም፣ ለእርሱ ታማኝ ሆና መቅረብ ትፈልጋለች። ስለዚህ፣ ዳንኤል ምንም ያስብ ምን ከእርሱ ጋር አብሮ መታየቱ መጥፎ ስም የሚያሰጥ መስሎ ነው የታያት።

ይህ ሁኔታ፣ በትናንትናው ዕለት፣ በአእምሮዋ ውስጥ ሁለት ተሚጋች ውሳኔዎችን ፈጥሮ ሲያጨቃጭቃቸው ከዋለ በኋላ፣ ማምሻውን ንግሥት በአንደኛው ውሳኔ ላይ ፀንታ ለዳንኤል ስልክ እንድትደውልለት አስገድዷት ነበር። በዚህ መሠረት ነው፣ የዛሬ ቅዳሜን ምሳ ከዳንኤል ጋር ለመብላት ያቀደችው።

ታክሲው ፍል ውሀ አጠገብ ሲደርስ አስቆመችና ወረደች። አካባቢውን ስትቃኝ፣ ወደ ፊንፊኔ የምግብ አዳራሽ የሚያስገባው በር አጠገብ ዳንኤል ፈጠነ ቆሞ አየችው። ሙሉ ቡናማ ሱፍ ልብስ ለብሷል። በነጭ ሸሚዝ ላይ ቡና ቀለም ባለው መደብ ላይ ነጣ ያለ ሠረዝ ሠረዝ ያለው ክራቫት አስሯል።

"እንደምን ዋልሽ?" ብሎ እጁን ዘረጋ።

"እንደምን ዋልክ?" ብላ ጨበጠችው።" ብዙ ጠበቅሽኝ እንዴ?"

"አይ፣ ብዙም አይደለም።" አለ ወደ ምግብ አዳራሹ እየመራት።

"ምሳ እዚህ እንድንበላ ነው የመረጥኩት። ምን አልባት ካልወደድሽው ሌላ ቦታ ይሆናል።" አለ።

"የምወደው ቦታ ነው። ጥሩ ምርጫ ነው።" አለች።

"ከወደድሽው ጥሩ ነው።"

ወደ ምግብ አዳራሹ ገቡ። ወንበሮች ይዘው እንደተቀመጡ አንድ አሳላፊ መዘርዝረ- ምግብ ይዞ መጣ።

ዳንኤል ተቀበለና፣ ከዝርዝሩ ውስጥ አንድ የምግብ ዓይነት መረጠ። "አንቺ ምን ትመርጪያለሽ ?" አለ መዘርዝረ- ምግቡን እያቀበላት።

"ክትፎ።" አለች፣ ካነበበች በኋላ።

ወደ አሳላፊው ቀና አለና፣" እሺ፣ አንድ ክትፎና አንድ ቀይ ወጥ፣ ከሚጠጣ ነገር ጋር ይዘህልን ና። "አለ ዳንኤል።

"የሚጠጣ ምን ?"ሲል ጠየቀ፣ አሳላፊው።

"ቢራ።"

አሳላፊው ሄደ።

"ይገርምሻል፣ ስትዘገይ ጊዜ፣ መቅረትሽ ነው ብዬ በጣም ነበር ቅር ያለኝ። "

"ታክሲ አጥቼ እኮ ነው። ከቢሮ ቀደም ብዬ ነበር የወጣሁት።" አለች፣ ቀና ብላ ሳታየው።

"እምቢ ስላልሽኝ ነው እንጂ እኔ 'ፒክ 'አደርግሽ ነበር - ከቢሮ።" አለ።

"አዎ ። ብለህ ነበር። ሰው ሲያይ ጥሩ አይሆንም ፣ ሌላ ትርጉም ይሰጠዋል ብዬ ስለፈራሁ ነው።"

"ለምን?" ሲል ጠየቃት።

ዝም አለች።

ዳንኤልም በጥያቄው አልገፋም። እርሱም ዝም አለ።



ቢራው ቀድሞ መጣ። አሳላፊው በብርጭቆ ግማሽ ግማሽ ላይ ቀድቶላቸው ሄደ። ከጥቂት ቆይታ በኋላ፣ የታዘዘውን ምግብ ይዞ ከች አለ። ዳንኤል የቀረበውን ምግብ በአንድ ትሪ ላይ አቀላቅሎ አቀረበው።

መብላት ጀመሩ።

"ብይ እንጂ ። ከቀረበ በኋላ፣ ብላ ብይ መባባሉ ጥሩ አይመስለኝም።"

"እየበላሁ ነው።"

"እኔ ስለራበኝ ቶሎ ቶሎ ነው የምበላው። አንቺም እንደእኔ ብትበይ ደስ ይለኛል።"

"ችግር አይኖርም። እኔም ስለራበኝ ሳልፎካከርህ አልቀርም።"አለች ፈገግ ብላ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ፣ ምሳ ተበልቶ ገበታው ተነሳ። ቢራ ደገሙ።

"ሽቶውን ወደድሽው?" ሲል፣ ፈገግ ብሎ ጠየቃት።

"በጣም እንጂ ። የፓሪስ ሽቶ መሆኑን ሳውቅ ደሞ፣ በጣም ነው ደስ ያለኝ። "

"ስለወደድሽው ደስ ብሎኛል። "

ዝምታ ሰፈነ።

"ፓሪስ ነበር እንዴ የሄድከው?" ስትል፣ ጠየቀች ንግሥት።

"አይደለም። ዱባይ ነበር የሄድኩት። ከዚያ ነው የገዛሁልሽ።"

"ግን ምን ዓይነት ውለታ ብሠራልህ ነው ይህን ያሰብክልኝ?"

"የዚያን ቀን ያ ደብዳቤ ባይደርስልኝ ኖሮ፣ የዱባይ ጉዞዬ ይሰረዝ ነበር። እቃዎቼን እንደሚገዛኝ- በነገራችን ላይ ነጋዴ ነኝ - ፋክስ ያደረገልኝ የዱባይ ነጋዴ፣ ቶሎ ይገድለት እንድመጣ ነግሮኝ ነበር። ብዘገይ ኖሮ፣ የሀምሳ ሺህ ብር ትርፍ ያመልጠኝ ነበር።"

"እሀ!" አለችና ቢራዋን ተጎነጨች። "ነጋዴ አትመስልም ግን።" አለች፣ በመቀጠል።

"እንዴት?"

"እነሱ ስለብራቸው ሲያስቡ ነው መሰል በአለባበሳቸው ግድ የለሽ ናቸው። አንተ ግን፣ ለአለባበስህ ማማር የምትጨነቅ ትመስላለህ፣ እምልህ ጥሩ ልማድ ነው።"

"አመሰግናለሁ::"

"ለምኑ?"

"ለሙገሳው::" አለ፣ ፈገግ ብሎ::

እርሷም ፈገግ ብላ ጎንበስ አለች::

"ነጋዴ ካልመሰልኩ ምን መስዬሽ ነበር?" ሲል ጠየቃት::

"የቢሮ ሰው:: ደህና ወንበር ያለው የቢሮ ሰው ትመስለኝ ነበር::"

"የቱን መሆን ይሻላል?"

"እኔ እንጃ:: "አለች፣ ፈገግ ብላ::

"ከዩኒቨርስቲ ተመርቄ እንደወጣሁ የመንግሥት ሥራ ይዤ ነበር:: ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የአስመጪና ላኪ ድርጅት ያለው አንድ አጎቴ፣ እርሱ ጋ ተቀጥሬ እንዳግዘው ጠየቀኝ:: የተሻለ ደሞዝ ስለነበረ ዓይኔን ሳላሽ ጥያቄውን ተቀበልኩ:: ከርሱ ጋር ስሰራ ቆየሁ:: ከጥቂት ዓመታት በኋላ፣ አጎቴ ድርጅቱን ለአባቴ ሰጠው:: አሁን እኔ ነኝ የማስተዳድረው:: በመንግሥት ሥራ ላይ ጥቂት ስለቆየሁ ይሆናል ከነጋዴዎች የለየኝ::"

"ስለተማርክም ሊሆን ይችላል::" አለች::

'እኔ እንጃ 'በሚል ስሜት አንገቱንና ትከሻውን ወዘወዘ::

"በምን ሙያ ነው የተመረቅሽው ?"ስትል ጠየቀች::

"በኢኮኖሚክስ::" አለ ቢራውን ከተጎነጨ በኋላ::

"ኢኮኖሚክስ ማለት ስለቁጠባ ነው፣ አይደል? በዚህ ሙያ የሰለጠነ ሰው መቼም ጋብሮቭ ነው የሚመስለኝ::" አለች፣ ፈገግ ብላ:: ሳታስበው ብዙ ከማታውቀው ሰው ጋር መቃለዷ አስገረማት::

"በጣም ተሳስተሻል :: ኢኮኖሚክስ ማለት ያለንን ሀብት ወይም ገንዘብ ከፍጆታችን ቀንሰን ማስቀመጥ ወይም መሰሰት አይደለም:: ያለንን ውስን ሀብት ርካታችንን ከፍ ሊያደረግ በሚችል መንገድ እንዴት እንደምንጠቀምበት የሚያስረዳን ሳይንስ ነው:: በአለማችን ላይ ሁሉ ነገር ውስን ነው:: በመሆኑም የምንፈልጋቸውን ነገሮች ማሟላት አንችልም:: ባሉን ሀብቶች ርካታችንን ከፍ ለማድረግ እንዴት እንደምንችል ነው የሚያስተምረን:: ገባሽ ?"

"በደንብ አልገባኝም::"

"ለምሳሌ አንቺ በወር አምስት መቶ ብር ደሞዝ አለሽ እንበል:: ይህቺ በጣም ውስን ሀብትሽ ናት:: በአንፃሩ ደግሞ፣



በሕይወት ላይ ለማግኘት የምትፈልጊያቸው ብዙ ነገሮች አሉ:: ጥሩ ጥሩ ምግብ፣ ልብሶች፣ ጌጣጌጦች የውበት ቅባቶችና ሌሎች ሌሎች ብዙ ነገሮች:: እነዚህን ሁሉ በፈለግሽው ጥራትና መጠን በአምስት መቶ ብር ላታገኚ ትችያለሽ:: ያለሽ ሀብት ውስን ባይሆን ኖሮ፣ የፈለግሻቸውን ነገሮች ሁሉ ማግኘት ትችይ ነበር:: ነገር ግን፣ ያለሽ ሀብት ውስን በመሆኑ፣ በአቅምሽ ሊኖሩሽ የሚችሉትን ዕቃዎች መምረጥ ትጀምሪያለሽ:: በአለሽ ውስን ገቢ ለየትኛው ቅድሚያ ሰጥተሽ ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጎትሽን ማርካት እንዳለብሽ ማጥናት ይኖርብሻል:: በአገር ደረጃም የወሰድነው እንደሆነ፣ አገሮች ሁሉ የተወሰነ ሀብት ነው ያላቸው:: የተፈጥሮ ሀብት፣ የሰው ጉልበት፣ የቴክኖሎጂ እና የሌሎችም ሀብቶች እጥረት አለ:: በአንፃሩ ደግሞ፣ የሕዝቦቻቸው ፍላጎቶች እጅግ ብዙ ናቸው:: ኢኮኖሚክስ እነዚህ አገሮች ያሉዋቸውን ውስን ሀብቶች እንዴት ተጠቅመው የሕዝቦቻቸውን ፍላጎቶች ማርካት እንዳለባቸው ያስገነዝባል:: እና ኢኮኖሚክስ ሆድን አስሮ ሀብትን ማስቀመጥ ማለት አይደለም፣ ወይዘሪት ንግሥት::"

ንግሥት ፈገግ አለች::

"በነገራችን ላይ ወይዘሪት ነሽ፣ አይደለም?"

"ወይዘሪት ነኝ:: "አለች፣ አሁንም ፈገግ ብላ:: "ስለጠኸኝ ማብራሪያ አመሰግናለሁ::" አለች፣ እንደመቀለድ እየሞከረች::

ትንሽ ዝምታ ሰፈነ::

ፊቱን ትንሽ ቅጭም አደረገና፣" ይሄ የጨጓራ በሽታዬ ሊነሳብኝ ነው መሰለኝ::"

"አለብህ ?"

"አዎ፣ በርበሬ የበዛበት ምግብ ስበላ ይነሳብኛል:: "አለ፣ ሆዱን ዳበስ ዳበስ እያደረገ::

"ብዙ ጊዜ ሆኖሀል?"

"አዎ፣ እየተጠነቀቅሁ ነው እንጂ፣ ብዙ ጊዜ ያመኛል::"

"በሀኪም ታይተሀል?"

"በጣም ብዙ ጊዜ:: ግን ምንም ውጤት አላገኘሁበትም::" አለ::

ንግሥት ጥቂት አሰበች::" እስኪ እንደገና በደንብ ተመርመር::"

"ምን ዋጋ አለው፣ ውጤት ከሌለው?"

"ለምን አባቴ አይመረምርህም? ዶክተር ነው። ብዙ ጊዜ እንደዚህ ዓይነት ችግር ያለባቸውን ሰዎች ሲረዳ አያለሁ።"

"አባትሽ ሀኪም ናቸው እንዴ?"

"አዎ። የግል ክሊኒክ ስላለው ብቅ ብለህ ቢያይህ ጥሩ ነው።" አለች ንግሥት።

"ማን ነው የሚባሉት፣ አባትሽ?"

"ዶክተር ናትናኤል ዘለቀ።"

"አላውቃቸውም። በቃ ታሳይኛለሽ፣ ክሊኒካቸውን።"

"እሺ። ችግር አይኖርም።"

"መቼ ይሁን?"

"በፈለከው ቀን።"

ጥቂት አሰበ።" የስልክ ቁጥርሽን ትሰጪኛለሽ ?"

"እሺ።"

ዳንኤል የማስታወሻ ደብተሩን አወጣና የነገረችውን የቢሮዋንና የመኖሪያ ቤቷን የስልክ ቁጥሮች ያዘ። ማስታወሻ ደብተሩን ኪሱ ከከተተ በኋላ አሳላፊውን ጠቀሰው።

"አቤት!" አለ፣ አሳላፊው።

"ቢራ ድገመን እስኪ። "አለ ዳንኤል።

"አይበቃም?" አለች ንግሥት።

"ጠጪ ባክሽ። ቤት እንቀይር እንዴ?"

"እንደፈለክ።" አለች ንግሥት።

"የታዘዘውን እንጠጣና እንወጣለን።" አለ።

አሳላፊው ይዞላቸው የመጣውን ቢራ ጠጡና ከፊንፊኔ የምግብ አዳራሽ ወጡ። ዳንኤል መኪናውን ያቆመበት ቦታ እየመራ ወሰዳት። እጅግ ዘመናዊ የሆነች ፔጆ መኪናውን ከፍቶ ገባና ሊላኛውን በር ለንግሥት ከፈተላት። ገባች። ሞተሩን አስነስቶ ጉዞአቸውን ቀጠሉ።

## 23

ቤት ከገባች አሥራ አምስት ደቂቃዎች አልፈዋል። አልጋዋ ላይ ጋደም ብላ ከዳንኤል ጋር ያደረገችው ውሎ ውጤት ምን



እንደሚሆን መተንበይ ጀመረች። 'አሁን እንዳው አንድ ገጽ ወረቀት በታይፕ ስለጻፍኩለት ነው ይህ ሁሉ መስተንግዶ? ያደረግሁለት ውለታ በትክክል ጠቅሞት ከሆነ የሸቶው ስጦታ ብቻ በቂ ነበር። የምሳ ግብዣው ትርፍ ነው። እሺ እሱም አስፈላጊ ነው ቢባል፣ በፊንፊኔ የምግብ አዳራሽ ውስጥ የተደረገው ደበቃ ነበር። ከዚያ በኋላ፣ በግዮን ሆቴል ውስጥ የተደረገው ግብዣ ትርፍ ነው። ሌላ መልዕክት የያዘ መሆን አለበት።' አለች በሀሳቧ። ይህንን ግምቷን የሚያጠናክርላት ነገር ካደረጉት ጭውውት ውስጥ አልፎ አልፎ አግኝታለች። ግን ርግጠኛ አልሆነችም። ከፊንፊኔ የምግብ አዳራሽ ከወጣ በኋላ፣ ያደረጓቸው ቃለ ምልልሶች። በአብዛኛው ስለንግሥት የሥራ፣ ስለዶክተር ናትናኤል የምርምር ሥራዎችና የአኗኗር ሁኔታዎች እንዲሁም የዳንኤልን የንግድ ሥራ የሚመለከቱ ነበሩ።

መጨረሻ ላይ፣ 'በወንድምነት መንፈስና ባደረኩለት ውለታ ነው የጋበዘኝ። ሌላ ምንም ትርጉም የለውም።' ስትል ደመደመች።

ስለ ዳንኤል፣ ከአንድ ራሷጋር ታደርግ የነበረውን ውይይት አቁመችና ስለግርማ ማሰብ መረች። አዲስ አበባ ውስጥ እያለ ለምን እንደማይደውልላት አሳስቧታል። ብዙ ጊዜ እንዲገናኙ ይፈልግ የነበረው ግርማ፣ ከዚያች ቀን ምሽት በኋላ ዓይንሽን ላፈር ያለበት ምክንያት አልገባትም። ለምን እንደራቃት፣ ለምን እንደሸሻት ማወቅ አልቻለችም። ባሳለፉት የአብሮ ቆይታ ውስጥ ፣ አልፎ አልፎ ቢኳረፉም፣ መልሶ ይደውልላታል። እርሷ ብታጠፋም ይቅርታ ይጠይቃታል። ወንድ ሲኮሩበት ነው የሚወደው የሚል ፈሊጥ አላት። ይህን እምነቷን ግርማ ላይ ብቻ ሳይሆን ከግርማ ቀደም ብሎ ይዛው በነበረው ፍቅረኛዋ ላይም ታንፀባርቅ ነበር። ይሁንና፣ የአሁኑ የተለየ ሁኔታ ፈጥሯል። ግርማ እስኪደውል ድረስ የነበራት ትዕግስት ተሟጠአል። ደውላ ለምን እንደጠፋ ለመጠየቅ ወሰነች። ከመኝታ ቤቷ ወጣችና ስልኩ ወደሚገኝበት የእንግዳ መቀበያው ክፍል ሄደች። ግን እኮ አሁን ቤት 'ላይኖር ይችላል።' ስትል አሰበችና፣ ለማንኛውም ልሞክር። ብላ በመደወሉ ፀናች። ቁጥሮች አዞረች።

ስልኩ ይጠራል።

ሀሎ አለና የምትፈልገው ቁጥር መሆኑን ለማረጋገጥ ጠየቀች።

"አዎ፣ ነው። ማንን ፈለጉ?"

ግርማን ፈልጌ ነበር።

"ይጠብቁ።" አለ፣ ስልኩን ያነሳችው ሴት ድምጽ።

ከጥቂት ሴኮንዶች በኋላ የግርማ ድምጽ ጆሮዋ ውስጥ ገባ።

"ግርማ ነህ?"

"አዎ። ማን ልበል?"

"አላወቅኸኝም?"

"አዎ። ማንነሽ? "

"ገምት እስኪ፣ ማን እንደሆንኩ።"

ጥቂት ዝም አለ። "አላወቅሁሽም።"

"ንግሥት ነኝ።" አለች።

ለጥቂት ሴኮንዶች ያህል ዝም አለና። "እ.. ንግሥት እንደምን ነሽ?"

"ደህና። አንተ ደህና ነህ?"

"ደህና ነኝ።" አለና ድምጹን አጠፋው።

ዝምታው ደስ አላላትም። "ምነው ጠፋህ? አዲስ አበባ ውስጥ አልነበርክም እንዴ?" አለች።

ሊዋሻት አልፈለገም። "እዚሁ ነበርኩ።" ብሎ ዝም አለ።

"ለመስክ ሥራ እወጣለሁ ብለህ አልነበር?"

"ጨርሼ ከመጣሁ ቆየሁ።"

"ታዲያ ለምን አልደወልክልኝም?"

"አልመች ብሎኝ ነው።"

"ስልክ ለመደወል ጊዜ አጥተህ ነው?"

እያቅማማ፣ "አዎ።" አላት።

"እሱስ ተው። ችላ ብለኸኝ ነው እንጂ።" አለች በመከፋት ድምጽ። "ግን ምንድን ነው ያጠፋሁት በምን አስቀየምኩህ?" አለች፣ እንቅ እንቅ በሚያደርግ የድምጽ ዜማ።

"ምንም አላደረግሽኝም። ተቀየምኩ አልኩሽ?"

"እሺ ታዲያ ለምን አትደውልልኝም?"

"ስላለተመቸኝ ነው አልኩሽ። "

"ምን ያህል እንደናፈቅኸኝ ታወቃለህ?"

መልስ አልሰጣትም።

"እሺ አሁን መቼ ነው የምንገናኘው?"

ዝም አለ። ከእንግዲህ ወዲያ አንገናኝም ብሎ ሊነግራት አልደፈረም። "ሲመቸኝ ብደውልልሽ አይሻልም?"



"እሺ።" አለች፣ ለማልቀስ በቃጣ ድምጽ። "ደህና እደር።" አለች በመቀጠል።

ከዚህ ሌላ የምትለው አልነበራትም።

ስልኩ ተዘጋ። የግርማ አነጋገር እንደመርፌ ልቧን ጠቅ አደረገው። 'ስላልተመቸኝ አልደወልኩልሽም።' ስላላት የተናቀች መሰሏታል። እና እሷ ፈልጋ በመደወሏ ተናደደች። እንደናፈቃት የነገረችው ቅመም እንደሌለው ሚጥሚጣ አንገበገባት። ግልጽ ሆና መናገሯ አቃጠላት። በተለይ፣ 'ሲመቸኝ እደውልልሻለሁ።' ያለው አልቅሺ አልቅሺ ነው ያሰኛት። የ'ሲመቸኝ እደውላለሁ።' መልዕክት ከእንግዲህ ወዲያ አንገናኝም እንደሆነ አውቃለች።

እልህ አናቷ ላይ ወጣ....

## 24

አልጋዋ ላይ ጋደም ብላ የመኝታ ቤቷን የኮርኒስ ክፍልፋዮች በዓይናቿ ትቃኛለች። ሥጋዊ አካሏ ቢያርፍም፣ አእምሮዋ አላረፈም። ግን፣ ስለምን እንደምታስብ አላወቀችውም።

በሩ ተንኳኳ።

ቀና ብላ በሩን እየችና፣"ክፍት ነው ይግቡ፣ "አለች።

ጠየም ያለ አጭር ልጅ ገባ። "እንደምን ዋልሽ ሽታዬ?"

"እ! ገብሩ፣ እንደምን አመሽህ?" አለች፣ ከአልጋዋ ቀና ብላ የተበታተነ ረጅም ፀጉሯን ሰብስብ በማድረግ ወደ ኋላ እያደረገች።

"ደህና። ደህና አመሸሽ?" አለና ጎላ ጎላ ያሉ ዓይናቿ ያሉበትን ቀይ ፊቷን በፈገግታ ተመለከተ።

በረጅሙ ተነፈሰችና፣ "ደህና ነኝ።" አለች። ለፈገግታው አፀፋውን አልመለሰችለትም። ስስ ከንፈሮቿን ፈልቅቆ ነጫጭ ጥርሶቿን የሚያሳይ፣ የሚያስደስትና የሚያስቅ፣ ሀይል ከእሷነቷ ከራቀ ሰንብቷል።

"ምነው፣ በጊዜ አልጋሽ ላይ ወጣሽ?"

"ታዲያ የት ልሂድ?"

"ትልቁ ቤት ሄደሽ ከቤተሰቦችሽ ጋር አትጫወቺም?"

"እንደ እኔ ዓይነቱ ከሰዎች ጋር መቀላቀሉ ምንም አያደርግለትም።" አለች ብሶት በደቋቆሰው ድምጽ። የተከፋ ስሜቷን ገብሩ እንዳያውቅባት ለመሸፈን ሞከረች።

ጥቂት ሴኮንዶች ተወልደው ሞቱ--ሳይነጋገሩ።

"ለመሆኑ በረታችሁ? ቤታችሁ መምጣቱን ተውኩት መቼም። አንድ ሁለት ወር ሳይሆነኝ አይቀርም።" አለች፣ የገብሩን አባት ሞት ሀዘን አስታውሳ።

"ደህና ነን። በርትተናል። እንዲ የሆነን ነገር መቼም ማንም አይመልሰውም። ከሞት ማን ይቀራል?" አለ ገብሩ።

የመጨረሻው እረፍተ ነገር ጠቅ አደረጋት። 'ከሞት ማን ይቀራል' ሰው ሟች መሆኑን ርግጠኛ ቢሆንም፣ መቼ እንደሚሞት ግን አያውቅም። እርሷ ግን ትክክለኛ ቀኑን ባታውቅም፣ በግምት ከእንግዲህ ወዲያ ምን ያህል ወራት፣ ወይም ዓመታት፣ እንደምትኖር መገመት ትችላለች። ሁኔታው እንደ አዲስ አስደነገጣት። ተስፋ የመቁረጥ ስሜቷ አገረሸ።

"እኔ ምልሽ..." አለና ንግግሩን ቆረጠ። ሊጠይቃት ያሰበውን ጉዳይ ለማንሳት ከምን መጀመር እንዳለበት አሰላሰለ።

አባቱ ሞቱ ከተባለበት ደቂቃ ጀምሮ የሚሰጋው ትተውት የሄዱትን ንብረት ከእርሱ ጋር ያደገው የአክስቱ ልጅ፣ ደምመላሽ፣ ይወርሳል ብሎ ነው። ገብሩ፣ አባቱ ከእርሱ ይልቅ የእህታቸውን ልጅ ደምመላሽን፣ እንደሚወዱና እንደሚያቀርቡ ያውቃል። ጥሩ ሥነ-ምግባር ያለውና አርቆ አስተዋይ ነው ብለው ይመኩበት ነበር። ከዚህ የተነሳ እስካሁን ያደራጁትን ሀብት ከእርሱ አሳልፈው ለደምመላሽ ይሰጣሉ ብሎ ሰግቶ ነበር። ሳይናዘዙ ድንገት መሞታቸው ፍርሀቱን ቢቀንሰውም፣ ቤተዘመዱ ከሚያሰማው ሹክሹክታ ደምመላሽ የሚመረጥ መሆኑን ጠርጥሯል። ገብሩ በደምመላሽ ሞግዚትነት ለመኖር አይሻም። በተወላጅነቱ ውርሱን እርሱ ብቻ ማግኘት እንዳለበት ያምናል። ይህንን ዕውን ለማድረግ ደምመላሽን ከዚህች ዓለም ለማጥፋት ወስኗል።

ሽታዬ በጉጉት አየችው።

ሲፈራ ሲቸር ጀመረ። "አንድ ወሬ ሰምቼ ነበር። እኔ እንኳ ልጠይቅሽ የፈለኩት ነገሩ እውነት ከሆነ..." አለና ንግግሩን ቆረጠ።

"ምንድን ነው የሰማኸው?" አለች በታከተ ስሜት–እሱን ሳታየው።

"የሚወራው እውነት ከሆነ ሊረዳሽ የሚችል ሰው ያለ ይመስለኛል።"

ሽታዬ አልጋዋ ላይ ተመልሳ ጋደም አለች።

"የኤድስ ቫይረስ ተሸካሚ ሆነሻል ይባላል?" ሲል ከጠየቀ በኋላ፣ ፊቷን ትኩር ብሎ ማየት ጀመረ።



መልስ አልሰጠችውም።

"እውነት ነው፣ ሽታዬ?" ሲል ጠየቀ።

"ሰው ብዙ ያወራል። የእኛ ሰው ፈጥሮ ማውራት ይወዳል።" አለች፣ ጣራ ጣራውን እያየች።

የነገሩ ውሸት መሆን ገብሩን አስደነገጠው። ውሸት በመሆኑ የሚፈልገውን ሊያጣና ያቀደው ላይሳካ ነው። ይህ ያበሳጨዋል። ግን፣ ሽታዬን አላመናትም። ሁኔታውን ለማስተባበል ሆን ብላ የዘጋችው ነው የመሰለው።

"የመጣሁት ሊያድንሽ የሚችል ሰው በማግኘቴ ልነግርሽ ነው። መድሀኒቱን ያገኘ ሰው አለ። ይልቅ፣..."

ንግግሩን ሳይጨርስ ከአልጋዋ ላይ ፍንጥር ብላ ተነሳችና ትላልቅ ዓይኖቿን ጎልጉላ ገብሩን አየችው። "እውነትህን ነው?" አለች።

ገብሩ ደስ አለው። "ሙች! አንድ ሀኪም አለ። በምስጢር ነው የሚያክመው።"

ከአልጋው ላይ ወርዳ ቆመች። "የት ነው ያለው ሰውዬው? አሁን ታሳየኛለህ? የት ነው የሚያክመው?" አለች፣ በችኮላ እየተንጋገረች።

"ቆይ ረጋ በይ። በችኮላ የሚሆን ነገር የለም። ሰውየው በምስጢር ስለሆነ የሚያክመው ተደብቀሽ ነው የምትሄጂው። መጀመሪያ ደግሞ ደምሽን ማየት አለበት። የተለያዩ የደም ዓይነት ላላቸው ሰዎች የተለያዩ መድሀኒቶች አሉት። ስለዚህ አሁን አመጣጤ ደምሽን በብልቃጥ ወስጄ ለሰውየው ለማሳየት ነው። ከዚያ በኋላ፣ አብረን እንሄድና ትታከሚያለሽ።" አለ።

"እውነትህን ነው?"

"ሽታዬ ሙች ስልሽ! አሁን ብቻ በዚህ ብልቃጥ ትንሽ ደም ትሰጪኛለሽ።" አለና ከኪሱ አነስ ያለች ብልቃጥ አወጣ።

"እንዴት አድርገህ ነው የምትወስደው?"

"ክንድሽን አምጪው። ከዚህ በፊት ሀኪም ሆኜ መስራቴን ረሳሽው እንዴ?" አለና ከሌላኛው ኪሱ የህክምና መሣሪያዎች አወጣ። የሚፈልገውን ያህል ደም ወሰደና አልኮል በተነከረ ጥጥ ክንዷን አሻሸው። "ነገ ውጤቱን እነግርሻለሁ። አሁን ደህና እደሪ።" ብሎ ከክፍሏ ወጣ።

ሽታዬ በሀሳብ ውስጥ ሆና አልጋዋ ላይ ጋደም አለች። ገብሩ መጥቶ ያበሰራት ዜና እንደገና የመኖር ፍላጎቷን አለመለመው። ለሕይወት የነበራት ጥላቻ መፋቅ ጀመረ። ተሎ የመዳን ጉጉት

አደረባት። ከጓደኛ፣ ከቤተሰብ፣ በአጠቃላይ ከሰዎች ተገልሎ መኖር ሊቀር ነው። የመንፈስ ጭንቀት ሊሸሽ ነው። ከፍቅረኛዋ ጋር ሆድና ጀርባ ያደረጋት በሽታ ተወግዶ እንደገና ፍቅራቸውን ሲቀጥሉ ታያት። ነገሩ ሁሉ የሚያጓጓና የማይሆን ጥሩ ህልም መሰላት። "ውይ እግዚአብሔርዬ እውነት ባደረከው!" አለችና በጎኗ ተኛች። ስለ ገብሩ ማሰብ ጀመረች። እንዲህ ያለ ቅን አስተሳሰብ ያለው ሰው አይመስላትም ነበር። አንድ ሠፈር ውስጥ ቢያድጉም፣ ከሩቅ መተዋወቅ በስተቀር የሚያቀራርብ ጭውውት አድርገው አያውቁም። ሰላምታ መለዋወጥ እንኳ የጀመሩት በቅርቡ ነው። ይሁንና፣ ገብሩ ብዙ መቀራረብ እንዳላቸው ሁሉ ችግሯን ተረድቶ ሊያድናት መጥቷል። አስገረማት። ገብሩ የወሰደውን ደም ለሀኪሙ አሳይቶ መልስ ይዞ እስኪመጣ ድረስ ቸኮለች። 'መቼ ነው ውጤቱን የማውቀው?' አለች ለራሷ። ውጤቱን ነገ በስንት ሰዓት እንደሚነግራት ልትጠይቀው ወስና ከአልጋዋ ላይ ተነሳች። ጋቢ ደረበችና ከክፍሏ ወጣች።

ገብሩ እቤት እንደገባ በፋሻ የተጠቀለለውን የደምመላሸን የእግር ቁስል ፈቶ በሙቅ ውሃ ማጠብ ጀምሯል። "አይዞህ ይሻልሀል። አሁን እንዳውም እየዳነልህ ነው። መድማቱንም እየተወ ነው።" እያለ በጀርባው ተንጋሎ በመተኛት እግሩን ከአልጋው ላይ አውርዶ ለሰጠው የአክስቱ ልጅ የማባበያ ቃላት አጎረፈ።

ከአልጋው ሥር ያስቀመጠውን የሽታዬን ደም የያዘ ብልቃጥ ከፈተና በደምመላሽ ቁስል ላይ አፈሰሰው። ልክ ግማሹን ጨምሮ እንዳበቃ ሽታዬ በሩን ከፍታ ስትገባ አንድ ሆነ።

ገብሩ በድንጋጤ ደርቆ ቀረ። ብልቃጡን ሊደብቀው ሞከረ። ግን ዘግይቶ ነበር።

እሷም ዘግይታ ነበር። "ምን እያደረክ ነው?" ስትል ገብሩን ጠየቀችው፣ ለደምመላሽ ተገቢውን ሰላምታ ካቀረበችለት በኋላ።

"ቁስሉን እያጠብኩለት ነው። ፋሻውን ለመቀየር ስለፈለኩ በሙቅ ውሀ እያጠብኩለት ነው።" አለ እንደመርበትበት እየቃጣው። "እንዴት መጣሽ ?"

"ቆይ።" ብላ ይዛው ወጣች።

"ምነው ለምን ፈለግሽኝ ?" አለ ደንግጦ።

"መቼ ነው ውጤቱን የምትነግረኝ? በጣም ቸኩያለሁ። ሀኪሙ ቤት ለምን አብረን አንሄድም?"



"እ....ይ...እይ። ጥሩ አይሆንም። መጀመሪያ ደምሽን ይየው ግ... ግዴለም። ነገ ውጤቱን ይነግረኛል። እነግርሻለሁ።" አለ።

"በስንት ሰዓት?"

"ውጤቱን እንዳወቅሁ።"

"አደራ በናትህ። እውነቱን ንገረኝ። ልክ እንደሰማህ ንገረኝ። ወይ ካለህበት ቦታ ሆነህ ስልክ ደውልልኝ።"

እነጋገሩ ለወጥ ስላለባት፣ አንድ አፍታ ቀና ብላ እየችው። ግንባሩ ላይ ላብ ቸፍ ብሏል። እንደደነገጠ አወቀች። ምክንያቱ ምን እንደሆነ ሳትረዳ ወደ ቤቷ ሄደች።

## 25

ዶክተር ናትናኤል፣ ከባህል ሀኪሙ ከአቶ ምስጋናው ጋር ባደረጉት የስልክ ንግግር የሰውዬው መኖሪያ የት እንደሚገኝ ተረድተዋል። ሽሮ ሜዳ በሚገኘው የአቶ ምስጋናው የህክምናና የመኖሪያ ቤት አካባቢ ሲደርሱ መኪናቸውን አቆሙ።

ዶክተር ናትናኤል በጥየቃ ያገኙትን የምስጋናውን ትልቅ ግቢ አስከፍተው ገቡ።

"ጌታዬ፣ ህክምና ከሆነ አሁን አይሰጥም።" አለ፣ አንድ ረጅም ዘበኛ።

"አይደለም። ለሌላ ጉዳይ ነው የመጣሁት። የት ናቸው አቶ ምስጋናው?" አሉ፣ ዶክተር ናትናኤል።

"ትልቁ ቤት ውስጥ ናቸው።" ብሎ በእጁ አሳያቸው።

ዘበኛው ያሳያቸው ቤት ለመድረስ ብዙ መራመድ ያስፈልጋል። ግቢው በጣም ሰፊ ነው። የባህር ዛፎች፣ ጥዶች፣ አበቦችና ልዩ ልዩ ዕፅዋት ሞልተውታል። የአብዛኞቹን ዕፅዋት አይነት ዶክተር አያውቁም። የባህል ሀኪሙ ለመድሀኒትነት የሚጠቀሙባቸውን ዕፅዋት በግቢያቸው ውስጥ እንደሚተክሉ በወሬ ሰምተው ነበር። 'የትኛው ዕፅ ይሆን ሰውዬውን የፈወሰው?' ሲሉ ራሳቸውን ጠየቁ።

በዋናው ቤት መስኮት ውስጥ ሲመለከታቸው የነበረ አንድ ቀላ ያለ ወጣት የእንግዳ መቀበያውን በር ከፈተላቸውና አስገባቸው።

ክፍሉ በጣም ሰፊ ነው። ቶሎ ዓይንን የሚስቡት የአደይ አበባ የፈሰሰባቸው የሚመስሉት ቢጫ ሶፋዎች ናቸው። ከእነሱ ሌላ ደግሞ ከውጭ ሀገር የመጡ ምንጣፎችን ለብሰው ወለል ላይ የተዘረጉ ፍራሾችና ግርግዳዎችን ታክከው የቆሙት ትራሶች ናቸው። የምግብ

ጠረጴዛና ወንበሮች፣ ትናንሽ በርጩማዎችና አንድ ኮንትሮ ቡፌ ሌሎች ዓይን የሚገቡ ዕቃዎች ናቸው።

"እዚህ ይቀመጡ።" አለ፣ ወጣቱ ልጅ።

"የሉም እንዴ አቶ ምስጋናው?"

"አሉ። ይመጣሉ። ዶክተር ናትናኤል የሚባሉ እርስዎ ናት?"

"አዎ።"

"ይመጣሉ ብለው ነግረውኛል። እስካሁን ሲጠብቅዎት ነበር።"

"አሁን የሉም እንዴ?" ሲሉ ጠየቁ ዶክተር።

"አሉ። ሰላት ላይ ናቸው።"

"እሀ..." ምስጋናው ሙስሊም መሆናቸውን አላወቁም ነበር።

"ምን ይፈላሎት ቡና ወይስ ሻሂ?" አለ ልጁ።

"የለም። ምንም አልፈልግም። አመሰግናለሁ።" አሉና ከኮት ኪሳቸው ውስጥ እንደማስታወሻ መጻፊያ የሚገለገሉበትን የተጠረዘ ወረቀት አወጡ። የንባብ መነጽራቸውን አደረጉና ማንበብ ቀጠሉ። ለአቶ ምስጋናው ሊያነሷቸው ያሰቧቸውን ጥያቄዎች ቅደም ተከተል እንደገና አጤኑ። በእነዚህ ጥያቄዎች በተቻለ መጠን ብዙ ነገሮችን ማወቅ እንዳለባቸው ተረድተዋል። በሚቻላቸው ሁኔታ የባህል ሀኪሙን ተባባሪያቸው እንዲሆኑ ማድረግ ይፈልጋሉ።

ከጥቂት ደቂቃዎች ቆይታ በኋላ፣ ወደ መኝታ ክፍል የሚወስደው በር ተከፈተና አንድ ዕድሜያቸው ስድሳ አምስት የሚሆኑ ረጅም ሰውዬ ገቡ። ፒጃማ ለብሰዋል።

"እንደምን ዋሉ?"

ዶክተር ብድግ ብለው፣"ናር ጌታዬ። እንደምን ዋሉ?"

"ኸረ ይቀመጡ። ለእላህ ብለው ይቀመጡ።"

ተጨባበጡና ተቀመጡ ሁለቱም።

"ቤቱን አልተሳሳቱም በቀጥታ አገኙት" አሉ ምስጋናው በጉንጮቻቸው ላይ የተኛውን ሽበቶ ጺማቸውን እንደማሻሸት እያሉ።

"አላስቸገረኝም። አንድ ልጅ አሳየኝና በቀጥታ መጣሁ።" አሉ ዶክተር።

"እይ ደህና። አያስቸግርም።" አሉና ዶክተርን ማየት ትተው ወደ ሌላ አቅጣጫ ሀሳብ የያዘው ሰው መስለው ማየት ጀመሩ።

ዶክተር አተኩረው አዩዋቸው።

በቀይ ዳማ ፊታቸው ላይ የሚታዩት ደፍረስ ያሉ ዓይኖቻቸው ቅዝዝ ብለዋል።



ቀላ ያለው ልጅ የጓዳውን በር ከፍቶ ሲገባ ምስጋናው አዩትና፣ "ቡና አስፈላልና ፣ ሁሴን።"አሉ።

"እሺ። ይፈላሎት ብዬ ጠይቄአቸው ነበር። አልፈልግም ስላሉኝ ነው።" አለ ሁሴን ዶክተርን ከበስተጀርባ እያያቸው።

"ለምን? ቡና አይጠጡም እንዴ?" ሲሉ ጠየቁ ምስጋናው።

"መጠጣት እንኳ እጠጣለሁ። ግን ትንሽ እቸኩላለሁ።" አሉ ናትናኤል። በቡና እንደማይጨክኑ ልባቸው ያውቀዋል።

"ቶሎ ይደርሳል። አስፈላልን። "አሉ ምስጋናው፣ ሁሴንን ካዩት በኋላ።

ሁሴን ትእዛዙን ተቀብሎ ወጣ።

ሁለቱ የህክምና ሰዎች ጥቂት ሴኮንዶች በዝምታ አሳለፉ። ዶክተር ናትናኤል ጉዳይዎትን ይንገሩኝ እስኪባሉ የጠበቁ ይመስል ዝም አሉ።

"ከሁለት ወራት በፊት እንዳገኝዎ ፈልገው ደውለው እንዳጡኝ ተነግሮኛል። በዚያን ጊዜ አዲስ አበባ ውስጥ አልነበርኩም ነበር። እባቴ ታሞ ወደ ክፍለ ሀገር ሄጄ ባለፈው ሳምንት መጨረሻ ላይ ነው የተመለስኩት።"

ዶክተር እንደመደንገጥ አሉና፣ "አዝናለሁ። አልሰማሁም፡ አሁን ተሻላቸው?" ሲሉ ጠየቁ።

"አዎ፣ አሁን ደህና ነው። በጣም ደህና ነው። አንዳንድ መድሀኒት ከሰጠሁት በኋላ፣ አሁን በጣም ደህና ነው።" አሉ ምስጋናው።

ናትናኤል ስለሰውዬው በሽታ ምንነትና ስላዘዙላቸው የባህል መድሀኒት ዓይነት ምስጋናውን ሊጠይቁ አሰቡና ተውት–የመጡበትን ጉዳይ ወደ ኋላ ላለማለት ብለው።

ዝምታ ሰፈነ።

"ለምን ኖሯል የፈለጉኝ?" አሉ፣ ምስጋናው ዶክተርን እያዩ።

"የመጣሁት ... ብዙ ሰዎችን ከተለያዩ በሽታዎች፣ በተለይም ዘመናዊ ህክምና ሊያድናቸው ካልቻላቸው፣ ማዳንዎ ስለተነገረኝ በጣም ደስ ብሎኝና በዕውቀቶ ኮርቼ ልተዋወቅዎ ፈልጌ ነው።"

"በጣም ደስ ይለኛል። መተዋወቁ ጥሩ ነው። "አሉ፣ ምስጋናው ፈገግ እያሉ።

"ዶክተር ናትናኤል ዘለቀ እባላለሁ። ሀኪምም መምህርም ነኝ።" ብለው ዝም አሉ።" ሌላም የመጣሁበት ጉዳይ አለኝ። እርሶም ሀኪም ነዎት። እኔም ሀኪም ነኝ። የሁለታችንም ዓላማ የሰው ልጅን

በአንዳንድ በሽታዎች ተሰቃይቶ መኖር ከሚችልበት ዕድሜ ወዲህ እንዳይሞት ማድረግ ነው:: ለሀገርና ለወገን ጠቃሚ የሆነ ጤነኛ ዜጋ ማፍራት ነው:: ለሰው ልጅ ሰብአዊ ግልጋሎት መስጠት ነው:: የምንጠቀምበት ዘዴ ቢለያይም ዓላማችን ይኸው ነው:: በእውነቱ የህክምና ባለሞያ መሆን በጣም ያኮራል:: የሰውን ልጅ ከሥቃይና ከሞት አፍ አውጥቶ በደስታና በጤና እንዲኖር ከማድረግ የበለጠ የሚያስደስት ነገር ያለ አይመስለኝም::

"ዘመናዊ የህክምና ዘዴዎች ሊፈውሷቸው ያልቻሏቸውን ህሙማን የባህል ህክምና ሲያድናቸው እናያለን:: የባህል ህክምና ሊፈውሷቸው ያልቻሏቸውን ህሙማን ደግሞ ዘመናዊ ህክምና ሲያድናቸው እናያለን:: የባህል መድሀኒቶች ፍንጭ እየሆኑ ዘመናዊ መድሀኒቶች እንዲፈለሰፉና እንዲዳብሩ ሲረዱ፣ ዘመናዊ የህክምና ሳይንስ ደግሞ የባህል መድሀኒቶች ጠቃሚ መሆናቸውን በማወቅና ሕብረተሰቡን በተሻለ ሁኔታ የሚጠቅሙበትን ዘዴ በማጥናት እንዲያገለግሉ ሀሳብ ይሰጣል:: እና፣ ይህንን ስናይ እኛና እናንተ አንድ ዓላማ እንዳለንና እኛ ያለ እናንተ ትብብር እናንተም ያለ እኛ ድጋፍ የሰውን ልጅ መርዳት እንደማንችል እንገነዘባለን::" አሉና የቡናውን መምጣት አይተው ንግግራቸውን አቆሙት::

ሁሴን ቡናውን ከፊት ለፊታቸው ካለው የቡና ጠረጴዛ ላይ ካስቀመጠላቸው በኋላ ወደ መጣበት ክፍል ገባ::

ናትናኤል የሚፈልጉትን ያህል ስኳር ጨመሩና ማማሰል ጀመሩ::

"ዶክተር፣ እርስዎ እንዳሉት የእኛና የእናንተ ዓላማ አንድ ነው::" ብለው ዝም አሉ::

ቡናውን ፉት ካሉ በኋላ፣" አዎ:: በዚያው መጠን፣ ያለ እናንተ ቀና ትብብር የእኛ ሥራ ብቻ ዋጋ እንደሌለው ግልጽ ነው::" አሉ:: በስተኋላ የተናገሩት አረፍተ ነገር ሰውዬውን ለማግባባትና የሚፈልጉትን ነገር ለማወቅ ሆን ብለው ያደረጉት ነበር::" በዓለማችን፣ በተለያዩ ጊዜያት፣ ብዙ ሕዝብ ለጨረሱ በሽታዎች መድሀኒት የተፈለሰፈው ከባህል ህክምና በተገኙ ፍንጮች ነው::" አሉና፣ ቡናቸውን ፉት አሉ::

አሁን በቀጥታ ወደ ጉዳዩ ለመግባት ወሰኑ:: ከዚህ ወዲያ የሚያደርጉት ገለፃ እሰልቺ ሊሆን ይችላል ብለው ሰግተዋል::

"ባለፈው ጊዜ አንድ እርስዎን የሚያውቅ ሰው፣ አዲስ ስለጀመርኩት ምርምር ስነግረው፣ ስለእርስዎ አጫወተኝ:: ለብዙ በሽታዎች መፈወሻ መድሀኒት እንዳሎት ከዚያ በፊት ሰምቻለሁ:: ነገር



ግን፣ የሰውን ልጅ በመቅጠፍ ላይ ላለው የኤድስ በሽታ መድሀኒት እንዳሎትና እንዳውም በዚህ በሽታ የተለከፈን ሰው እንዳዳኑ የሰማሁት በጣም አስደስቶኛል:: ነገሩ ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን እንዳረጋግጥ ገፋፋኝ:: የሰማሁት ነገር እውነት ከሆነ በአሁኑ ወቅት የሰው ልጅ የሚፈልገውን ነገር በማግኘቶ ኩራቱ ለርሶ ብቻ ሳይሆን፣ ለሀገርና ለመላው የኢትዮጵያ ሕዘብ ነው:: ኢትዮጵያ ከምትባል ሀገር ውስጥ በሰው ሕይወት ላይ አንዣቦ ያለውን የሞት ጥላ በጣጥሶ የሚጥል መድሀኒት መገኘቱ በብዙ ሚሊዮን ዓመታት አንድ ጊዜ በድንገት እንደሚገኝ ደስታ የሚቆጠር ነው:: በእውነቱ ሊኮሩ ይገባዎታል፣ ነገሩ እውነት ከሆኑ::"

"በእርግጥ፣ አንድ ህመምተኛ አንድ ጊዜ መጥቶ ካከምኩት ከጥቂት ቀናት በኋላ፣ ተመልሶ መጥቶ ከበሽታው እንደተፈወሰ ነግሮኛል::" አሉ::

ዶክተር ናትናኤል በከፍተኛ ተመስጦ ማድመጥ ጀመሩ:: ሆኖም፣ የባህል ሀኪሙ ንግግር አጭር ሆኖ ቀረ:: ዶክተሩ ተጨማሪ ማብራሪያ መፈለጋቸውን ምስጋናው ያጤኑ አልመሰሉም::

"የሰውዬው በሽታ፣ ኤድስ መሆኑን እንዴት ሊያውቁ ቻሉ?" አሉ ዶክተር::

"እውነቱን ልንገርዎ፣ እኔ በሽታውን አላወቅሁትም:: ከዳነ በኋላ መጥቶ ሲነግረኝ ነው ያወቅሁት:: ከዚያ በፊት ምንም ያወቅሁት ነገር አልነበረም::" አሉ::

"በሽታውን ሳያውቁ እንዴት መድሀኒት ሊሰጡት ቻሉ?"

"በሽታው እንዴት እንደሚያደርገው ነገረኝ::"

"ምን ብሎ ነግሮት?"

ጥቂት ዝም ብለው ከቆዩ በኋላ መናገር ጀመሩ:: "አንዳንድ ምልክቶች ነገረኝ:: ለምሳሌ፣ ክብደቱ እንደቀነሰ፣ ተቅማጥ፣ ትኩሳትና ሳል እንዳለበት ነገረኝ::" ብለው ድንገት ዝም አሉ::

ንግግራቸውን ሲጨርሱ አይታወቅም::

ዶክተር ናትናኤል ምስጋናው ይህንን መልስ ከሰጡአቸው በኋላ መቀጠል ያለበትን ጥያቄ ከማንሳታቸው በፊት ሌሎችን ነገሮች ማወቅ ፈለጉና፣" ህሙማን የእርስዎን ዕርዳታ ፈልገው ሲመጡ፣ ምርመራ የሚያደርጉበት ዘዴ አለ?" አሉ::

"አዎ:: እናንተ እንደምታደርጉት ደምና ሽንት የምመረምርበትና ራጅ የማነሳበት መሣሪያዎች ባይኖሩኝም፣ የራሴ የሆኑ ከልምድ ያገኘኋቸው ህሙማንን የመመርመሪያ ዘዴዎች አሉኝ::

በመጀመሪያ ህሙማን የሚነግሩኝን ምልክቶች እሰማለሁ። ከዚህ በኋላ የሰውነታቸውን አንዳንድ አካላት በማየትና በእጄ በመዳበስ በሽታዎች እለያለሁ።"

"ይሄ የኤድስ በሽተኛ ከነገሮት ምልክቶች ሌላ በአካሉ ላይ ያይዋቸው ምልክቶች ነበሩ?"

"አዎ።"

"እንደምን ያሉ?" አሉ፣ ዶክተር ናትናኤል ለማወቅ ጓጉተው።

ምስጋናው እንደማሰብ አሉና፣ "ሁሴን፣ ሁሴን፣..." ሲሉ ተጣሩ።

ያ ቀይ ወጣት ልጅ ፈጥኖ ገባና፣ "አቤት!" አለ።

"እስኪ የታካሚዎችን የህክምና ሁኔታ የሚገልጸውን መዝገብ አምጣልኝ።" አሉ።

ልጁ ተመልሶ ሄደ።

ዝምታ ተፈጠረ።

ዶክተር ለምስጋናው የተቀዳውን ቡና አዩና፣ "ለምን አይጠጡትም? ቀዘቀዘበት እኮ።" አሉ።

"ይቀዝቅዝ። አውቄ ነው። እንደውሀ ሲቀዘቅዝ ነው የምጠጣው።"

"ለምን?"

"ያመኛል። ጨጓራዬን ያመኛል።"

ዶክተር ትንሽ እንደመደንገጥ አሉ። "ታዲያ ለምን ወደ እኛ ሆስፒታል ብቅ አይሉም?"

"ምን ሊማድረግ?"

"የሚረዱበትን መንገድ እንፈጥራለን።"

"ለዚህ በሽታ መድሀኒት አጥተው ወደ እኔ የሚመጡት ህሙማን ምንም ዋጋ እንደሌለው እየነገሩኝ ወደ እናንተ ልምጣ?"

ዶክተር ሊሰጡ የነበረውን መልስ የሁሴን መግባት ገታው።

ሁሴን አንድ ትልቅ መዝገብ ለምስጋናው ሰጣቸው።

"የዚያን ሰውዬ ስም ታስታውሰዋለህ?" አሉና መገላለጥ ጀመሩ።

"የየትኛውን?" አለ ሁሴን።



"ያ እንኳ፣ ከኤድስ በሽታ ስለፈወሱኝ አመሰግናለሁ ብሎ የመጣው ወጣት?"

"እ... አዎ። ግሩም ተረፈ ነው የሚባለው።" አለና ቆመ።

"እሺ። በቃ ሂድ።" አሉ መቆሙን እይተው። የመዝገቡን ገጾች ከገለጡ በኋላ፣ "ግሩም ተረፈ።" ብለው በመጀመር ማንበብ ጀመሩ።

"የበሽታው ምልክቶች፣ አንደኛ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከሰባ ኪሎ ግራም ወደ ስድሳ ሶስት ኪሎ ግራም ዝቅ ብሎ ነበር። ተቅማጥ፣ ትኩሳትና ሳል ያጠቃው እንደነበር ነግሮኛል።" አሉ ናትናኤልን ቀና ብለው ካዩዋቸው በኋላ።" የአፉ መቁሰል፣ የምላሱ መኮማተርና የጉሮሮው መቁሰል፣ እኔ ያየኋቸው ሌሎች ምልክቶች ናቸው።" አሉ በመቀጠል።

"ምን ዓይነት መድሀኒት ነው የሰጡት?" ሲሉ ጠየቁ። ለዚህ ጥያቄያቸው የሚፈልጉትን መልስ እንደማያገኙ ቀድሞውኑ ያውቁታል። አብዛኞቹ የባህል ሀኪሞች ጥበባቸውን ለሌሎች ሰዎች ለማሳወቅ አይፈልጉም። እባብ ከበላች በኋላ፣ ለመርዙ ማርከሻ እንደምትፈልገዋ ፍየል፣ መድሀኒታቸውን ማንም እንዲያውቅባቸው አይፈልጉም። ነፍሳቸው ልትወጣ ስትል ጥበቡን ለልጃቸው ያወርሳሉ ወይም ይዘውት ይሞታሉ እንጂ፣ እያሳውቁም። ዶክተር ናትናኤል ይህንን ጥያቄያቸውን ያነሱት እንዳው ምናልባት ብለው ነው።

ጥቂት ዝም ብለው ካሰቡ በኋላ፣ "የመድሀኒቱን ስም እንኳ አልነገርዎትም።" አሉ።

ዶክተር ናትናኤል ፈገግ አሉ። "ምነው... መድሀኒቱን እኔ እንዳገኘሁ አድርጌ የማሳውቅ መሰሎት እንዴ?" ሲሉ ጠየቁ።

ምስጋናው መልስ አልሰጡም።

"ስሙ ጌታዬ፣ እኔ ምፈልገው መድሀኒቱ ትክክለኛ መሆኑን ከተረዳሁ በኋላ በዚህ በሽታ እየተሰቃየና ነገ በእኔ ይደርስ ይሆን እያለ ለሚሰጋው ሕዝብ ባለውለታ የሆኑ ኢትዮጵያዊ መሆኖን ማሳወቅ ነው። ይህንን ለማድረግ ማየት፣ ማጥናትና በቂ መረጃ መያዝ አለብኝ። ለማደርግሎት የምስክር ቃል፣ ጆሮ እንዳገኝ ማረጋገጥ አለብኝ።"

"ቢሆንም፣ እኔ የተጠቀምኩበትን መድሀኒት አልናገርም።" አሉና የቀዘቀዘ ቡናቸውን መጠጣት ጀመሩ።" ባይሆን፣ ካላመኑኝ ከበሽታው የተፈወሰውን ሰው ማነጋገር ይችላሉ።"

ዶክተር ናትናኤል ግሩም ተረፈ የተባለውን ሰው ማነጋገር እንዳለባቸው የወሰኑት ቀደም ብሎ ነበር።" የት አገኘዋለሁ?"

"እዚህ እንዲመጣ ላደርግ እችላለሁ። አለበለዚያ ደግሞ፣ አድራሻውን ልንገሮትና ፈልገው ያነጋግሩት።"

"ጥሩ። ይንገሩኝ።" አሉና ማስታወሻ ይይዙበት በነበረው ወረቀት ላይ አነጣጠሩ።

ምስጋናው ነገሯቸው።

"አመሰግናለሁ። ግን አቶ ምስጋናው፣ ነገሩ ጥሩ የሚሆነው የተጠቀሙበትን የመድሀኒት ዓይነት ለእኔ ሳይሆን ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሰዎች በማሳወቅ ምርምር ቢደረግበት እርሶም የባለቤትነት መብት አግኝተው ህዝቡን መርዳት ይችላሉ። ከዓለም ሕዝብ ምስጋናና ክብር ይቸሮታል። ከፍተኛ ጥቅምም ያገኛሉ።" አሉና ለመሄድ ተዘጋጁ።

ሀሳብ ውስጥ ሆነው ምስጋናውም ብድግ አሉ።

"አይመስሉትም? በዘመናዊ መንገድ ተሠርቶ ብንጠቀምበት የሚያስደስቶት ይመስለኛል። እስቲ አስቡበትና ይደውሉልኝ።" አሉና የስልክ ቁጥራቸውን የያዘ ማስታወሻ ሰጧቸው።

"እስኪ እንግዲህ አስብበታለሁ። የሚሆን ከሆነ እነግሮታለሁ።"

"አቶ ምስጋናው፣ ይሄ አስቸጋሪ የሚሆንቦት አይመስለኝም። ሳይውሉ ሳያድሩ በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠረውን ህመምተኛ ሊያድኑት ይገባል። የብዙ መቶ ሺህ ህሙማን ነፍሶች በእጅዎ ነው ያለው። በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠር ብር፣ እጅግ ከፍተኛ የሆነ ሽልማትና ከፍተኛ የሆነ ክብር ማግኛ ቁልፍ ያለው በእጅዎ ነው። ሳያወላውሉ ትብብሮን በማሳየት ወደ እኛ ብቅ ሲሉ ነው የሰው ልጅንና አምላኮን ማስደሰት የሚችሉት። እና ማሰቢያ ጊዜ የሚያስፈልገው አይመስለኝም።" ብለው፣ ዝም አሉ ዶክተር።

ሁለቱም ወደ በረንዳው ከወጡ በኋላ ቆሙ።

"በኤድስ በሽታ የተለከፉ ሌሎች ሰዎች መጥተው ነበር?"

"ከግሩም ተረፈ በስተቀር ሌላ ሰው አልመጣም። እኔም ሥራ ላይ ስላልነበርኩ፣ ቅድም እንደነገርኩዎ ከፍለሀገር ሄጄ ነበር፣ ሌላ በሽተኛ ይምጣ አይምጣ አላወቅሁም።"

"ጥሩ። በሉ ደህና ይዋሉ። "አሉ ዶክተር ናትናኤል ብዙ ሴኮንዶች ሲያስቡ ከቆዩ በኋላ።



## 26

መኪናቸውን አስነሱና ቁልቁል ወደ ሽሮ ሜዳ የሚወስደውን መንገድ በፍጥነት መንዛ ጀመሩ። ሀሳብ ውስጥ ነው ያሉት። ወዴት እንደሚሄዱ ግን ያውቁታል። ግሩም ተረፈ የተባለውን ሰው ለማነጋገር ተጣድፈዋል። ወደ ስድስት ኪሎ የሚወስደውን ዋና ጎዳና ተያያዙት። የስድስት ኪሎ አደባባይን ከዞሩ በኋላ፣ ወደ ምኒሊክ ሆስፒታል የሚወስደውን ጎዳና ጀመሩ። ጥቂት እንደተጓዙ ወደ ቀበና ታጠፉ። ምስጋናው የሰጧቸውን አድራሻ አነበቡ። በአድራሻው የተጠቀሰው ከፍተኛ አሁን የደረሱበት አካባቢ ቢሆንም ቀበሌውን ለይተው አያውቁም። መኪናቸውን አቆሙና ወረዱ። በአካባቢው ያሉትን ሰዎች ጠየቁ። የግሩም መኖሪያ ቤት የሚገኝበትን ቀበሌ ጽሕፈት ቤት አገኙና ገቡ።

አንድ የቆርቆሮ ግቢ አጠገብ ሲደርሱ፣ "ይሄ ነው ቤቱ።" አለ የግሩምን ቤት ሊያሳያቸው ከጽሕፈት ቤቱ አብሯቸው የመጣው ልጅ።

"አመሰግናለሁ።" አሉና ልጁ መሄዱን ካዩ በኋላ፣ ማንኳኳት ጀመሩ።

አንዲት ጠቆር ያለች ትንሽ ልጅ በሩን ከፍታ ብቅ አለች።

"የግሩም ቤት ይሄ ነው?" ሲሉ ጠየቁ ናትናኤል።

"አዎ።" አለች።

"አለ?"

"አዎ። ይግቡ።"

ዶክተር ገቡ። ብዙ ሰዎች ተጎራብተው የሚኖሩበት ግቢ ነው።

"ኑ በዚህ በኩል።" አለች ልጅቷ፣ ፊት ፊት እየቀደመች።

ተከተሏት። አንድ አነስ ያለ ቤት በር አጠገብ ሲደርሱ ቆሙና፣ "ጥሪው። እኔ አልገባም።" አሉ።

"ኧረ ግቡ።" አለች ልጅቷ።

"ግዴለም። አልገባም። ብቻ ጥሪልኝ።"

ልጅቷ ገባች።

ከጥቂት ሴኮንዶች በኋላ የቤቱ በር ተከፍቶ ጠየም ያለ፣ ቀጭን፣ መካከለኛ ቁመት ያለው አንድ ሰው ወጣ። ዶክተርን ግራ በመጋባት ስሜት እየተመለከታቸው ተጠጋ።

"ጤና ይስጥልኝ! ዶክተር ናትናኤል ዘለቀ እባላለሁ።" አሉና እጃቸውን ለመጨበጥ ዘረጉለት።

"ጤና ይስጥልኝ! ግሩም ተረፈ።" አለና ጨበጣቸው።

ዶክተር የሚለውን ቃል ሲሰማ እንደመደንገጥ አድርጎታል። አልወደደውም።

"ስለ አንድ ጉዳይ ላነጋግርህ ፈልጌ ነው የመጣሁት።" አሉ ዶክተር።

አሁንም ግራ በመጋባትና በድንጋጤ ስሜት እያያቸው፣"ስለምን?" ሲል ጠየቀ።

ትንሽ አቅማሙና፣ "ቤት ገብተን መነጋገር እንችላለን ወይም መኪናዬን ከአጥር ውጭ አቁሚያለሁ። እዚያ ውስጥ እንነጋገር?" አሉ።

ጥቂት እንደማሰብ አለ። "መጣሁ። መኪና ውስጥ ጠብቁኝ።" ብሎ ወደ ቤት ገባ።

ዶክተር ከግቢው ወጡና መኪናቸው ውስጥ ገቡ።

ከትንሽ ጊዜ በኋላ መጣና መኪናው ውስጥ ገባ፣ ግሩም።

ናትናኤል ከጥቂት ሴኮንዶች ዝምታ በኋላ ማውራት ጀመሩ። "ግሩም፣ አቶ ምስጋናውን ታውቃቸዋለህ?"

"ማን ናቸው አቶ ምስጋናው?" ሲል፣ ጥያቄያቸውን በጥያቄ መለሰ።

"ከሽሮ ሜዳ በላይ ከሚገኝ አንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩ የባህል ሀኪም።" አሉ ዶክተር፣ ዓይኖቻቸውን ከፊቱ ላይ ሳያነሱ።

ቶሎ አልመለሰላቸውም። ዶክተሩ ከርሱ የሚፈልጉት ምን እንደሆነ ሊገምት አልቻለም። ከሞት አፋፍ ላይ የመለሱትን የባህል ሀኪም እንደማያውቅ ሆኖ፣ መናገርም አለመናገርም ፈለገ።

"ለምንድን ነው ይህንን የሚጠይቁኝ?"

"ለመጥፎ ነገር አይደለም። አንዳንድ ሁኔታዎችን ለማወቅ ፈልጌ ነው። የሚያስፈራ አይደለም።"

ግሩም ፈራ። ምስጋናውን እንደሚያውቅ ከተናገረ፣ እንዴት ተዋወቅህ? በሽታህ ምን ዓይነት ነበር? የሚሉ ጥያቄዎች እንደሚከተሉ ገምቷል። ለእነዚህ ጥያቄዎች ደግሞ ትክክለኛ መልሶች ከሰጠ ሲደብቀው የነበረውን፣ ከእርሱ፣ ከምስጋናውና ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ውስጥ ከሚገኙ ጥቂት ሀኪሞች በስተቀር የሚያውቁትን ምስጢር ይፋ ማድረጉ ነው። ይህ ሁኔታ፣ በብዙ ሰዎች ዘንድ ከተሰማ መጠቋቆሚያና መነጋገሪያ ይሆናል። ይህ እንዲሆን ግሩም አይፈልግም።



"ይሄን ያህል እኮ የሚያሳስብ አይደለም።" አሉ ዶክተር።

"አላውቃቸውም።" ሲል ተነፈሰ።

ዶክተር ደነገጡ። እንደዚህ ዓይነቱን መልስ አልጠበቁም ነበር። ግሩም ምስጋናውን ሳያውቃቸው ቀርቶ ሳይሆን፣ ደብቋቸው መሆኑን መረዳት አላቃታቸውም። ምስጋናው ስላደረጉለት የህክምና እርዳታ እና ስለሰጡት የመድሀኒት ዓይነት ሰፋ ያለ ማብራሪያ ይሰጠኛል ብለው ገምተው ነበር። ይሁንና፣ ያሰቡት አልሆነም። ግሩም ሁኔታውን በምስጢር ለመያዝ ፈልጓል። እንዴት አድርገው በማግባባት ሊያውጣጡት እንደሚችሉ ግልጽ አልሆነላቸውም።

ትንሽ ዝምታ ተፈጠረ።

"አሁን በዓለንበት ወቅት ውስጥ፣ እያሌ ወገኖቻችን እንደቅጠል ለሚረግፉበት በሽታ፣ እኚህ የባህል ሀኪም መድሀኒት አላቸው የሚል ወሬ ሰምቻለሁ። ይህ ነገር እውነት ከሆነ፣ እነዚህን ህሙማን ከመፈወስ ሌላ ለዚህች ድሀ አገራችን መድሀኒቱ ተሰርቶ ሲሸጥ ጥሩ ገቢ ይሆናል። በእኒህ ሰው ስም የሚጠራው መድሀኒት፣ አገራችንን በሳይንስ መስክ አንድ ትልቅ ሥፍራ ሊያደርሳት ይችላል። እና እኚህ ሰው በትክክል መድሀኒቱን ማግኘት አለማግኘታቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። አዳንኩአቸው ያሉትን ህሙማን ማነጋገርና የምስክርነታቸውን ቃል መስማት ጥሩ ሆኖ አይቼዋለሁ። እና አንተ..." ካሉ በኋላ የሚቀጥሉትን ቃላት ለማውጣት ተቸገሩ።

ግሩም ምን ሊናገሩ እንደፈለጉ ገባው። "እኔ ይሄ የሚሉትን ሰው አላውቅም። ለምን ስለ እሱ ሊነግሩኝ እንደፈለጉ አልገባኝም።" አለ፣ ትንሽ እንደመቆጣት ብሎ።

"ምንም የሚያስፈራም የሚያሳፍርም ነገር የለም። ማንኛውም ነገር በምስጢር ይያዛል። ትናንት አንተ ትሰቃይ በነበረበት በሽታ ዛሬም ተይዞ ተስፋ የቆረጠውን ወገን ከማዳን ሌላ የሚያስደስት ነገር የለም። ሁላችንም፣ የበኩላችንን እርዳታ ብናደርግ ትልቅ ነገር ነው። የሰውን ልጅ ጤናና ደስታ ለማየት ስንል የምንባለውን በመስዋዕትነት ብንቀበል የሚጎዳ አይሆንም። ህሊናችን ሊደሰት ይችላል። ያ ሳይሆን ቢቀር ግን አካላዊ ደስታ ቢኖረንም ህሊናችን አታርፍም። አትደሰትም። ለሰው ልጅ ደግሞ ትልቁ ነገር የህሊና ደስታ ነው። እኔ እውነቱን ልንገርህ... ከዓለም ህሙማን መሀል የመጀመሪያው ተፈዋሽ መሆን ራሱ ትልቅ ዕድል ነው። ተአምርም ነው። ይህ በአጋጣሚ ሳይሆን በእግዚአብሄር ርዳታ ሊሆን ይችላል የተገኘው። በርሱ የተገኘ የፈውስ ተአምር በርሱ ሊነጠቅ ይችላል።

ሁልጊዜ፣ ለሰዎች ደግ ስንሆን ነው እግዜር ደግ የሚሆንልን::" አሉና ንግግራቸውን አቆሙ:: ሳያስቡት ይህን የተናገሩት ለምን እንደሆነ ለራሳቸው ግራ ሳይገባቸው አልቀረም::

ይሁንና፣ በግሩም ስሜት ላይ ትንሽ ስጋት ሳይፈጥር አላለፈም:: ለእርሱ ብቻ የተሰጠን የፈውስ ተአምር እንዳያጣ ስጋ:: ቢሆንም፣ በመጀመሪያው ሀሳብ ጠና:: "ምን አድርግ እንደሚሉኝ እኮ አልገባኝም?" ሲል ጠየቀ::

"የምስጋናው ታካሚ እንደነበርክ ተረድቻለሁ:: የያዘህን የኤድስ በሽታ አቶ ምስጋናው እንዳጠፉልህ አውቄያለሁ:: ይህንን ሀኪሙ ራሳቸው ነግረውኛል:: ለምን ትደብቀኛለህ?"

"ምስጋናው ምን ያውቃል? የኔ በሽታ ኤድስ አልነበረም:: እሱ ዝም ብሎ ነው የሰው ስም የሚያጠፋው::" አለ በንዴት ተውጦ፣ ግሩም::

ዶክተር የግሩም ቁጣዊ አነጋገር ቢያስደነግጣቸውም፣ አንድ እውነታ አግኝተዋል:: ግሩም ምስጋናውን ያውቃቸዋል:: የህክምና አገልግሎትም አድርገውለታል::

"ይህ ሁኔታ እኮ የሚያናድድ አይደለም:: በዚህ በሽታ ታምሚያለሁ ማለት እኮ የሚያሳፍር ሊሆን አይገባውም:: ችግሩ የመጣው ባንድ ባለመወሰን፣ ከብዙ ሰዎች ጋር ግብረ ሥጋ ግንኙነት በማድረግ ወይም በመባለግ ብቻ አይደለም:: ሌሎች ብዙ ምክንያቶች አሉ፣ ሳናስበው በሽተኛ የሚያደርጉን:: ምናልባትም፣ በንጹህ መርፌዎችና ምላጮች ባለመጠቀም፣ ወይም በደም መስጠቲ ተግባር ላይ ታላቅ ጥንቃቄ ባለመደረጉ ይሆናል:: ስለዚህ፣ አንተ እንደምታስበው የኤድስ በሽተኛ መሆን ባለጌ አያሰኝም:: ሁልጊዜ አመንዝራ አያስብልም::"

ግሩም ረጋ ባለ ሁኔታ አንገቱን ወደ መሬት አጥፎ መስማት ቀጠለ::

ዶክተር አንድ ሀሳብ መጣላቸው:: ግሩምን ለማሳመን መዋሸት እንዳለባቸው ተረዱ:: "ምንም የሚያስፈራ ነገር አይኖርም:: እነዚህ ህሙማን የሚድኑበትን መንገድ ለመፍጠር የበኩልህን አስተዋጽኦ አድርግ:: ሁሉም ነገር በምስጢር ይያዛል:: እኔ ራሴ..." አሉና ንግግራቸውን ገቱ:: "አዎ፣ አልደብቅህም:: አላፍርህም:: የቫይረሱ ተሸካሚ ነኝ:: እኔንና ሌሎች መሰል በሽተኞችን ለማዳን የበኩሌን እያበረከትኩ ነው:: የህክምና አዋቂ ሆኜ የዚህ በሽታ ተጠቂ መሆኔ ቢታወቅ፣ ከአንተ ይልቅ የእኔ ሁኔታ ብዙ ሰዎችን ያስገርማል::



በሥራ ጓደኞቼ፣ በቤተሰቦቼና እኔን በሚያውቁ ዘንድ ትልቅ ትረታ ሊያመጣ ይችላል:: ይሁንና፣ ህሙማንን ለመፈወስ የእኔ መታወቅ የሚያስፈልግ ከሆነ፣ በዜና ማሰራጫዎች ቢገለጽ ግድ የለኝም:: እና ይህ ሊያስፈራህ አይገባም፣ የኔ ወንድም:: ደግሞ ሁሉም ነገር በከፍተኛ ምስጢር ይያዛል:: አንተ እኮ ድነሃል:: ሰዎች ያገሉኛል የሚል ስጋት ካለህ፣ ይህ አይሆንም:: አንተ ጤነኛ ነህ::"

ግሩም ዝም ብሎ ሊቆይ አልቻለም:: በተለይ የዶክተር ናትናኤል የህዋሱ ተሸካሚ መሆንን ካወቀ በኋላ ስሜ ይጠፋል የሚለው ስሜቱ ለቆት ሂዷል::" እሺ ምንድን ነው ለማወቅ የሚፈልጉትት?" አለ::

"በመጀመሪያ፣ ምስጋናው ዘንድ ለመታከም ሄደህ ነበር?" ሲሉ ጥያቄያቸውን ጀመሩ::

"አዎ::"

"የያዘህ በሽታ ኤድስ መሆኑን ሀኪሙ እንዴት ሊያውቁ ቻሉ?"

"እሳቸው ቤት ከመሄዴ በፊት፣ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ውስጥ ተመርምሬ ኤድስ እንደያዘኝ ተነገረኝ::"

"እህ... እዚያ ተመርምረሃል?"

"አዎ::"

የምርመራ ታሪኩን ከዚያው እንደሚያገኙ ተረዱ:: ግሩም በትክክል በበሽታው ተይዞ እንደነበር የሚያረጋግጥ ሠነድ ከሆስፒታሉ ማግኘት እንደሚችሉ አወቁ:: "ምስጋናው በሽታውን እንዴት ሊለዩ ቻሉ?"

"እርሳቸውም አላወቁም ነበር:: ሌላ በሽታ እንደሆነ አድርጊ ነው ልታከም የቻልኩት:: መድሀኒት ሰጥተውኝ ከተሻለኝ በኋላ ነው፣ ስለበሽታዬ ምንነት ነግሬያቸው እንዳዳኑኝ የገለጽኩላቸው::"

"ምኔን አመመኝ ብለህ ነው መጀመሪያ የነገርካቸው?"

"ሰውነቴ እንደሚደክመኝ፣ ተቅማጥና ትኩሳት እንዳለብኝ ነገርኳቸው:: እንዲሁም ክብደቴ መቀነሱን ሁሉ ገለጽኩላቸው:: ከዚያ በኋላ፣ መድሀኒት አጠጡኝ::"

"ምን ዓይነት መድሀኒት ነው? የመድሀኒቱን ዓይነት ታውቀዋለህ?"

"አላውቀውም:: የሚመር አረንጓዴ ነገር ነው በጥብጠው የሰጡኝ::"

"በምን ያህል ጊዜ ተሻለህ::?"

"ቶሎ ነው የዳንኩት::"

"መዳንህን በምን ምልክት አወቅህ ?"

"የታመምኩ ጊዜ ያየኋቸው ምልክቶች ጠፉ::"

"ከዳንክ በኋላ በዘመናዊ ህክምና እንደገና አልተመረመርክም?"

"አልተመረመርኩም::"

"ጥሩ::" አሉ ዶክተሩ::

አሁን ትልቅ ነገር አውቀዋል:: ግሩም የኤድስ በሽተኛ እንደነበርና የምስጋናው መድሀኒት እንዳዳነው ተገንዝበዋል:: የግሩምን የህክምና ታሪክ ከጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ውስጥ ፈልገው በማንበብ ግሩም የበሽታው ሰለባ እንደነበር ማረጋገጥ እንዳለባቸውም ተረድተዋል:: ከዚህ ሌላ አንድ ትልቅ ጥያቄ ለግሩም ለማንሳት ወሰኑ::

"በሽታው በምን እንደያዘህ ታውቅ ነበር?"

"እንዴት?"

"ማለቴ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ነው ወይስ በሌሎች መተላለፊያ መንገዶች፣ ለምሳሌ ሰዎች በተወጉበት መርፌ በመጠቀም..."

"በግብረ ሥጋ ግንኙነት ነው::" ሲል አቋረጣቸው::

"ያስያዘችህን ልጅ በትክክል ታውቃታለህ?"

"በደንብ::" አለና ሀሳብ ውስጥ ገባ::

አንድ ምሽት ከወንዶች ጓደኞቹ ጋር ዳህላክ ፓራዳይዝ በሚባለው ዳንስ ቤት ውስጥ ሲጫወት የተዋወቃት ቀይ ቆንጆ ልጅ ትዝ አለችው:: የለበሰችው ሱሪ አካሏ ላይ ልክክ ብሎ፣ ውብ ቅርጿን በላሳየው የተጠጋት ልጅ፣ በዓይን ህሊናው ብቅ አለችበት:: ውብ ተክለ ቁመናዋ ብቻ ሳይሆን፣ በዚያች ምሽት አድርገዋቸው የነበሩት ቃለ ምልልሶች እንደገና ተሰሙት::

"ጥሩ የሰውነት አቋም አለሽ?"

"በጣም አመሰግናለሁ::"

"እንደንሳ?"

"ደስ ይለኛል::"

መደነስ ጀመሩ:: አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን፣ ደጋግሞ እያስነሳ በፈጣኑም በለስላሳውም ሙዚቃ ተጫወቱ:: ብዙ ቃላት ተለዋወጡ:: ተግባቡ:: ከንጋቱ አሥራ አንድ ሰዓት ላይ የዳንሱ ድግስ ሲያበቃ ወደ



ቤቱ ይዞአት ሄደ:: በማግስቱም ከአልጋ ውስጥ ሳይወጡ ዋሉ... በዚያን ቀን ብቻ አይደለም:: ነገሩ በተለያዩ ቀናት ቀጥሎ አንድ ሁለት ዓመታት አለፉ:: በዚያ መሀል፣ የግሩም ጤና ማጣት ብቅ ብቅ አለ:: በሀኪም ምርመራ የበሽታው ምንነት ታወቀ::

"እኔ ምልህ... በሽታው በትክክል ከዚህች ልጅ እንደያዘህ እንዴት አወቅህ ?" አሉ ዶክተር ናትናኤል::

"እርሷን ካፈቀርኩ ጀምሮ፣ ከርሷ ሌላ ሴት አላውቅም::"

"እሷ የቫይረሱ ተሸካሚ መሆኗንስ ታውቃለች?"

"አዎ:: ኸረ እንዳውም በምትኖርበት አካባቢ ሁሉ ስለእሷ ህመም ነው አሉ የሚወራው::"

"የት ነው አካባቢዋ?"

ነገራቸው::

"ለዚህ ነው እኔ በበሽታው ተይዤ እንደነበር እንዲታወቅ ያልፈለኩት:: እኔና እሷ አብረን እንደነበርን ብዙ ሰዎች ያውቃሉ:: ብዙ ሰዎችም የእሷን የቫይረሱ ተሸካሚ መሆን ሰምተው፣ የእኔን ሁኔታ የጠየቁኝ አሉ:: ግን፣ የእኔ አማራጭ ደግሞ ውሸት መሆኑን መናገር ነው::"

"ጥሩ:: ሌላ አንድ ጥያቄ ላቅርብልህ:: ይቺ ልጅ ማን ናት ያልከኝ?"

"ስሟን አልነገርኮትም::"

"ለመንገር ፈቃደኛ አይደለህም?"

ዝም አለ::

ዶክተር ጠበቁና ምንም የማይናገር መሆኑን ሲረዱ፣ "ምስጋናው ጋ ሄዳ እንድትታከም ነግረሀት ነበር?" ሲሉ ጠየቁ::

"አልነገርኳትም::"

"ለምን?"

"ተጣልተናል:: የትም እየተልከሰከሰች እየመጣች እኔን በበሽታ ስለለከፈችኝ ደብድቤያት፣ አሁን አንነጋገርም::"

"እህ..." ብለው ዝም አሉ:: ጥቂት ካሰቡ በኋላ፣" ግሩም፣ መቼም እስካሁን ግልጽ ሆነን ተወያይተናል:: የአቶ ምስጋናው መድሀኒት አንተን እንደፈወሰህ ሁሉ ሌሎችንም ህሙማን እንዲፈውስ ሳትፈልግ አትቀርም:: ይሁንና፣ የዚህ በሽታ ተጠቂ እንደነበርክና በባህል መድሀኒት እንደዳንክ ምስክር ሆነህ መናገር አትፈልግም?"

"አዎ::"

"አንድ ሌላ አማራጭ ልንገርህ። የአንተ ማንነት ሳይታወቅ የምስጋናው መድሀኒት ትክክለኛ መድህን መሆኑን ማረጋገጫ ሌላ ዘዴ አለ፡ የአንተ ፍቅረኛ የነበረችውና የማይረሱ ተሸካሚ የሆነችውን ልጅ ምስጋናው ጋ ሄዳ እንድትታከም እናድርጋት። መድሀኒቱ ማዳኑን እናረጋግጥ። ከዚያ በኋላ የሷን ምስክርነት እወስዳለሁ። ያንተ ስም አይጠራም ማለት ነው። ገባህ?"

"አዎ።"

"አድራሻዋን ንገረኝ።"

ነገራቸው በድጋሚ።

"ስሟ ማን ነው?"

"ሽታዬ ጋሻቸው።"

## 27

እሁድ ከሰዓት በኋላ ነው። ንግሥትና ሲሳይ የእንግዳ መቀበያ ክፍል ውስጥ ተቀምጠው ሲጫወቱ፣ ከአንድ ሰዓት በላይ ሆኗቸዋል። በዚህ ቆይታቸው ውስጥ፣ እስካሁን ያልተነሳ ርዕስ ሲሳይ ድንገት አነሳች።

"እኔ ምልሽ ንግሥትዬ፣ የዳንኤልና የአንቺ ግንኙነት በምን መልክ ነው?"

ንግሥት ፈገግ ብላ ዝም አለች። ወዲያው ደግሞ ሲሳይ ላነሳችው ጥያቄ መልስ መስጠት እንዳለባት ስላወቀች ፣ "እንዲሁ ነው።" አለች።

"እንዴት እንዲሁ? አይመስለኝም።" አለች፣ ሲሳይ ሳቅ ብላ።

"እንዴት አይመስልሽም?"

"መቀራረቡ በዛ ብዬ ነዋ። በየቀኑ መደወል፣ አብሮ ሻይ ቡና ማለት ትርጉሙ ምንድን ነው? መጀመሪያ ቀን ያደረገልሽ ስጦታና የምሳ ግብዣሽ ይሁን፣ ውለታ ስለሰራሽለት ነው ተባለ። ከዚያ ወዲያ የተደረጉትስ ግብዣዎች? ቤትሽንም አውቆታል፣ አይደል?"

"አዎ። ለመታከም ሲመጣ ነው ያየው። የጨጓራ በሽታ ስለነበረበት፣ አባዬ እንዲያክመው ፈልጎ ነው ቤት የመጣው።"

"አሂሂ... እሱ ሰበብ ነው።" አለች ሲሳይ፣ በጥርጣሬ ስሜት።

"ሙች! ታሞ ነው። ለምን እዋሻለሁ?"

"ፋዘር ምን አሉ ግን ከርሱ ጋር ስታስተዋውቂያቸው?"



"እኔ ቤት አልነበርኩም ነበር። የቤታችንን አድራሻ በስልክ ጠየቀና መጥቶ ታከመ።"

ፈገግ አለች። "ጥሩ ነው። ግን ነገር አለ።"

"ለእኔም አልገባኝም።"

"ምኑ?"

"አዝማሚያው።"

"እሱስ ተይ! እንዳውም ጀምራችኋል!" ብላ፣ ፍርጥ አደረገችው።

"በፍጹም ። ስለፍቅር ጉዳይ አንስተን የተጫወትንበት ጊዜ የለም።"

"በቃላት ባትጫወቱ በዓይኖቻችሁ ሳትነጋገሩ አልቀረም። ያን ቀን ሁለታችንንም የጋበዘን ጊዜ፣ ነገር መኖሩን ከዓይነውሀችሁ ተረድቼያለሁ።"

"ሲሳይ ሙች! ምንም ነገር የለም። ለምን እደብቅሻለሁ። እስካሁን የጀመርነው ነገር የለም።"

"ግን ሁኔታችሁ የጀመራችሁ ነው የሚያስመስላችሁ። እንዳሰበ ግን ይግባሽ። አንቺም አስበሽዋል። አይደለም?"

"አልዋሽም። አዎ።"

"ጥሩ ሰው ሳይሆን አይቀርም።"

"በጣም ጥሩ ሰው ነው። ትህትናው፣ ጨዋታው በጣም ደስ የሚል ሰው አድርጎታል።"

"በዚህ ላይ ቆንጆ ነው።" አለች ሲሳይ።

ንግሥት ምንም አስተያየት አልሰጠችም። ፈገግ ብላ ዝም አለች።

ጥቂት ሴኮንዶች በዝምታ ካለፉ በኋላ "ንግሥትዬ፣ የአንቺና የግርማ ነገር እንዲህ ድንገት መቋረጡ እስካሁን ሊገባኝ አልቻለም። ምክንያቱ ምንድነው?"

ስለ ግርማ እንዲነሳባት አትፈልግም። "ባክሽ ተይው!"

"የተጣላችሁበትን ነገር ለምን አትነግሪኝም?"

"ምን ያደርግልሻል?"

"ምን አለበት ባውቀው?"

"ደግሞ አልተጣላንም።"

"እንደድሮ አይደላችሁም።"

"እንደድሮ አለመሆን ታዲያ መጣላት ነው?"

"መራራቅ ከአለመግባባት የሚመጣ መሰለኝ።"

በታከተ ስሜት በረጅሙ ተነፈሰችና ዝም አለች።

"ከመቼ ጀምሮ ነው ግን እንዲህ የሆናችሁት?" ስትል ጠየቀች ሲሳይ። ሁኔታውን ለማወቅ የምትጓጓበት ምክንያት አለ።

"ቆይታል።" አለች፣ ትካዜ በተሜነው ስሜት።

ከዚህ በኋላ ምን እንደምትጠይቅ አላወቀችም።

"የአፈወርቅ ስልስት ጊዜ ከግርማ ጋር አብረን እንዳመሸን ታስታውሺያለሽ?"

"አዎ፣ አስታውሳለሁ።"

"ከዚያን ቀን ጀምሮ ነው።" አለች።

ሲሳይ ማሰብ ጀመረች። የዚያን ቀን ምሽት የንግሥት አባት ለቅሶ ቤት መጥተው፣ የንግሥትን መገኛ ቦታ መጠየቃቸው ትውስ አላት። ለምን ጉዳይ እንደፈለጓት ንግሥትን ጠይቃት አታውቅም። ከግርማ ጋር ለማደር መኝታ ቤት የያዘችበት ሆቴል ድረስ አባቷ መጥተው ሲያነጋግሯት ምን ዓይነት ስሜት እንደተሰማት አልነገረቻትም። ልትጠይቃት ታስብና ትዘነጋዋለች። ጉዳዩን ማንሻ አጋጣሚ ያገኘች መሰሎ ታያት።

"ንግሥት ፣ የዚያን ቀን አደራችሁ?"

"አዎ።"

"አባትሽ አገኙሽ የዚያን ቀን ማታ?"

ግራ በመጋባት ካየቻት በኋላ፣ "የት?" አለች ንግሥት።

ሲሳይ ዝም አለች። በዚያን ቀን ማታ ናትናኤል ንግሥትን እንዳላነጋገሩ አወቀች። አንድ ሥጋት ነበራት። ንግሥት ያለችበትን ቦታ ለአባቷ በመናገሯ ትቀየመኛለች ብላ ፈርታ ነበር።

ለጥቂት ሴኮንዶች ያህል ዝምታ ተፈጠረ።

"ያንን እንስሳ አየሁት እኮ።" አለች ሲሳይ እንደዘበት ዓይኖቿን ወለሉ ላይ ተክላ።

"የቱን?" አለች ንግሥት፣ ከሀሳቧ ወጥታ።

"ያንን ልክስክስ ነዋ!"

"የቱን?" አለች አሁንም ንግሥት፣ ሳይገባት ቀርቶ።

"አርአያን።"

ስሙ ሲጠራ እንዳች ነገር ወረራት።

"ከአንዲት ሴት ጋር አየሁት።"



"የራሱ ጉዳይ ባክሽ!" ብላ ዝም አለች። "ከእርሱ ጋር የምትውል ሴት ከአራዊ ጋር እንደሚውል በሬ ነው መታየት ያለባት።"

"ባለ ትዳር ናት እኮ። እንዳውም የልጆች እናት።"

"እውነትሽን ነው?"

"ሙች!"

"በባሏ ላይ ለምኗ ነው ይህንን ርኩስ የተጠጋችው?"

"ምን አውቃለሁ። በምላሱ ተብትቧት ይሆናላ። ይሄኔ ስንቱን ቀባጥሮላታል።"

"አንቺ እንዴት አወቅሻት?"

"እሷን የምታቃት አንድ የመሥሪያ ቤቴ ልጅ አለች። እሷ ናት ስለእርሷ የነገረችኝ።"

ከዚያ በኋላ ስለ አርአያ ያነሱትን ወሬ ገቱና ለጥቂት ደቂቃዎች ያህል በየግል ሀሳቦቻቸው ውስጥ ሰጠሙ።

"እኔ ምልሽ ሲሳይ፣ ለዳንኤል ስልክ ብደውልለትስ?" ስትል በድንገት ጠየቀች፣ ንግሥት።

ሲሳይ ትኩር ብላ አየቻትና ዝም አለች። ወዲያው ደግሞ፣ "ልታነጋግሪው ፈለግሽ?" ስትል ጠየቀቻት።

"አዎ። ድምፁ ጠፋብኝ እኮ።"

"መቼ ነበር የተገናኛችሁት?"

"ዛሬ እሁድ ነው፣ አይደል?"

"አዎ።"

"ከሶስት ቀናት በፊት፣ ሐሙስ።"

"ሐሙስ ቅርብ ጊዜ አይደለም?"

"ቆየ እንጂ።"

"እሱ እስኪደውል ብትጠብቂ አይሻልም?... ወንድ ልጅ ሴት ከደወለችለት እኮ ኩራቱም መከራ ነው።" አለች ሲሳይ።

"ምን ያኮራል ደግሞ!" አለች በማናናቅ። "የፈለገውን ይበል! እኔ ግን ግልጽ ሆኜ ነው የምቀርበው።"

የስልኩን ማናገሪያ አነሳችና ቁጥሮች ማዞር ጀመረች።

"ቆይ፣ አሁን ደውለሽ ምን ልትይው ነው?"

"ምን የምለው ይመስልሻል?"

"ናፈቅኸኝ።"

"የማፍር መሰለሽ? ... ናፈቅኸኝ ብቻ ሳይሆን፣ ወደድኩህ ነው የምለው።" አለችና ቁጥሮቹን ማዞር ጀመረች።

ስልኩ ጥቂት ከጮኸ በኋላ ፣ዳንኤል አነሳው።

## 28

ህክምና ለማግኘት ተራቸውን በመጠባበቅ ላይ ካሉ ሀሙማን መሀከል አንዷ ሆናለች። ከአለችበት ሥቃይና ጭንቀት ያወጡሻል ተብላ የፈውስ እጃቸውን ለማግኘት ከመጣች አንድ ሰዓት አልፏታል። ከሰው በታች የሆነች ያስመሰላትን ህዋስ ከደሟ ውስጥ የማጥራት ችሎታ ያላቸውን አቶ ምሥጋናውን ለማየት ጓጉታለች። ሰውዬውን የምታይበት ደቂቃ እንደከርስቶስ መምጫ ቀን ናፍቃታል።

ትናንትና ፣ ዶክተር ናትናኤል ከምትኖርበት ቤት ድረስ መጥተው ከበሽታዋ ሊፈውሷት የሚችሉ ሰው እንዳሉ ሲነግሯት ልታምን አልቻለችም ነበር። ከዚህ ቀደም፣ ገብሩ እንደሰጣት ዓይነት ባዶ ተስፋ አድርጋ ነበር ያየችው። ግን፣ ዶክተር ናትናኤል የነገሯት በቀላሉ የምታልፈው ሆና አላገኘችውም። መጀመሪያ ላይ ሁሉን ነገር ገልፃ ለመናገር ፍላጎት አልነበራትም። የሀዋሱ ተጠካሚ መሆኗን እንኳ መናገር አልፈለገችም ነበር። የሰውዬው አነጋገር እንዴት ሊያሳምናት እንደቻለ ማስታወስ ሞከረች። ትናንት ዶክተሩን ካየችበት ደቂቃ ጀምሮ የነበረውን ሁኔታ ለጥቂት ሴኮንዶች በዓይነ ህሊናዋ ማየት፣ በአዝነልቦናዋ ማድመጥ ያዘች።

ታናሽ እህቷ ነበረች፣ ከክፍሏ ድረስ መጥታ የጠራቻት። "እታባ፣ አንድ ሰውዬ ይፈልጉሻል።"

"የምን ሰውዬ?"

"እኔ እንጃ። ግቢያችን በር ላይ ቆመዋል። መኪና ይዘው ነው የመጡት።"

"እንቺ አታውቂያቸውም? " ስትል ሽታዬ ፣ ታናሽ እህቷን ጠየቀች።

"አይቻቸውም አላውቅም።"

ከአልጋዋ ላይ ቀና አለችና፣ "ማ ይሆኑ?" ስትል ራሷን ጠየቀች። ነጠላ ሚግ አጠለቀች።

በስስ የሌሊት ልብሷ ላይ ጋቢ ደረበችና ወጣች።

ምሽቱ ለዓይን ያዝ ማድረግ ጀምሯል። ጨለማ ጊዜውን ከቀን በመረከብ ላይ ነው።



ከግቢ ወጣች።

"ጤና ይስጥልኝ። ወይዘሪት ሽታዬ?"

"አዎ።" ብላ የዘረጉላትን እጅ ጨበጠች።

"ዶክተር ናትናኤል እባላለሁ።"

ምን እንደምትመልስ እርግጠኛ ስላልነበረች ዝም አለች።

"ለአሥር ደቂቃዎች ያህል ላነጋግርሽ ፈልጌ ነበር።"

"ስለ ምን?" አለች ግንባሯን ቋጥራ።

"ስለአንቺ።"

"ስለእኔ ምን?" አለች አሁንም፣ ፈርጠም ብላ።

"እዚህ ቆመን ከምናወራ ለምን መኪናዬ ውስጥ ገብተን አንነጋገርም" አሉ፣ በአንድ እጃቸው መኪናቸውን እያሳዩ።

አመነታችና ገባች።

"ግሩም ተረፈን ታውቂዋለሽ?"

ክው ብላ ቀረች። ድንጋጤ በመላ ሰውነቷ ውስጥ ተሠራጭቶ መተንፈስ አሳሰችል አላት። የምትናገረው ቃል አጣች። እርሱ ዓይንሽን ለአፈር ቢላትም፣ ትወደዋለች። ቢሸሻትም ስለእርሱ ታስባለች። ክፉውን መስማት አትፈልግም።

ናትናኤል ዝም ብለው አዩዋት። እርሳቸውም አልተናገሩም፣ ጠበቋት።

"ምን ሆነ?" አለች፣ ለዘብ ባለ ድምጽ።

"ምንም አልሆነም። ደህና ነው። "አሉና አዩዋት።

"ታዲያ ለምን ጠየቁኝ?"

"የጠየቅኩሽ ጥሩ ነገር ልነግርሽ ነው። መጀመሪያ ግን እሱን እንደምታውቂው ማረጋገጥ ስለፈለኩ ነው። እሱን እንደምታውቂው ሁኔታሽ ነግሮኛል። ግን ለአንቺ እጅግ ጠቃሚ የሆነውን ነገር ከመንገሬ በፊት፣ ከእርሱ ጋር ምን ዓይነት ግንኙነት እንዳላችሁ ብትነግሪኝ ደስ ይለኛል።"

"ምንም ግንኙነት የለኝም።" አለች እንደመቆጣት ብላ።

ትንሽ ደንገጥ አሉ፣ ዶክተር። "ምን ዓይነት ግንኙነት እንደነበራችሁ ብዬ ጥያቄዬን ባስተካክልስ?"

አልመለሰችላቸውም።

ዝምታ ሰፈነ።

ዶክተር በቀጥታ ወደ ጉዳዩ መግባቱ ጥሩ መስሎ ታያቸው። ጥያቄዎችን ከማንሳት ይልቅ፣ ለማሳወቅ የሚፈልጉትን ነገር ሁሉ

ተናግረው መሄዱን መረጡ። "ግሩም ተረፈ፣ የኤድስ ቫይረስ ተሸካሚ ሆኖ ተገኝቶ ነበር። ወደ ኤድስ በሽተኛነት የሚያሸጋግሩ ምልክቶች እየታዩበት እንደነበረ የጤንነት ማኅደሩ አሳውቆኛል። ይሁንና ግሩም አሁን ፍጹም ጤነኛ ሆኖ ተገኝቷል። ጤንነቱ ሊመለስ የቻለው አቶ ምስጋናው የሚባሉ በሽሮ ሜዳ አካባቢ የሚኖሩ የባህል ሀኪም ባደረጉለት የህክምና ርዳታ መሆኑን አረጋግጫለሁ። እና፣ የእኚህ ሰው ህክምና ግሩምን በመፈወስ ብቻ መወሰን እንደሌለበት አምኛለሁ። መድሀኒታቸው በዘመናዊ ዘዴ ምርምር ተደርጎበት ለመላው የዓለም ህሙማን መፈወሻ እንዲሆን፣ ከአቶ ምስጋናው ጋር ተመካክረንበታል። ከዚያ በፊት ግን፣ አሁን በአለበት ዘዴ እንድትታከሚና ጤነኛ እንድትሆኚ ፈልጌ ነው ወደ እርሳቸው ጋ እንድትሄጂ ልነግርሽ የመጣሁት።"

ሽታዬ ልታምን አልቻለችም። የምትናገረው ጠፍቷት ፍዝዝ ብላ አየቻቸው።

"ምነው?"

"አይ ምንም። እውነት ስላልመሰለኝ ነው።"

"እውነቴን ነው። በግሩም ተረፈ ላይ ያደረግነው ጥናት ከዚህ ቀደም የበሽታው ሰለባ እንደነበረ፣ አሁን ደግሞ ጤነኛ እንደሆነ አሳውቆናል።" ሲሉ ዋሹ።

"የት ነው ሀኪሙ የሚገኙት?"

"ሽሮ ሜዳ። ትንሽ ከፍ ይላል ብቻ። ግን እዚያ አካባቢ ሆነሽ፣ የአቶ ምስጋናው ቤት የት እንደሆነ ከጠየቅሽ ሰዎች ይነግሩሻል። እኔም ቢሆን፣ አካባቢው ድረስ ላደርስሽ እችላለሁ–ቤታቸው ውስጥ ባልገባም።"

"በጣም ደስ ይለኛል። በጣም ነው የማመሰግንዎ። አሁን ለምን አይወስዱኝም?" አለች ሽታዬ ፣ ቸኩላ።

"አይ አሁን መሽቷል። ቤቴ በጊዜ መግባት አለብኝ። እኔንም የሚጠብቁኝ ህሙማን አሉ። ቶሎ መሄድ አለብኝ።"ጥቂት አሰቡ፣ ዶክተር። "አሁን እንሂድና ቤቴን ላሳይሽ። ለነገ ቀጠሮ እንያዝና እንገናኝ።" አሉ ዶክተር። ሽታዬን ቤታቸው ወስደው ለምርመራ እንዲሆን ደሟን ለመውሰድ ፈልገዋል።

አብሮ የመሄዱን ጉዳይ ለመቃወም አሰበች። ጥርጣሬ ገባት። ይሁንና፣ ከዶክተር ሁኔታ ምንም የሚያስፈራ ነገር አልታይ አላት።



'ምን እንዳያደርጉኝ ነው? ለየትኛው ረጅም ዕድሜዬ ነው የምሰጋው?'

"እንሂድ አሉ?" ዶክተሩ።

"አዎ።"

ጥቂት ደቂቃዎች ከተጓዙ በኋላ ፣ ግቢውን አስከፍተው ገቡ። ብዙ ህሙማን በመኖሪያ ቤታቸው ግቢ ውስጥ ካሉ አግዳሚ ወንበሮች ላይ ተቀምጠው ሲጠብቋቸው ነበር።
ከመኪናቸው ወረዱና ሽታዬን እየመሩ፣ ወደ ክሊኒካቸው ገቡ። ኮታቸውን አወለቁና በካፖርት ማንጠልጠያው ላይ ሰቀሉ። ነጩን የሥራ ካፖርት ደረቡ። ሽታዬ ዶክተሩ የሚያደርጉትን ከማየት ሌላ ያደረገችው አልነበረም።

"ሽታዬ ፣ አንድ ነገር አስቤያለሁ። አቶ ምስጋናው ሀኪም ቤት ከመሄድሽ በፊት፣ ደምሽን በትንሹ ለመውሰድ ፈልጌያለሁ። ጤንነትሽን ለመከታተል ነው። የባህል ሀኪሙ ህክምና ካደረጉልሽ በኋላ ደግሞ እንደገና ወደ እኔ ትመጪና ምርመራ አደርግልሻለሁ። ጤንነትሽን መመለሱን እነግርሻለሁ ከተወሰነ ቀናት በኋላ። ገባሽ? "
የላስቲክ ጓንት ካደረጉ በኋላ ፣ መርፌአቸውን አሹለው ቀረቧት። በአንድ እጃቸው አንድ ክንዷን ደገፍ አደረጉና፣ እጅጌሽን ወደ ላይ ሳብ አድርጊው።" አሏት።

እንደታዘዘችው አደረገች። ከሥሯ ላይ ደሟን በመርፌ ስበው የሚፈልጉትን ያህል ከወሰዱ በኋላ አልኮል በጠጣ ጥጥ አሸት አሸት አደረጉ። "እጅሽን ትንሽ እጠፊውና ቆይ።" አሉ። የወሰዱትን ደም አንድ ትንሽ ብልቃጥ ውስጥ እየጨመሩ፣ "ነገ አሥር ሰዓት ላይ ትመጪና አብረን እንሄዳለን። አሁን ንግሥት፣ የኔ ልጅ፣ ቤትሽ አድርሳሽ ትመለሳለች፤" አሉ።

"እሺ እመጣለሁ።"

"ቤቱ አይጠፋሽም፣ አይደል?" አሉ እያዩዋት። "አይ፣ አያሳስትም። ድል ገበያ ብዬ ከሚክሲኮ አደባባይ መሳፈር እችላለሁ።"

"ጥሩ።" አሉና ከክሊኒካቸው ወጡ። ከጥቂት ቆይታ በኋላ ፣ ከንግሥት ጋር ተመልሰው ገቡ።"

"ንግሥቴ፣ ተዋወቂያት። "

"ንግሥት ናትናኤል።" አለችና እጇን ዘረጋችላት። ረጅም ፣ ቢጫ፣ የሌሊት ልብስ ለብሳለች።

"ቤቷ አድርሽያትና ነይ።" በማለት፣ የመኪናቸውን ቁልፍ ከተሰቀለው ኮታቸው ውስጥ አውጥተው ሰጧት።

"እሺ።" አለች ንግሥት።

ሽታዬ ከተቀመጠችበት ተነሳችና ወደ በሩ ተጠጋች። ግን ከመውጣቷ በፊት ዶክተርን ልትጠይቃቸው የምትፈልገው ነገር እንዳለ አወቀች። "ዶክተር ደሚ በየጊዜው ሲወሰድ ጉዳት ላይ አይጥለኝም?" ስትል ጠየቀች።

"ይሂ እኮ በጣም ትንሽ ነው። አሁን ከወሰድኩት በላይ አልወስድም። አይዞሽ አታስቢ። አንቺን የሚጎዳ ምንም ነገር አይደረግም።" አሉ በማጽናናት።

"አሁን ብቻ አይደለም። ከዚህ በፊትም ደሚ ተወስዷል።" አለች ሽታዬ።

"ማን ወሰደ? ለምን?" አሉ ዶክተር ጥቂት ኮስተር ብለው።

"ለማስመርመር ብሎ።"

"ምን ያህል፣ ብዙ ነው?"

"እይ አሁን ከወሰዱት እንኳ አይበልጥም።"

"እይ፣ ብዙ አይደለም። አትስጊ። ደም ለጋሾች ከዚህ በላይ ነው እኮ የሚሰጡት።" ሲሉ አጽናኗት። ወዲያው በመቀጠል፣" የት ሀኪም ቤት ነው ደምሽን የወሰዱት?" አሉ።

"ሀኪም ቤት አይደለም። አንድ ጎረቤቴ ነው መድሀኒት ያላቸው ሰው ስላገኘሁ አንቺ ከመሄድሽ በፊት ደምሽን ልውሰድና ይመርምሩት ብሎ ነው የወሰደው። እርሶም እንዲሁ ሲወስዱ ለእዚህ ለተባለው ሀኪም የሚሰጡ መስሎኝ ነበር።" አለች።

ዶክተር፣ ሽታዬ በተናገረችው ነገር ስሚታቸው ነቃ አለ። "ምንድን ነው ያልሽው? መድሀኒት አላቸው የተባሉ ሰው አገኘሁ ያለ ሰው አለ ነው ያልሽው?"

"አዎ።"

"ማን ነው እሱ? የት?" ሲሉ ጥያቄዎቻቸውን አከታተሉ።

ገብሩ ከዚህ በፊት ያጫወታትን ነገረቻቸው።

በጥሞና ካዳመጧት በኋላ ፣ "ከዚህ ሰው ጋር ብታስተዋውቂኝ እወዳለሁ።" አሉ።

"እሺ። እነግረዋለሁ።"



"ደምሽን ዝም ብለሽ መስጠት የለብሽም። ከጥንቃቄ ጉድለት የተነሳ ሌላ ጤነኛ ሰው ሊበክል ይችላል። ስለዚህ ትልቅ ጥንቃቄ አድርጊ።" አሉ ዶክተር።

በልዩ ልዩ መጽሔቶች፣ በውጭው ዓለም አንዳንድ የኤድስ ቫይረስ በሽታ ተጠቂዎች ሌላውን ለመበከል ስለአደረጓቸው ሙከራዎችና ጥፋት ተጽፈው አንብበዋል። ይህንን ነገሯት።

ንግሥት ከክሊኒኩ ወጥታ፣ የመኪናውን ሞተር አስነስታ፣ ሽታዬን መጠበቅ ከጀመረች ጥቂት ደቂቃዎች ተቆጥረዋል። ትዕግስቷ አልቆ ከመኪናው ወጥታ ልትጣራ በሩን ስትከፍት ሽታዬ መጣች። መኪናዋም ከግቢው ወጣች።

ከዚያ በኋላ ያለውን ማስታወስ አስፈላጊ ሆና አላገኘችውም፣ ሽታዬ። አካባቢዋን መቃኘት ጀመረች። የምስጋናው ታካሚዎች ቁጥር እየጨመረ ሄዷል። ምን ያህል ዝነኛ መሆናቸውን ይናገራል።

"ሽታዬ ጋሻቸው!" ሲል ተጣራ፣ የሀኪም ቤቱ አስተናባሪ።

"አቤት!" አለችና ቶሎ ቶሎ እየተራመደች ህክምና ወደሚወሰድበት ክፍል ገባች። ሸበቶ ሰውዬ አየች። ነጭ ካፖርት ቢጤ ለብሰዋል። ክፍሉ መጠነኛ ስፋት አለው። የሱቅ መደርደሪያ የመሰሉ እንጨቶች፣ ግርግዳ ታከከው ቆመዋል። በርከት ያሉ ጣሳዎች ተደርድረዋል።

አቶ ምስጋናው ወደ ሽታዬ ጠጋ አሉና፣ "ምንሽን ነው የሚያምሽ?" ሲሉ ጠየቁ።

"በአሁኑ ሰዓት ምንም ዓይነት ህመም አይሰማኝም። ግን ሆስፒታል ሄጄ ተመርምሬ ነበር። የኤድስ ህዋስ በደምሽ ውስጥ አለ ብለው ነገሩኝ። ይህንኑ ህዋስ የሚያጠፋ መድሀኒት እንዳሎት በማወቅ ነው ወደ እዚህ የመጣሁት።" አለች።

ስሚታቸው ትንሽ ቆንጠጥ አለና፣ "ማን ነው ወደ እኔ የላከሽ?" ሲሉ ጠየቁ።

ዶክተር ናትናኤል ያሏት ትዝ አላት። እርሳቸው እንደላኳት መናገር እንደሌለባት አስጠንቅቀዋታል። "ግሩም ነው የላከኝ። ከዚህ በፊት እርሶ ጋ መጥቶ እንደዳነ ነግሮኝ ነው የመጣሁት።" አለች።

"አሀ! ከግሩም ጋር ትተዋወቃላችሁ?"

"አዎ። ፍቅረኛዬ ነው።" አለች። ነበር ማለቱን ለምን እንደጠላቸው አልታወቃትም።

"አሀ! .... ጥሩ ። ትድኛለሽ። አይዞሽ! አላህ የሰጠኝ መድሀኒት አለ።" አሉና ወደ ተደረደሩት ቆርቆሮዎች ፊታቸውን አዞሩ።

ከአንደኛው ቆርቆሮ ውስጥ፣ ከማይካ በተሠራ ማንኪያ ዱቄት ነገር ሰፈሩና ስኒ ውስጥ ጨመሩ። ከሌላ ቆርቆሮ ውስጥ ደግሞ እንደ ጨው ነጣ ያለ ዱቄት ወስደው አከሉበት። በውሀ በጠበጡና ሰጧት። "ጨልጭው።"

ጠጣችው። ፊቷን አጨፈገገችው።

"አልኮል ነገር እንዳትጠጪ። በርበሬና ጨው የበዛበት ነገር እንዳትበይ።"

"እሺ። እስከመቼ ይሻለኛል?" ስትል ጠየቀች፣ እጅግ ጓጉታ።

"በዚህ ሳምንት ውስጥ ትድኛለሽ። አይዞሽ አታስቢ። ግሩምን ያሻለ መድሀኒት አንቺንም በጥቂት ቀናት ውስጥ ይፈውስሻል።"

"እሺ። ምን ያህል ልክፈል?" ስትል ጠየቀች።

"አምስት ብር ብቻ።"

'አምስት ብር ብቻ!' የሚል የመደነቅ ስሜት በግንባሯ ላይ ተነበበ። ለዚህ ታላቅ መድሀኒታቸው፣ የሰውን ልጅ ከሞት መንጋጋ ውስጥ መንጭቆ ለሚያወጣ መድሀኒታቸው፣ አንዲት አምስት ብር!

"ምነው? በዛ?" አሉ፣ አለመናገሯን ሲያዩ።

"አይ አልበዛም።" ከቦርሳዋ አወጣችና ሰጠቻቸው። "አመሰግናለሁ።" ብላ ወጣች። ወደ ሸሮ ሜዳ የሚያወርደውን ቀጭን መንገድ በፍጥነት ተራመደችው። የዶክተር ናትናኤል መኪና አጠገብ ስትደርስ፣ እርሳቸውን አጣቻቸው። ወዲያው ከአንድ ሱቅ በር ላይ ሆነው ሲጋራ ሲለኩሱ አየች።

ፈጠን እያሉ በመራመድ ወደ እርሷ ቀረቡና፣ "አገኘሻቸው?"

"አዎ።"

"መድሀኒት ሰጡሽ? "

"አዎ።"

የመኪናቸውን በር ከፍተው ገቡ። ለርሷ ሌላውን በር ከፈቱላት። ገባች። የመኪናዋን ሞተር አስነሱና ጉዞ ጀመሩ። "ምን ዓይነት መድሀኒት ሰጡሽ?"

"የሚጠጣ።"

"ምርመራ አደረጉልሽ?"

"ምንም ምርመራ አላደረጉም። ምኔን እንደሚያመኝ ጠየቁኝ። አሁን ምንም ህመም እንደሌለብኝ ገለጽኩላቸው። የኤድስ ህዋስ እንዳለብኝ ነገርኳቸው። ከዚያ በኋላ ለግሩም የሰጠሁት



መድሀኒት ነው ብለው፣ ሁለት ዓይነት መድሀኒቶች በጥብጠው ሰጡኝ።"

"ሌላስ ምን አሉሽ ?"

"መጠጥ እንዳልጠጣ፣ ጨውና በርበሬ የበዛበት ምግብ እንዳልበላ አስጠነቀቁኝ።"

"ማን አሳየሽ ብለው አልጠየቁሽም?"

"ጠይቀውኛል። ግሩም እንዳሳየኝ ነገርኳቸው።"

"ጥሩ። እስከመቼ ድረስ እንደምትድኚ አልነገሩሽም?"

"በዚህ ሳምንት ውስጥ እንደምድን ነው የነገሩኝ።"

"ጥሩ። አሁን እቤት እንሂድና ትንሽ ቆይታ ካደረግሽ በኋላ፣ ምርመራ አደርግልሻለሁ። ደም፣ ሽንት ፣ ሠገራና አክታ ትሰጪኝና ጥናት አደርጋለሁ። እሺ?"

"እሺ።"

"ለምን መሰለሽ ... የእኚህ ሰውዬ መድሀኒት እውነት የሚፈውስ ከሆነ፣ በግቢያቸው ብቻ መወሰን የለበትም። መላው የዓለምን ህዝብ መጥቀም አለበት። ሰውዬውንና አገራችንን ታዋቂ ማድረግ ፈልጊያለሁ። ያንን ለማድረግ፣ ፀሙያዬ የምስክርነት ቃል መስጠት አለብኝ። የምስክርነት ቃል ከመስጠቴ በፊት ግን፣ መረጃዎች መሰብሰብ አለብኝ።" አሉ።

መኪናቸውን ከንፍ ያላት አስመሰሏት። ጥናታቸውን ለመጀመር ቸኩለዋል።

## 29

ተጣጥባ፣ በጣም የምትወዳቸውን ልብሶች ለባብሳ፣ ተፈጥሮ የሰጠቻትን ውበት በሰው ሠራሽ ማጋጌጫዎች አጉልታው፣ ከቤት የምትወጣበትን ደቂቃ በናፍቆት እየጠበቀች ነው።

ሳሎን ግርግዳ ላይ ቋንጠልጥሎ ከሚታየው ሰዓት ላይ ዓይኖቿን ወረወረች። በቀጠሮው ሰዓትና ቦታ ለመድረስ ከቤት መውጣት ያለባት ጊዜ በሠላሳ ደቂቃዎች የሚሠፈር ነው። በጣም ረዝሞ ታያት። በእጇ ላይ ያለው ሰዓት አሳጥሮ ይነግራት ይመስል አየችው። ያው ነው። ደቂቃዎቹ እስኪያልፉ ድረስ በሶፋው ላይ ተቀመጠች። ግን አልሆነላትም። ሰዓቱን እንደገና ተመለከተችው። የደቂቃ ቆጣሪው እንደ ኤሊ ይንፏቀቃል።

'ለምን መንገድ አልጀምርም? ደግሞ እርሱ ከመድረሱ በፊት እኔ ደርሼ ስጠብቀው ይኩራራ ይሆናል። ለወንድ ልጅ ይቺ ይቺ ጥሩ አይደለችም። ግን እኮ፣ ዳንኤል እንደሌሎች ወንዶች ዓይነት አይደለም። እንደ እነሱ ተመጻዳቂ አይደለም።' ብላ በሀሳቧ ከተናገረች በኋላ፣ ለመሄድ ተነሳችና መልሳ ተወችው። 'ትንሽ ኮራ ማለት—አለብኝ።' አለች አሁንም በልቧ፣ የቀድሞውን ሀሳብ ተቃርና።

ወዲያው ደግሞ፣ እነዚህን ደቂቃዎች በትዕግስት ለማሳለፍ ለምን እንዳልቻለች ገረማት። እነዚህን ደቂቃዎች ብቻ ሳይሆን፣ በአንድ ቀጠሮ ከዳንኤል ጋር ከተገናኘች በኋላ በሌላ ቀጠሮ እስከታገኘው ድረስ ያለው ጊዜ የምዕተ ዓመት ያህል እየረዘመባት መምጣቱ አሁን ትዝ አላት። 'ወይኔ እምላኬ! ፍቅር ሊይዘኝ ነው እንዴ?'

ከዳንኤል ጋር ፍቅር እንደጀማመራት ይህ ትኩሳዋ ሳያሳውቃት አላለፈም። ይሁንና፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ ይህ ሁኔታ መከሰቱ በጣም ነው ያስገረማት።

"እንዴት በአጭር ጊዜ ውስጥ?" አለች ለራሷ እንደመናገር ብላ።

ለአራት ዓመታት ያህል ከመጀመሪያ ፍቅረኛዋ፣ ከመላኩ፣ ጋር አብረው ሳሉ ያልተሰማትን ስሜት አሁን ማዳመጧ አስደነቃት።

'መላኩን አልወደውም ነበር ማለት ነው? የመጀመሪያ ፍቅር ጠንካራ ነው የሚባለው ውሸት ነውን? ወይስ ከዚህ በፊት ፍቅር ይዞኝ አያውቅም ነበር ማለት ነው? እንዴት ላይዘኝ ቻለ? አራት ዓመታት ሙሉ ከርሱ ጋር ለምን ቆየሁ? መላኩ ያልሰጠኝ፣ ግን ዳንኤል ያሟላልኝ ወይም እንዳፈቅረው ያደረገኝ ነገር ምንድነው? መላኩ በአራት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ደብቆኝ ፣ ዳንኤል ሁለት ወራት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ያሳየኝ ነገር አለ? ወይስ ዳንኤል ሀብታም፣ ቆንጆና የተማረ ስለሆነ ይሆን? አይሆንም። መላኩም እኮ የሚበቃው ያህል ብር አለው። ሀብታም ከሚባሉ ነጋዴዎች አንዱ ነው። ኮሌጅ ባለመግባቱ ይሆን? አይደለም። ለእኔ የሚያንስ አልነበረም። ታዲያ በምን ይሆን ዳንኤልን ያፈቀርኩት? ግን እኮ መላኩ የማልወዳቸው ባህሪያት ነበሩት። ስለራሱና ስለቤተሰቦቹ ሀብት በመመጻደቅ ያወራል። እራሱን ከፍ ከፍ አድርጎ ያያል። በገንዘብ ሀይል ልቤን ለማሸነፍ ይሞክራል። ሳያስፈልግ ከፍተኛ ዋጋ የሚያወጡ ስጦታዎች ይሰጠኛል። ሲጋብዘኝ እንኳ ትላልቅ ሆቴሎች ውስጥ ነበር። ለገንዘቡ ስል



እንድወደው ስላደረገ ይሆን አላውቅም ደስ አይሉኝም ነበር እንዲህ ያሉ ድርጊቶቹ። ዳንኤልስ? አሀ! እሱ ቁጥብ ነው። ቢናገርም አይቸኩልም። ስለራሱ ብዙም አውርቶልኝ አያውቅም። ምክሩ በጣም ደስ ይለኛል። ቀልዶቹን በሚያስፈልግ ጊዜና በሚያስፈልጉ ቦታዎች ስለሚያቀርባቸው ለዛ አላቸው። አነጋገሩ ይማርካል። ሁልጊዜ ሲያወራ ቢውል ቢያድር አይሰለቸኝም። ለዚህ ይሆን?' እያለች በሀሳቧ ከራሷ ጋር ተነጋገረች።

ከሁለት ቀናት በፊት ከዳንኤል ጋር በራስ ሆቴል ውስጥ ያሳለፉት ምሽት ከፊቷ ድቅን አለ። በዚያች ውብ በምትላት ምሽት ካደረጓቸው ቃለ ምልልሶች መሀከል፣ ጥቂቱ በጆሮዎቿ ውስጥ እንደገና መጥለቅ ጀመሩ።

"ንግሥት ፣ ያኔ ታይፕ በማድረግ ከተባበርሽኝ ቀን በፊት ታውቂኝ ነበር?"

"አላውቅህም።"

"ብዙ ጊዜ መሥሪያ ቤታችሁ እመጣ ነበር። ሁልጊዜ ወደ ውጭ አገር ከመሄዴ በፊት፣ ወደ እናንተ መሥሪያ ቤት ብቅ እላለሁ። ሥራ አስኪያጁ ቢሮ ስገባ አይሽ ነበር።"

"እኔ ግን አይቼህ አላውቅም። ብዙ ባለጉዳዮች ስለሚመላለሱ፣ ሰዎችን ለይቶ ማስታወሱ ይቸግራል። "

"እሱስ ልክ ነሽ። " ብሎ ዝም አለ። "ለመጀመሪያ ጊዜ የመጣሁ ቀን ነው ያየሁሽ። " ሲል ቀጠለና ሠርቶ አያት።

"ከመቼ ጀምሮ ነው ወደ እኛ ቢሮ መምጣት የጀመርከው?"

"ጊዜው እንኳ ቆይቷል። ግን በመሀሉ አልፎ አልፎ ውጭ አገር እየቆየሁ ስለነበር የምመጣው አጋጣሚውን አላገኘሁም ነበር።"

"ለምን?"

ለጥቂት ሴኮንዶች ያህል ዝም አለ። "እንደምወድሽ ታውቂያለሽ ?"

መልስ ሳትሰጥ ጥቂቿ ቆየችና ፣ "አዎ።" አለች ቀና ሳትል።

"ይህንኑ ለመግለጽ ነበር አጋጣሚ ያላገኘሁት።"

ነገሩን በልባቸው ከተነጋገሩ ቆይተዋል።

"ግን በምን ልትወደኝ ቻልክ?"

ትንሽ ፈገግ ብሎ፣ "መጀመሪያ በውበትሽ፣ ቀጥሎ ደግሞ በትህትናሽና ባደረግሽልኝ ውለታ።"

ከዚህ በኋላ ያደረጓቸውን ቃለ ምልልሶች ትታ፣ ከቤቷ በር ድረስ ሲሸኛት ከመለያየታቸው በፊት መኪና ውስጥ ሳሉ፣ በከንፈሮቿ ላይ ያረፉት ከንፈሮቹ ያሳደሩባትን ስሜት አስታወሰች። በቃላት ልትገልፀው የማትችለው የደስታ ጊዜ!

ሰዓቷን አየች። አሥራ አምስት ደቂቃዎች ቀርተዋል– ዳንኤልን ልታየው። እየተጣደፈች ወጣች። ታክሲ ያዘች። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ሜክሲኮ አደባባይ ደረሰችና ወረደች። ለባለታክሲው ሂሳቡን ከፈለችና ሜክሲኮ ባር አጠገብ ቆሞ ከሚጠብቃት ከዳንኤል መኪና ውስጥ ገባች።

ጉንጮቻቸውን ለሰላምታ ካገጣጠሙ በኋላ፣ ከንፈሮቿን በከንፈሮቹ ጨረፍ አደረጋቸው– ዳንኤል።

"ቆየሁ እንዴ?" አለች፣ ከላይ የደረበችውን ጃኬት እያወለቀች።

"አምስት ደቂቃ ብቻ ዘግይተሻል።" አለ፣ በዓይኖቿ እየገረመማት።

ጠይም ፊቷ ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ማራኪ ሆኗል። ነጭ ጥርሷ ብቻ ሳይሆን፣ ዓይኖቿ ላይ ያለው ኩል ፊቷ ላይ ይታይ የነበረውን ውበት ጉልበት ሰጥቶታል። ረጅም ፀጉሯን ከፋፍላ በግራና በቀኝ በኩል አምጥታ ደረቷ ላይ አስተኝታዋለች። ጡቶቿን ወጠር አድርጎ ከያዘው ነጭ ሹራቧ ጋር ሲታይ ጥቁረቱ ጎልቶ ይታያል።

እሷም ሳታውቀው አየችው። ዛሬም እንደሌላው ጊዜ ሽክ ብሏል። ጥቁር ሰማያዊ ሱፍ፣ ከውሀ ሰማያዊ ሸሚዝ ጋር ለብሷል። በጥቁር ሰማያዊ ሸሚዝ ላይ ቡላማ ስትሪፕ ያለው ክራቫት አስሯል። የልብሱ ቀለም የቀይ ዳማ ፊቱን አጉልቶታል። ጥቅጥቅ ያለ ሪዙ ዛሬም ይማርካል።

የእሱም የእሷም ዓይኖች ከማድነቅ ጎዳና ሲመለሱ መሀል ላይ ተጋጩ።

ለጥቂት ሴኮንዶች ያህል ዝምታ ሰፈነ።

"ዛሬ ወዴት እንሂድ?" ሲል ጠየቃት።

"እኔ እንጃ። እኔ ምን አውቃለሁ?" አለች።

"እዚሁ ራስ ምግብ ቤት እንግባ?"

"እይ ወደ ሌላ ቦታ እንሂድ።"

"እሺ ።" አለና የመኪናዋን ሞተር አስነሳ።" ቦሌ ካራማራ.... እንሂድ?"

"እዚያ ይሻላል።" አለች።



"ይሻላል። ከዚህ ሌላ ያሰብሽው ጥሩ ቦታ አለ?"

"የለም። የትም ይሁን፣ ሁለታችን ብቻ የምንሆንበትን ቦታ እመርጣለሁ።" አለች።

ሳታስበው የተናገረችው ትንሽ አስደነገጣት። ይሁንና ፣ በልቧ ያሰበችውን ዳንኤል የገባው አይመስልም።

"ጥሩ። ሐራምቤ ሆቴል እንሂድ።" አለና የመኪናዋን ማርሽ አስገባ። ጎማዎቿ መሽከርከር ጀመሩ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ሆቴሉ ደርሰው ገቡ። ለእነሱ አመቺ መስሎ ያገኙትን ቦታ መርጠው ተቀመጡ።

አሳላፊው መጣ።

"ምን ይምጣልሽ?" ሲል ዳንኤል ጠየቃት።

"ለስላሳ።"

"ቢራ ጠጪ።"

"ውሀ ጠምቶኛል። ለስላሳ ልጠጣ።"

"ቢራም ለውሀ ጥም ይሆናል። ሁለት ቢራ አምጣልን።"

አሳላፊው ሄደ።

"እኔ እኮ አልኮል ነገር ባልጠጣ ይሻለኛል። ሁልጊዜ ሳልወድ ነው የምጠጣው።" አለች።

"ምን ያደርግሻል? ከቢራ ሌላ አትጠጪ። እሱንም ሳይበዛ። ሁለት ሶስት ምንም አያደርግሽም።"

"ቢራ መጥፎ ነው። ቦርጭ ያመጣል ስለሚባል እሱን እጠላለሁ።"

"ታዲያ ቦርጭ ብታወጪ ምን አለበት?"

"ኧረ ባክህ! ታየኝ ስድበለበል!"

"እኔ የምወደው ድብልብል ያለች ሴት ነው።"

"ታዲያ እኔ ጋ ምን አመጣህ ?"

"ይህንኑ ዓይቼ ነዋ።"

"ምኑን?"

"አይደለሁም እንዳይትይኝ።"

"ምን? ድብልብል?"

"አዎ።"

ሳቀች።

"ሴቶች ስትባሉ መቼም ለውበታችሁ ትጨነቃላችሁ።"

"ወንድስ ቢሆን? እሱ በጣም የሚጨነቁ።"

"በጣም ጥቂት ናቸው።"

"በጣም ብዙ ናችሁ። አንተ አትጨነቅም?"

አሳላፊው መጣ። ቢራ የያዙትን ጠርሙሶች ከፍቶ ብርጭቆዎች ውስጥ በግማሽ ቀዳና ሄደ።

"እኔ ምልህ፣ ቢራ ስትጠጣ የሚያምህ ተወህ?"

"አዎ። አሁን በጣም ደህና ነኝ። እድሜ ለአባትሽ! እርሳቸው ናቸው ያዳኑኝ። ይገርምሻል፣ ብዙ ሀኪሞች አይተውኝ ማስታገሻ ከመስጠት ሌላ ያደረጉልኝ ነገር አልነበረም። እሳቸው ያዘዙልኝን መድሀኒት ከወሰድኩ በኋላ ደህና ነኝ። በርበሬ እንኳ መድፈር ጀምሬአለሁ።"

"ተመሳሳይ ችግር ያለባቸውን ብዙ ሰዎች አድኗል። እንዲያውም በኢትዮጵያ የዚህ በሽታ መንስኤ፣ መከላከያውና ህክምናው በሚል የሠራው አንድ ጥናት አለ። ምናልባት ለዚህ ይሆናል ህክምናው የሚሳካለት።"

"ምርምር ያደርጋሉ ማለት ነው?"

"አዎ።"

"ጊዜው እንዴት ይበቃቸዋል? በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ያክማሉ፣ በህክምና ኮሌጁ ያስተምራሉ፣ እቤታቸው በሚገኘው የግል ክሊኒካቸው ውስጥ ደግሞ ህክምና ይሰጣሉ። እንደሚገባኝ ከሆነ የምርምርና የጥናት ሥራ ሰፋ ያለ ጊዜ ይፈልጋል።" አለ ዳንኤል።

"እውነትህን ነው። አባቴ ግን የተለየ ሰው ነው። ያለውን ጊዜ ሁሉ የሚሰዋው ለእነዚህ ጉዳዮች ብቻ ነው። ከዚህ ውጭ የሚያደርጋቸው ወይም የሚያከናውናቸው ምንም ተግባራት የሉም። ከሰዎች ጋር ማለት፣ ከእኔ፣ ከሞግዚቴ፣ ሾፌሩና ከዘበኛው፣ ከተገኘ ሌላ ግንኙነት አያደርግም። ከእኛ ጋርም ቢሆን የሚጫወተው ወይም የሚነጋገረው ቁርስ፣ ምሳና ራት በሚበላባቸው ጊዜያት ብቻ ነው። ቅዳሜና እሁድ እንዲሁም በየዓመቱ የሚመጡ የህዝብ በዓላት ለርሱ የሚያርፍባቸው፣ የሚዝናናባቸው ቀናት ሳይሆኑ የምርምር ሥራዎቹን የሚያከናውንባቸው ጊዜያት ናቸው። በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሲኖር በጣም ብዙ ዓመታት አሳልፏል። ህፃን ሳለሁ የሚወዳት እናቴ በሞት ከተለየችው በኋላ ፣ ህይወቱን ሙሉ የሰጠው ለህክምና ጥበብ መበልፀግና ማበብ ነው።" አለችና ቢራዋን ተጎነጨች።

"ምን ያህል ጊዜ ይሆናል እናትሽ ከሞቱ?" አለ ዳንኤል በተመስጦ ሲያዳምጣት ከቆየ በኋላ ።

"አሥራ ዘጠኝ ዓመታት አልፈዋል።"



"በጣም ረጅም ጊዜ ነው።"

"አዎ።"

"በዚህ ጊዜ ውስጥ ካደረጋቸው ምርምሮች ለፍሬ የበቁ የሉም?"

"ብዙ ጥናቶችና ምርምሮች አካሂዷል። ግማሾቹ ደግሞ ከመንግሥት የሚሰጠው የገንዘብ ዕርዳታ አነስተኛ በመሆኑ፣ በጅምር የቀሩ ናቸው። ያም ሆኖ ግን ፣ የኔ አባት ጎበዝ ነው። ይፍጨረጨራል። የሚያገኛትን ገንዘብ፣ ከደረጃው በታች እየኖረ፣ ለዚሁ ሥራ ነው የሚያውለው። ይሄን ያህል የሠራውም ቤተሰቦቹ ትተውለት ያለፉት ገንዘብ ስለነበረው ነው።"

"በጣም ጠንካራ ሰው ናቸው።" ሲል ተናገረ።

"በጣም፣ በጣም ጎበዝ ነው። አሁን ደግሞ የኤድስ በሽታ መድሀኒት ለማግኘት ምርምር ጀምሯል። ግን በነገርኩህ ምክንያት የሚሆንለት አይመስለኝም።"

"ብዙ ገንዘብ ያስፈልጋል ማለት ነው፣ ለሥራቸው? ሳስበው ከክሊኒካቸው የሚያገኙት ገቢ ራሱ ብዙ ይመስለኛል።"

"በቂ አይደለም። በየጊዜው አባቴ ሲነግረኝ እንደምረዳው ፦ የህክምና ምርምር ለማድረግ ቀላል አይደለም። በሀገር ውስጥ ብቻ የሚያልቅ አይደለም። ሀገር ውስጥና ውጭ ሀገር ካሉ የሙያ ጓደኞቹ ጋር መነጋገርና ሀሳብ መለዋወጥ ያስፈልጋል። አንዳንድ ጊዜ ምርምርን ለማድረግ የሚመረጡ ቦታዎች ይኖራሉ። በቦታው ተገኝቶ ሥራውን ለማከናወን ፣ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ገንዘብ ያስፈልጋል።"

"አዎ፣ እሱስ ልክ ነሽ። "

"እና በዚህ ምክንያት ነው መሰለኝ፣ መበሳጨት ጀምሯል። በተለይ ከትርብ ጊዜ ወዲህ፣ ፍጹም ይበሳጫል። ከእራሱ ጋርም የሚጋጭ ይመስለኛል። ከእኔ ጋርም መጨቃጨቅ ከጀመረ ሰንበት ብሏል። እውነቱን ነው። ህይወቱን ሙሉ የሰዋለት ሥራ ፍሬ አልባ ሲሆን ያበሳጫል። በዚህ ላይ ሀሳቡን የምትካፈልለት ሚስት የለውም።" አለች፣ ትንሽ እንደመከፋት ብላ። ትንሽ ቆየችና ለምን ይህንን ሁሉ እንደተናገረች ማሰብ ጀመረች። መናገር እንዳልነበረባትና እንደነበረባት ለማወቅ ራሷን ጠየቀች። ይሁንና መልስ እስከታገኝ ድረስ ዳንኤል አልጠበቃትም። አናገራት።

"እኔ እምልሽ ንግሥትዬ፣..." አለና ንግግሩን አቋረጠ።

'ንግሥትዬ' ብሎ ለመጀመሪያ ጊዜ በፍቅር አቆላምጦ ስለጠራት፣ አንድ የሆነ ስሜት ተሰማት - በደስታ። ጆሮዎቿን አቅንታ ሰጠችው።

"አባትሽን እኔ ልረዳቸው የምችል ይመስለኛል።"

"እንዴት?"

"ዶክተር ናትናኤል በትክክል በገንዘብ እጦት ብቻ ሥራዎቻቸውን ለፍሬ ያላበቁ ከሆነ፣ እኔ እረዳቸዋለሁ። የምርምራቸው ውጤት በሥራ ላይ ሲውል ይመልሱልኛል።" አለ ዳንኤል። "የውጭ ሀገር ገንዘብ ማግኘት ለእኔ ከባድ ስላልሆነ፣ በዚህም ልረዳቸው እችላለሁ። በተለይ ለኤድስ በሽታ ማጥፊያ ምርምር ከጀመሩ በፈለጉት መንገድ ልረዳቸው እችላለሁ።"

"እንዲህ ቀላል ገንዘብ የሚፈልግ ይመስልሃል?"

"የፈለገው ያህል ይሁን፣ ምርምሩ የሚሳካላቸው ከሆነ እረዳቸዋለሁ።"

"በጣም ጥሩ ነው። ግን ብዙ ገንዘብ ማውጣቱ ለአንተ የሚቸግር ይመስለኛል። አንዳንድ ጊዜ እኮ ብዙ የተለፋበት ምርምር ፍሬ አልባ ይሆናል።"

"አውቃለሁ። ግን ውጤቱ በደንብ ሳይታያቸው ብዙ ገንዘብ የሚፈጅ ሥራ ውስጥ ራሳቸውን የሚያስገቡ አይመስለኝም። የሆና ሆኖ፣ ከእርሳቸው ጋር የምንነጋገርበትን መንገድ ትፈጥሪልኛለሽ።"

"በጣም ደስ ይለኛል።" አለች።

ንግሥት በትክክል ደስ ብሏታል። የአባቷን ድካም ለውጤት አብቅቶ ደስታ የሚሰጣቸው ሰው በማግኘቷ ልቧ ፈንድቋል። አባቷ ለእርሷ ፊታቸውን ያጠቆሩበትን መንስዔ ከአንድ እራሳቸው ጋር የሚያጋጭን ምክንያት መንግሎ የሚጥል ሰው በማግኘቷ እጅግ በጣም ደስ ብሏታል።

"ንግሥት፣ አንድ ያልነገርኩሽ ነገር አለ። የኔ ገንዘብ ይባክናል ብለሽ አስበሽ ወይም ሰግተሽ ከሆነ አትጨነቂ። ውጭ ሀገር፣ አሚሪካ ውስጥ፣ አንድ የአባቴ እህት አለች። ባሏ አሚሪካዊ ነው። አንድ ትልቅ ካምፓኒ አለው። እሷም የራሷ የሆነ ትልቅ ሱቅ አላት። መጀመሪያ ለአጎቴ መንቀሳቀሻ ገንዘብ ሰጥታው የአስመጪና ላኪ ድርጅት አቋቋመ። አሁን እኔ የማስተዳድረው ድርጅት የርሱ ነበር። በኋላ ነው ለአባቴ የሰጠው። መንፈሳዊ ሆኖ ፊቱን ወደ ቤተክርስቲያን ከማዞሩ በፊት እርሱ ነበር ንግዱን የሚያካሂደው። ከጊዜ በኋላ ነው ሥራውን ለእኔ የተወልኝ። እና፣ ለምርምሩ የሚፈልጉትን ያህል



ገንዘብ ከእኔ ባያገኙም፣ ከአክስቴ ማግኘት ይችላሉ። እሷ ሀብታም ናት። በዚህ ላይ ሰው መርዳት ትወዳለች። ለሀገራቸው ትልቅ ነገር ሠርተው ለመሞት ከሚፈልጉት ሰዎች አንዷ ናት።" አለና ቢራውን ጨለጠው።

"እሰቲ እሺ። ሁኔታውን እነግረውና የምትገናኙበትን ሁኔታ አመቻቻለሁ።" አለች።

"ጥሩ።" ብሎ ዝም አለ። ከትንሽ ዝምታ በኋላ ፣ "ቢራውን ጠጪ እንጂ።" አለ። አሳላፊውን ጠራና ሌላ ቢራ እንዲመጣ አዘዘ።

ለጥቂት ሴኮንዶች ያህል ዝምታ ሰፈነ።

"ምን ታስባለህ?" አለች በሀሳብ ጭልጥ ማለቱን አይታ።

"ፍቅር ልታሲዥኝ ነው መሰለኝ።"

ሳትናገር ጥቂት ቆየችና፣ "ታዲያ ምን አለበት?"

"ምንም የለበትም። ጥሩ ነው። ግን ከሁለታችንም በኩል ሲሆን ነዋ ጥሩ የሚሆነው። ላቭ ኢዝ ስዊት እንሊ ሁዌን ሼርድ ይላሉ ፈረንጆች።"

ዝም አለች።

"አይመስልሽም?"

"ይመስለኛል።"

"እና?"

"እና ምን?"

"እኔ እወድሻለሁ።"

ዝም አለች አሁንም።

ጥቂት ሴኮንዶች አለፉ።

"ታፍሪኛለሽ መሰለኝ። አንድ ያልነገርኩሽ ነገር አለ።"

"ምን?" አለች ፈገግ ብላ።

"ግልጽ ሴት በጣም እወዳለሁ። ስሜቷን የማትደብቅ ሴት በጣም ነው የምወደው። ምን አልባት፣ ይህንን አትወጂው ይሆናል። በአጠቃላይ ሴቶች በግልጽ ወደድኩሽ የሚሏቸውን ወንዶች የሚወዱ አይመስለኝም።"

"ሁሉም ላይሆኑ ይችላሉ። እኔ ለምሳሌ ወደድኩሽ የሚለኝ ወንድ እወዳለሁ።" አለች ፈገግ ብላ።

"እዎ። አንቺ እንዲህ መባልን እንደምትወጂ ሁሉ እኔም የሚለኝ ሰው እወዳለሁ። በርግጥ ከልብ መሆን አለበት።"

አሳላፊው ቢራውን ይዞ መጣና አስቀምጦ ሄደ።

"ከእኔ ጋር ከመተዋወቅህ በፊት፣ ከሴቶች ጋር ስለነበረህ ግንኙነት ንገረኝ እስኪ?" አለች በድንገት።

ያልጠበቀውን ጥያቄ በማንሳቷ ግር አለው። መልስ ሳይሰጣት የቀረበለትን የጠርሙስ ቢራ ብርጭቆ ውስጥ ቀዳና፣" ጥያቄሽ ግልጽ አይደለም። ከሴቶች ጋር ብዙ ዓይነት ግንኙነቶች ነበሩኝ። የትኛውን ነው ማወቅ የምትፈልጊው?" ሲል ጠየቃት።

"ከዚህ በፊት ስለነበረህ ፍቅረኛ ንገረኝ።"

"ከዚህ በፊት ፍቅረኛ አልነበረኝም።"

"አትዋሽ።"

"አልዋሽሁም። ፍቅረኛ የምለው በሀሳብ ተግባብተን ፍቅር ያስያዘችኝን ሴት ነው። እስካሁን ፍቅር ያስያዘችኝ ሴት የለችም። እርግጥ ከእኔ ጋር ለተወሰነ ጊዜ ሆያ ሆዬ የሚሉ አልጠፉም። እንደነዚህ ዓይነት ሴቶች እንደ አረም የትም ይገኛሉ። ችግሩ ግን የፍቅር ፍሬ ያላትን ሴት ማግኘት ስለሆነ እስከዛሬ አላጋጠመኝም። ስለዚህ ፍቅር አልነበረኝም ማለቱን እመርጣለሁ።"

"እነዚህ የምትላቸው ሴቶች ፍቅር እንዴት ሊሰጡህ አልቻሉም?"

"ፍቅርን ፈልገው አይደለም የሚቀርቡት። ለጊዜው ብቻ አብሮ ለመሆን፣ ለመዝናናት ለመጨፈር ብቻ ነው። ያለ ፍቅር መዝናናት፣ መጨፈር ትርጉም እንደሌለው አያውቁም። ወንድን የሚቀርቡት ለፍትወተ ሥጋ ርካታና ለገንዘብ ነው። ፍቅር ከሌለው ወሲባዊ ግንኙነት ሜካኒካል ነው። በጣም ተራ ነገር ይሆናል። በፍቅር ካልታገዘ ትርጉም የለውም።"

"እሱስ ወንዶችም የሚቀርቡት ለሴክስ ብቻ ነው።"

"አዎ። ሴቶች ብቻ አይደሉም። ምናልባት ሁለቱም ጾታዎች ማፍቀርን ፈርተው ሳይሆን መተማመን ጠፍቶ ነው። አንዱ በፍቅር ተጠምዶ ሲጃጃል ሌላው አሿፊ ይሆናል። ይህ እንዳይሆን ተብሎ ይሁን በሌላ፣ ወንዱም ልብ አይሰጥም፣ ሴቷም ልብ አትሰጥም። እንዳውም ፍቅር እንዳይዛቸው እያሉ በድራቢ ሌላ ሰው ይይዛሉ። በተለይ ሴቶች፣ ቋሚና ተለዋጭ ወይም ደግሞ ግንድና ቅርንጫፍ የምትሏቸው ፍቅረኞች አሉዋችሁ። አንዱ ፈቱን ሲያዞር ሌላውን ለመጠጋት። ግን ለምን አንዱን አናጠብቅም? እዚያም እዚያም ስንል በህይወታችን ውስጥ ፍቅር ሊሰጠን የሚችለውን ደስታ እናጣለን። ፍቅር በህይወታችን ላይ አንድ ትልቅ ነገር ነው። እና ንግሥት፣



የቀረብኳቸው ሴቶች በሙሉ ፍቅር ሳይሆን ገላቸውን ነው የሰጡኝ።" አለና ቢራውን ተጎነጨ። "ብዙ አወራሁ መሰለኝ። እንዳላሰለቸሽ።"

"ዳንኤል፣ ችግር አለ። አንድ ሴት ሙሉ ለሙሉ ልቧን የሰጠችው ወንድ ሲሸሻት፣ ለተወሰኑ ቀናትም ቢሆን የሚደርስባትን የመንፈስ ችግር አቅለህ ነው ያየኸው። ወዶኛል ብላ ግልጽ ሆና ስትቀርብለት የሚሸሻት ሆኖ ታገኘዋለች። ያፈቀሩት ሲከዳ ማየት በጣም ከባድ አደጋ ነው።"

"ጥሩ አስተሳሰብ አይመስለኝም። እኔ በበኩሌ ትወደኛለች ብዬ ገምቼ ሙሉ ልቤን ሰጥቼያት ፍቅር ከያዘኝ በኋላ ዞር ብትል፣ የሥነ ልቦናና የሞራል ችግር ሊገጥመኝ ይችላል አልፈራም። ለፍቅር ስል የሚመጣውን እቀበላለሁ። ትዝታ ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም።" አለና እንደገና ቢራውን ተጎነጨ። "ያሰለቸሁሽ መሰለኝ።" አለ በመቀጠል።

"አልሰለቸኸኝም። በጣም የሚጥም ጨዋታ ነው።" አለች፣ እርሷም የተሞላ ብርጭቆዋን ከፍ አድርጋ።

ለጥቂት ሴኮንዶች ያህል ዝምታ ሰፈነ።

"በእኔ በኩል ግን፣ አንድ ሴት ወንዱን ሳትፈልግ አልጋ ላይ የምትወጣ አይመስለኝም። ሳታፈቅረው ወይም ሳትፈቅደው ከእርሱ ጋር ጊዜዋን የምታጠፋ ሴት አትኖርም።"

"ተሳስተሻል። ወንድን ተከትላ መኝታ ቤት የገባች ሴት ሁሉ ፍቅር ስላላት አይደለም። በሥጋ አንድ ሊሆኑ ቢሞክሩም፣ በመንፈስ አንድ አይሆኑም። ልቦቻቸውና አእምሮዎቻቸው እንደ ሥጋዊ አካሎቻቸው ካልተዋሀዱ ፍቅር የለም።" ንግግሩን ገታ በማድረግ ትንሽ እንደማሰብ አለና፣ "አንድ ጊዜ አንድ ሽማግሌ በመሰል ጨዋታ መሀል ያሉኝን ልንገርሽ። በዛሬ ጊዜ አመንዝራነት ተስፋፍቷል። ባልና ሚስት በግብረ ሥጋ ግንኙነት ላይ በአካል ሁለት ቢሆኑም፣ በመንፈስ አራት ናቸው። እሱም እሷም በልባቸው ሌሎችን እያስታወሱ ነው...' ብለዋል። እውነታቸውን ነው። በዚያች ደቂቃ፣ በዚያች ክፍል ውስጥ የአካላዊ ውህደት ቢኖራቸውም፣ የመንፈስና የሀሳብ አንድነት የላቸውም። ስለዚህም ነው ወሲብ በእነዚህ ሰዎች ዘንድ ሜካኒካል የሚሆነው። የምልሽ ግልጽ ነው?"

"አዎ ።" ብላ ዝም አለች። ተከራክራ ማሳመን አልቻለችም።

"ምን ያህል ሴቶችን አይተሀል?"

"ከአራት የማያንሱ።"

"ታዲያ ከእነዚህ ውስጥ አንተ የምትፈልገውን አላገኘህም?"

"አላገኘሁም። ማፍቀር አስቸጋሪ መሆኑን አስረድተውኛል። " አለና ቢራውን ተጎነጨ።

"ላምን አልቻልኩም።"

"እንዴት ልታምኚ አልቻልሽም?"

"ማለቴ፣ ሴቶች የምንፈልጋቸውን ነገሮች ሁሉ ያሟላህ ይመስለኛል።" አለች። ከተናገረች በኋላ ግን፣ አባባሏ እንዳያስገምታት ሳትሰጋ አልቀረችም።

"ከእነዚህ ውስጥ ሁለቱ ይለያሉ። ሌሎቹ ቋሚ ወይም ተለዋጭ ብለው ቢይዙኝም፣ ሌሎቹ ሁለቱ ደግሞ ስለጋብቻ ሳያነሱልኝ አላለፉም። በተገናኘንባቸው የመጀመሪያ ቀናት ከእኔ ጋር በጋብቻ ለመኖር ማሰባቸውን በቀጥታ ሳይሆን፣ በተዘዋዋሪ መንገድ ጠቆሙኝ። ይህ ደግሞ እንድጠላቸው አደረገኝ።"

"ለምን?"

"ስለጋብቻ ለመወሰን ከፍቅረኛሽ ጋር ብዙ አብረሽ መቆየት አለብሽ። አንድ የምትሆኑባቸው ነገሮች መኖር አለባቸው። ትዳር አንዱን ጾታ ለመጥቀም የሚደረግ ጉድኝት መሆን የለበትም። ትልቅ ቁምነገር መቅደም አለበት። ፍቅር። መግባባት፣ መተሳሰብና መዋሀድ። ሁለቱም ጾታዎች እንደ አንድ ሰው መሆን አለባቸው። ትዳር በሁለቱ ጾታዎች መዋሀድ የሚመጣ ጥያቄ መሆን አለበት። በሁለቱም ሰዎች እኩል መነሳት የሚገባው ርዕስ መሆን ነው ያለበት። ገና በተያዩ ደቂቃ ስለትዳር ማሰቡ ጥሩ አይሆንም። ደግሞ ትዳር ቀደም ብሎ ስለታቀደ አይመሰረትም፣ ቀደም ተብሎ ስላልታሰበም ሳይመሠረት አይቀርም። ትዳር ሁለቱ ጾታዎች በሚያደርጉት የፍቅር ግንኙነት ቆይታ ውስጥ ጊዜ የሚያነሳው ጥያቄ ነው። አይመስልሽም ንግሥትዬ?"

"ልክ ነህ። "

"አሁን እያወቅሽኝ የመጣሽ ይመስለኛል።"

"እንዴት?"

"ማንኛውም ሰው የሚያደርጋቸውና የሚናገራቸው ነገሮች ስለእርሱ ብዙ ይናገራሉ። ታዲያ በእነዚህ ስለእኔ ማወቅ ይቻላል።"

"በመጠኑ ሊታወቅ ይቻላል። ሙሉ በሙሉ ማወቅ አስቸጋሪ ነው። አዳማጭ ወይም ተመልካች ይኖራል ብለው ባላሰቡበት ጊዜ በሚያደርጓቸው ድርጊቶች ሰዎችን እናውቃቸው ይሆናል። በተረፈ አዳማጭና ተመልካች ፈልገው በሚያደርጓቸውና በሚናገሯቸው ነገሮች ማወቅ አስቸጋሪ ነው። ብዙ ጊዜ አዳማጭና ተመልካች ሲኖራቸው፣ ትክክለኛ ማንነታቸውን ይደብቃሉ። የሚያደርጉትም ሆነ



የሚናገሩት አሳሳች ጭምብል ለብሰው ነው። እዚህ ላይ አንተን አላወቅሁህም ማለቴ አይደለም። ከሚገባው በላይ አውቄሀለሁ። እንዲህ የተናገርኩት ግን አጠቃላይ የሆነውን ሁኔታ ለማንሳት ብዬ ነው።"

"ያልሽው ትክክል ነው። ግን እነዚህ ሰዎች ሁልጊዜ ጭምብል ለብሰው አይቆዩም። አንዳንድ ጊዜ አውልቀው ሲገኙ የሚያደርጓቸውና የሚናገሯቸው ብዙ ይገልጿአቸዋል። ዋናው ያንን ጊዜ መጠበቅ ነው።"

ፈገግ አለች። "ያ ጊዜ መቼ ነው? አንድ ልጅ 'ማን ቢካምስ ናቹራል ሁዌን ሂ ድሪንክስ፣ ሰው ሲጠጣ ተፈጥሮአዊ ባህሪውን ይይዛል፣' ይል ነበር። እና ሲጠጣ እንዳትለኝ?"

"አንዱ መንገድ እሱ ሊሆን ይችላል። ትክክል ነው። ሆድ ያባውን ብቅል ያወጣዋል ይባል የለ በእኛ አገርስ?"

"እኔ እንጃ፣ ሰውን ማወቅ አስቸጋሪ ነው። ፍጹም የሆነ ሰው ማግኘት አስቸጋሪ ነው።" አለች እንደመተከዝ ብላ።

"እሱማ ፍጹም የሆነ ሰው በዚህች ዓለም ላይ ማግኘት አትችይም። ሰው በተፈጥሮው ፍጹም አይደለም። ለፍጹምነት የቀረበ ሰው ይኖራል እንጂ፣ ፍጹም የሆነ ሰው የለም።" አለ ዳንኤል።

ሀሳቡን ተቀበለችው።

ለጥቂት ሴኮንዶች ያህል ዝምታ ሰፈነ።

ዳንኤል አተኩሮ ካያት በኋላ፣ "ተጫወቺ እንጂ።" አለ።

"እሺ ። እስካሁን ካጋጠሙህ ሴቶች ጋር ስታስተያየኝ ስለእኔ ምን ትላለህ? እውነቱን ንገረኝ?።"

"አንቺ የፍቅር ምንጭ ነሽ። "

"ያየሀቸው ሴቶች ያላቸው ፍላጎት ዓይነት እንደሌለኝ በምን አወቅህ?"

"ልቢ ውስጥ ባለው ፍቅርሽ። "አለና እጇን ትከሻዋ ላይ ጣል አደረገው።" ትወጂኛለሽ? "

"በጣም።" አለችና አንገቷን ሰበር አደረገች።

## 30

ገና ቤት ከመግባቱ አባቱና እናቱ እሱን ሊያነጋግሩ የፈለጉበትን ምክንያት አላጣውም። ቀደም ሲል ሲያደርገውም፣ አንድ ቀን ነገሩ እንደሚወጣ ያውቃል። ምንም ዓይነት ድንጋጤ አይታይበትም። በዚህች ዓለም የሚፈራውም፣ የሚጓጓለትም ምንም

ነገር የለም። እናቱ ላይ ወጥቶ የሚጨፍርበትም አልኮል፣ በህይወት ዘመኑ እንደ እግዚአብሄር ይፈራቸው የነበሩትን አባቱን በንቀት ሰሚት፣ 'ለምንድን ነው እኔን የሚፈልገኝ ይሂ ሽማግሌ?' እንዲል አደፋፍሮታል።

ከተጎዳኝ ክፍሉ ወጣና በዋናው መኖሪያ ቤት ውስጥ ወደሚገኘው ዕንግዳ መቀበያ ክፍል የሚያስገባውን በር ከፍቶ ገባ። በሰፊው ሳሎን ውስጥ፣ በግርግዳው ቅርጽ ከተሠራው ሶፋ ላይ እናትና አባቱ ተቀምጠዋል። እናቱ ጠይም ናቸው። ዕድሚያቸው አርባ ስምንት ይሆናል። ውሀ ሰማያዊ ቀለም ያለው የሌሊት ልብስ ለብሰዋል። ከጎናቸው የተቀመጡት ባለቤታቸውም የሌሊት ልብስ ለብሰዋል። ዕድሚያቸው ሀምሳ አራት ይደርሳል። ብስል ቀይ ናቸው። ፊታቸው የፈላ ውሀ ውስጥ እንደገባ ቲማቲም መሸብሸብ ጀምሯል። ዓይኖቻቸው የተቆጡ መሆናቸውን ይናገራሉ።

"እንደምን ዋላችሁ?" አለ ተሰማ በጥንቃቄ፣ መስከሩ እንዳይታወቅበት።

"እንደምን ዋልክ?" አሉ እናትየው።

አባትየው ምንም አልተናገሩም።

ተሰማ ቀስ እያለ ቀረበና ከሶፋው ላይ ከእናትና ከአባቱ ፊት ለፊት ተቀመጠ።

ጥቂት ሴኮንዶች በዝምታ አለፉ።

"ለመሆኑ ዛሬ እንዴት ቤት ገባህ? "አሉ ፣ እንደዋዛ አባትየው።

"ሁልጊዜ እገባለሁ እኮ።" አለ፣ ተሰማ ለስለስ ባለ ድምጽ።

"መግባትማ ትገባለህ። አታድርበትም እንጂ። ለወጉ ፊትህን አሳይተህ ክፍልህ ትገባለህ። እኛ ስንተኛልህ አጥር ዘለህ እየወጣህ፣ የትም ስትዘፍን፣ ስትጨፍር ታድራለህ!"

"ውሸት ነው፣ አባባ።"

"ዝም በል! ዝም በል! ቀጣፊ! ሌባ! አንተን መች አጣሁህ!" አሉ በቁጣ። ንዴት ቀይ ፊታቸውን በርበሬ አስመሰለው። ሲበሳጩ የግንባራቸው ሥር ያብጣል። "አንተ ምን ታደርግ? በአንተ ላይ ጥፋት የለ፣ ያበላሸችህ እናትህ! እኔ ስቆጣጠርህ ፣ እርሷ አጨማለቀችህ! ብትቆጣጠርህ ኖሮ፣ 'የትዋልክ? የት አመሸህ? የት አደርክ?' ብትልህ ኖሮ መድሀኒት በሌለው በሽታ ተለክፈህ፣ እኛንም በሀሳብ አትገድለንም ነበር! የትም ስትልከሰከስ ያፈስከውን በሽታ



ደብቀህ፣ አፍንህ መያዝ ሲገባህ፣ በየመሸታ ቤቱ እያደርክ ሕዝብን ትበክላለህ! ይህ ተገቢ ነው? ይህ ጥሩ ሥራ ነው? እኔ ከሞትኩ በርዶ አይብቀል ሥራህ ጥሩ ነው? አምላክ ይወደዋል ይህንን ሥራ?"

"እኔ አምላክ የምትለውን አላውቅም! አምላክ የለኝም!"

"እንዴት ባክህ ?"

"አምላክ ቢኖር ኖሮ፣ ከሰዎች ሁሉ መርጦ፣ በእንዲህ ያለ በሽታ እኔን እያሰቃየኝም ነበር! አምላክ የምትሉት አለ ካላችሁ ደግሞ፣ እሱ ጨክና፣ ፍጥረታትን በዚህ በሽታ እንዲሰቃዩ ማድረጉ ሳያስወቅሰው፣ የኔ ለምን ያስወቅሳል?" አለ በድፍረት።

"እንዴት ባክህ?" ሲሉ ጥያቄያቸውን ደገሙ፣ የተናገረውን ባለማመን።

መልስ አልሰጠም። ዝም አለ፣ ተሰማ።

"ተናገር እንጂ!"

"አባባ ተወኝ ባክህ። አሁን ከእኔ ጋር መነጋገር አይጠቅምም። እኔ የሞትኩ ሰው ነኝ። መሞቴን ያረጋገጥኩ ሙት ነኝ። ሬሳ መውቀስ ምን ያደርግልሀል? ተወኝ።" አለ ተሰማ፣ እጅግ ሀዘን በተቀላቀለበት ስሜት።

እናትየውን የልጃቸው ሀዘን ደቆሳቸው። ዓይኖቻቸው ዕንባ አቀረሩ። ልባቸው ደማ።

አባትየው ትንሽ መለስ ለማለት ሞከሩ። ግን አልቻሉም። "ስማ፣ የቤተሰባችን ስም እንዳይጠፋ፣ የሰው መጠቋቆሚያ እንዳንሆን ነው ጥረቴ። የአንተና የቤተሰቡ ምስጢር፣ ገበናችን፣ እንዳይወጣ ነው ድካሚ። ለዚህም ነው ከህፃንነቱ አግኝቼው ያሳደግሁትን አፈወርቅን በሕይወት እንዳይኖር ያደረግነው። ባልወልደውም ልጄ ነበር። ግን ለአንተ ያለኝን ፍቅር ለመግለጽ ስል አደረግሁት። ካደረግሁትም በኋላ በፀፀት ካራ የምተፈተፈው ለአንተ ባለኝ ፍቅርና ለአንተ ስም ስል ነው!" አሉ በቁጣ።

ተሰማ ግንፍል አለበት። "ለሞተ ሰው ስም ምን ያደርግለታል? እኔ ምንም የምፈራው ነገር የለኝም! ለእኔ አታስብ!"

"እንዴት ነው ይሄ ደደብ የሚለው?" አሉ አባትየው፣ ባለቤታቸውን እንደመጠየቅ ብለው።

የተሰማ ንዴት እየናረ ሄደ። "ደግሞ ለእኔ ሳይሆን፣ ለራስህ ክብር፣ ዝናና ስም ስትል ነው ሁሉን ነገር ያደረከው! እኔ እንዴ መሞቴ የታወቀ ነው።"

"ምን አልክ አንተ እበት? ምን አልክ አንተ እከካም?" አሉ አባትየው ከመቀመጫቸው ተነስተው።

"ታዲያ ለእኔ አዝነህ ነው አባባ? ለእኔ አስበህ ያደረከው ምንም ነገር የለም!" አለ ተሰማ በንዴት። የጠጣው አልኮል በንዴት ያንተከትከው ጀመር።

"እንዲህ ሆነ ነገሩ? አንተ እንዲህ ትለኛ? አንተ ደደብ! ጥሩ ነው! በጣም ጥሩ ነው! እንዲህ ልክ ልኬን ንገረኝ!" አሉ እየተቅበጠበጡ።

የተሰማ አባት እንደዛሬ ተናደው አያውቁም። ይሁንና እንደሌላው ጊዜ ቱግ ብለው ርምጃ ለመውሰድ አልቻሉም። በውስጣቸው አንድ ስጋት ስሚታቸውን እንቆ ይዞታል። ልጃቸውን በከዘራ ፈረካክሰው እንጀታቸውን ማራስ አቅቷቸው አይደለም። ልጃቸው ማመጹን ካወቁ ውለው አድረዋል። ተስፋ መቁረጡንና ለቋሚ ግድ የሌለው መሆኑን ከተረዱ ሰንብተዋል። ከአንዳንድ አነጋገሩ እንደተገነዘቡት የአፈወርቅ መገደል አስቆጭቶታል። እርሱን መምታት ወይም ማጥቃት ተሸፍኖ የቆየውን የአፈወርቅን ሞት ምስጢር ማውጣት መስሎ ታይቷቸዋል።

ለጥቂት ሴከንዶች ያህል በቤቱ ውስጥ ዝምታ ነገሠ።

"እሺ ጥሩ። ይሁን። እሱን እግዜር ያውቀዋል!" ብለው ጥቂት ዝም አሉ፣ የተሰማ አባት። "መኪናዋ ያስገኘችውን ገንዘብ ለምንድን ነው በወቅቱ ገቢ ያላደረከው?" ሲሉ ረጋ ብለው ጠየቁት።

ተሰማ ዝም አለ።

ለወትሮው የጭነት መኪናቸው የሠራችውን ገንዘብ ከሾፌሩ እየተቀበለ፣ በአባትየው ስም በተከፈተው የባንክ ሂሳብ እንዲገባ ያደርግ ነበር። የጭነት መኪናዋ በተሰማ ስም የተገዛች ቢሆንም፣ ገቢዋ በአባትየው ስም ነው ባንክ የሚገባው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን፣ ተሰማ ባንክ ማስገባት መተውን ደርሰውበታል።

"አትናገርም እንዴ?" ሲሉ፣ አሁንም ረጋ ብለው ጠየቁት።

"መኪናዋን ሸጪያታለሁ።" አለ በድፍረት።



ባልና ሚስቱ በድንጋጤ እንደሀውልት ደርቀው ቀሩ። ተሰማ የተናገረው እውነት መሆኑንና አለመሆኑን ለማወቅ ዓይናቻቸውን አሳረፉበት።

"ምንድ ነው ያልከው ተሰማ?" አሉ እናትየው። ለመጀመሪያ ጊዜ መናገራቸው ነበር።

"መኪናዋን ሸጪያታለሁ።"

"ማን አባክ ፈቅዶልህ፣ በማን ትዕዛዝ?" አሉ አባትየው።

"በእኔ ትዕዛዝ!" አለ በድፍረት።

"ምን አባክ አግብቶህ?" አሉ አባትየው ፣ አጠገቡ ደርሰው እያፈጠጡበት።

"መኪናው የእኔ ነው። በለራሴ መኪና ጉዳይ ሌላ ሰው ማማከር አያስፈልገኝም።" አለ አሁንም በንቀት መንፈስ።

"መኪና ከየት አባክ አምጥተህ ነው የገዛኸው? ይሄ ብጣሽም ደሞዝህ ነው የጭነት መኪና የገዛው? እከካም!"

"በስሜ እስካለ ድረስ የኔ መኪና ነው!" አለ በፍጹም ድፍረት።

"ካድከኝና አረፍከው! በማጅራቴ አረድከኝ! ጥሩ ነው! ምን ታደርግ? አሁን እኔ እና አንተ በቃቃናል! የቤቴን መተዳደሪያ ሸጠህ ልጆቼን ለችጋር ሰጠሀቸው! ግድ የለም፣ እግዜር ያውቅላቸዋል። እኔ ምንም ማድረግ አልችልም።" አሉ ቁጣቸው በቀነሰና ተስፋ በቆረጠ ድምፀት። "ጥሩ ሥራ ነው።" አሉና ሶፋው ላይ ተቀመጡ።

በቤቱ ውስጥ ድንጋጤ ያመጣው ያልታሰበ ዝምታ ለጥቂት ደቂቃዎች ያህል ሠፈነ።

እናትየው የባለቤታቸው ንዴት በስሜታቸው ላይ ቢጋባም፣ በልጃቸው ላይ የደረሰው ሀዘን በእሳቸውም አድሮ አይሏል። ልጃቸው በደሙ ውስጥ ኖኤድስ ቫይረስ አለበት ተብሎ ሲነገራቸው አባትና እናት ያዘኑት እኩል ቢሆንም፣ የእናትየው ቀን በጨመረ ቁጥርና ልጃቸውን ባዩት ቁጥር፣ ሀዘናቸው እያደገ ከሰውነት ጎዳና አውጥቷቸዋል። ተሰማ የመጀመሪያ ልጃቸው በመሆኑና በልጅነቱ በገጠመው ህመም ባዩት መከራ እጅግ ይወዱታል። እጅግ ያፈቅሩታል። እሱ ባጠፋው ጥፋት ቤተሰቡ ሊገጥመው የሚችለውን መከራ ለመቀበል ዝግጁ ሆነዋል። በደሙ ውስጥ የሚላወሰው ጠላቱ ከሚያደርስበት የሥጋት ሥቃይ ሌላ ከአባቱ ጋር በሚፈጠረው ጭቅጭቅ የበለጠ እንዲያዝንና እንዲያስብ አልፈለጉም። አሁን ያለው

ጭቅጭቅ እንዲቀር መላ ፈጥረዋል። ርዕሱን በቀጥታ ወደ ሌላ ለማሻገርና በቤቱ ውስጥ ሰላም እንዲፈጠር ተሰማን አንድ ጥያቄ መጠየቅ ፈለጉ።

"ተሰማ ፣..." ሲሉ ተጣሩ ፍጹም በሆነ የእናትነት ፍቅር።

ቀና ብሎ አያቸው።

"በሃምሳ ሰዓት ገደማ ያነጋገሩህ ሰዎች ምንድን ናቸው?" ሲሉ ጠየቁ።

"መርማሪዎች ናቸው።" ሲል ዋሸ፣ አባቱን በማስደንገጥ ለመበቀል ብሎ።

መርማሪዎች የሚለው ቃል ባልና ሚስቱን ክፉኛ አስደነገጠ።

"የምን መርማሪ?" ሲሉ በአንድ ጊዜ፣ ሁለቱም ሳይታወቃቸው ጠየቁ።

"የወንጀል መርማሪ።" አለ ተሰማ።

"ምን ጠየቁህ?" አሉ እናትየው።

"አፈወርቅን ማን እንደገደለው ለማወቅ ነው የመጡት።"

"አፈወርቅን ሰው እንደገደለው በምን አወቁ?" አሉ አባትየው።

"ምን አውቃለሁ?"

ባልና ሚስቱ ጭንቅላቶቻቸውን በእጆቻቸው ይዘው አቀረቀሩ።

"እና ምን መለስክ?" አሉ አባትየው ፍጹም ረጋ ብለው።

"የኤድስ ሰለባ መሆኔን ሰዎች እንደነገሯቸው ገልጸውልኛ፣ እውነት መሆኑን ከእኔ ለማረጋገጥ እንደመጡ አስረዱኝ። እውነት መሆኑን ነገርኳቸው።"

አባትየው አፍጠው አዩት።

"አፈወርቅን ሰው ነው የገደለው ይባላል። እውነት ነው ወይ ብለው ጠየቁኝ። አዎ አልኳቸው። የአንተ አባት ስም ማን ነው ሲሉ ጠየቁኝ። ገበየሁ ሁሉቃ። ስል መለስኩኝ። አባትህ አፈወርቅን በመርዝ ከገደሉ በኋላ፣ ራሱን የሰቀለ አስመስለው አስከሬኑን አንጠለጠሉት ይባላል። እውነት ነው ሲሉ ጠየቁኝ። "ብሎ ዝም አለ።

"ምን መለስክ ታዲያ?" ሲሉ ባልና ሚስቱ ጠየቁ።

መልስ አልሰጠም። ዝም አለ።

ገበየሁ አንድ ነገር ብረር ብረር ብሎ ሹክ እንዳላቸው ሁሉ ፈንጠር ብለው ተነሱና ወደ መኝታ ክፍላቸው አመሩ። አልቆዩም፣



ወዲያው ተመልሰው መጡ። ሁለት እጆቻቸውን ወደኋላ ያጣመሩ መስለው ወደ ልጃቸው ቀረቡ።

"እና ምንድን ነው የመለስክላቸው?" አሉ ያልተናደዱ በሚያስመስል ድምጽ።

"እውነት ነው ብዬ ነገርኳቸው።" አለ አሁንም፣ በፍጹም ድፍረትና ትዕቢት።

"እኔና እናትህ ለአንተ ስንል፣ በሰው ዘንድ መጠቋቆሚያ እንዳትሆንና እንዳትሳቀቅ በማዘን ለፈፀምነው ውለታ ገደልከን! በቁማችን ቀበርከን! ለዚህ ውለታ ምላሹ ሞት መሆን አለበት! አንተን ገድሎ እጅን ለፖሊስ መስጠት ያፀድቃል!" አሉና ፍጹም አውሬ በሆነ ስሜት ውስጥ ሆነው፣ ከጀርባቸው በደበቁት እጃቸው ይዘውት የነበረውን ሽጉጥ፣ በተሰማ ግንባር ላይ አነጣጠሩት።

የተሰማ እናት በድንጋጤ ዘልለው የባላቸውን እጅ ጥርቅም አድርገው ለመያዝ ሞከሩ። ግን ዘግይተዋል። ገበየሁ በተሰማ ላይ የለቀቋቸው ሁለት ጥይቶች ግንባሩን የተነደለ ጣሳ አስመሰሉት። በተሰማ አካል ላይ ተደፍተው የእናትነት ፍቅራቸውን በመሪር ለቅሶ ገለጹ።

ገበየሁ ወደ ስልኩ ሮጡ። ሁለት ጥሪዎች አደረጉ። አንዱን ለቴሌኮሙኒኬሽን መሥሪያ ቤት፣ ሁለተኛውን ቴሌ በሰጣቸው ቁጥር ለፖሊስ ጣቢያ።

ከተሰማ ግንባር የሚፈልቀው ደም የቤቱን ወለል የደም ጅረት አስመሰለው። ተሰማ ግን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አንቀላፍቷል።

## 31

ዶክተር ናትናኤል፣ በግል ክሊኒካቸው ውስጥ ሆነው፣ ከፊት ለፊታቸው ካለው የጽሕፈት ጠረጴዛ ላይ ያሉትን ወረቀቶች በድጋሚ በከፍተኛ ተመስጦ አነበቡና ቀና አሉ። የንባብ መነጽራቸውን አወለቁና የግል ክሊኒካቸው ረዳታቸው የሆነውን ካሣሁንን ተመለከቱ።

ካሣሁን ነጭ ካፖርቱን አልቀየረም። ሥራ ስንጨርስ ላነጋግርህ እፈልጋለሁ ስላሉት ነው የዛሬውን የእሁድ ግማሽ ቀን ህሙማን ከሸኙ በኋላ፣ ከጎናቸው ተቀምጦ የተፈለገበትን ጉዳይ ለመስማት በመጠባበቅ ላይ ያለው። ዶክተር ናትናኤል ሊያነጋግሩት የፈለጉበት ምክንያት ከወትሮው ለየት ያለ መሆኑን ሳይረዳው አልቀረም።

ምክንያቱም፣ ከሚያደርጉት ምርምር ጋር የተገናኘ ቢሆን ኖሮ፣ እንደወትሮው 'ዛሬ እስኪ ስለዚህ ጉዳይ በእከሌ የተጻፈውን ይህንንና ያንን መጽሐፍ አንብበህ አንዳንድ ሀሳብ ይዘህ ና። ዛሬ እስኪ ቤተ ሙከራ ሂድና እነዚህን ነገሮች ፈትሽና ውጤቱን ንገረኝ።' በማለት ይነግሩት ነበር።

ካሣሁን አንድ ነገር ይፈራል። ከእንግዲህ ረዳት እንደማያስፈልጋቸው ወይም ሌላ እንደቀየሩ የሚገልጹ ቃላት ከዶክተሩ አፍ እንዲወጡ አይሻም። በህክምና ትምህርት ያገኘውን እውቀት ከእርሳቸው ጋር አብሮ በመስራት በልምድ ማዳበር ይፈልጋል። በምርምሩም ሆነ በህክምና ሥራ ከእርሳቸው ብዙ ተምሯል። ወደፊትም ብዙ ለመማር ይፈልጋል። በተለይ በምርምር ዓለም ገፍቶበት አንድ እውቅ ኢትዮጵያዊ ሳይንቲስት መሆን ይመኛል።

"ካሱ።" አሉ ጠይም ፊቱን እየተመለከቱ።

ዶክተር ናትናኤል ካሱ እያሉ በማቆላመጥ የሚጠሩት ከጥቂት ዓመታት በፊት በጥቁር አንበሳ የህክምና ኮሌጅ ተማሪያቸው ከነበረ ጊዜ አንስቶ ነው። በችሎታውና በጥረቱ እጅግ ያደንቁት ነበር። እስከዛሬ ካስተማሩዋቸው ተማሪዎች የእርሱን ያህል ድንቅ ጭንቅላት ያለው ተማሪ አላጋጠማቸውም። ካሣሁን ከተመረቀ በኋላ ለጥቂት ዓመታት ክፍለ ሀገር ሰርቷል። ወደ አዲስ አበባ ቅያሪ አግኝቶ ሲመጣ መጀመሪያ ያነጋገራቸው ዶክተር ናትናኤልን ነበር። እሱም ለእርሳቸው በሥራቸውና በትጋታቸው የተነሳ ጥልቅ አክብሮትና ፍቅር አለው። በትርፍ ጊዜው በሚያደርጉት ምርምር ረዳታቸው እንዲሆን ጠይቆአቸው በፈቀዱለት መሠረት ነው የእርሳቸው ተባባሪ ሊሆን የቻለው። በምርምር ሥራቸው ብቻ ሳይሆን፣ በግል ክሊኒካቸው ውስጥ በሚያደርጉት ህክምና ላይም አልፎ አልፎ ረዳታቸው በመሆን ላለፉት ሶስት ዓመታት አብሮ ሠርቷል።

"አቤት!" አለ ካሣሁን አገጩ ላይ በስሱ የወጣ ጺሙን እያፍተለተለ።

"ያ ነገር አልሆነም እኮ።" አሉ።

"የቱ?"

"የዚያች ልጅ ህክምና። ሽታዬ ጋሻቸው የምትባል፣ የኤድስ ቫይረስ ሰለባ ናት ብዬ የነገርኩህ።" አሉ፣ ዶክተር ናትናኤል አዝነው።

ዶክተር ናትናኤል ያዘኑት የምስጋናው መድሀኒት ሽታዬን ባለማዳኑ ብቻ አይደለም። በተገኘው ትንሽ ተስፋ የንግሥት ዕድሜ ሳይራዘም በመቅረቱም ነው። አንድ ሰሞን ያነጫነጫቸው፣



ያበሳጫቸው፣ ከእራሳቸውና ከልጃቸው ጋር ያጋጫቸው የነበረው አባዜ የባህል ሀኪሙ በግሩም ላይ ባገኙት ድል ተሰውሮ ነበር። አሁን ግን እንደገና ብቅ ብሎ ዶክተርን መበጥበጥ ጀምሯል።

"እ የባህል ሀኪሙ የረዷት?"

"አዎ።"

"ታዲያ እንዴት አልሆነም? ወንዱን ልጅ ማነው ስሙ?..."

"ግሩም።"

"አዎ ግሩምን ካዳነ፣ ይቺ ለምን አልዳነችም?"

"በጣም ገርሞኛል።" አሉ ዶክተር።

ለጥቂት ሴኮንዶች በሀሳብ ውስጥ ሆነው ቆዩ።

"ዶክተር፣ ይቅርታ አድርጉልኝና የግሩምን ከዚህ በፊት የኤድስ ቫይረስ ሰለባ መሆን እጠራጠራለሁ።" አለ ካሣሁን።

"በእሱ እንኳ አትጠራጠር። በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ውስጥ ተመርምሮ በትክክል የቫይረሱ ሰለባ መሆኑ በሶስት ዶክተሮች ተረጋግጧል። ዶክተሮቹን አነጋግሬ የቃል ምስክርነታቸውንም ሰጥተውኛል።" ብለው ዝም አሉ። "ግን አንድ የተረዳሁት ነገር አለ። ግሩም ቫይረሱ የተላለፈበት ከሽታዬ ሳይሆን፣ ከእሷ በፊት ካያቸው ሴቶች ከአንዷ ነው። እሱ ነው እሷ ላይ ያስተላለፈው ። ምክንያቱም፣ ከሽታዬ ጋር ከተጎዳኙ ሁለት ዓመታት ብቻ ነው የተቆጠሩት። በሁለት ዓመታት ውስጥ ግሩምን በሽተኛ ሊያደርገው የሚችል አይመስለኝም።"

"እህ፣ እንደዚያ ነው። ታዲያ እርሷ እንዴት ሳትድን ቀረች? ምን አልባት የባህል ሀኪሙ የሰጡት መድሀኒት ለግሩም ከሰጡት የተለየ ይሆናል።"

"አይመስለኝም። ምክንያቱም፣ ሽታዬ በቀጥታ የበሽታዋን ዓይነት ነግራቸዋለች።"

"ህክምና ከወሰደች በኋላ፣ ምርመራ አድርገውላት ነበር። አይደል?"

"አዎ። ህክምና ከወሰደች በኋላ ወዲያው፣ እንዲሁም ህክምናውን ከወሰደች ከአሥራ ሁለት ቀናት በኋላ ማለትም ከትናንት ወዲያ ደሟን ወስጀው ነበር።"

"የእሱ ውጤት እንዴት ነው?"

"የአሁኑ ምርመራ በደሟ ውስጥ ህዋሱ እንዳለ ይናገራል። አለመዳኗን እንረዳለን። ግን ህክምና ከወሰደች በኋላ ባደረኩት ምርመራ አቶ ምስጋናው የሰጧት መድሀኒት ፀረ ቫይረስ ባህሪ ያለው

ይመስላል። እንደ ኤች አይ ቪ ያሉትን የሪአ ቫይረስ ዘሮችን የሚያጠቃ ግን አልመሰለኝም። ምንአልባት ከሌሎች ሰባት የቫይረስ ዓይነቶች ለአንዱ ውጤታማ ሊሆን ይችላል።" አሉ ዶክተር።

"ግሩም ታዲያ እንዴት ሊድን ቻለ?"

"በጣም የገረመኝ እሱ አይደል!"

"ዶክተር፣ የግሩምን በበሽታው መለከፍ እጠራጠራለሁ።"

"አትጠራጠር። ምክንያቱም፣ አንደኛ ሽታዬ ጥሩ ምስክር ናት። እሷ የበሽታው ተጠቂ ናት። ከእርሱ ጋር ወሲባዊ ግንኙነቶችን ማድረጓን ነግራኛለች። ሁለተኛ ራሱ ግሩም የቃል ምስክሩን ሰጥቶኛል። ሶስተኛ በሆስፒታል የተደረገለት ምርመራ ውጤት። እነዚህ ሁሉ አረጋግጠውልኛል።"

"አሁን በትክክል ጤነኛ መሆኑስ ተረጋግጧል?"

"ቫይረሱ በደሙ ውስጥ እንዳለና እንደሌለ የተረጋገጠ አይመስለኝም። እንዳየሁትና ግሩም እንደነገረኝ የኤድስ በሽተኛ የሚያሰኙት ምልክቶች ጠፍተዋል። ለምሳሌ ክብደቱ ጨምሯል። አካሉ የዳበረ ነው።" ብለው ዝም አሉ። ወዲያው በመቀጠል፣ "ይሁንና፣ እንደገና ምርመራ ማድረግ ይኖርብናል።" አሉ።

ትንሽ ዝምታ ነገሠ።

"በትክክል እነዚህ ውጤቶች ታይተው ከሆነ ቀላል ግኝት አይደለም። መድሀኒቱ በስፋት መጠናት አለበት። ግን፣ የባህል ሀኪሙ የተጠቀሙበትን መድሀኒት ምንነት አውቀዋል?"

"በትክክል እንዲህ ነው ብዩ አልለየሁም። ግን ሶስት ዕፅዋትን በመላምት ወስጄ ሙከራ ለማድረግ አስቤያለሁ።"

"የዕፅዋቱ ዓይነት ምን ምን ናቸው?" ሲል ጠየቀ፣ ካሣሁን።

ዶክተር ናትናኤል ለተነሳላቸው ጥያቂ መልስ ከመስጠታቸው በፊት፣ የክሊኒኳ በር ተከፈተና ሸዋዬ በትሪ የቡና ስኒዎችና የቡና ማቅረቢያ ጀበና ይዛ ገባች።

"ቡና አድርሻለሁ።" አለች እያቀራረበችላቸው። ቡናውን ቀድታ ከመውጣቷ በፊት፣ "ዶክተር፣ ሽታዬ የምትባል ልጅ ቀጠሮ አለኝ ትላለች። ትግባ?"

"መጣች?" አሉ፣ ዶክተር።

"አዎ። ኸረ ብዙ ቆየች። እስክትጨርሱ ድረስ ጠብቂ ብያት ነው።" አለች ሸዋዬ።



"እስገቢያት።" አሉና ሸዋዬ መውጣቷን ካዩ በኋላ፣ "ካሱ በኋላ እንቀጥላለን። እስከዚያው ወደ ሌላ ክፍል ሄደህ ብትቆይ።"

ካሣሁን በስኒ የተቀዳለትን ቡና ከነማስቀመጫው ይዞ ወደ ቤተ ሙከራው ሄደ።

ሽታዬ ገባች። ዛሬም እንደወትሮው ሱሪ ለብሳለች። ረጅም ፀጉሯን በሻሽ አፍና አስራዋለች። ቀይ ፊቷ ጉስቁል ያለች አስመስሏታል። የአቶ ምስጋናውን ህክምና ከወሰደች በኋላ፣ እንደገና በዚህች ዓለም ለመኖር በጣም ጓጉታለች። ስለዚህም፣ ዶክተር ናትናኤል የህክምናውን ውጤት እንዲነግሯት በየጊዜው እየደወለች ጨቅጭቃቸዋለች። በህይወት መኖር አለመኖሯን ቶሎ ማወቅ ፈልጋለች።

"እንደምን አደሩ፣ ዶክተር?" አለች።

"ደህና እግዚአብሄር ይመስገን። አንቺ ደህና ነሽ?" አሉ ለስለስ ባለ አነጋገር።

"ደህና ነኝ።"

"ተቀመጪያ።" አሉ።

ሽታዬ ተቀመጠች።

ዶክተሩ ከአጠገባቸው ያለውን ደውል ተጫኑት።

ሸዋዬ ገባች። "አቤት!"

"ለሽታዬ ስኒ አምጪላትና ቡና ትጠጣ። ወይስ ሻይ ይፈላልሽ?" አሉና ሸዋዬንም ሽታዬንም ተራ በተራ አዩ።

"ግዴለም፣ ቡናውን እጠጣለሁ።" አለች ሽታዬ።

ሸዋዬ ስኒ ይዛ መጣችና ቡናውን ቀድታ ለሽታዬ አቀረበችላት።

ሁለቱም ሰዎች ለጥቂት ሴኮንዶች ያህል በየግል የሀሳብ ጎዳና በዝምታ ተጓዙ። ሽታዬ የዶክተርን የምርመራ ውጤት ምን እንደሚሆን ከሁኔታቸው ለማወቅ በመሞከር ፊታቸውን እተኩራ አየች። ዶክተር ናትናኤል ደግሞ እንዲህ ዓይነቱን አስቃቂና ተስፋ የሚያስቆርጥ ዜና ላለመንገር እንዴት እንደሚያመልጡ እያሰላሰሉ ነው። ወደ ህክምና ሙያ ሲገቡ ከፈፀሟቸው ቃለ መሀላዎች አንዱ ትዝ አላቸው።

ቡናቸውን ጠጥተው ከጨረሱ በኋላ ፣ በመፋጠጥ ጥቂት ሴኮንዶች አለፉ።

"ሽታዬ፣ ዛሬ ጠዋት አንድ ወዳጄ አሜሪካ ውስጥ ከሚገኝ አንድ የኤድስ በሽታ ምርምር ማዕከል ስልክ ደወለልኝ። አሜሪካዊ ፕሮፌሰር ነው። እስከዛሬ ድረስ የዓለምን ህዝብ ሲያሰቃይ ለነበረው

በሽታ አዲስና አስተማማኝ የሆነ መድሀኒት ማግኘታቸውን ነገረኝ። በዚህ አጋጣሚ እንኳን ደስ ያለሽ! መድሀኒቱ በቅርቡ በገበያ ላይ እንደሚውል ነግሮኛል። ይህ ጉዳይ ማለት፣ መድሀኒቱ ተሠርቶ ለገበያ ሲቀርብ፣ በዜና ማሠራጫያዎች ይነገራል። ርግጠኛ ነኝ፣ በዓመት ውስጥ፣ እጅግ ቢዘገይ ፣ በሁለት ዓመታት ውስጥ የመድሀኒቱ ተጠቃሚ ሆነሽ እንደምትፈወሺ ። የዚህ በሽታ ጥሩ ባህሪ ጊዜ መስጠቱ ነው። እና ጥሩ ዜና ያሰማሁሽ መሰለኝ።" አሉ ዶክተር።

"የወሰድኩት መድሀኒት አላዳነኝም ማለት ነው?"

ዶክተር የጠበቁት ጥያቄ ቢሆንም፣ ምን እንደሚመልሱ ጨነቃቸው። "አዎ፣ የአቶ ምስጋናው መድሀኒት ውጤት አሳይቷል። ሙሉ ለሙሉ ባያድንሽም፣ የህዋሱን ዕድገት ፍጥነት ሀምሳ በመቶ ቀንሶታል። ይህ ማለት እንግዲህ በአራት በዓምስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ሰውን ያጠፋ የነበረው ሀይሉ ተዳክሟል። ሊገድል የሚችለው ከዛሬ አሥር ዓመታት በኋላ ነው። ይህ ጥሩ ዜና መሆን አለበት።"

ሽታዬ ዶክተር ናትናኤል በመጀመሪያ የነገሯት ዜና ጥርጣሬ ውስጥ ቢከታትም፣ የአሁኑ ግን ትንሽ ተስፋ ሰጣት። 'ከእንግዲህ ወዲያ አሥር ዓመታት መኖር መቻሉ ራሱ ትልቅ ነገር ነው። ከዚያ በኋላ የሚመጣውን እግዜር ያውቃል!' አለች ለራሷ። "በጣም አመሰግናለሁ ዶክተር። በጣም ነው የማመሰግንዎ አለች" ሽታዬ ፣ ከወንበሯ ተነስታ።

"ምንም አይደለም። አይዞሽ! ራስሽን አበርቺ! እንዳልኩሽ አንድ ቀን ትድኚያለሽ። እስከዚያ በትዕግስት መኖር ነው። ደግሞ ስትተኚም ሆነ ስትነሽ ፀልይ። እግዜር ይረዳሻል። ሁልጊዜ ለሰው አስቢ፣ እዘኚ። ሰዎች መከራ ውስጥ እንዳይገቡ የተቻለሽን አድርጊ። እግዜር የልብሽን አይቶ ይረዳሻል። ጥሩ አሳቢ ሁኚ። የደረሰብንን መቀበል እውነቴን ነው ጥሩ ነው። እግዜር ሊክሰን ሲፈልግ ነው የሚጣላን። ፊትሽን ከጥሩ ልቦና ጋር ወደ እግዚአብሄር አድርጊ።" አሉ ዶክተር፣ እምነት የሚሰጠውን የሥነ-ልቦና ጥቅም በማስታወስ።

"እሺ ።" አለች፣ ለመውጣት በመዘጋጀት።

"አትጥፊ። ጠይቂኝ። ደውይልኝ። ሲመችሽም ብቅ በይ።"

ሽታዬ ተሰናብታ ወጣች። በአንድ ጊዜ የተለያዩ ስሜቶች በውስጧ ተፈራረቁ። የመኖር ጉጉት፣ ተስፋ የመቁረጥ፣ የመቆጣት፣ የመናደድ። ዶክተር የነገሯት ሁሉ እርሷን ለማጽናናት እንጂ እውነት አለመሆኑን አመነች። ተስፋ እንዳትቆርጥ ብለው የዋሿት መሆኑን ገና ከግቢያቸው ስትወጣ ነው የገባት። ዕንባ አነቃት። አፍ አውጥታ 'ኡ! ... ኡ!...' ብትል ደስታውን አትችለውም ነበር። ፀጉሯን እንጩብራ ፣ ጨርቋን ጥላ ፣ ጫማዎቿን ወርውራ እግሮቿ ያደረሷት ቦታ ድረስ 'ኡ!.... ኡ!.... ኡ!....' እያለች ለመጮህ አሰበች። ግን አልደፈረችም። ዕንባዋ እንደ እሳተ ገሞራ ፈንድቶ ከዓይኖቿ ወጣ። መግታት አልቻለችም። አለቀሰች። አነባች–እርር ብላ።



## 32

ስፈሯ እንደደረሰች በቀጥታ ወደ ቤቷ ገብታ መተኛት ብትፈልግም፣ በህይወት ለመኖር ያላትን የመጨረሻ ተስፋ ለማወቅ ወሰነች። የግሩምን መፈወስና እርሷም ልትድንበት የምትችልበት የባህል ህክምና እንዳለ ዶክተር ናትናኤል ከነገሯት ወዲህ ገብሩ የሰጣትን የተስፋ ጭላንጭል ወደ ኋላ ብላ ነበር። ዶክተር ናትናኤል የግሩምን መፈወስ ማስረጃ አድርገው የነገሯት ዜና ገብሩን እንድትረሳው አድርጓት ነበር። ዛሬ ግን አስታወሰችው። መዳን እንደምትችል ከዚህ በፊት የነገራትን ማረጋገጥ ትፈልጋለች።

ግቢውን አለፈችና የዋናውን ቤት በር ማንኳኳት ጀመረች።

በሩ ተከፈተ። አጠር ብሎ ወፈር ያለ፣ የቀይ ዳማ ፊትና ጎፈር ያለ ፀጉር ያለው ሰው ብቅ አለ። "እንደምን አረፈድሽ ሽታዬ?" አለ።

ሽታዬ ሰላምታ መስጠቷን ዘንግታና ደምመላሽን እንደ መገፍተር ብላ ልትገባ ስትል ነው፣ ሰላምታ ማቅረብ እንደ ነበረባት ያስታወሰችው። ከነበረችበት የሀሳብ ባህር ውስጥ ወጣችና፣ "እንደምን አረፈድክ? ገብሩ የለም?" አለች፣ ቤቱን በዓይኖቿ እየበረበረች።

"ገብሩ ወጣ አለ።"

"ወዴት ሄደ?"

"እዚህ አካባቢ ነው። ቶሎ ይመለሳል። አረፍ በይ እስከዚያ። " አለ፣ በክፍሉ ውስጥ የሚገኘውን ወንበር እያሳያት።

ተቀመጠች። ደምመላሽም በክፍሉ ውስጥ ወደሚገኘው አልጋ እያነከሰ ጠጋ ብሎ ጋደም አለ።

"እንዴት ነው ተሻለህ?"

"ምን ይሻለኛል? የእግሬ ቁስል አልድን አለ። እያመረቀዘና እየደማ አስቸገረኝ። "የሌሊት ሱሪውን ከፍ አደረገና ደም በጠገበ ፋሻ የተጠቀለለውን ቅልጥሙን አሳያት።" ይኸውልሽ፣ በደም ርሷል። ዛሬ

ጠዋት ነበር ፋሻው የተቀየረልኝ። እየሸው እንዴት እንደራሰ?" ብሎ ቁስሉን እያየ ጠየቃት። ግን መልስ ሳትሰጠው በመቅረቷ ቀና ብሎ አያት።

ሸታዬ ዓይኖቿን በደምመላሽ እግር ላይ አነጣጥራ አንድ ትልቅ ተአምር የተገለፀላት ይመስል አፈጠጠች። ለጥቂት ሴኮንዶች ያህል እሷነቷን ከአለችበት ጊዜ ወደኋላ መልሳ፣ የተገለፀላትን አሳዛኝ ትርኢት በድጋሚ ማየት ጀመረች። ዓይኖቿን በማስታወስ ዓይነት አጠበበችና ሩቅ የምትመለከት መሰለች። ገብሩ ግንባር ላይ ኩሬ ሰርቶ አንድ ቀን የታያት ላብና ድንጋጤ አዘል ንግግሩ ከፊቷ ድቅን አለ። ዶክተር ናትናኤል አንድ ቀን ደሟን ሲወስዱ የነገሯት ነገርም በጆሮዋ አቃጨለ። ገብሩ መድሀኒት የሚሰጣት ሀኪም እንዳለ ነግሯት ደሟን የወሰደው ለምን ተግባር እንደሆነ ገባት። የዚያን ቀን ተከትላ ቤቱ ስትገባ፣ ያየችው ትርኢት ምንም ትርጉም አልሰጣትም ነበር። ጭራሽም ልብ አላለችውም ነበር። አሁን ደግሞ ሌላ ነገር ትዝ አላት። አሁን ከተከሰተላት ነገር ጋር ተያይዞ ታያት። ቤተዘመድ፣ የአቶ ይልማን ሀብት እንዲያስተዳድር ደምመላሽን በለመረጠ ገብሩ አኩርፏል። ከደምመላሽ ጋር ይጨቃጨቃል። 'ማስታመም ሲገባው፣ እየሰከረ እየመጣ ካልገደልኩህ' ይለዋል። እያሉ ሰዎች የሚያወሩት ነገር ትክክል መሆን እንዳለበት ተረዳች። ገብሩ ደሟን ቀድቶ የወሰደው ደምመላሽን ሊገድል መሆኑ ተገለፀላት።

ሁኔታዋ ግራ አጋብቶት እንደጉድ የሚመለከታትን ደምመላሽን አየችው። እርሷን ሲያኝካት የከረመው ሥቃይ በርሱ ላይ በመጋባቱ ከፋኛ አዘነች። የእርሷ ሥቃይ አንሶ የእርሱ መጨመር ልቧን አደማው። በርሱ ላይ ለደረሰው መከራ ምክንያት የሆነችው ርሷ በመሆኗ ራሷን ከመቼውም በላይ ጠላች። እሷነቷን እንዴት አድርጋ እንደምትቀጣው ሊገባት አልቻለም። አሁንም እንደቅድሙ ጩኺ የሚል ስሜት ተሜናት። 'ኡ...! ኡ...!' በይ የሚል ነገር ሹክ አላት። ጩርቅሽን ጥለሽ ብረሪ ብረሪ አሰኛት። ይሁንና ይህን ሁሉ ማድረግ አልቻለችም። ወተት እንደ ቋጠሩ የአራስ ላም ጡቶች ያበጡት ዓይኖቿ ዕንባዋን ዘረገፉት። ግንባሯን ጉልበቷ ላይ ደፍታ ስቅስቅ ብላ አለቀሰች።

ደምመላሽ ሁኔታው አስደንግጦት ተጨንቆ ተመለከታት። ወዲያው በር ተከፈተና ገብሩ ገባ።

ገብሩ ሸታዬን ሲያያት በድንጋጤ ልቡ ቡጭቅ ብሎ ሆዱ ውስጥ የወደቀ ያህል ተሰማው። "ምን ሆነች?" ሲል በመጨነቅ፣ ደምመላሽን ጠየቀው።



ሸታዬ ድምጹን ስትሰማ ቀና አለች። ዓይኖቿ ቀልተው ደም የምታነባ አስመስለዋታል። ገብሩን ስታየው አፈጠጠች። የግንባሯ ሥሮች ተግተረተሩ፣ ከንፈሮቿ ተንቀጠቀጡ፣ ጥርሶቿ ተፋጩ፣ የእጆቿን ጥፍሮች አሹላ ዘላ አንገቱን አነቀችው። "አንተ አረመኔ! አንተ ጨካኝ! አንተ ሰይጣን! አንተ ነፍሰ ገዳይ!"

ገብሩ ለማስለቀቅ ሞከረ። ታገላት። ግን የተናደደች የቤት አንበሳ ሆናለች። በጥፍሮቿ ፊቱን ነዳደለችው። ጃርት የበላው ዱባ አስመሰለችው። ይሁንና፣ በመከላከል ብቻ ሊታገሳት አልቻለም። እሱንም ንዴት አመሰው። ከክንዷ ላይ ወልቆ እስኪበር ድረስ አንድ እጇን ጠመዘዘና በሌላ እጁ በጥፊ እያገላበጠ ደጋግሞ መታት። አፏና አፍንጫዋ በደም ተለውሰው ወደቀች።

ደምመላሽ እያነከሰ በመሀከላቸው ገብቶ መገላገል አልቻለም። "ምን ነካህ? ሴት ልጅ እንዴት እንዲህ ትመታለህ?" ሲል ሳይታወቀው ጮኸ።

"አንተ ደግሞ ምንድን ነህ? ምን አገባህ?" ሲል በንዴት ጮኸ፣ ገብሩ በተራው።

"ለምን አያገባኝም? ሴት ልጅ እንዲህ ትመታለህ?"

"ታዲያ በጥፍሯ ዘንጥላ እስክትጥለኝ ድረስ ልጠብቃ?"

"መከላከል ስትችል መማታቱን ምን አመጣው? የተበሳጨችበትን ነገር ጠይቆ ማጽናናት ሲገባህ ትመታታለህ? ጥሩ ሥራ አይደለም የሠራኸው። እሷ ጥፋተኛ ልትሆን ትችላለች። እልህዋ እስኪበርድ መታገስና ችግሩን በውይይት መፍታት ሲገባህ እንዲህ እስክትሆን ድረስ መማታትህ ጥሩ አይደለም።" አለ ደምመላሽ ፣ እንደመገሰጽ ብሎ።

ሸታዬ ከወደቀችበት ወለል ላይ ተነሳችና እየተንገዳገደች ከክፍሉ ወጣች።

"ሸታዬ! ቆይ እንጂ! አንቺ?" አለ ደምመላሽ። እያነከሰ ሊደርስባት አልቻለም። ርቃለች። "ለመሆኑ ምን አገናኛችሁ?" ሲል ገብሩን ጠየቀው።

"አንተ ምንም የሚያገባህ ነገር የለም! እርፈህ ተጋደም። ከአንተ ጋር ንግግር ካቆምኩ ቆይቻለሁ! እርፈህ ተጋደምና ብላ!"

ደምመላሽ ምንም አልተናገረም። ገብሩ የተናገረው ነገር የጋለ ብረት ምጣድ ላይ እንደተቀመጠ የሥጋ ቁራጭ እንጀቱን አኮማተረው።

"አባቴን የገደልከው ለዚሁ አይደል!" ሲል ጩምሮ ተናገረ ገብሩ።

"እንደዚያ አሰብክ? እንደዚያ አሰብክ ገብሩ? እንደዚያ አሰብክ?" አለ ደምመላሽ እንባ እየተናነቀው። ጥሩ ነው። ባይወልደኝም፣ አባቴ ነው። አባትህን አውቀህ ገደልክ ነው የምትለኝ? ገብሩ ከልጅነት ጀምሮ እንደወላጅ አባት፣ ከማንኛችሁም አስበልጦ ያሳደገኝን አባቴን ገደልከው አልከኝ?" አለ፣ ብሶት ባንኮታኮተው ድምጽ።

"አዎ አውቀህ ነው የገደልከው! ተሳካልህ! ቤተዘመድ በሙሉ ንብረቱን እንድታስተዳድርና እንድትበላ ስልጣን ሰጠህ! ያሰብከው ይሄ ነበር ተሳካልህ!" ሲል ጮኸ ገብሩ።

ደምመላሽ ምንም ሳይናገር አልጋው ላይ ተቀመጠና እንገቱን አቀረቀረ። "እሺ ጥሩ። ገብሩ እኔን ባታውቀኝ ነው። እኔ በላቤ፣ በጉልበቴ ደክሜ መኖር የምፈልግ ሰው ነኝ። በሰው ላብ፣ ሰው ደክሞ ባፈራው ሀብት ውርስ መኖር እንደማልፈልግ፣ ባለማወቅህ ነው፣ የልቤን ባለመረዳትህ ነው። ከቀናት በኋላ ታየኛለህ። ትንሽ ታገስ። ይህ ቁስል እስኪድንልኝ ድረስ ታገሰኝ። እኔ ከዚች ቤት ሰባራ ሣንቲም አልፈልግም። ሁሉም ለአንተ ይሆናል። እስከዚያ፣ በፈጠረህ አምላክ አባቴን ገደልክ አትበለኝ። ከምንም አብልጬ የምወደውን አባቴን ገደልከው አትበለኝ።"

ድንገት በሩ ተከፈተ። ሽታዬ ተንደርድራ ገባች። ከኋላዋ ዩኒፎርም የለበሱ ሁለት ፖሊሶች ተከትለዋት ገቡ። "ይኸው። እኔን በመደብደቡ ብቻ ሳይሆን፣ በነፍስ ገዳይነትም የሚጠየቅ ሰው ነው።"

ፖሊሶቹ ገብሩን ይዘውት ወጡ።

## 33

ከቀኑ አሥር ተኩል ሲል የእጅ ሰዓቱ ነገረው። የሲሳይ መምጫ ጊዜ ደርሷል። እስካሁን ግን ብቅ አላለችም። ግርማ በቀጠሮው ቦታ ቀደም ብሎ በመገኘት ሲጠብቅ አሥራ አምስት ደቂቃዎች አልፈዋል።

ከንግሥት ጋር የነበረውን የፍቅር ግንኙነት ካቋረጠ በኋላ፣ ሲሳይን በግንባር አግኝቶ የተነጋገሩበት ጊዜ አልነበረም። ዛሬ ጠዋት ቢሮዋ ደውሎላት ሊያገኛት መፈለጉን በገለፀላት መሠረት ነው በዚህ ካፌቴሪያ ውስጥ በአሁኗ ሰዓት ለመገናኘት የተቀጣጠሩት።



ግርማ፣ ዶክተር ናትናኤል በአንድ ምሽት ከንግሥት ጋር አብረው ሳሉ መጥተው የነገሩት ነገር በጊዜው ቢያስደነግጠውም፣ ከቀናት በኋላ ችላ ብሎት ነበር። ከልጃቸው ጋር የጀመረውን ፍቅር በመጥላት፣ ዶክተር ሆን ብለው ያቀረቡት ምክንያት መስሎ ነበር የታየው። ይሁንና፣ ከንግሥት ጋር የነበረውን ግንኙነት ቆርጧል። ዶክተሩ የነገሩትን ወደ ኋላ ብሎ የንግሥትን ፍቅር መቀጠልም አልደፈረም፣ ሀኪሙ ያሉት እውነት ሊሆን ይችላል በማለት።

ሲሳይ ካፌቴሪያው ውስጥ ገባችና ግርማ ወደ ተቀመጠበት ቦታ ተጠጋች። ጠቆር ያለ ሱሪና ቀይ ሹራብ ለብሳለች። አጭር ከርዳዳ ፀጉሯ የጥድ ክርክም መስሏል። ከግርማ ጋር ጉንጭ ለጉንጭ ተሳሳሙና ተቀመጠች።

"እንደምን ነህ ግርማ?"

"ደህና። አንቺ ደህና ነሽ ?"

"ደህና ነኝ። አንተስ?"

"ደህና ነኝ።"

"ጠፋህ። "

"አዎ። ምን ጊዜ አለኝ ብለሽ ነው። ብዙ ጊዜ አዲስ አበባ አልቀመጥም።" አለና አሳላፊውን ጠራው።

"ምን ልታዘዝ?" አለ አሳላፊው።

"ለስላሳ።" አለች ሲሳይ። አሳላፊው ከሄደ በኋላ፣ "ቢሆንም፣ ስትመጣ እንኳ አላስታወስከንም።" ስትል ተናገረች።

"አዎ ፣ እዚህ ስመጣም ጊዜ የለኝም። ከፍለሀገር ቆይቼ ስመጣ ብዙ ጉዳዮች ተፈጥረው ይጠብቁኛል። እነሱን ለመፈጸም ስል ዘመድ፣ ጓደኛ እረሳለሁ።"

አሳላፊው ለስላሳውን ይዞ መጣና ከፍቶ ሄደ።

"በተረፈ ግን ደህና ነህ ?"

"ደህና ነኝ።"

ዝምታ ተፈጠረ። ሁለቱም የግል ሀሳባቸውን ማስተናገድ ጀመሩ። ሲሳይ ግርማ ስልክ ደውሎ እንዲገናኙ ቀጠሮ ካስያዛት ጊዜ ጀምሮ፣ ለምን ጉዳይ እንደተፈለገች ራሷን ስትጠይቅ ነው የዋለችው። ስለንግሥት ይሆናል ብላ ግን ገምታለች። 'ስለ ንግሥት ምን? አስታርቂኝ ብሎ ሊጠይቅ ወይስ ምን?' የሚሉት ጥያቄዎች በአእምሮዋ ውስጥ ሲመላለሱ ነው የዋሉት። ግርማም በበኩሉ 'በንግሥት ላይ ተከስተ ስለተባለው ነገር ፣ በፊቱኑ ታውቅ ይሆን? ካላወቀችስ እንዴት